# ከምድራዊነታችን ባሻገር

## አንደኛ መጽሐፍ

### ከግለሰብ እስከ አገር - ማስታወሻና ማስተዋያ

መ. ኃ. መስቀል (ዶ/ር)

# ጸሎት

አቤቱ ፈጣሪአችን አምላካችን ቸሩ እግዚአብሔር ሆይ!
የእውር ሰውን ልቦና ባለ አይን ከሚያየው የበለጠ እንዲያይ
ማድረግ የምትችል አንተ ነህና፤
ይህ መጽሐፍ ለአንባብያን የሚጠቅም ሆኖ ይጨረስ ዘንድ፥
ስለአንተ ፈቃድ እለምናለሁ።
አሜን።

Copyright © 2020 by M.H. Meskale (PHD)
ሁለተኛ እትም

መልሶ የማሳተም መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

ከዚህ መጽሐፍ ሽያጭ የሚገኝ ገቢ ሁሉ ለመንፈሳዊ እና ለበጎ አድራጊ ድርጅቶች
የሚሰጥ፥ ለድኩማንም መርጃ የሚውል ይሁን።

# መታሰቢያ

## ለባለቤቴ እና ለልጆቼ

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ እዚህ ያደረሰኝን ፈጣሪ አምላኬን በከፍተኛ ደረጃ አመሰግነዋለሁ። በእውነት ፍጹምና ኃያል፥ ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ፈጣሪ አምላካችን የጨለመውን የሚያበራ፥ ቀናውንም መንገድ የሚያሳይ፥ እኔ በእውቀት ሳይሆን፥ በብዙ ዓመታት ጥረትና በጸሎት የተጋሁበትን ሥራ አይቶ እርሱ እንደረዳኝ አምኛለሁ፤ የተማመንኩበት አምላኬ አላሳፈረኝም።

በአካላዊነት የማትታየው ባለቤቴን እና በኑሮዬ ደስ እንዲለኝ የሚያደርጉኝ ልጆቼን  በጣም አመሰግናለሁ። ለደገፉኝ ለኔ ዘመዶችና ለባለቤቴ ዘመዶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በቅርብም ሆነ በሩቅ ሆናችሁ በመንፈስ ላልተለያችሁኝ ወገኖቼ ሁሉ ሙሉ ምስጋናዬን ከመንፈሳዊ ፍቅር ጋር አስተላልፋለሁ።

በከፊልም ሆነ በብዛት መንፈሳዊ ትምህርትን ላስተማሩኝ (ለሰበኩኝ) ኦርቶዶክሶች፥ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። የሁላችንም ሕይወት በምድር ላይ እክል እንዳይበዛበት መንፈሳዊነትን የሚያስተምሩ፥ የሚያጽናኑ፥ የሚመክሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።

በእርማትም ሆነ አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ ሁሉ፥ በተለይም ለወንድሜ ለአዲስ አለሙ እና ለጓደኛዬ ለተስፋየሱስ መንግሥቱ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

# የአጻጻፍ መመሪያዎች

ይህ መጽሐፍ ለምሁራኑ እንዲሁም ለሠፊው ሕዝብ ቀላል ምንባብ እንዲሆን የሚከተሉትን የአጻጻፍ መመሪያዎች ተከትሏል፡-

- በተቻለ መጠን አረፍተ ነገሮችን በማሳጠር፥ በቀላል አማርኛ ተዘጋጅቷል።
- ከተጠቀሱት ዋቢ መጻሕፍት ሌላ፥ የድረ ገጽ ምንጮችና ተጨማሪ ማብራሪያዎች በግርጌ ማስታወሻዎች (foot notes) እንዲያመላክቱ ተደርጓል።
- አንዳንድ ቃላት በትእምርተ ጥቅስ (quotation mark) የታጠሩት፥ አረፍተነገሩ ከሚያመለክተው ውጪ ሌላም ትርጉም ሊሰጠው ስለሚችል የመጽሐፉ ስሜት እንዲጠበቅ ሲባል ነው ትእምርተ ጥቅስ ያስፈለገው። ለምሳሌ፡- በሥጋም በመንፈስም "አንድ" ነን ሲል፥ "አንድ" የሚለው ቃል አንጻራዊ ስለሆነ ለአረፍተነገሩ የተለያየ ፍቺ ይሰጠዋል - ሰውን ሁሉ "አንድ" ሊያስመስለው ይችላል - ሳይሆን።
- አንዳንድ ቃላት በመጥበቅም ሆነ በመላላት ሲነገሩ የተለያየ (አሻሚ) ፍቺ እየሰጡ እንዳያደናግሩ፡- አልፎ አልፎ (እንደየአስፈላጊነቱ፥ አሻሚ ፍቺ እንዳይኖር) አንዳንድ ሆሄዎች ላይ በመጥበቅ መነገር ሲኖርባቸው ከሥራቸው ተሰርዞባቸዋል። ለምሳሌ፥ አ<u>ል</u>ለይህም (ሰረዙ አንድ ሆሄ ላይ ብቻ ነው)፤ አ<u>ይገባ</u>ም (ሰረዙ ሦስት ሆሄዎች ላይ ነው)። ይህ የተደረገው፥ በተለይ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ሆኖ፥ ወይንም በውጭ አገር ብዙ ስለቆዩ፥ ወይንም ከዛ ስለተወለዱ፥ የአማርኛን ስነጽሐ#ፍ ምንባብ ላልተለማመዱ አንባቢያን እንዲቀላቸው ለማድረግ ነው እንጂ፥ በዚህ ረገድ የአማርኛን ስነጽሑፍ ለማሻሻል ታስቦ አይደለም።
- ከመደበኛው የአጻጻፍ ዘዴ ወጣ ቢልም፥ ልክ እንደ ንግግር ሆኖ ቀለል ይል ዘንድ፥ ነጠላ ሰርዞች በዛ ብለውበት ይሆናል።
- ብዙሓኑ ሲያነቡት "የማውቀውን ቀስቅስ እንጂ አትንገረኝ.." እንዳይሉ፥ በተቻለ መጠን ገኃድ የሆኑ ሃሳቦች መጠቀሳቸው ለአንዳንድ የአስተሳሰብ ዘገባዎች የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፥ ተወግደዋል።
- የወንድ ጾታ ብቻ አልፎ አልፎ ቢጠቀስ፥ የሴትን ጾታም በውስጠ ታዊቂነት አብሮ በማጠቃለል ነው።

- አንባቢ ዘና ብሎ እንዲያነብ፥ ጠለቅ ያሉ ሃሳቦችን ለማፍታታት፥ በዚያውም መጽሐፉ የራሱ የሆነ ጣዕም እንዲኖረው ለማድረግ፥ አልፎ አልፎ ግጥሞች ታክለውበታል።
- በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሃይማኖት ነክ ጉዳዮች አላማ፥ ከመንፈሳዊ ይዘታቸው አልፈው፥ በማንኛም ሃይማኖት ላይ ነቀፌታ - አጉል ትችት ወይም የግል ስሜትን ለማንጸባረቅ አይደለም።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተጠቀሱት፥ አንዳንድ ሃሳቦችን ለማብራራት ነው እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያመለክተው መንፈሳዊ ትርጉም ጋር ለማመሳሰል አይደለም።
- አንዳንድ ፖለቲካዊ ወይንም ሃይማኖታዊ አመለካከቶች ሲብራሩ፥ የሚያነበው ሁሉ ከራሱ ሃሳብ ርቆ የሚሄድ ባለ አንድ አቅጣጫ አከራሪ ሃሳብ እንዳይጎላበትና እንዳይሰናከል ጥንቃቄ ተደርጓል። ምናልባት በግላጭ ወይንም በድብቅ ወገናዊነት ቢታይባቸው፥ የአንባቢ ይቅርታ ይጠየቃል።
- ይህ መጽሐፍ፥ አንዳንድ እስከ ዛሬ ያልተደረሰባቸውን ፍሬ ሃሳቦች ስለሚያካትት፥ ለወደፊት ትኩረት እንዲሰጣቸው በማሰብ፥ እጅግ በተቃለለ መንገድም ቢሆን፥ ደራሲው የራሱን ነፃ አስተያየት ከመሰንዘር አልተቆጠበም።

# መቅድም

አርእስቱ እጅግ ከባድ መሆኑ እሙን ነው፤ ግን መጻፉ ግዴታ ሆኗል። ለጸሃፊው የከበደውን ያህል ለአንባቢውም እንዳይከብድ፥ የተደረገውን ጥረት የሚያመላክተውን ምዕራፍ አንድን ማቅረብ አስፈልጓል። መጻሕፍትን የመጻፍ ሥራ ከመጀሩ በፊት፥ “ለመሆኑ እኔስ ማነኝና? ምንስ አውቄ? እንዴትስ ብደፍር?.. እስቲ እራሴን በቅድሚያ ልመርምር....” በማለት የምድራዊነቴን እና የነፍሴን (የመንፈሴን) ጉዳይ ሳሰላስል የተጻፈ፥ “ውስጣዊ ስሜታዊ ውይይት” ነው - የአራቱም መጻሕፍት መነሻቸው።

የዚህን “ከምድራዊነታችን ባሻገር” የተሰኘ አቢይ ርዕስ ሳይለቅ፥ ይህ ከአራቱ መጻሕፍት የመጀመሪያ ሲሆን፥ ምናልባት ስሜታዊነት ቢታይበት ነው እንጂ፥ እንደ እውነት የሚመስል ልብ ወለድ ታሪክ፥ ወይንም ነገር በማጋነን ወደ ውሸት የሚያመራ የፈጠራ ወሬ የለበትም።

ከመጽሐፍቱ መልእክቶች ባሻገር፥ አንባቢያን እንደየግንዛቤአቸው ትልቁን፥ ዋነኛውንና ጠቃሚውን፥ በእውነት “ከምድራዊነታችን ባሻገር” የሚታሰባቸውን (ወርቁን) በስነ ልቡናቸው በአጽንኦት እያገናዘቡ እንዲያነቡትና የራሳቸውንም እምነት እንዲያጠናክሩበት ምኞቴ ነው።

ብዙ ነገር እናውቃለን፥ ግን እውቀታችን እርስ በርስ ተያይዞ ወደ አንድ የጋራ እውነት አይመራንም። የሁላችንም ሕይወት በአንድ “ሁለንተናዊ እውነት” የሚመራ መሆኑን እናውቃለን። ታዲያ፥ ወደዚያ እውነት ለመጠጋት ዘዴው ምንድነው? ሰዎች ይህን ጥያቄ ለመመለስ ሲሉ በብዙ የእውቀት ዘርፎች፥ ከሳይንስ እስከ ሃይማኖት እጅግ ሠልጥነዋል። ግን ሁሉም በየአቅጣጫው እየሄደ፥ በሕብረት ከማሰብና አብሮ ከመሆን ይልቅ፥ በተናጠል እያሰቡ መለያየት አመዝኗል።

ነገር ግን፥ ከነገሮች ሁሉ ምድራዊ አመለካከትን እያወጣን፥ በአካላዊ አለም የማይተረጎም፥ አፋዊ ገለጻ የማይበቃውን ሁሉ (መንፈሳዊነታችንን) ከመመልከት ወደኋላ የማንል ብንሆን፥ የምድራዊ ሕይወታችን ወርቃማ መልክ (ደጋጉ) ቁልጭ ይል፤ የተለያዩ የሃሳብ ቅራኔዎች (ግጭቶች) ይደመሰሱ፤ ሉላዊ አንድነታችን እና ሰላማችንም የሚገኘው በዚህ መንገድ ይሆን?

“ከምድራዊነታችን ባሻገር” በተሰኘ አቢይ አርእስት ሥር ይህ መጽሐፍ እና ሌሎችም ተከታታይ መጻሕፍት ከላይ የተጠቀሱትን ለመመለስ ችሎታ ባይኖራቸውም፥ ሁላችንንም ወደ ጋራ ግንዛቤ የሚመሩን አንዳንድ “ሃሳቦች” እንደማይታጣባቸው ይታመናል።

ስለ አገራችን የተጻፉ በርካታ ጽሑፎች ቢኖሩም፥ በዚህ በአንደኛ መጽሐፍ፥ ከግል ታሪክም ቢሆን ከሕዝቦች ታሪክ በስተጀርባ፥ መንፈሳዊነትና መልካሙ የሰው ልጅ ጠባይ (ቅንነት፥ ደግነት፥ አዎንታዊነት፥ እውነተኛነት፥ ወ.ዘ.ተ.) ለኢትዮጵያችን አንድነት፥ የጋራ ብልጽግና እና እድገት ወሳኝ መሆኑን ይህ መጽሐፍ በአጽንኦት ያመለክታል።

ይህና በዚህ አቢይ አርእስት ሥር የተጻፉት መጻሕፍት በእጃችሁ የገባ፥ በውስጣችሁ ያለው እውነት እንዳይበረዝባችሁ እየተጠነቀቃችሁ፥ በእናንተው እንደተጻፉ እየቆጠራችሁ፥ ከአበቦች መካከል ጣፋጩን ጮርቃ እንደሚቀስሙ ወፎች፥ ወይንም ከጭቃ ውስጥ የወደቀ ወርቅ እንደሚፈልግ ሰው ሆናችሁ፡- “ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለኔ የሚጠቅም ምን አገኘሁበት?" በማለት እራሳችሁን እየጠየቃችሁ፥ የፍሬ ሃሳቦችንም እድገትና ሂደት እየመዘናችሁ እንድታነቡ ተጋብዛችኋል። የእውነት ምንጭ አንድ፥ እርሱም እግዚአብሔር ብቻ ነውና፤ የበለጠውን የሚያሳውቅ መንፈስ ቅዱስን እርሱ ይሰድላችኋል።

## <u>**የሁለተኛው መጽሐፍ ይዘት - ሁሉም ለአንድነት - ማስታወሻና ማስተዋያ ግጥሞች፡**</u>

“ከምድራዊነታችን ባሻገር” በሚል አቢይ ርዕስ ሥር ከተዘጋጁት ሌሎች መጻሕፍት የተጠቀሱ አንዳንድ “ጠቃሚ” ሃሳቦችን በስእሎችና በግጥሞች ያጠናክራል። ግጥሞቹ የተዘጋጁት በስሜቶች ብቻ የሚገባን ከሚመስለን ጋር መቆየታችንን ለማስታወሻ፥ መሠረታዊ ጥያቄዎቻችንንም ለማሰላሰል እንዲረዳን ሲሆን፥ በአጠቃላይ የግጥሞቹ ይዘት በኢትዮጵያችንም ሆነ በተቀረው አለማችን ውስጥ ግለሰብአዊ፥ ቤተሰብአዊና ሕብረተሰብአዊ ኑሮአችንን ይመለከታል፤ ትኩርት በምድራዊ ኑሮ ብቻ እንዳይሆንም የሰውን መንፈሳዊ ጠባይ አጉልቶ ለማሳየት ይሞክራል።

## <u>**የሦስተኛው መጽሐፍ ይዘት - ሳይንስ፥ እምነት፥ ሥልጣኔ፥ ማስታወሻና ማስተዋያ፡**</u>

ምድራችን ከመፈጠሯ በፊትና በኋላ እንዴት እንደነበር ግምታዊ - ሳይንሳዊ ማብራሪያ ያቀርባል። በጂኦሎጂ (ሥነ ምድር) ምርምር ከተገኙ መረጃዎች በመነሳት፥ በምድራችን የተከናወኑትን ተፈጥሮአዊ ክስተቶች - ተፈጥሮአዊ እድገት በአካላዊነቱ ከዝግመተ ለውጥ (evolution) እንዴት ተለይቶ እንደሚታይ ያብራራል። ለአንዳንድ መሠረታዊ ሳይንሳዊ ጥያቄዎችም ጥንቃቄ በተመላበት መንገድ፥ ሃይማኖታዊ (መንፈሳዊ) አስተያየት ያቀርባል። ቀጥሎም ስለ ሰው ዘር አመጣጥ፥ ስለ ስደቶቻችን እና ስለ ቀደሙ ሥልጣኔዎች በማውሳት፥ ስለ መንፈሳዊ አንድነታችን

ጉዳይ ያሳስባል። የሁሉም አቅጣጫ ሳይንስ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ እንጂ የሚያርቅ አለመሆኑን ለማስረገጥ ነው።

## የአራተኛው መጽሐፍ ይዘት - መንፈሳዊ ጉዞ - ማስታወሻና ማስተዋያ፡

ለብዙዎች - ሃሳቦችን ከመጋበዝ (ከማስረጽ) አልፎ፥ የሚያሳውቀው ነገር ባይኖረውም፥ ከምናየው አለም የማናየውን አለም ለማየት ስንሞክር የሚታሰበንን (ፍቅር፥ ደስታ፥ ሃይማኖታዊ - መንፈሳዊ ስሜት..) የሚጠቃቅስ፤ ሁሉም የገዛ እምነቱን ይዞ እንዲጸና ለየት ባለ መልክ የሚያሳስብ ነው ይህ መጽሐፍ።

## ሁሉም ለአንድነት - ድረገጽ፡

ቀደም ሲል፥ ሁሉም ለአንድነት በሚል መርሆ፥ የሚከተለው ድረገጽ ተዘጋጅቶ አያሌ ግለሰቦች በአለም ዙሪያ ተመልክተውታል። ጽሑፎቹ ሁሉ፥ ከስዕሎቹም ጋር ሆነው "ከምድራዊነታችን ባሻገር" የተሰኘውን አቢይ አርእስት ባይመጥኑት ይቅርታ።

https://www.amharicbooksforunity.org/

# ማውጫ

| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ምስጋና፡ | | iv |
| የአጻጻፍ መመሪያዎች፡ | | v |
| መቅድም፡ | | vii |
| ማውጫ፡ | | x |
| | | |
| መግቢያ፡ | | 1 |
| ምዕራፍ አንድ፡ | ውስጣዊ ስሜታዊ ውይይት፡ | 3 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ | ግለሰብና አብዮታዊ ውዝግቦች፡ | 31 |
| ምዕራፍ ሦስት፡ | ቅሪተ ሃሳብ፡ | 125 |
| ምዕራፍ አራት፡ | ምድራዊት ኢትዮጵያ ሰማያዊ፡ | 137 |
| ምዕራፍ አራት፡ | ኢትዮጵያችን እና አንድነታችን፡ | 159 |
| ዋቢ መጻሕፍት፡ | | 193 |
| (ለአራቱም መጻሕፍት)፡ | | |

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ “በኢትዮጵያችን በውስጧ የተሠራውና የሚሠራውም ሁሉ፡- የግለሰብ ኑሮም ቢሆን፥ የአገር ፖለቲካም ቢሆን ካለ መንፈሳዊነት ብቻውን ምድራዊ እየሆነ መምጣቱ፥ በተለይ እኛን ኢትዮጵያውያኖችን ወደ ኋላ አስቀርቶን ይሆናል፤ ግን “ይህች ኢትዮጵያችን ምድራዊ እንኳን ብትሆን፥ ያቺ ኢትዮጵያችን ሰማያዊነቷ ብድግ ሳያደርጋት አይቀርም..” በሚል እምነት ተጀመረ።

በጊዜ ውስጥ ያለፍናቸውን ጊዜያቶች፥ እንዱን ከሌላው ለማወዳደር፥ ወይንም በውስጡ ፖለቲካዊ/ታሪካዊ ትንተናዎችን በማቅረብ ሳይሆን፥ ጠቅላላ የመጽሐፉ ይዘት ከግለሰብ አብዮታዊ ተሳትፎ በመነሳት ወደ አጠቃላይ የአገር ጉዳይ ያመራል። የዚህ መጽሐፍ አላማ፡-

ሀ) አባቶች/እናቶች በበኩላችን የሄድንበትን ጎዳና፥ ያሳለፍነውን - ክፉውንም ደጉንም ጊዜ ለልጆቻችን እንድናሳውቅ፤

ለ) በአሁኑ ጊዜ እና ለወደፊት፥ ስለአገራቸው በመቆርቆር በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የሚሳተፉ ሁሉ፥ ካለፉት የፖለቲካ ትግሎች/ስህተቶች እየተማሩ፥ የራሳቸውን ግላዊ ፍላጎት ከአገራቸው (ከሕዝባቸው) ጋር ማጣጣምንም እንዲያስቡበት ነው።

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ 1966 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በኩል በተካሄደው አብዮታዊ ትግል ውስጥ ደራሲው ካሳለፈው ወቅታዊ ተሳትፎ በመነሳት፥ በወታደራዊው የደርግ ዘመን ውስጥ የነበረውን ሕብረተሰብአዊ ተቋአም በአጭሩ ያወሳል። ይህም፥ ከደርግ በፊት (በንጉሡ በኃይለ ሥላሴ ዘመን) የነበረውን የፊውዶ ካፒታሊስት ስርአት በሶሻሊስት ስርአት የለወጠ አብዮት፥ እንደ አሽናፊነቱ መላው ኢትዮጵያን ያስደሰተ የኢኮኖሚና የሶሻል እድገቶችን አለማሳየቱን ከሚያንጸባርቁ ምድራዊ እይታዎች ባሻገር፥ ለኢትዮጵያችንስ አምላካችን ዝም እንደማይል፥ ግን የእግአብሔርን ቀጥተኛ እርዳታ ለማግኘት የአንድነት ቅድመ ሁኔታ መሟላት ማስፈለጉን ለመግለጽ ነው።

ቀጥሎም፥ በዘመኑ የወያኔ (በብዛት ከትግራይ ተወላጆችና ጥቂት ሌሎች ብሔሮች የተውጣጣ) መንግሥት የደርግን መንግሥት በመደምሰስ በአሸናፊነቱ ያመጣው ለውጥ፥ እንደ አሸናፊነቱ መላው ኢትዮጵያን ያስደሰተ የኢኮኖሚና የሶሻል እድገቶችን አለማሳየቱን ከሚያንጸባርቁ ምድራዊ እይታዎች ባሻገር፥ ለኢትዮጵያችንስ

አምላካችን ዝም እንደማይል፥ ግን የእግአብሔርን ቀጥተኛ እርዳታ ለማግኘት የአንድነት ቅድመ ሁኔታ መሟላት ማስፈለጉን ለመግለጽ ነው።

በመጨረሻም፥ ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ሥራ ምክንያት የሚሆን የሰው ጠባዩ ስለሆነ፥ ሁሉም የራሱን ግንዛቤ - አለማዊ (ጠፈራዊ) ርዕዮቱን እንዲመረምርና ወደ አንድነታችን የሚመራንን ጥሩውን መንፈሳዊነታችንን እንድናጠናክር ይመክራል።

መልካም ምንባብ

# ምዕራፍ አንድ

## ውስጣዊ ስሜታዊ ውይይት

<u>ቶማስ</u>

"ኮከቤ የተባለች ውዲቷ ባለቤቴ ድንገት ብትለየኝ፥ ከሃዘን ብዛት፥ ከምድራዊ እውነታ የወጣሁ መስሎኛል፤ ብዙ አወራለሁ ከኔው ጋር።

የሰው ተፈጥሮ ሁለት ባይሆን ኖሮ፥ ብቸኝነት ሲሰማ የብቸኝነተ ብቸኝነት ምን ያህል የከፋ ይሆን ነበር? በችግር ጊዜ የሰው ሁለትነት በገሃድ ይታወቃል። በእውነት በውስጤ ልክ እንደራሴ ያ<u>ለ</u> ሌላ ሰው መኖር አለበት። ሰው ሁሉ ሁለት ስለሆነ፥ ከራሱ አምሳያ ሰው ጋር ያወራል (ይጫወታል)፤ ይህም፡- ድመት ከገዛ ጭራዋ ጋር እንደምትጫወት አይነት አይደለም በእውነት።

ስለዚህ፡- ይህ የሥጋ ሰው እስኪሞት ድረስ፥ ከውስጡ አካለ ብርሃን እና መንፈስ ብርሃን ካለ መቀላቀል በውሕደት፥ ከሞቃት የሕይወት እስትንፋስ ጋር ይኑሩ፤ በሃዘኑም ሆነ በደስታው፥ የመንፈስ ሰው አብሮት ይሁን እንጂ አይለየው፥ የሚል ውስጣዊ ስሜት ቀስቅሶኛል።

ልባዊ ጭምጭምታ፥ ካለ ድምጽ የሚያናግር፥

ካለ ብርሃን - እንደ እውን የሚከሰት ምስል፥

ከጎኔ - የኔው አጋር፥

ባለቤቴ ብትሄድ፥ ብቻዬን እንዳልቀር፤

ከውስጣዊው እኔ፥ ከዮሐንስ ጋር ምክር፥

ከምድራዊነቴ ስላቀቅ፥ በመንፈሴ እንድከበር፤

ይህ ነው መነሻዬ፥ የመሰንበቴም ምሥጢር።

ከብቸኝነት የሚያወጣኝ እራሴን ስፈልግ፥ ከራሴ ውስጥ አጋር መንፈስ መኖሩ ትዝ ይለኛል። በመንፈስ እኔን የሆንክ - አንተ ዮሐንስ ነህ፥ ለኔ አጋር ሆነህ ከጎኔ የተቀመጥክ። ስለዚህ፥ በዚህ ጭንቅ ቀን አብረኸኝ ሁን ዮሐንስ፤ አ<u>ትለ</u>የኝ።"

**ዮሐንስ**

“አዎ! ማንም ሰው ጭልጥ ብሎ እስኪጠፋ ድረስ፥ ከሁለት አለም መካከል መጠነኛ ሽርሽር ይኖራል። እንደምፈልገውና መሆን እንዳለበት አልሆንኩም። ከነልዩነቶቻችን አብረን ብንኖርም፥ እድሜ ሲገፋ መመሳሰልና መስማማት ይመጣል በማለት አስብ ነበር። ሁለት የማይጣጣሙ ፍጡሮች በአንድ ላይ መኖር እንደማይችሉ ጊዜና ሁኔታ አረጋግጦልናል።

በስተርጅናም ቢሆን ጨብጠህ የያዝከውን ምድራዊነትክን ጣል ብልህ አትሰማኝም። ካንተ ጋር አብሬ እንድኖር የሚያበቃ ሁኔታ ካልፈጠርክልኝ ተለያይቶ መኖር ግዴታ ይሆናል። ሰው በተፈጥሮው የተደነገገለት መንፈሱ ከሥጋው ጋር ተስማምቶ እንዲኖር ነው እንጂ፥ እየተቃረነ እንዲኖር አልነበረም። የተገነጠልኩ እኔም ልሁን አንተ፥ የመለያየታችን እውነታ እንዲህ ቁልጭ ብሎ ሲታይ ምንም ማድረግ አይቻልም።”

**ቶማስ**

“ሰው የራሱን ቤት ይንከባከባል፤ ግርግዳው ቢወድቅ፥ ጣሪያው ቢሸነቆር፥ የበሩ ወይም የመስኮቱ እንጨት ቢበሰብስ፥ አስፈላጊውን ጥገና ያደርጋል፤ ቀለም ቀብቶ አዲስ ያስመስለዋል እንጂ፥ የገዛ ቤቱ ሲፈራርስ ዝም ብሎ አያስተውልም፤ ወይንም ጥሎት አይሄድም። እስከ ሥጋዊ ሕይወቴ ፍጻሜ የምትኖርብኝ ስለሆንክ፥ እንደ ቤት ቁጠረኝ፤ ተንከባከበኝ እንጂ፥ አሁን ከባድ ችግር በላያችን ሲወድቅ ከኔ ተገንጥለህ ለመሄድ አታስፈራራኝ።

አይምሮ ከሁለት ተከፍሎ እንደ ሁለት ሰው ሆኖ የሚያወራ ይመስል፥ አካሌ ሰውነቴ፥ ነፍሴ መንፈሴ እያልኩ እለፈልፋለሁ። ባለቤቴ ተለየችኝ፤ አንተም ከኔ ተገንጥለህ ከሄድክ፥ እኔ ብቻዬን ግራ የማጋባ ልዩ ፍጡር እሆንና ሰዎች ከሩቅ ይሸሹኛል። አንድ ሰው ከራሱ ተገንጥሎ እንዴት ይኖራል? አንተ ማለት የኔ ግልባጭ ማለት ነህ። ሁለታችንም በምድራዊነት ክልል ውስጥ የምንኖር ነን፤ ተረዳድተን እንኑር እንጂ።”

**ዮሐንስ**

“ከሰማይም ከምድርም መሆን አቅቶት የሰው ልጅ መንፈሱ ብቻውን ሲንከራተት፥ የሚያርፍበትም ሥፍራ ሲያጣ፥ ለማደሪያም የሚሆን ቤት ሲፈልግ፤.... እህ! ከሰዎች መካከል ለኔ ማደሪያ ቶማስ ሆነህ ተገኘህ! ብቻዬን መኖር ብችል ደስ ባለኝ ነበር።

ግን፥ ብቻዬን ሆኜ ምን እንደምመስል ማወቅ እንዳልችል፥ ከምድር ተጥዬ ከአካል ጋር ተደባልቄአለሁ። አዎ! ይህ ነው የሰውእነት ታሪክ (ምድራዊ ተፈጥሮ)፥ ከሰማያዊ ድንጋጌዎች አንዱ (ወደ ምድር መጣል ማለት)።

"የሰማይን ሥራ መርምሮ ማወቅ፥ ከሥጋው ለይቶ ነፍሱን፥ ከነፍሱም ለይቶ ሥጋውን ማየት ይህ ነፍሴ ነው፥ ይህ ሥጋዬ ነው ብሎ መናገር የሚቻለው ማነው።" ሄኖክ 35፡34

ሞት ማለት ዘላለማዊ ሁለት መከፈል ማለት ነው። ግን ሃሳብ ሲገባ፥ እንዲሁ በቁም ከሁለት እየተከፈሉ መሞትና መኖርን እንደ መለማመድ ይቆጠራል። በሁለት ተከፍለን፥ ከገነት ደጃፍ ቆመናል። አዳምና ሔዋን ከገነት ደጃፍ ቆመው፥ ተመልሰው ወደ ገነት እንዳይገቡና የሕይወትን ፍሬ በልተው ለዘለአለም እንዳይኖሩ "ኪሩቤልና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ..." ዘፍ. 3፡24 ተከላካዮች ሆነው እንዲጠብቁ እንደተደረገው መሆኑ ነው። አንተ ግን በራስህ የምትንቀሳቀስ ነፍስ ያለህ ቤት ሆነህ፥ እኔም በውስጥህ ብኖር፥ ይህ ለጊዜው መሆኑን አስታውሳለሁ። አንተን ትቼ "እውነተኛው እኔን(?)" ብጠብቅ ምን እንደሚሆን አላወቅሁም።

አንተ ምድርን ከሚገባው በላይ ወደሃታል። እግዚአብሔር ወዳለበት ለመሄድና ኑሮህን ከሰማይ ቤት የሚጣጣም ለማድረግ ስትል አልተጋህም። ከመንፈስም ከሥጋም ነካክተህ፥ እያታለልክ እድሜህን ልትቆጥር ፈልገሃል፤ ግን አትችልም። ከእንግዲህ እኔም በምድር ላይ ከአንድ አካላዊ ጋር በመዛመድ ለሰብአዊነት የማበረከተው ከሌለኝ ተገነጥዬ እሄዳለሁ። ሥጋ ጊዜያዊ መኖሪያ ቤት፥ ጥቅሙ ለመሬት ስለሆነ፥ በቅቶኛል፤ ከመጣሁበት ልመለስ።

በሁለታችን መካከል የእግዚአብሔር መንፈስ ከሌለ፥ እኔም ቀባጣሪ ነኝ። የሁኔታዎች መፈጠር ሁለታችንም የተለያየን ፍጥረታት መሆናችንን አረጋግጦልናል። አንተ የምታደርገውና የምታስበው ሁሉ ከምድር የማይላቀቅ ነው። እኔ ላንተ ብዬ ደከምኩ፤ ካንተ ያገኘሁት ምንድነው? መንፈሳዊ ስሜቶቼን ላንተ ብዬ አልለውጥም። በጣምራነት አብረን መኖራችን ለእግዚአብሔር የማይጠቅመው ከሆነ፥ እርሱ በፈቃዱ ይለያየናል።"

**ቶማስ**

*"እኔ በእግዚአብሔር ሥራ ጣልቃ አልገባም፤ ግን የለሁም እስከል ድረስ ተስፋ ቆርጬ፥ ጎዶሎነቴ ሲሰማኝ፥ መንፈስ አይራቀኝ፥ መንፈስ አይራቀኝ እያልኩ ስማጸንህ ተገነጥዬ እሄዳለሁ እያልክ ታስፈራራኛለህ፤ ጨኸቴን ስትቀማኝ የኔን ላንተ አደረግህ።*

*መናፍስት የሚያድሩበትን ሥጋ እራሳቸው እንዲመርጡ ዕድል የተሰጠበት ዘመን አይደለም ያለነው። በፈቃድህ ከኔ ተለይተህ ለመሄድ ምንም ሥልጣን እንደሌለህ እያወቅኸው፥ ከመስማማት ይልቅ ቅራኔዎችን ታበዛለህ።"*

**ዮሐንስ**

*"እውነትክን ነው እኮ ጃል! እህ!....ምን ይደረግ፤ ይህስ የበላይ ትእዛዝ ሊሆን ይችላል፤ እህ!....ምን ይደረግ - ካለፈቃዴ ካንተ ጋር እንድቆይ ሲነገረኝ........። አዎ! እኔ ላንተ የተሰጠሁ ነኝና አልለይህም።*

*ይሁን! ይሁን! ይሁን! .. ግን! እኽ!! .. ለጊዜውም ቢሆን የምኖርበትን ቤት ላድስ - ልጠግን ብዬ ብነሳ መች እሺ ትላለህ? በስብሰህ በመውደቅ ላይ እንዳለህ እራስህ እያወቅኸው፥ አንተን ለማቅናት የሚደረገውን ሙከራ ሁሉ የምትከላከል የራስህ ጠላት በመሆንህ እኮ ነው አንድ ወጥ እራስክን ያጣኸው።*

*መናፈቅ፥ መከጀል፥ መጓጓት፥*

*ላይደርሱበት አጉል መንጠራራት፥*

*ብቅ ጥልቅ አንድ ቦታ አለመርጋት፤*

*ባጥር ላይ መንጠልጠል፥ ዥዋዥዌ - ወዲያ ወዲህ ማለት፥*

*የጥሩን ጥሩነት፥ የመጥፎን መጥፎነት አለመለየት፥*

*አንዱን መርጦ አለመርጋት።*

*ጸጸት የማናውቅ፥ በኃጢአታችን የማናፍር፥*

*ሁሉንም ሽፍንፍን - ሽፍንፍን፥ ተብለጭልጮ መስሎ ማደር።*

*ጥፋትን በሌላው ላይ ማላከክ፥ እራስን ማሞካሸት፥*

*ይህ ነው ለሥጋው የሚያድር፥ የሰው ፍጥረት ማለት።"*

**ቶማስ**

*"እነሆ! የራሴን የክፋት ማዕበል ለመቀነስ እና ጥሩ ሰው ለመሆን ስለፈለግሁ፥ የምሄድበትንና የምደርስበትን ሥፍራ ሁሉ ውሱን አደረግሁ። የንግግሬ ቋንቋ ወደ ጥቅል ሃሳቦች እያዘነበለ ተራ ወሬ ማውራት እስኪያቅተኝ ድረስ፥ እኔ በራሴ ክልል ውስጥ ሆኜ እኔነቴን በማሳነስ ድምጼን አጥፍቼ ተቀመጥኩ፤ አካል ሆኜና በአካል ታጥሬ ሳለሁ፥ እውነተኛውን ሰው ከውስጤ እስካገኝ ድረስ ብቻዬን ስቆይ፥ ይህ ወደ መንፈሳዊነት ያዘነበለ ኑሮ፥ ተሐድሶ መንፈስ የማገኝበት መስሎኝ....።*

*የአስተሳሰቤ ዝንባሌ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ወደ አለማዊነት ያመዘነ እየመሰለኝ፥ ምንጊዜም እራሴን ለማስተካከል እሞክራለሁ፤ እራሴን ለማስተካከል ስሞክር ደግሞ፥ እራሴን እጠራጠረዋለሁ። ታዲያ፥ የእኔን ምድራዊ አስተሳሰብ ለሌሎች አላስተጋባም ብዬ ነው፥ ከሰዎች የምርቅ።*

*እራሴን በራሴ በደልኩ፤ የሚሰማኝም ሰሜት ሁሉ (የንዴት፤ የቁጣ፥ የሃዘንም ቢሆን) እኔን ተቆጣጠረኝ እንጂ፥ እኔ በራሴ ላይ ምን ሥልጣን አለኝ? ፍላጎቴና አስተሳሰቤ አልጣጣም ሲል፥ እኔ ቤት ሆኜ በውስጤ የሚኖር ሌላ ሰው ስላለ እኔ አልናገርም፤ ዝም ብዬ ልኑር አልኩ። ማነው ቤቱ? ማነው ነዋሪው? ማነው ባለ ሥልጣን?*

*ብዙ ብዙ መንፈሳዊ ክስተቶች ሲፈጸሙ እየታየኝ፥ "እኔ ከኃጢአቴ እስክነጻ ድረስ ሃዘንተኛ ሆኜ፥ ደንዝዤ እቀራለሁ እንጂ፥ ማን ደፍሮ ይናግረኛል - አንተ ሰው ለራስህ የሚጠቅምህን ባለማወቅህ ከፉኛ ተጎድተሃል ብሎ። እኔን ማን ሊመክረኝ ይችላል? በማለት እራሴን በራሴ ወሰንኩ። በጭንቀቴ "እባካችሁ ይህን ታሪካዊ እንቅስቃሴዬን ሁሉ ከሰማይ ቤት መዝግቡልኝ" ብዬ መላእክቶችን ተማጽኘለሁ። መልስ አጥቼ ስጠባበቅ ብዙ ከቆየሁ በኋላ፥ እነርሱም፡*

*"ይህ እንቅስቃሴህ የሥፍራና የጊዜ፥ የሥጋና የመንፈስ ይዘት ከሌለው፥ ለሰው ልጆች ትምህርት አይሰጥም። የጽሑፍህ ግዴታዊነት አሁን ነው፤ ከእንግዲህስ ታሪክህን ወደመፈጸሙ ተቃርበሃልና፤ ይህ የደረሰብህ ስባሬ ሕይወት ያለህበትንና የምትሄድበትን ስለሚያሳውቅህ፥ ለጥያቄዎችህ ሁሉ መልስ ይሆንህ ዘንድ ይጻፍ። ከሰማይ ቤት እርሳስና ወረቀት ስለሌለ፥ መላእክቶችም የሰው ታሪክ መጻፍ ሥራቸው አይደለምና፥ በል አንተው ጻፍ.........." ብለው የነገሩኝ ይመስለኛል።*

*ሁኔታዎች አስገድደውኝ በራሴ ላይ ሃሳብ አብዝቼ ሳለ፥ በየወቅቱ እውነት የሚመስለኝን ሁሉ በወረቀት አሰፍር ነበር። ስጽፍ እየተማርኩ ብዙ ከዘለቅሁ በኋላ፥ ሁሉም በሁሉም ዘንድ ያለውን መናገሬ ለማን እና ለምን እንደሚጠቅም ባለማወቄ ግራ እየተጋባሁ ብዙ ቆይቻለሁ።*

ኦ! እኔ፡- ምንጊዜም በኃጢአቴ የማፍር፥ የማውቀው ሁሉ የሚያሳዝነኝ፥ የማላውቀውም ሁሉ የሚያስፈራኝ፥ በሥጋዊነቴና በመንፈሳዊነቴ የሚታየኝን - የታሰበኝን፥ በስሜት የተቀሰቀስኩበትን ሁሉ (የማውቀው የሚመስለኝን፥ የማምንበትንም)፥ በእውነት ብዙ ብዙ እያለቀስኩ፥ ለእግዚአብሔር እየሰገድኩና ስለ እርሱ ፈቃድ ብቻ እየለመንኩ ጻፍኩ።

ኦ! እኔ፥ በአንድ ግለሰብ የሕይወት ታሪክ (አለማዊ፥ አብዮታዊ፥ መንፈሳዊ....ወ.ዘ.ተ.) ውስጥ፥ ስለዚህች አለም እና ከዚያም ባሻገር ቢሆን የሚሰማኝን በሳይንሳዊና በመንፈሳዊ ፍልስፍናዎች ላይ ተመርኩዤ፥ ባቅሜ ለመግለጽ ስነሳ፥ ምናልባት በዚህ ጽሑፍ ሰዎች የበለጠ ሊቀራረቡና ሊስማሙ ይችሉ ይሆናል በማለት ነበር እኮ።

ከዚያ የከፉ ቀን ጀምሮ፥ መንፈሳዊ ጉዞዬን ለማፋጠን ከምንጊዜውም የበለጠ የተጋሁ ይመስለኛል። ለዚህም ይህ እየተማርኩበት የምጽፈው ምሥክር ነው። ከበድ ያሉ ጉዳዮችን ሳወራ፡- ሰዎች ሆይ፥ እኔስ እንደ አላዋቂ ለፍላፊ ሆኛለሁ እያልኩ እናገራለሁ እንጂ፥ እውነት ነው ብዬ በመጮህ የሌሎችን እውነት አልሸፍንባቸውም። ይህ ነው መነሻዬ።

ካቅሜ በላይ እየተንጠራራሁ፥ የተሰማኝን ወይም ያወቅሁትን እንድናገር ተፈጥሮዬ ያስገድደኛል። በውስጤ ያሉ እውነቶች በራሳቸው ይጮሃሉ፤ ከአንባቢያን እውነቶች ጋርም ተመሰቃቅለው በጋራ የሰብአዊነትን እውነታ ሲያስተጋቡ ይታየኛል።

ሰዎች አለማወቄን አይተው እንዳያሳፍሩኝ መደበቅን ስፈልግ፥ ስፈራ፥ ብስጨት ስልም፥ ከምድራዊነታችን ባሻገር ስለሚኖር ተስፋ እንዲህ አስባለሁ፡- “መሬት ስላለን ብዙ ችግር ደረሰብን እንጂ፥ ሌላ ደጋግ ሰዎችና ደጋግ መንፈሶች ብቻ ያሉበት ሥፍራ ብንኖር ኖሮ፥ ይህ ሁሉ ችግር አይደርስብንም ነበር።”

ደግሜ ሳስብ እድለኞች መሆናችን ትዝ ይለኛል። እኛ የምንኖረው ክፉና ደግ በተቀላቀለበት አለም ነው። ከሰዎች ግንዛቤ ውጪ በሆነ መንገድ፥ በየቅጽበቱ - በየሰኮንዱ ክፋትና ደግነት ይጣራሉ። ክፋት ብቻውን ይቀራል፤ ደግነትም ይለያል። ክፋት ብቻ የሚያይልበት አለም አለ፤ ከዚያም የሚኖሩ ሰዎች አሉ። ደግነት ብቻ የሚያይልበት አለም አለ፤ ከዛም የሚኖሩ ሰዎች አሉ (ይመስለኛል)።

በዚች እኛ በምንኖርባት አለም ውስጥም እንደ መላእክት ተደስተው የሚኖሩ ሰዎች አሉ፤ እንደ ሰይጣናትም ሃዘንተኞች ሆነው የሚኖሩ አሉ። ሃዘንተኞቹ ሁሉ ሰይጣናውያን ወይንም ኃጢተኞች አይደሉም። ግን በምድር ስላሉ ብቻ ያለቅሳሉ። ሲያለቅሱ የሚጮሁት በጠፈር ውስጥ ለሚኖርና መጠነኛም ሆነ ከፍተኛ ግንዛቤ ካለው ሁሉ የሚዳረስ ይመስለኛል።

አጥቂና ተጠቂ ካለበት ሥፍራ ሁሉ ጩኸት ይኖራል። ይህ ከእንስሳትም ሆነ ከሰዎች በየጊዜው ወደሰማይ የሚገባ ጩኸት መልስ ሳያገኝ (ውጤት አልባ) ሆኖ የሚቀር አይመስለኝም።"

__ዮሐንስ__

"በሰዎች መካከል በግልጽ ከሚታዩ - የቆዳ ቀለም፥ የገጽታና የቁመና አካላዊ ልዩነቶች በስተጀርባ፥ በመካከላቸው የሚገኝ የመንፈስ ልዩነት ምንኛ ታላቅ እንደሆነ በድብቅ ተናገርክ።

የማይታየውን ለማየት ስንሞክር ልዩ አለም ውስጥ ይከተናል። ልባዊ ስሜትህ ገብቶኛል። በሰዎች እግር ዙሪያ የሚንጎራደድ ድመትን ስለ ሰዎቹ የምታውቀውን ተናገር ማለትና፥ አንተን ከምድራዊነታችን ባሻገር ጻፍ ማለት አንድ ናቸው። ቢሆንም በትጋት የደከምክበትና የጸለይክበት ስለሆነ ጻፍ። ግን በመጀመሪያ ውሸት ከመናገር ተቆጠብ። ውሸት በመናገር ሌላውን የሚያሳምን ሰው እና ኑሮውን በስርቆሽ ላይ የመሠረተ ሰው አንድ ናቸው።

እራሱን ለተወሰነ አላማ አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ከራሱ ይልቅ እውነትን አስቀድሟል። ስለዚህ ከውስጡ እውነት ቢጮህ፥ ያ ሰው እንደ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ሆነ ማለት ነው።

አላዊቂ ሰው ዝምታው ለሚያውቁ ሰዎች እንቅፋት አይሆንም። አውቃለሁ ብሎ የሚለፈልፈው ግን የሚያውቁትን ያደናግራል፤ ያናድዳልም።

በመጀመሪያ ምድራዊ ችግሮችን ከቅጣት ለይተህ እወቅ። ሰው ሰራሽ ችግር ቅጣት አይደለም። ከሰው የመጣውን ሁሉ እንደራስህ ችግር አድርገህ ማየትና፥ ከሌላው ሁሉ ጋር ሆነህ ከችግር ለመውጣት መጣር ይኖርብሃል።

በሰው ሁሉ ዘንድ ያ<u>ለ</u> እውነት፥ በብዙ አቅጣጫዎች እየፈሰሰ፥ ያለማወቅ ፍርኃትን ያጠፋል። እናም፥ ጩኸት ከሕመም የሚያስታግስ መድኃኒት የሚሆንለት ሰው፥ እኛም በጠፈር ውስጥ የሚሰማን አለን ብሎ የሚያስብ ቢሆን፥ ይህንን በማሰቡ ብቻ መጽናናትን ያገኝ ይሆናል።

በምድራዊ መበላለጦች ምክንያት ተለያይተን የተቀመጥን ሁሉ በመንፈስ አንድ የምንሆንበት ጊዜ ይመጣል። ስንሞት ይቀለናል፤ እስከዚያው ድረስ በምድር የሚኖር ሁሉ ይጮሃል። የጋርዮሽ (የሰውም የእንስሳም) ቃል (የመንፈስ ጸሎት) በጋርዮሽ ከምድር ወደ ላይ ይወጣል። ይህ ጩኸት በጠፈር ሁሉ እንደሚሰራጭ አትጠራጠር። ሰሚ እንዳለን እመን።

“በልሳን ብጸልይ፥ መንፈሴ ይጸልያል፤ አይምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።” 1ኛ ቆሮ፡ 14፡14

ክርስቶስ “አንዲት መበለት ዳኛውን ስለጨቀጨቀቺው ሰማት…” (ሉቃ. 18፡ 1) በሚል ምሳሌ ያስተማረን፥ እኛም ሳንታክት ዘወትር መጸለይ እንደሚገባን፥ ሰሚም እንደማናጣ ሲነግረን ነው።

እነሆ! ሰዎች (የዱር አራዊትም ቢሆኑ) በምድራዊ መጠቃት ላይ እንዳሉ የሚያሰሙት ጩኸት ሁሉ የመንፈስ ጸሎት ሆኖ፥ አንድ ቀን ፍርድ እንደሚያመጣልን አትጠራጠር። ሰሚ አለን፤ ስለዚህ፡- “ሁል ጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ”። 1ኛ ተሰ. 5፡17

ለሁላችንም እንደ እድል ፈንታችን በተሰጠን ብቻ ተደስተን እንኑርበት። ጊዜአችን እስኪደርስ እየጸለይን በተስፋ እንኑር። አዋቂም ብትሆን አላዋቂ፥ ምንጊዜም ተስፋ በውስጥህ ይኑር፤ እርሱ ያቆይሃል፤ እርሱም ያዘልቅሃል።

በሰማይ ብዙ ከመሬት የተሻሉ መኖሪያ ሥፍራዎች ይኖራሉ። በምድር ላይ ኑሮ ባይደላህ፥ አንተ ጥሩ ሰው ከሆንክ፥ የሰማይ ቤት ኑሮ ያካክስሃል። የክርስቲያናዊነት ምሥጢሩ አንዱ ለሌላው እራሱን መስዋእት እስከማድረስ መሆኑን አትርሳ። ፍቅር ካለ ምድራዊ ክፍያ ይለገሳልና፥ አንተም ፍቅርህን ካለ ክፍያ ስትለግስ ደስ እያለህ ይሁን።

ከምድራዊነት ባሻገር በመንፈሳዊነት ብቻ መኖር ቢቻል፥ የሰብአዊነት ፍጹማዊነት ይረጋገጣል። ግን ይህን በምድር አናገኘውም። ሆኖም ለዚህ የመጨረሺያ ግብ የሚያልም ከሁሉ በላይ ፍቅርን ያስቀድማል።

“.. በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባርያዎች ሁኑ”። ገላ. 5፡13 አንዱ ሰው ለሌላው እንደ ባሪያ ሆኖ ቢኖርም፥ ፍቅር ካለ ባርያ የሚለው ስሜት ይጠፋል።

ሰው ከራሱ በመነጨ ጠባዩ ብቻ እርስ በርሱ ጠላት ሆኖ ሊጣላ አይችልም፤ ኃይለኛው ሰይጣን እየታገለው ነው እንጂ። ግን በያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያለ ፍጹማዊ እውነት (የእግዚአብሔር ኃይል - ፍቅር) ከፉውን ሰይጣን ያቸንፈዋል።

አንተ በመጥፎው ጠባይህ ወደ ክፋት በሚወስደው ጎዳና ላይ እንዳለህ፥ መንፈሳዊነትህ ይወቅስሃል። በዚህን ጊዜ በሁለት ትከፈልና ከራስህ ጋር ክርክር ትገጥማለህ። የክርክሩም አይነት፡- በዚሁ በክፋት ጎዳና ልቀጥል ወይንስ ልመለስ የሚል ይሆናል። በክፋት ጎዳና መዝለቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ምድራዊነትህ ይደብቅብሃል፤ መንፈሳዊነትክም ቁልጭ አድርጎ ያሳይሃል። በመጨረሺያ ምርጫው ያንተ ፈቃድ ነው የሚሆነው። ግን ያ ያንተ ፈቃድ እኔና አንተን በአንድላይ ማጠቃለል

አለበት። ከሁሉ አስቀድመህ፥ “ከውሸት ጋር ብዙ ቆይቻለሁ ወይ?” ብለህ እራስክን ጠይቅ።

“እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤ ቀርቦም ሳለ ጥሩት፤ ክፉ ሰው መንገዱን፥ በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ፤ እርሱም ይምረዋል..።” ኢሳ. 55፥6-7

መንፈስ ሲቀርብህ እግዚአብሔር ይገኝልሃል፤ መንፈስ ሲርቅብህም እግዚአብሔር ይርቅብሃል፤ እርምጃዎችህን የምትቆጣጠር፥ የምትሄድበትንም አቅጣጫ የምትወስን አንተው ነህና።

መቼም የሰው ጠባዩ ገና ከፍጥረቱ መሆኑ ጥርጥር የለውም። መንፈሳዊነት ግን ከሰው ጠባይ ርቅቅ ያለና የተለየ፥ ከአካላዊነት ውጪ በራሱ ፍጹማዊነት ውስጥ የሚኖር ነው። መንፈሳዊነት ከሰው ጠባይ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲህ ባጭሩ ተነግሮ የሚያበቃ አይደለም። ስለሰው ጠባይና መንፈስ ግንኙነት እና ልዩነት ተመራምሮ በሳይንስ የተደገፈ መረጃ ማቅረብ አይቻልም። ግን፥ መጨረሺያው ወደ እምነት የሚያመራ ከሆነ፥ ከእምነት የሚፈልቀው አዎንታዊነት ደስታንም ያመጣል።

ጥሩ ጥሩውን ብቻ አስብ፤ ይጠቅምሃል። መንፈሳዊነትን የራስህ አድርግ። ማንም ሰው ምንም ቢናገር (መጥፎም ቢናገር ጥሩም ቢናገር)፥ በጩኸት፥ በንዴት፥ በቁጣም ቢሆን፥ ወይንም በትህትና፤ ሁሉንም በጥሞና አዳምጥ፤ በሰዎች መካከል መግባባት ሊፈጠር የሚችል፥ አንዱ ሌላውን በጥሞና ሲሰማው ብቻ ነውና።”

**<u>ቶማስ</u>**

“ለምንድነው ሰው አንድ እራሱን እንኳን ማስተዳደር የሚያቅተው? ለሰው የራሱ የሆነ በውስጡ ሌላ አስተዳዳሪ አለው እንዴ? ሕይወታችን ከራስ አስተዳዳሪ ጋር የሚኖር የስምምነትና የቅራኔ ውጤት ይመስለኛል።

የሰው ጠባይ የሚመነጨው ከምድራዊነታችን ከሆነ፥ ይህ መንፈሳዊነት የምንለው ደግሞ ከምድራዊነት ባሻገር የሚገኝ መሆን አለበት። ታዲያ ከምድራዊነት የሚያስወጣ መድኃኒት ቢገኝ፥ ያ መድኃኒት ሊገድልም ይችላል እላለሁ። የሚያድን ይገድላል ወይ? የሚገድልስ ያድናል ወይ?”

**ዮሐንስ**

“የሚገድል ሕይወት የሚሰጥ ከሆነ ያድናል ማለት ነው፤ የሚያድን ግን አይገድልም። መጥፎውን ጊዜያዊ፥ ጥሩውንም ዘላቂ ለማድረግ ስንጥር ነው መሻሻል የሚፈጠር። የእለት ህኪቶችን ከመደበቅ ይልቅ፥ በየጊዜው ገልጾ መናገር፥ ችግሮችን ከራስ ላይ ለማራገፍ፥ አማራጭ መፍትሔዎችንም ፈልጎ ለማግኘት ይጠቅማል።

ለንግግር በር ከፍተሃልና፤ ካንተው ጠባይ እንጀምር። አለመደሰት፥ አለመሳቅና ሰውን አለማመስገን፥ ከአሉታዊነት የሚመነጩ፥ ሦስት አበይት መጥፎ ጠባዮች መሆናቸውን አስተውል። እነኚህን ሦስት ጠባዮች ይዞ፥ በዚህ አለም ላይ ከሰው ጋር ተስማምቶ መኖር ይከብዳል።

ሰውን ንግግሩ ያስከብረዋል። እራሱን የማያከብር ሰው ከአፉ ስለሚወጣው አይጨነቅም፤ ስለዚህ የገዛ ንግግሩ ክብር ያሳጣዋል። ክብር ከሌለው ሰው የሚወጣ ማንኛውንም ነገር (ቁም ነገር ቢኖረውም) ሰዎች ይንቃሉ፤ ከእንዲህ ያለ ሰው ምንም ነገር መስማት አይፈልጉም። ክብር ያለው ንግግር ለመናገር አስቀድሞ መከበር ያስፈልጋል። አስቀድሞ ለመከበር ከአፍ ለሚወጣው አስቀድሞ ማሰብና መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ለራስህ እውነት ነው የምትለውን ሁሉ ወደሌላው በምታስተላልፍበት ወቅት፥ ለስለስ እያደረግህ ካልሆነ በስተቀር፥ ለማስተላለፍ የምትሞክረው መልእክት አይዘልቅልህም።

ትእግስት፥ ብልሃትና እውቀት ያለው ሰው የራሱን እውነት፥ ከሌሎች አዋቂዎች እውነቶች ጋር በማዛመድ፥ የእውነትን ሁለንታዊነት - ባለቤት አልባነት በማንጸባረቅ፥ ነገር አስተካክሎ ይናገራል። ሞኝ ሰው ግን አወቅሁ ብሎ፥ ሌሎችን አላዋቂ አስመስሎ ይናገራል።

ምንጊዜም እውነት የጋራ ሆኖ ሳለ፥ በየግለሰብም ደረጃም የሚወሰን (ሁሉም ለራሱ - እንደብጤው) መሆኑን የሚረዱቱ ቶሎ የሚግባቡ ናቸው። እነርሱም ላለመስማማትም እየተስማሙ በሰላም ይለያያሉ እንጂ፥ በጭቅጭቅ ጊዜያቸውን አያጠፉም። ያንዱ እውነት ለሌላው ሙሉ በሙሉ የማይዘልቅ መሆኑን በመገንዘብ፥ ምንጊዜም የራስን እውነት ለራስ አድርጎ ከማንም ሰው ጋር ቢሆን መግባባት ይቻላል።

ምንጊዜም የሰውን የሁለትነት ባህሪ አትርሳ፤ ሰው ካፍህ የሚወጣውን እንጂ ከልብህ ያለውን እንደማይመረምርልህ አትዘንጋ። ብዙውን ጊዜ ካፍህ የሚወጣውና በልብህ ያለው የተገላቢጦሽ ሊሆን ይችላል። ካፍህ የምትወጣ እያንዳንዱ ቃል ለምትደርሰው ሰው ምን ያህል ተስማሚ መሆኗን ሳታረጋግጥ፥ በከንቱ አትለፍልፍ (አትጻፍ፤ አትናገር)። አንተ እውነት ተናግረህ ያን እውነት እንደ መልካም ስጦታ ደስ

እያለህ ካላቀረብክ በስተቀር፥ የምትናገረውም የሚያስደነግጥ (የሚያስፈራ) ከሆነ፥ ካንተ እውነት ይልቅ ለጊዜውም ቢሆን የሌላው ውሸት የተሻለ መስሎ ሊታይ ይችላል።

ካንተ ሰው ሲርቅ፥ ምኔ ነው ለሰው የማይጥመው ብለህ ጠይቅ። ከአንተ አፍ የሚወጣውና የልብህ እውነት ለምን እንደማይጣጣሙ እራስህን መርምር።

እንደምትፈልገው መኖር ሲያቅትህና እንድትጨነቅ የሚያደርግህ የገዛ ቅብጥብጥ ጠባይህ ሊሆን ይችላልና፤ በመንፈሳዊነት አረጋጋው። ላንተ ያልገባህን (ሊገባህ የማይችለውን ሁሉ) አጠገብህ ካለው መልካም መንፈስ (የቅርብ ጓደኛ) ጋር ተነጋገርበት።

"ሁሉን ፈትኑ፥ መልካሙን ያዙ፤ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ።" ፲ኛ ተሰሎ. 5፡21

በተስፋ ጭላንጭል ለማይጓዝ፥ ይህቺንም አለም በአሉታዊነት ብቻ ለሚመለከታት ሰው፥ አስተሳሰቡ ሁሉ (ክፉም ሆነ ደግ) ፋይዳ ቢስ (ጥቅም የማይሰጥ) ስለሆነ፥ የትም የማይደርስ፥ አጉል መፈናጠር (እየዘለሉ መፍረጥ) ሆኖ ሊቀር ይችላልና፥ በተስፋና በአዎንታዊነት ለመጓዝ ሞክር።

በውስጥህ እውነት ቢኖር፥ አንተ በፈለግኸው ሰዓትና አንተ በምትፈልገው መንገድ ሊቀርብ አይችልም። ጥርት ያለው ልመናህን ለፈጣሪ አምላክህ በተስፋና በአዎንታዊነት ከማቅረብ (ከመጸለይ) አትቦዝን።"

**ቶማስ**

"ሰው ከዚህ አለም ውጪ ያለውን ማየት ስለሚያቅተው በውሸት ብቻ ሳይሆን "በተራ እውነቶችም" ይታለላል። ከመንፈሳዊነት ጋር ያልተዋሐደ ምድራዊ እውነት ሁሉ ተራ በመሆኑ ለክፉም ለደግም ሲውል ተመልክተናል። ተራ የሆኑ እውነቶች ክብደት የላቸውም፤ የእውነትነታቸውም ጠቀሜታ ለብዙ ሰው አይዳረስም። ታዲያ፥ አስተሳሰቡ እንደ እንጨት የደረቀ ሰው በተራ እውነቶች እየተታለለ (እየተጠመደም) በቀላሉ ጉዳት ላይ ሲወድቅ አይተናል። በምድር ላይ ከተራ እውነት በስተቀር ምን እናገኝባታለን? አዎ! ሰዎች ተራ የሆነ እውነተኛነታቸውን ለማረጋገጥ ሲሉ እርስ በርስ ይተላለቃሉ፤ ይኸውም ይቀጥላል።

በዚህች ምድር ላይ ታሪክ ሲወራ በታሪኩ ውስጥ በጉልህ የሚታየው ሥጋዊው ክስተት እንጂ መንፈሳዊው አይደለም። በዚህም ምክንያት ግማሹ የሰው ልጅ ታሪክ ተሸፍኗል። ታሪክ ጸሐፊዎች የሚታየውንና የሚጨበጠውን

(በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችለውን)፥ አርኪዎሎጂስቶችና ሌሎችም የስነ ፍጥረት ተመራማሪዎች በቁፋሮ የሚያገኙትን አካለ ቅሪት፥ የሃይማኖት መሪዎችም ከራሳቸውም ግላዊ አስተያየት ጋር በማዳቀል፤ ሁሉም ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔር - ከእግዚአብሔር የሆነውን እውቀት ግላዊ በማስመሰላቸው፥ በምድር ላይ እውነት ሁሉ ተራ እየሆነ መጥቷል። ምድራዊ እውቀት ከመንፈስ ውጪ በሥጋው ብቻ እርቃኑን ሲቀር አስተውለናል።

የሚመስለንን ሁሉ ለማረጋገጥ የሚያበቃ እድሜ አልተሰጠንም፤ በመምሰልና በማወቅ መካከል ያለውን ልዩነት እንኳን አለማወቃችን አንዱ የሰብእነታችን ጉድለት መሆኑ ነው። እውነትን ለመንካት የሚሮጡ፥ ቶሎ ብለውም ለእውነት የሚቀርቡ፥ ከቀረቡም በኋላ እውነትን ለመንካት የሚፈሩ ብዙዎች ናቸው። በሩጫም ሆነ በዝግታ እውነትን የሚነኳት ግን፥ እነርሱ ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ፥ እግዚአብሔርም የሚያስጠጋቸው ናቸው።

ይህች ምድር ለሁለት የማይጣጣሙ ሥጋና መንፈስ ማደሪያ ሆና የሰብአዊነትን አላማና ግብ ታካትታለችና፤ አውቀን አይናችንን ከምንሸፍን፥ ከዚያ ማዶ እንመልከት፤ ከሰው ታሪክ ውስጥ፥ የሥጋ ያልሆነውን የመንፈሱን ታሪክ እንናገርለት፤ ትልቁም ትንሹም ምሥጢር በሆነበት አለም ውስጥ፥ በቀላሉ የሚታወቅና የሚታይ እንኳን ለብዙ ሰዎች ድብቅ ሆኗልና።

በዚህ ባለንበት አለም ውስጥ፥ የመግባቢያ ቋንቋችን መደነጋገሪያም በመሆኑ፥ አንዱ የተናገረውን መልሶ መድገም ጆሮን የሚያሰለች ሆነ። እውነት ግን፥ ካንዱ ወዳንዱ እየተዛመተ ሲሄድ ደጋግመው ቢያወሩትም የእውነት እውነትነቱ እየተጋነነ ስለሚሄድ፥ ሲያወሩትም ሲሰሙትም ደስ ያሰኛል እንጂ አይሰለችም።

ምድራዊ እውቀት ሲጎላ ሰውን ከሰው ያበላልጣል። መበላለጥ ሲኖር፥ የአንዱን ሰው ሃሳብ ማክበር፥ የሌላውንም ማጣጣል ይከተላል። አንዳንድ አዋቂዎች፥ ምሁራንና ፈላስፎች ከሚናገሩት እውነት ይልቅ ስለ እውቀታቸው የሚመጻደቁት ይበልጣል። የነርሱም ጩኸት የትሁታንን አስተሳሰብ ይጨቁናል።

ክብደት የሌለው ንግግር የሚናገር፥ ይህ ሰው ትንሽ ነው እየተባለ ሰሚ ያጣል። አበይት ቁምነገሮችን በአይምሮው አምቆ፥ ያንን አውጥቶ ሲናገር ሰሚ ያጣ እንደሆነ ደግሞ፥ የዝቅተኝነት ስሜት ሊሰማው፥ የአስተሳሰብ እድገቱንም ሊያቀጭጭበት ይችላል። ሰው ሁሉ መናገር ያለበትን መናገር ባይችል፥ የመናገሪያው ጊዜ እስኪደርስ ድረስ እያሰላሰለ ቢጠብቅ ይመረጣል (ለሁሉም ቦታና ጊዜ አለው)። አ! ወደራሴው ልምጣ እስቲ።

እነሆ! እስከ ሽምግልና እድሜዬ ድረስ ጥቂት ነገሮችን ብቻ ተገነዘብኩ። ከዚህም ከዚያም ወደ አንድ አቅጣጫ የሚያመሩ ሁኔታዎችን በማገናዘብና በማጠናቀር እኔ መናገርም ባልችል፥ እራሴን ልተው (ባዶ ልሁን)፤ ከሰብአዊነት ማሕደር እየቀረፍኩ ልጻፍ - እውነትን ከማይፈራ ሰው ጋር ሁሉ (ሃይማኖተኛም ቢሆን ወይም ሃይማኖት የሌለው) ልባዊ ጭውውት ላድርግ በማለት ተነሳሳሁ።

ስለ ሰብአዊ ጠባዮች፥ ስለ ሳይንስና ስለ ሃይማኖት፥ ስለ ቅጣትና ስለ ሃዘን፥ ስለ ምድራዊ ምሬት እና ስለ መጨረሺያው እኔን እያነጫነጨ እንድጽፍ የሚገፋፋ ኃይል በውስጤ አለ በእውነት። ይህ ሰው ኃጢአተኛ ነው ብለህ አትናቀኝ። ኃጢአተኛም ሰው በውስጡ እውነት አይጠፋም።

ሕዝቦችን ሁሉ በአንድ አቅጣጫ የሚመራ ኃይል ሰውን እስኪያነቃው ድረስ ሥራውን ይቀጥላል። ከግርግርና ከልፍለፋ ባሻገር እውነት የሚገለጥበት ጊዜ እስከሚመጣ ድረስ፥ ጩኸት፥ ልቅሶና ማላዘን ስለማይቀር፥ ለወደፊት ይህ እና ይህን የመሳሰሉ ጽሑፎች ግዴታዎች ይሆናሉ (ይመስለኛል)።

**<u>ዮሐንስ</u>**

“ባንድ በኩል ይታይሃል፤ ለደግ ሥራም ታልማለህ። በአይምሮህ የተሰረጹት መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ፍልስፍናዎች ከብዙ ሰዎች አእምሮ ውስጥም ያሉ ናቸው። አውቃለሁ ሳትል የሚመስልህን (የሚሰማህን) በነፃነት ልትናገር፥ በፍርኃት ወይንም ባለማወቅ ታፍነውና ተደብቀው የቆዩ ዋና ዋና ሃሳቦችንም ልትቀሰቁስ ተነስተሃል።

ከምድራዊነታችን ባሻገር እንመልከት ነው የምትል። ይህቺን ምድራችንን እንኳ የምናውቃትን ያህል ስናውቃት፥ ከብዙ አለማወቆች ጋርም እንደሆነ አላወቅንም። ከምድራዊነት ባሻገር ብዙ ክንውን ቢኖር ሥጋዊ በስሜት፥ መንፈሳዊ በልቡና ነው እንጂ፥ ሁሉም ነገር በግልጽ አይታወቅም። ሆኖም፥ ከምናውቀው ባሻገር ሌላም መኖሩን እንመርምር፤ ወይንም ለምናውቀው ነገር ሁሉ ሌላ ሰማያዊ ፍቺ ለመስጠት እንሞክር ማለት አይከፋም። ስለዚህ፥ እኔ ስለፈልፍ እናንተ ስሙኝ፥ ሰማያዊ ትርጉም እየሰጣችሁ የምትል ይመስላል።

ሰዎች ሲስቁ፥ ሲዘምሩ፥ ሲዘፍኑ፥ ስሜቶቻቸውን ሁሉ በተለያየ መንገድ ሲገልጹ፤ ምንጊዜም ትንሽ ትንሽ ከምድራዊነታቸው፥ ትንሽ ትንሽ ደግሞ ከሰማያዊነታቸው ቆንጠር ቆንጠር እያደረጉ ነው።

ሰው የሚያስታውሰው በብዛት ያለፈውን ነው፤ ግን የወደፊቱንም ትንሽ ትንሽ ያስታውስ ይሆናል ከቀሰቀሱት። እንደ ኖሕ ገና በሕጻንነት አፍ አውጥተው

የተናገሩ፥ ከመወለዳቸው በፊት እንደነበሩ ያረጋግጣል (አይደለም?)፤ ከመወለዱ በፊት የነበረ፥ የሚጠብቀውን ስለሚያውቅ የወደፊቱንም ያስታውሳል (አይደለም?)።

ጊዜና አካል የማይለያዩ መሆናቸውን ከሳይንስ ተምረናል። አካል ያልሆነ መንፈስ ለብቻው ቢለቀቅ ጊዜ ምኑ ነው? መንፈስን ጊዜ አፍኖ ስለማይዘው የወደፊቱን እንዳለፈው አድርጎ ያስታውሳል። ለመንፈስ ጊዜ ባለ አንድ አቅጣጫ ጦር አይደለም፤ ስለዚህ ወደፊትም ወደ ኋላም መጓዝ ይችላል፤ አካል ነው በጊዜ የሚገታና በአንድ አቅጣጫ (ወደፊት) ብቻ የሚጓዝ።

ብዙ ነገሮችን (ምድራዊ - ሰማያዊ) አጠናቅረን ስንመለከት፥ ካንድ አለም ሲወጣ፥ ወደሌላውም ሲገባ፥ ሁለቱ አለማት ሲነካኩ፤ በመሃል የሰው ሚናው (ተሳትፎው) ለምክንያት እንደተደነገገለት እንገነዘባለን።

ከሰው ተለይተህ፥ ከራስህ ጋር ስትሟገት በመቆየትህ፥ ስሜቶችህን መቆጣጠር ሲያቅትህ፥ መጻፍ ጀመርክ። ከምድራዊነትህ ነጻ ለመውጣት ስትል፥ የጊዜና የቦታ ወሰን የሌለበት ሃሳብህን መጓዣ መንገድ በማድረግ፥ ስነ አይምሮህን ለቀቅ አድርገህ፥ ሃዘንክን ወደ ፍልስፍና ለውጠህ፥ የማይታየውን ለማስተላለፍ ትሞክራለህ። ደግ ሥርቼ ልሙት ብለህ ተነሳስተሃል፤ ግን ከአንደበትህ የሚወጣው በውስጥህ ያለውን ጥሩነት በማንጸባረቅ ፋንታ መጥፎነትህን እንዳያሰራጭ ተጠንቀቅ።

መጥፎ ጠባዮችህን ሁሉ አስወግደህ፥ እውነት የምትለውን መጻፍ ከቻልክ ጻፍ። ፍሬ ሃሳቦችህን ካለ ብልግና፥ ካለ እልኸኛነትና ካለ ቁጣ መግለጽ ከቻልክ ግለጽ። ብዙውን ጊዜ ሰዎች ጠባያቸው ሆኖ፥ መንፈሳዊ ነገርም ሲጽፉ በትእቢት፥ በመመጻደቅና በትሁታን ሰዎች ላይ የበላይነትን በማሳየት ነው። በእውቀት መኩራራት ስነአይምሮአዊ የእውቀት ግርግዳ ይፈጥራል።

"አትታበዩ በኩራትም አትናገሩ....." (ሳሙ. ቀዳ. 2፡3)።

አስቀድመህ አንተ አንድ እልኸኛ ደንቆሮ መሆንክን ተገንዝበህ፥ እራስህን ከሰው ሁሉ በታች ዝቅ አድርገህ፥ ይህ እኔ የምጽፈው "ከዝቅተኝነትና ከወራዳነት" የመነጨ ሃሳብ ነው ብለህ መጻፍ ከቻልክ ብቻ ጻፍ፤ አለበለዛ አትጻፍ።"

***ቶማስ***

*“እውቀትም መራቀቅ ሆኖ ቋንቋ ቢከብድ ያደናቁራል እንጂ አያስተምርም፤ በቀላል አማርኛ፥ ሕይወቴ፥ እስከዛሬ ቆይታዬ፥ ኃጢአት ብቻ ሆነብኝ፤ ፍሬ ሳላፈራ እንዳልነቀል ፈርቻለሁ።*

*የአይምሮ ሥራ ከማናውቃቸው ነገሮች መካከል አንዱ ነውና፤ እኛን ለማገልገል ብቻ ላይሆን ይችላል በአንገታችን ላይ ቁጭ ያለው። ከጠቅላላ ጠፈር ጋር ግንኙነት ቢያደርግና፥ እኛ ከምናስበው ውጪ ሌላ ሥራ ቢኖረው እኛ አናውቅም። የእግዚአብሔርን ሥራ ማን ያውቃል?*

*አንተ ጥሩ ካልሆንክ የምትጽፈውም ጥሩ አይሆንም የምትል ይመስላል። እኔ ግን፥ በዚህ ግርግር በመላበት አለም ውስጥ ሥጋዊነታችን ሲያስጨንቀን፥ “እስቲ ሰዎች ሰማያዊነታችንንም እየተመለከትን እንጽናና..” በማለት አንዲት ምክር ልመክር ነው የተነሳሳሁት። ይህንንም የማደርገው፥ ሰዎች በቀላሉ የሚገነዘቡትን የምድራዊነታችንን ነገር በማስቀደም ሲሆን፥ ሰው የመንፈሱን ነገር - መንፈሳዊ ማንነቱ ይመረምር ዘንድ የሚረዳ ጽሑፍ ለማስከተል ነው ምኞቴ።*

*ሁሉ ነገር የጋራ ነው፤ የአንዱ ሰው ሕልውና ለሌላውም ዋስትና ነው። ይህማ ባይሆን ኖሮ ሰው ሁሉ እጅግ (ሲበዛ) ግለኛ ይሆን ነበር። ለሕዝቦች ሲሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ሕይወት የጋራ መሆኗን ያረጋግጣሉ። አንዱ ለሌላው የጋራ መሆኑን የተገነዘበ ሰው ለብቻው እንዳይቀር የሚገፋፋውም ኃይል የጋራ ነውና፤ ከምድራዊነታችን ባሻገር ሰማያዊነታችን እንመልከት እያልኩ፥ የስነ አይምሮዬን እርግጠኛነት ከተራ እውነት ጋር በማመሳከርና ከአይምሮዬ ውጪ ያለውን ኃይል በመከታተል የማደርገው ጥረት - በእውነት ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ለሌሎች የማካፈል ጥረት - ይህ ለሰዎች መሰናከል ከሆነ እተወዋለሁ።*

*ሰማሁህ ዮሐንስ፤ አሁንስ በጣም ገባኝ። ሥራችን ሁሉ ለሌላው የሚጠቅም፥ በቅድሚያ ራሳችንን ማረም ስንችል መሆኑ ገብቶኛል።*

*አለማወቅ እያደገ ሰብአዊነትን ሲያሳምመው፥ ወደ ጥፋትም ሲከተው፤ እኔ በበኩሌ የሚታየኝን ብርሃን በገዛ ፈቃዴ አላጨልመውም ብዬ፥ ይህ ምድራዊነቴ አንዳንድ ጠቃሚ ጉዳዮችን ለኔ ከማሳወቁ በፊት ቢፈርስ፥ በማይፈርሰው መንፈስ ውስጥ አለማወቅ እንዳይዛመት ለመከላከል - እኔ ለእኔ (ለመንፈሴ) ብዬም ነው የተነሳሳሁት።*

*በተለይ ይህች ምድር በየጊዜው ለምታስደነግጠን ሰዎች አይዞን! አይዞን! አይዞን! እያልኩ የምጽፈውን፥ አይመለከተኝም የማይል፥ በራሱ የማይመካ ትሁት ሰው ያነበዋል። በአንድ በተወሰነ መንገድ የተቀሰቀሰ የመንፈሳዊነት ስሜት በቀላሉ*

የማይረጋ ስለሆነ፥ ለኔ እውነት የሆነ ሁሉ እውነትነቱ ለኔ ብቻ ሆኖ እንዳይቀር፥ በዝምታ ከመቀመጥ ይሻላል ብዬ፤ ሰውም ብዙ ለማውራት ሲሻ፥ ዘና ብሎ እንደሚጽፈው እንዳይሆን በመቆጠብ መጻፍ ጀመርኩ።

ሰዎች የገዛ ሕይወታቸው ሲበላሽባቸው ረጋ ብለው እንዲያስተውሉ፤...በዚህ አለም ላይ የሚሆነው ሁሉ በምክንያት መሆኑን እንዲገነዘቡ፥ በበኩሌ የሚሰማኝን ለመናገር ተነስቼአለሁ። አንተም በኔ የምትደምቅ ነህ፤ እኔም መንፈሳዊ የሃሳብ ብርሃን ለማግኘት ስል ነው አንተን ሆኜ ልጻፍ ያልኩት። በእኔነቴ ተገንጥዬ ለብቻዬ ለመጻፍ አልደፍርም።"

__ዮሐንስ__

"በዚህ አለመግባባት በሰፈነበት አለም ሁለንታዊ እውነትን አምጥቶ፥ የመረጋጋት መንፈስ በሰው ሁሉ ዘንድ እንዲኖር ሊያደርግ የሚችል እርሱ አምላካችን ብቻ ነው። እግዚአብሔር የሰብአዊነትን የመጨረሻ ግቡን በእርጋታ ይመለከታል፤ አኬሄዱንም ይቆጣጠራል።

አዎ! እኛም የገነት ሰዎች ነበርን፤ በኃጢአታችን ከገነት ብንወጣ፥ አውላላ ሜዳ ላይ ተጥለን አልቀረንም። እውነት ነው፤ ሁለታችንም በምድር ላይ እስካለን ድረስ የኔና ያንተ ተለይቶ አይታወቅም። ግን፥ በመካከላችን ልዩነት ይኖራል፤ ሰው ሁሉ በመንፈሱና በሥጋው ፍጹም ተዋሕዶ የሚኖርበት አለም ውስጥ አይደለም ያለነው። ለሁለት ተከፍለን የምንለፈልፈውም ለዚህ ነው።

ስለ እግዚአብሔር መኖርና ስለ ሥራው እኔን የገባኝ በእንደዚህ አይነት መንገድ ነው በማለት፥ ማንም ሰው በየጊዜው የሚሰማውን ቢመዘግብ ትልቅ ጥራዝ ይወጣዋል። እነሆ! በአለም ላይ አንዳንድ ሰዎች በችሎታቸው ብስል ብለው ተናገሩ፤ እንዲሁም ጻፉ። ከነኚህም መካከል እግዚአብሔርን ያስደሰቱ፥ ያሳዘኑትም ይኖራሉ።

የሃይማኖት ልዩነት መኖሩ አንዳንድ ሰዎችን ሲያስጨንቃቸው፥ በሕይወታቸውም ውስጥ ህኪት ሲፈጠር አስተውለናል። ነገር ግን፥ ሁሉም በጌታ የተማሩ የሚሆኑበት ቀን እስኪመጣ ድረስ፥ ማንም ሰው ምንም ቢያውቅ ጨርሶ ሊያውቅ አለመቻሉን ተገንዝቦ፥ በማንኛውም አቅጣጫ አለማወቅ ፍርኃት እንዳይሆን በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛልን። 2ኛ ጴጥ. 1፡2-3

አንዳንድ ሰዎች ምን ጊዜም መስማት የሚፈልጉትን ነገር ብቻ እየሰሙ መቆየት ስለሚፈልጉ ለዛሬውና ለነገው የሚጠቅማቸውን መለየት ያቅታቸዋል። ቀስ

በቀስ እና በመከራ ብዛት ብዙ ነገር ይከሰታል። እውቀት ተደማምሮ ጠቃሚ የሚሆነው፥ በጥቅል ሃሳቦች ላይ ተስማምተን በጋራ ማሰብ ስንጀምር ነው፤ ትምህርት ቤት ገብተን የምንማረውም ለዚህ ነው።

እንግዲህ አንተ በምድራዊ አመለካከትህ የሰውን ሕይወት ከመጠን በላይ እያቃለልህ፥ በራስህ እና ባካባቢህ፥ በሰውም የእድሜ ገደብ ላይ ብቻ አታሳርፈው። አስተሳሰብህን በብዙ ሺህ ዘመናት በሚቆጠረው የሰብአዊነት እድሜ ጋር አዛምደው፤ ሰማያዊውን ምሥጢር በምድራዊ ርዕዮት አትመዝነው። በትእግስት የሚሠራ ሥራ ሁሉ በቅዱስ መንፈስ ደጋፊነት ውጤቱ ያማረ ይሆናል።

ከፍተኛ በሆነ ስሜት የሚታሰብህ ሁሉ በከፍና ዝቅ እየተርገበገበ ነው ያለው፤ ረጋ እስኪል ካልጠበቅህ ከንግግርህ ስሜትህ ይቀድምብሃል። እውነትን ስትናገር በመጀመሪያ እራስህን ረስተህ መሆን አለበት፤ የዚያን ጊዜ አንተ ኃጢአተኛ ብትሆንም እውነት ለሰብአዊነት መተላለፏ (መነገሯ) ብቻ ተፈላጊና ግዴታ ይሆናል። የዚያን ጊዜ፥ ብትፈልግም ባትፈልግም፥ እውነቶች ካይምሮህ እየወጡ ሌሎችን ያስተምራሉ።

አንዳንድ ግለሰቦች ይህ ታይቶኛል (መልአኩ ሚካኤል ነገረኝ፤ ማርያም ተገለጸችልኝ....) እያሉ በታላቅ ስሜት እንደሚናገሩት ባይሆንልህም፥ እውነት በተለያየ መንገድ ለሰብአዊነት መተላለፏ (መነገሯ) ተፈላጊና ግዴታ ስለሆነ፥ ስትጽፍ ከራስህም የስነ አመክንዮህን ቀጥተኛነት እየመረመርክ መሆን እንዳለበት አትርሳ።"

**<u>ቶማስ</u>**

"ጸሓፊዎችም ከበስተጀርባቸው አነጋጋሪ ሲኖራቸው ነው ጥሩ ውጤት የሚያመጡት የምትል ይመስለኛል።"

**<u>ዮሐንስ</u>**

"ያስኬዳል። መንፈሳዊነት በሃይማኖት ይጎለምሳል፤ የሰብአዊነት እድገቱ መንፈሳዊነቱንም ጨምሮ ነውና። የእውነት ምንጭ አንድ ስለሆነች፥ እውነትን ለመናገር ከፈለግህ ከራስህ ወጣ ብለህ በመንፈሳዊ አይኖችህ ተመልከት። በሰዎች ዘንድ ግልጽ ሁን።

ከእንግዲህ ሕይወቴ ጥሩ ነገር በመሥራት ላይ ብቻ የተመሠረተ ይሁን፤ ከእኔነቴ እውነትን ላስቀድም ብለህ ተነሳ። ጥሩ መሥራት ካቅምህ በላይ ቢመስልህ፥ ወይንም ሰውነትህ ባይፈቅደውም እንኳን፤ በግድም ቢሆን ጥሩ ሰው ለመሆን ጣር።

ጥሩ መሥራት ከቆርፋዳ ጠባይ ጋር እና መጥፎ መሥራት ከለስላሳ ጠባይ ጋር በመጨረሺያ የሚያመጡት ውጤት ሊቀራረብ እንደሚችል ተገንዘብ።

ደግነት ከለሰለሰ ጠባይ ጋር ሲሆን ይጣፍጣል፤ ከሸካራ ጠባይ ጋር ሲሆን ግን ይጎመዝዛል። ስለዚህ በቅድሚያ ጠባይህን አሻሽል (አርቅ)፥ እራስህን ገስጽ (ምከር፥ አርም፥ ተገታ)።

በውስጥህ ደግ እንዲሁም ለስላሳ ሳትሆን መልካም ውጤት ያለው የንግግር ልውውጥ ማድረግ ያስቸግርሃል። ያልኩህን ካሚላህ በኋላ፥ ከሰዎች ጋር ስትነጋገር፥ አስቀድመህ አንተ ከምታናግረው ሰው በታች መሆንክን የሚገልጹ ምልክቶች አሳይ፤ ይኸውም አንገትህን ዘንበል ቀለስ በማድረግ፥ እንደምንም ተጨንቀህ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ሁለት ሦስት አረፍተ ነገሮች ከተናገርክ በኋላ፥ የሚያዳምጡህን ሰዎች ስሜት ለመረዳት ሞክር። ንግግርህ ምንጊዜም የሰዎችን ስሜት እየጠበቀ መሆን አለበት።

እስቲ አስበው፤ አንተ በልብህ እጅግ ጥሩ ሰው ሆነህ፥ ካፍህ የሚወጣው (የምትጽፈውም) ሰዎችን ካንተ ቢያርቅ፥ ያንተ ጥሩነት ለማን ይጠቅማል? ማንም ሰው፥ መጥፎ ሆኖ ሰውን እንዳይጎዳ፥ ጥሩም ሆኖ ጥሩነቱ ሰውን የማይጠቅም እንዳይሆን፥ ድርብ ኃላፊነት አለበት።

ስለዚህ ምንጊዜም በሁለት በኩል (ከራስህ ለሚፈልቀው፥ ከሰውም ለሚመጣው) ጥሩ ሁኔታዎችን የማስተላከል ኃላፊነት ይኖርብሃል። ይህም ማለት በልብህም በአፍህም ጥሩ ሰው መሆን አለብህ ማለት ነው።

“ኮሶን ለልጅ መስጠት በማር ጠቅሎ ነው፤ ማሩ እየጣፈጠው ቆሶው እንዲያድነው” እንደሚባለው ሁሉ፥ ከሰው የሚመነጭ እውቀት ጣፋጭነት ከሌለው፥ ደረቅ እውነት ስለሚሆን፥ ተጠቃሚ ያጣል። ስለዚህ፥ በጽሑፍ ልታስተላልፍ የፈለግኸው ተቀባይነት የሚኖረው፥ ይህን የነገርኩህን ሁሉ ስታሟላ ስለሆነ፥ በቅድሚያ እራስክን አሻሽል። በቆይታ አስብበትና፥ የሰብአዊነትን መልካም (ቆንጆ) ገጽታ ለማንጸባረቅ ተነሳ።

እውነትን እንዴት እንናገራት? አይምሮ ዳዊቱን ሲያነቡለት ይረጋጋል፤ ጽሑፍም ለሁሉ ሰው እኩል አይጥምም። እንግዲህ፥ የሁለታችን የሃሳብ ጉዞ፥ ከምድራዊው ወደ ሰማያዊው ስለሆነ፥ ብዙ መንገድ ይጠበቅብናል።

የማይታወቁ ፍሬ ሃሳቦች የጉዞአችን መሰናክሎች ናቸውና፤ ወዳሰብነው ሥፍራ ካለ ችግር ስተት ብለን የማንገባ መሆናችንን ማወቅ ይኖርብናል።

ችግሮች (የሚታዩና የማይታዩ - በሃሳብና በአካል) በተከታታይ እየመጡ ሲያደናቅፉን፥ ወደተፈላጊው አቅጣጫ እንዳናመራ የሚከላከል ጠላት እንዳለብን

ያስታውቃል፤ ግን ይህ የኛ ጥረት ለመልካም ውጤት ከሆነ፥ የሚረዳን ኃይል ከጎናችን ሊኖር እንደሚችል እወቅና ጸልይ።

መሰናክል ሲበዛ - ሲደራረብ ችግር፥

ያ በአይን የማይታየው ሌባ አጥር እስኪሰብር፥

እንግዲህ ሰሚ ጆሮ ካለህ ስማ -

ይህ ነውና የመከላከያው ምሥጢር፥

ጸሎት - በዙሪያህ የመስቀል አጥር።

የዘመኑ ሰው እውነትን ለመቅመስ የሚፈራ አይመስለኝም፤ ነገር ግን፥ ሰዎች ሁሉ የየግል እምነቶቻቸውን ይዘው በሚኖሩበት ምድር ይህ ነው ትክክሉ ብሎ የጋራ እውነትን ማንጸባረቅ ነው ከባድ። የእውነት እውነትነት ለሁላችንም የጋራ ቢሆን ኖሮ፥ አቴይስቶች (ሃይማኖት የሌላቸው) እና ሃይማኖተኞች ለአንድ እውነት ሲሮጡ፥ ካንድ ሜዳ ላይ ስለሚገናኙ፥ በሃሳብ ይቀራረቡ (ይደጋገፉም) ነበር።

ከምድራዊነት ባሻገር የሚታይ ነገር ባይኖር ኖሮ፥ ለምን ገዳማት በአለም ላይ በዙ? መንፈስም እንደ አካል ሕልውናውን ለሚቀርቡት ሰዎች ያረጋግጣል። ሰዎች ፍርኃት ሲያስጨንቃቸው፥ ወይንም በአለማዊነት ለመኖርም ምድራዊ ብቃት ሲጎድላቸው፥ እንደ መብል እና መጠጥ ለመኖር አስፈላጊ የሆነውን ሰላም ለማግኘት ሲደክሙ፥ ሳያስቡት ወደ መንፈሳዊነት ያዘነብላሉ። አዝማሚያችን ወደዚያው እስከሆነ ድረስ ሁሉም ደግ ነው።"

**<u>ቶማስ</u>**

"ስለ ምክርህ ሁሉ አመሰግንሃለሁ። ሕይወታችንን ወደኋላ መለስ ብለን ስናስተውል፥ ብዙ ስህተት የበዛበት ሆኖ እናገኘዋለን። ምንጊዜም በወቅቱ የምናደርገው ሁሉ ትክክል እየመሰለን ካንድ ስህተት ወደ ሌላ ስህተት እንሸጋገራለን። "ምነው እንዲህ ባደረግሁ ኖሮ!" የማይል የለም። ታዲያ፥ እኔም ያለፈው አልፏልና፤ በምድራዊነት ተጽእኖ፥ ሕይወቴ ስህተት እንዳይበዛበት ነው ወደ መንፈሳዊነት ማምራት የፈለግሁት። ይህም ጽሑፍ በኔ በኩል፥ ላንተም ቢሆን ለምድር ተራፊ ሆኖ የሚቆይ ኑዛዜ (የሃዘን መዝሙር) ነው።

እንደሚሰማኝ የሰብአዊነትን ሁለት ጎን የማሳይበት፥ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ቢመስለኝ (ወይንም አለማወቄ እንዲመስለኝ ቢያደርገው)፥ በሰው ሁሉ ቤት ያለውን ሰው ሲያየው ያውቀዋል ብዬ እገምታለሁ። ብቻዬን አይደለሁም፤ እጠነቀቃለሁ።

ከኔ የሚወጣ ነገር (ወሬ) መልሶ እራሴኑ ፍርኃት ውስጥ እንዳይከተኝ ስል፥ ለአንባቢ የማይጥመው የትኛው ነው? የትኛው ነው እውቀት የጎደለው (እውነት የራቀው)? እያልኩ እራሴን ስጠይቅ ብዙ ዓመታት አለፉ። እኔ ከራሴ ካልወጣሁ በስተቀር እውነትን መናገር የማልችል ደካማ መሆኔን ስገነዘብ ይጨንቀኛል።

ካልሞቱ በስተቀር፥ ሙሉ በሙሉ ከምድራዊው እኛነታችን መላቀቅ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ይገባኛል። ሆኖም፥ እራሴን እያየሁ፥ የሰው ልጅ ይህን ይመስላል ከሚለው ተነስቼ፥ ለሰው ልጅ ስነ አይምሮአዊ ግንዛቤ የሚከብዱ ብዙ ብዙ ፍሬ ሃሳቦችን ለማብራራት የምሞክር፥ "እኔስ የእግዚአብሔር መንፈስ ካልመራኝ በስተቀር፥ በማልችለው ጉዳይ ውስጥ ገብቼ የሰዎችን ቅን አስተሳሰብ አልበጠብጥም.." እያልኩ በማሰብም ነው።

ኃጢአተኛን የእግዚአብሔር መንፈስ አይመራውምና፤ የኔም እውነት ከኃጢአተኛነቴ፥ ከአይምሮ አለመብሰል (ወይንም የእውቀት ማነስ) ጋር ተዳምሮ፥ ከተራነት የማያልፍ መደናቆር ይሆንብኛል ብዬ ፈራሁ። ነገር ግን የሰውን አስተሳሰቡንና ድርጊቱን ሁሉ የሚመራው በጭንቅላቱ ውስጥ የሚገኝ ኬሚካል ከሆነ፥ ያንን ኬሚካል ለጥሩነት የሚያስተካክል (የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ)፥ ወይንም ለክፉ የሚለዋውጥ (የሰይጣን እርኩስ መንፈስ) መኖር አለበት። ታዲያ፥ የሚጠቅምና የማይጠቅመውን እኔ መለየት ባልችልም፥ በበኩሌ ግዴታዬን ልወጣ። ሁላችንም በፍልስፍና ደፈር ብለን ብንነሳ፥ ስለማናውቀውና ስለማይገባን፥ ማስረጃም የማናገኝለትን ጉዳይ ሁሉ መነካካት ባንፈራ፥ ይህ ምድራዊነት የደበቀብን ሁሉ ይታየን ይሆናል።

የማይታዩን ክንውኖች ባናውቃቸውም ይኖራሉ ብለን፥ ያየነውንና የምናውቀውን አስደግፈን በድፍረት እንደምንነጋገረው ሆኖ ቢጻፍ ምናለበት? ሰው ካላወራ ወይም ካልጻፈ፥ የተፈጥሮ ምሥጢር እንዴት ይገለጻል። ከማላውቀውና ከማይገባኝ ሁኔታ ጋር እራሴን ለማስታረቅና ቀሪ ሕይወቴን እንድኖርበት ስነ አይምሮዬን ለመደለል ስል እለፈልፋለሁ። ለተጨነቀች ሥጋዊ ሕይወቴ መጽናኛ በማሰብ፥ እውነተኛ ታሪኬን እንደ ምርኩዝ አድርጌ መጻፍ ስጀምር፥ ዘላቂ ወደ ሆነው የዘላለም ቤቴ የሚያመራኝ መስሎኝ ነው። ለምድራዊው ኑሮዬ እልባት ላበጅለት፥ ለነፍሴም መጽደቂያ፥ እንደ ሥጋ ማደንዘዣ፥ እንደ ንስሐ መግቢያ - ለኔ እንደ "መንፈሳዊ ተጋድሎ" እንዲቆጠርልኝ ብዬ ነው።

አዎ! አዎ! የሰው ልጅ ሥራው ሁሉ እየመሰለው ነው እንጂ፥ በውሱን ችሎታው ላይ ብቻ የሚረጋ አይደለም። በአይነ ሥጋ የማላያት ባለቤቴ (ኮከቤ) ከኔ እንዳትለየኝ ስል፥ ለብቻዬ መሆንና ከርሷ ጋር እየተነጋገርኩ መጻፍን መረጥኩ።

እርሷም፥ “ለኔ የምታወራልኝን ሁሉ፥ እኔ ብቻ ሳልሆን ልጆቻችን፥ ዘመድ፥ ወገን፥ ጠቅላላ የሰው ልጅ እንዲያነበው ጻፈው..” ብላ የምታስተላልፍልኝ የማደፋፈሪያ ቃል መንፈሴን ቀሰቀሰውና፥ “እኔስ እስከ ዛሬ በምድራዊው እኔንቴ ደከምሁ፤ ለቀሪው ሕዝብ ምን ላቆይለት? በራሴና ባካባቢዬ ያለውንስ መንፈስ ምንም ባለማድረግ አላሳዝነውም..” በማለት ለመጻፍ ተነሳሳሁ። ኮከቤም በማይገለጽ አንደበት እንዲህ አለች፡- “ጻፍ (ተናገር) እኛ “ክብራችን” ከምድራዊነት ባሻገር መሆኑን በደንብ አድርገህ ግለጽ።”

የስሜቶቼ ሁሉ ግፊት በል በል ይለኛል። እኔ በምድር ብቸገር፥ መንፈሴ ከባለቤቴና አብረዋት በሰማይ ከሚኖሩት ሁሉ ጋር እንዲሆን እየተመኘሁ፥ እርሷ የተናገረችውን እፈጽማለሁ። እኸኸኸ!! ኃጢአቴ ሁሉ ቁልጭ ብሎ ታየኝ፤ ጥሩነቴንም አስተዋልኩት። መጥፎነቴን ለልጆቼና ለልጅ ልጆቼ እንዳላስተላልፍ ጥሩነቴ በአደራነት ይማጸነኛል። እኔ በተፈጥሮዬ፥ የሰዎችን የመጨረሺያ መጥፎ ጠባይና ርካሽነት የማስተጋባ ብሆንም (በሕይወቴ ሐረግ ከመጥፎነት በስተቀር ጎልቶ የሚታይ አንዳች ጥሩ ነገር ባይኖርም)፤ እግዚአብሔር እኔን ካለ ምክንያት አልፈጠረኝም እኮ።

በሕይወቴ ችግር ባጋጠመኝ ጊዜ፥ ምድራዊ ከፋቶች ሁሉ በረድፍ በረድፍ ተደርድረው መንፈሴን ደብተውት ነበረ። ስሜቶቼ ሁሉ ወደ ልቅሶና ወደ ሃዘን እያዘነበለ ስለመጣ፥ ከሳቅና ከጨዋታ ተወግጄ ነበር። ግን ያም ሆኖ፥ ቤተ ክርስቲያን መሄድን አዘውትሬአለሁ፤ ከዚያም የሚገኘውን መድኃኒት ተቀብያለሁ። ታዲያ፥ ጨለማን ወደ ብርሃን የሚለውጥ አምላክ በውስጤ ያለውን ጽልመት ሊያጠፋልኝ ተነስቷል ብል ቅዠት አይመስለኝም።

መጽሐፍ ቅዱስን እያነበብኩ፥ መንፈሳዊነትን በማገኝበት በዚህ የመጻፍ ሥራ ልቀጥል፤ በቃህ ስባል መጻፍ አቆማለሁ። ይህ የኔ መፍጨርጨር፥ በኑሮዬ ውስጥ ከቃረምኳቸው አበይት ፍሬ ሃሳቦች ውስጥ (ሃይማኖትም ቢሆን/ ሳይንስም ቢሆን) ሁሉንም በሚገባ እንዳስተላልፍ፤ በበኩሌ የሰብአዊነቴን ግዳጅ እንድፈጽም፥ በየቀኑ ለምኖረው ሕይወቴ “ይሰብሕዎ ለእግዚአብሔር” እንድል፥ በቀሪ እስትንፋሴ እግዚአብሔር ኃያል አምላክ መሆኑን እንድመሰክር ነው።

የሰው ልጅ መንፈሳዊ ታሪኩ እየተዳፈነ ምድራዊ ታሪኩ ብቻ ሲወራ፥ የሥጋ ሕይወቱ ሲበረታታ፥ መንፈሳዊ ሕይወቱ ሲዳከም ይታያል። ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች ሁሉ ውስጥ ያለ ስለሆነ፤ ማንም ሰው በሥጋው ደካማነት ቢታይበትም፥ የርሱ ለራሱ እንዲሆን ከተሰጠው መንፈሳዊነት ብርታት ያገኛል። ታዲያ በምድር ታሪክ ላይ ብቻ ማትኮር እንዳይሆንና፤ ከዛም አልፈን እንድንሄድ ስል፥ እኔና ብጤዎቼን ለማደፋፈር ተነሳሳሁ።

አዎን! አውቃለሁ፤ በገዛ አይምሮ ብዙ መተማመን ከስህተት ሊጥል ይችላል። ይገባኛል፤ በሃሳብ ጠንክሮ፥ ከራስ አመንጭቶ መናገር - የድፍረት ንግግር - መጨረሺያውም ከእውነት መራቅ ሊሆን ይችላል። እንደኔ ያለ ደንቆሮ እውነትን ከየት ያገኛታል? በተለይ አንዳንድ አከራካሪ ጉዳዮች ላይ እራስን ለሁለት ከፍሎ በተለያየ አቅጣጫ መመልከት፥ ተቃራኒ ሃሳቦችንም ለማገናኘት መሞከር፥ የተደበቀውን እውነት ለማፈላለግ ይጠቅም ይሆናል። ታዲያ እውነትን ለሁለት ተከፍለን እንናገራት እንጂ፤ ከዚህም ሆነ ከዚያ አንባቢ እንዲያገኛት።"

**<u>ዮሐንስ</u>**

"መኖራችን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ ፈጣሪ አምላካችን በተለያዩ መንገዶች ፈጣሪነቱን እንድናውቅና እንድናምን አደረገን። በተለያዩ መንገዶች ብዙ ነገር አስተምሮናል። እኛ ግን አንማርም፥ ወይንም ተምረን እራሳችንን አናርምም። አንዳንድ ጊዜ አንድ ነገር ትክክል አለመሆኑን እያወቅን፥ በዛው ትክክል ባልሆነ ነገር ላይ እንሠለጥንበታለን እንጂ፥ በዘልማድ የምናደርገውን በቶሎ እርግፍ አድርገን የተሻለውን መርጦ ለመውሰድ አንወድም (እንፈራለን)። በእመርታ የጋራ መንፈሳዊ ንቃት እስክናገኝ ድረስ ገና ብዙ ይቀረናል - "ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ ስላልሁህ አትገረም።" ዮሐ. 3፡7

ቀድሞ በነቢያቶች፥ በኋላም ራሱ ከሰማይ ወርዶ በምድር ላይ እውነትን ብቻ ስለተናገረ፥ መድኃኒ አለምን አሰቃይተው ገደሉት። ተከታዮቹም እንደሱ እውነትን ስለተናገሩ እየተሰቃዩ ተገደሉ። የተለያዩ ሃይማኖቶችን ለሚከተሉ የአለም ሕዝቦችስ፥ እግዚአብሔር ምን ያላደረገው ነገር አለ። ግን ስንመለከት፥ ከሁሉም ሥፍራ እንዳሰበው አልሆነለትም እንድንል ወይንም እንዳንል የሚያደርጉንን ድርጊቶች አልፎ አልፎ እናያለን።

እግዚአብሔርስ የፈለገውን ማድረግ አልቻለም ከማለትና ገና ፈጥሮ አልጨረሰንም ከማለት የትኛው ይቀላል? እግዚአብሔርስ ፈጥሮ አልጨረሰንም ከማለትና፥ እግዚአብሔር እኛን በመንፈስ እርሱን አስመስሎ ፈጥሮን ሳለ፥ ከምድራዊነታችን ጋር እየታገልን መንፈሳዊነታችንን እንድናጎለምስ ለኛው ለራሳችን ፈቃዳዊነት ለቆናል ከማለት የትኛው ይቀላል? እግዚአብሔርስ ፈጥሮ ለቀቀን፥ እኛስ በፍጥረታችን ላይ ያመጣነው ለውጥ ምንድነው?

ከጥንት ጀምሮ፥ እግዚአብሔር በሰውና ለሰው የሞከረው ሁሉ መንፈሳዊ እድገትን ቢያሳይም፥ በውስጡ ብዙ ውድቀት የበዛበት እንደነበረ፤ የእግዚአብሔር አላማ ገና ሙሉ በሙሉ አለመሳካቱንም ነው ከመንፈሳዊ ታሪካችን የተማርነው።

እግዚአብሔርስ የሚፈለገውን ማድረግ አላቃተውም። እኛ ነን እንጂ የወደፊቱን ማየት ያቃተን፤ እግዚአብሔርስ የሚፈልገውን አድርጓል - በእርሱ ጊዜ - አዎን በእርሱ ጊዜ።

አንዳንዴኮ፥ “እኔ በራሴና ከራሴ የሚመነጭ እውቀት የለኝም” ብሎ፥ ስለ መንፈስ ነገር ክፍተት መስጠት (እምነት) ይጠቅማል። እኛ በጸሎት ተነስተን የምንሠራውን ሥራ እግዚአብሔር ይባርክልናል ብለን እናምናለን። አባት ልጆቹን እንደሚያስተምር ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ልጆቹን ያስተምራቸዋል። ከሚሰለች፥ ከሚያደክም እና ከሚያበሳጭ አለም ፈቀቅ የሚያደርግ፥ በችግርና በመከራ ተምሬ ይህን አወቅሁ የሚል ጽሑፍ የተባረከ ነው። ወደ እውነት የሚወስደውን ጎዳና ሲያገኝ ደስ የማይለው ማነው? እንግዲህስ ለአንባቢያን የሚጠቅመውን ለማስተላለፍ፥ የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ማስተዋል ይገባናል፡-

1ኛ) እውነት ሲነገር፥ እውነተኛነቱን ብቻ ተከትሎ ስሜታዊነት እንዳይበዛና፥ ሰሚዎችን (አንባብያን) እነርሱንም ካለውዴታቸው አላስፈላጊ ስሜት ውስጥ እንዳይከታቸው፥ ከግል ስሜት ተጽእኖ መውጣት ያስፈልጋል።

2ኛ) የራስን ስሜት ለራስ አቆይቶ፥ ለብዙኃን የሚቆየውን በጊዜ ውስጥ (ብዙ ዓመታትም ቢፈጅም) ፈትኖ፥ የሚጠቅመውን ማስተላለፍ ያስፈልጋል። ሆኖም፥ ታሪክን ታሪክ የሚያደርገው በጊዜው የሆነውን ካለመለወጥ በማቅረብ ብቻ ነው።

ጥሩነት አንድ አይነት ነው፤ ፍጹምም ስለሆነ፥ የሰው ልጅ ጥሩነቱ ከመላእክት ጥሩነት የተስተላከለ እንጂ፥ የሚያንስ ወይም የሚበልጥ አይሆንም። ሰው ግን ሥጋን ስለተሸከመ፥ እየበላና እየጠጣ፥ ፍጹም ጥሩ ይሆን ዘንድ ይቸገራል። ሆኖም፥ በምድር ላይ የጥሩነት መጨረሺያው መጥፎ ሊሆን አይችልም። ከእንግዲህ ከግለሰብ እስከጠፈር የምታስበውን ሁሉ ለመጻፍ አትፍራ። ግራ የተጋባህበትንና ልትገታው ያልቻልከውን ምድራዊ እይታህን ስትጽፍ ዝም አልልህም፤ አይዞህ፥ አብሬህ እሆናለሁ።

ስለራሱ የሚጨነቅ ሰው ስለ ሌላው ማሰብ ያቅተዋል። አንተ ከራስህ ሳትወጣ የምትጽፈው ሁሉ ውሱን ስለሚሆን፤ ቆይ! ቆይ! እስኪገባህ ድረስ ብዙ ቆይ እያልኩ አዘገየሁህ። አሁን ግን ካንዱ ታሪክ ሌላው ስለሚማር የምድርን ለምድር በመተው፥ እራስህን ከሰብአዊነት ጋር በማዛመድ (በልብህ የተከፉ ወገኖችህን እቅፍ አድርገህ) በፍቅር ትጽፍ ዘንድ እኔም ልተባበርህ ወስኛለሁ። የእግዚአብሔርን ኃያልነት ማንጸባረቅ ለፍጥረታት ሁሉ የተሰጠ ጸጋ ነው። “የሰማነውንና ያወቅነውን፥ አባቶቻችንም የነገሩን፥ ለሚመጣ ትውልድ ከልጆቻቸው አልሰወሩም።” መዝ. 77፡3

አዎ! ሰዎች “እብድ” ብለው የሚጠሩትን ብቻውን ከመንገድ ላይ ቆሞ የሚለፈልፈውንም፥ ለሰዎች ጠቃሚውን እንዲናገር የሚያስችል አምላክ አለን። ወሰን

የሌለው አምላካችን ትንሽ መሆንንም ያውቅበታል፤ በታናናሾች ውስጥም እየገባ ሰዎች መሥራት የማይችሉትን ሥራ ያሠራቸዋል፤ መላእክትንም ለሰዎች ተራዳኢ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ፥ የነርሱን እርዳታ የሚጠይቅም የጠየቀው ይሰጠዋል።

አወቅነው፥ አየነው ከምንለው በስተጀርባ የሚበዛው ያላወቅነውና ያላየነው መሆኑ፥ ከምድራዊነታችን ባሻገር ልዩና አዲስ አለም እንደሚኖር ያመለክታል። በምድር የሞተ ሕይወት ሁሉ በሰማይ ነፍስ ሲዘራ፥ ምድራውያን የሚማሩበት መንገድ ቢኖር ማን ያውቃል? ምድራዊ እውቀት ብቻውን በቂ አይደለም። መንፈሳዊ ስሜቶችን በጎን የሚያነካካ ቢኖር፥ ይህ በአይምሮ የሚታሰብ ብቻ መሆን አለመሆኑን የሚያውቅ የለም።

የግድ እንድትናገር የሚያቅበጠብጥህን ሌላው ሰው ከሚያውቀው ጋር እያመሳከርህ ተናገር እንጂ፥ ሌላው የማይገባውን ወይም በማስረጃ ያልተደገፈ ወሬ አትቀባጥር። ማወቁን ለማሳወቅ ብቻ የሚናገር ሰው የሌላውን እድገትና መሻሻል አይመኝም። ከሰው ሁሉ ጋር አብሮ የማያድግ እውቀት ያደናቁራል እንጂ ምንም አይጠቅምም። አንድ ግለሰብ ለብቻው የሚያውቀው አንዳችም ነገር የለም ማለቴ ነው።

የአጠቃላይ ሰብአዊነት እውቀት እዚህ እንዳደረሰን ሁሉ፤ ለወደፊትም ይህ የጋራ እውቀታችን አብሮ ሲያድግ ነው የማይታየውንም የሚያሳየን። አንተም ከዚህ የጋራ እውቀት ተገንጥለህ፥ ብቻህን የምታውቀው ነገር አይኖርም። ሁሉም የሁሉም ነው።

እውነት በኃጢአተኞች ውስጥም ባትገኝ ኖሮ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአተኞች ጋር ምግብ ባልበላ ነበር። እውነት ከማንም ዘንድ ትገኛለች። እውነትን ሲናገሯት ኀልታ ትታያለች፤ ታብባለች። እውነት ኀልታ ስትታይ፥ እርሷ እጅግ ቆንጆ ስለሆነች፥ ተናጋሪዋንም ቆንጆ ታስመስለዋለች። በውሸት እውነት ትንንቅ መካከልም ቢሆን፥ እውነት በሰዎች ታድጋለች። እውነትን ይዞ የሚደብቃት ግን፥ እርሱ የራሱን እድገት በገዛ ራሱ የሚከላከል ነው። በሥጋው የተጎዳ ሰው ከቀደሙ መንፈሳውያን ጋር የተያያዘ መንፈሱ ያጸናዋልና፤ እየጸለይክ ጻፍ። እውነት ሲጋነን ወደ ውሸት ይዞራልና፤ ጽሑፍክንም በጥንቃቄ እየጻፍክ በተደጋጋሚ ከልስ።

ሰዎች በምድራዊ ቋንቋ ቢናገሩ (ቢጽፉም) የማይስማሙት ፍጹምነትን ቋንቋ የማይገልጸው በመሆኑ ነውና፤ ከደከሙ ቃላቶች (ወይንም አስተሳሰቦች) በስተጀርባ፥ አንባብያን የራሳቸውን ፍጹማዊ ጥሩነት እንዲቀሰቅሱ፥ ከመንፈስ ቅዱስም እንዲማሩ እንጸልይ። የሰው ልጅ አሉታዊነትን እየቀነሰ፥ በአዎንታዊነት ቢጓዝና ጠቃሚ በሆነው ላይ ብቻ የሚያተኩር ቢሆን ኖሮ፥ መጥፎው ወደ ጥሩ መለወጡ

አይቀርም ነበር። በዚህም ሆነ በዚያ ሕይወታችን በሰው ችሎታና መፍጨርጨር ብቻ እንደማይወሰን ሁሉ፥ የጎበጠውን እንዲያቀና፥ የቀናውንም ወደ ሰዎች አይምሮ ገብቶ ጥሩ ጥሩውን እንዲያስመለክተን በጸሎት መማጸንና መቆየት ያስፈልጋል።

እስከ ዛሬ ድረስ በአለም ላይ የነበሩ፥ ያሉና ወደፊትም የሚኖሩ ሰዎች እውቀት ቢደመር፥ ለአንድ እግዚአብሔር ኢምንት እንደሚሆን ሁሉ፥ ከግለሰብ ማንነትና ከግላዊነት ከሚመነጭ እውቀት ይልቅ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለበት ጽሑፍ ነው ለሰው ልጅ የሚጠቅም። ስለዚህ፥ "ለይኩን ፈቃደ አምላክ" ብለህ ተነሳ።

ጊዜና ለውጥ በአንድነት ወደፊት ብቻ ይጓዛሉ። የጠቅላላ ሰብአዊ ችሎታ መጨረሺያው፥ አቅጣጫውና አካሄዱ፥ ለዛ ለወሳኝ ቀን ያዘጋጀዋል። ሰው ሲሞት፥ እውነት በምድር ብልጭ ሲል፥ ፍቅር ሲዘራ፤....ይህ መጽሐፍ ከምድራዊነታችን ባሻገር ለሚሰማን መንፈሳዊ ደስታና ብሩህ ተስፋን የሚሰጥ፤ የፈጠረን ቸሩ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ምልክት - እርሱ የሚፈልገውን ፈቃዱን መፈጸሚያ ያድርግልን። አሜን።"

# ደብዳቤ

ይድረስ ለተከበርሽውና በጣም ለማፈቅርሽ ለውድ ባለቤቴ ኮከቤ።

ሁለታችንም ባለንበት የሚጠብቅ አምላክ ስለ ደህንነትሽ አሳውቆኛልና፤ ደስ ብሎኛል። በሥጋ ከመለየትሽ በፊት ስለእኔነቴ ሙሉ ለሙሉ እንድነግርሽ መንፈሴ በየጊዜው ያሳስበኝ ነበር። ብዙ ሰው የራሱን ታሪክ ባደባባይ ያወራል፤ የኔው ግን በአፍ ማውራት ቀርቶ፥ በጽሑፍ እንኳን ለማቅረብ ይከብዳል። የቅርብ ጓደኛዬ የሆንሽ አንድ አንቺ ብቻ ብትኖሪኝ፥ ወሬዬን በየጊዜው እየጀመርኩልሽ የማልጨርስበት ምክንያት፥ የማስታውሰው ነገር ድንገት ጥፍት ሲልብኝ የማቋርጥ በመሆኔም ነበር። አልጨረስኩትም እንጂ አብዛኛውን አውርቼልሻለሁ።

ሁሉንም ገልጬ ያልተናገርኩ፥ ሕይወትሽና ሕይወቴ ደግ ደጉን በመስማት ላይ ብቻ የተመሠረቱ እንዲሆን በመመኘት ነበር። ወሬ የማያስጨርስ መንፈስ እየተከላከለኝ ብዙ ቆይቼ ሳለሁ፥ አንቺ ድንገት ታመምሽብኝ። እኔም ጭንቀት ያዘኝና፥ ባይሆን ይህን ባፌ ማውራት ያቃተኝን እስቲ ልጻፈው ብዬ መጻፍ ጀመርኩ።

አንቺ ከምድር ለቀሽ ስትሄጂ ከፍተኛ ድካም ተሰማኝ። በእጆቼ እቃ ማንሳት እንኳን ተሳነኝ። ግን መቼም ሰው ደግ ነውና፤ የኔና ያንቺ ዘመዶች፥ ጓደኞቻችን እና ወገኖቻችን - በራሴ ብርታቱን እስካገኝ ድረስ ረድተውኛል። ምስጋና ይገባቸዋል። ተመስገን።

እኔን ካንቺ ጋር የሚያገናኘኝ እና ብርታት የሚሰጠኝ መንፈሴ እስኪረጋጋ ድረስ፥ የጻፍኩት እንዳይጠፋ፥ ሰውም እንዳያየው በማለት፥ ከጌጣ ጌጦችሽ ጋር አድርጌ፥ ወደ ባንክ ሄድኩና ባለ ዋስትና ሳጥን ተከራይቼ አስቀመጥኩት። ልጆቻችንም “ለምን ይህን ታደርጋለህ?” ብለው ጠየቁኝ፡ እኔም “እናንተን ለማሳደግ የተረፍሁ እኔው ስለሆንኩ፥ አይምሮዬ እስኪረጋጋ ድረስ ሃሳቤ ሁሉ በእናንተ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ብዬ ነው አልኳቸው።” እግዚአብሔር ይመስገን፤ አሁን ደህና ነኝ፤ ልጆቻችንም ደህና ስለሆኑ አታስቢ ኮከቤ።

ከጊዜ በኋላ “ብዙ ነገር በጣም ሲገባኝ” በኔ በኩል ያለውን ሁሉን ነገር እንድታውቂ በማለት ጽሑፉን ከባንክ በማውጣት ለመጨረስ ወሰንኩ። በእውነት እኔ ገና ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙውን ጊዜ ከሰው ጋር ከማወራ ከራሴው ጋር ባወራ ነበር የሚቀለኝ። አንቺን ካገባሁ በኋላ ግን፥ ካንቺ ጋር ሳወራና ስጫወት ያሳለፍኳቸው ወርቃማ ጊዜያቶች በእርግጥ የሰው ልጅ ደስታው ከሌላ ሰው ጋር እንጂ በብቸኝነት የማይገኝ መሆኑን አረጋግጠውልኛል።

አንቺ ስትለዪኝ፥ እኔም ከጎኔ ላገኝሽ የማልችል መሆኔ በደንብ ሲገባኝ፥ ካንቺ ጋር ደስ እያለኝ የኖርኩት ጊዜ ብቻ ምድራዊ ሰማያዊ ትዝታ ሆኖ ቀረ። የብቸኛ ኑሮ አስመረጠኝ። ሞቃት ኑሮን የሚያሰናክል ሞት ቅስሜን ቢሰብረውና በምድራዊነቴ ተስፋ ቢያስቆርጠኝም፥ አሁንም በመንፈሳዊነቴ አብረን እንዳለን ሆኖ ነው የሚሰማኝ።

ያሳለፍናቸው ጊዜያቶች ለመንፈሳዊ ጉዞአችን ምክንያቶች በመሆናቸው፥ የአንቺ ሕይወት እና የኔ ሕይወት አብዛኛው በመንፈሳዊነትም የተሳሰረ እንደነበር ሁሉ፥ አሁንም በዚሁ ጸንቷል።

ባለቤቴ ሆይ! በምድር ሳለሽ በጣም አፈቀርኩሽ፤ አሁን ደግሞ በፍጹማዊ ፍቅር የባሰ አፈቀርኩሽ። አንቺ ግን፥ እኔ አንዴ ሄጃለሁና ልቅሶ አታብዛ ብለሽ በድምጽ አልባ አንደበትሽ ተናገርሽኝ። እኔም እንዲህ አልኩ፥ “እርግጥ ሰው በኑሮው ውስጥ ደስታን ሲሻ አያለቅስም፤ ግን ሰው ሲበደል ከጎኑ ያ<u>ለ</u> ሌላ ሰው ካላዘነ - ካላለቀሰ (ሰውን ሰው ካልሰማው) የእግዚአብሔርስ መንፈስ እንዴት ከሰዎች መንፈስ ጋር ሊተባበር ይችላል? የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሰብአዊ ርህራሄዋ በሚወዷትና በምትወዳቸው መካከል ሲኖር አንዱ ለሌላው ማዘኑ አይቀርም። እመቤታችን ድንግል ማርያም በምድር የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እየተመለከተች ለሰዎች ሁሉ ስታዝን - ስታለቅስ፤ በእውነት በአንድ ሺህ አቅጣጫ ለሚጠቁ ሰዎች የሚያዝኑቱ፥ በእውነት መንፈሳዊ ርህራሄ ከስነአይምሮአቸው የተቀረጸባቸው ናቸውና፤ ማርያምንና የተጎዱ ሰዎችን ሁሉ እያሰቡ ያዝናሉ። አንዳንዴም እንባቸው ሳያስቡት እንደ ውሃ ይፈሳል።

እህህ ኮከብዬ!........ በምድር የመኖር ትርጉሙ የሰው ልጅ በአካላዊ ሕይወቱ ላይ የሚደርስበት ሁሉ ለመንፈሱ ትምህርት ሆኖ ለመጪው ዘለአለማዊ ሕይወት እንዲያዘጋጀው በመሆኑ፥ እኔ በውዴታም ሆነ በግዴታ ሳልመጣ ቀርቻለሁ። በምድር ተሳታፊ እንጂ አድራጊ - ፈጻሚ አለመሆኔ እየገባኝ ሲመጣ፥ ለካስ ኑሮ ማለት እንዲሁ ነው እንድል የሚያደርገኝ ፍልስፍና ውስጥ ሳልወድ ገብቼ፥ ይኸውልሽ የጽሑፍ ለፍላፊ ሆኛለሁ። ምን ይደረግ ብለሽ! አፍ የምታካፍቺኝ አንቺው ብትኖሪ፥ ከጎኔ እልም ብለሽ ስትሄጂ።

ከልጆቻችን ጋር መሰንበት ለኔ አንድ ትልቅ በአካል የመገኘቴ ምክንያት (ጸጋ) ሆኖልኛል። ለነርሱ ብዬ የምኖር ቢሆን እንኳን ይበቃኛል። በአፌ የነገርኳቸው የልጅ አዋቂዎች አድርጓቸዋል። በኋላ ሲያድጉ ደግሞ ከጽሑፉ ብዙ ብዙ እንደሚማሩልኝ እተማመናለሁ። ከሃብትና ከንብረት፥ ከወርቅና ከከበረ ሽቱ የሚበልጠውን - መንፈሳዊነታችንን ከምድራዊነታችን ባሻገር አርቅቀው እንደሚመለከቱት፥ እንደሚኖሩበትም ተስፋ አደርጋለሁ።

አሁንም ለአንቺ በአካላዊነት ለማትታዪ ደግ ሴት በእውን በአካል እንዳለሽ አስመስዬ ይህን ስጽፍልሽ፥ ካጠገቤ የማይለየው መልካሙ አስተሳሰብሽ መንፈሳዊ ግፊት እየሆነ፥ ሁለታችንም በፈጠረን አምላካችን ያለን እምነት የምንገልጽበት መድረክ ውስጥ የከተተኝ እየመሰለኝ ነው።

እንዲህ ሆነ፤ ይህ ተፈጸመ እያልኩ እኔ ለብቻዬ እንዳላወራና ካፌም ውሸት እንዳይወጣ አንቺ ጠባቂ (ምስክር) ትሆኛለሽ እያልኩ እጽፋለሁ።

በይ እንግዲህ ኮከብዬ! ወዳንቺ እስክመጣ ድረስ፥ ስለ “ሁሉም ነገር” የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየለመንሽ ጠብቂኝ። እስከዛው ደህና ሁኚልኝ፤ በሰላም ለመገናኘት ያብቃን።

በቶማስና በዮሐንስ የተከፈልኩ እኔው ነኝ ባለቤትሽ።

# ምዕራፍ ሁለት

## ግለሰብና አብዮታዊ ውዝግቦች

ሞኝ አይሉት ብልጥ፥ ፈሪ አይሉት ደፋር፥ ደንቆሮ አይሉት ጠቢብ፥ አላዋቂ አይሉት አዋቂ፤ እንዳው ባጠቃላይ የቅጽል ስም የማይሰጠው፥ በአንድ ወቅት አንድ ግለሰብ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይኖር ነበረ። ይህም ግለሰብ እኔው ነኝ። ሰዎች "የት ጠፍተህ ነበር? ከየት ብቅ አልክ"? ሲሉና እኔም መልስ ለመስጠት ያልቻልኩበትን፥ ጊዜ ከዝምታ ፈልቅቆ ያወጣውን ወሬ አውርቼ ልጨርሰው ተነስቻለሁ።

በኢትዮጵያ አብዮታዊ ታሪክ ውስጥ፥ ጥቂት ዓመታት (ከ1966 - 1970 ዓ.ም[1]) ለብዙዎቻችን የቀውጢ ዘመን ነበረ። በተጠቀሰው የቀውጢ ዘመን ውስጥ እኔው ያለፍኩበትን የሚመለከት ነው የማወራው፤ ሠፋ ያለ የፖለቲካ ትንተና ውስጥ ሳልገባ፥ የግለሰብ እውነተኛ መጠሪያ ስሞችንም ሳልገልጥ።

አብዮቱ ሊፈነዳ አካባቢ (ከ1966 ዓ.ም. በፊት) ባለ ከፍተኛ ሕሊናዊ ተሳታፊ የሆንኩበት፥ የኮሙኒስትት መጻሕፍትን እያሳደድኩ ማነብበ የጀመርኩበት አንድ ወቅት ነበረ። ይህ ወቅት እኔን ባለ ከፍተኛ ምድራዊ (ፖለቲካዊ) ተሳታፊ አደረገኝ። እነኚህን መጻሕፍት እንደኔው ካነበቡ ግለሰቦች ጋር ስለ ሕብረተሰብ መጨቆንና ስለ መፍትሔው ጉዳይ ማውራት በጀመርኩበት ወቅት፥ በሶሻሊስት ፍልስፍና የተጠመዱ፥ ደረጀ እና ኃይሉ የተባሉ ግለሰቦች አጋጠሙኝ። ከእነዚህ የሥራ ባልደረቦቼ ጋር በማውራት ብዙ "እውቀቶችን" ሸመትኩ። በዚያን ወቅት፥ "እግዚአብሔር ለፍጡራኑ ሥጋዊ ኑሮ ካልተቆረቆረና ካላሰበላቸው እኛ ለምን እናምንበታለን?" በማለት፥ የሶሻሊስት ፍልስፍናን በመከተል፥ እግዚአብሔርን ለመካድ የደፈርንበት ዘመን ነበር።

እኔና የሥራ ባልደረቦቼ፥ በሥራ ጉዳይ ገጠር የምንሄድበት ወቅት ደረሰና ወደ ትግራይ አመራን። ሥራችን በየጫካውና በየዱሩ የሚያዘዋውር የሥነ ምድር ምርምር (ጂኦሎጂ) ስለነበር፥ በመሸበት ድንኳን መትከል፥ ሲነጋ ድንኳን ነቅሎ መጓዝ፥ የተሰጠንን ሥራ እስከንጨርስ ድረስ (አንድም ሆነ ሁለት ወር) የማያቋርጥ የቀን ተቀን ተግባራችን ነበር። በዚህ አይነት የትግራይን አውራጃዎች ሁሉ ገጠር

---

[1] እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር

ገጠሩን ስንዞር፥ በእረፍት በእረፍት ጊዜም ስለ ኮሙኒስታዊ ርዕዮት መወያየት ከመደበኛ ሥራዎቻችን አንዱ ሆኖ ነበረ።

ከእለታት አንድ ቀን፥ ቀኑ መሸና ድንኳን የምንተክልበት ማደሪያ ሥፍራ ስንፈልግ፥ አንድ በዛፍ የተከበበ ገላጣ ሜዳ አገኘን። ከሜዳው ዳርቻ (መቼም ትግራይ፥ እንደ ሕዝቡ ደግነት፥ ገዳምና ቤተ ክርስቲያንም የበዛበት ነውና)፥ አንድ እጹብ ድንቅ የሆነ ቤተ ክርስቲያን አየን። ድንኳናችንን ከቤተ ክርስቲያኑ ራቅ አድርገን ከሜዳው ላይ ተከልን።

ሦስታችንም በአንድ ድንኳን ውስጥ ተጠቃለን ተኛን። ሞቃት ሥፍራ ስለነበር፥ የድንኳኑን በር (ዚፑ) ሙሉ ለሙሉ አልዘጋነውም ነበር። ሌሊት በእንቅልፍ ልቤ፥ ደረጀና ኃይሉን ከእንቅልፋቸው የሚቀሰቅስ፥ ጥርት ባለ አማርኛ ንግግር አደረግሁ፤ ለፈለፍኩ። ምን እንዳልኩ የሚያውቅ የለም፤ ግን ያካባቢውን ጭቁን ሕዝብ የሚመለከት ንግግር ይመስላል። ምናልባትም ከመምሸቱ በፊት ስላጋጠመን ስለ አንድ ጭቁን ገበሬ ኑሮ፥ በቀን የታሰበኝ ይሆናል፤ በሌላ መልኩ (በቅዠት) መልክ የመጣብኝ።

አንድ ጭቁን የትግራይ ገበሬ ድንጋይ ለድንጋይ እያማታ ያርሳል፣ በእርሻው ላይ ከአፈሩ ብዛት የድንጋዩ ብዛት ሳይበልጥ አይቀርም። ከሩቅ ሲያየን ሥራውን አቋርጦ እጅ ነሳን፤ ወዲያው ሊረዳን ፈለገና እኛ መንገድ ስንጠይቀው፤ እርሱ ደግሞ “እባካችሁ ኑ፥ ወደኔ ቤት እንሂድ፤ ሚስቴ ከእንጨት ለቀማ ስትመለስ ወጥ ትሠራልናለች። ቶሎ ካልተመለሰችና እናንተም ከቸኮላችሁ “ጣይታ ብበርበሬ ጌርና ክንበልእ፤ በጀኻትኩም ገዛ ንእትው፤” (እንጀራ በበርበሬ እንበላለን እባካችሁ፥ ወደ ቤት እንግባ)” እያለ ተማጸነ። የሕዝቦች ደግነት፥ የአስተዳደር መዛባት፥ የእኛም ሕዝቦች ያሉበትን ሁኔታ በደንብ አለመረዳትና ዘላቂ መፍትሔ አለመፈለግ፥ ይህ ሁሉ ታስቦኝ ይሆናል ሌሊት የቃዠሁት።

ሊነጋጋ ሲል ደግሞ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያኑ ካለበት አቅጣጫ ተነስቶ በተከፈተው የድንኳን በር በኩል ሲያልፍ “ተመለከትኩ” (የመምሰል መመልከት - የሚመስል ሁሉ እውነት አይደለም)።

ጧት፥ ገና ፀሐይ ሙሉ በሙሉ ሳትወጣ፥ ከእንቅልፋችን እንደተነሳን፥ ሲያቀብጠኝ ይህንኑ አስገራሚ ትእይንት ለጓደኞቼ ተናገርኩና፥ መሳቂያ - መቀለጃ ሆኜ ቀረሁ። ያየሁት የሰው ቅርጽ በሰው ቀለም ሳይሆን፥ ሰማያዊና ነጭ ሆኖ ነበር የታየኝ። ነገር ግን “ይህ የተመለከትከው መልክ የኢየሱስ ክርስቶስ መልክ ነው፤” የሚል ሃሳብ፥ ልክ እንደማይታበል ሃቅ በመሆን፥ እስካሁን በጭንቅላቴ ተቀርጾ አልጠፋ ብሏል።

ጓደኞቼ ግን "ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በማደራችን በአይምሮህ የምታሰላስለው ተከሰተብህ፤ አንተ አሁንም አይዲያሊስትነት (በእግዚአብሔር አማኝነት) ያልተላቀቀህ መሆንክን ተረዳን፤" ብለው አዘኑብኝ።

እኔም የበኩሌን እውነተኛነት ከጓደኞቼ አስተሳሰብ ጋር እያነጻጸርኩ በነገሩ ብዙ አሰብኩበት።

"መቼም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ በሥጋም ሆነ በመንፈስ የሚንገራደድ ሰው አይታጣም። መቼም ሳይንቲስትና ኮሙኒስት ሲደመር አይዲአሊስት ሊሆን አይችልም። የቀን ተቀን ተግባሬ ሳይንሳዊ ምርምር ሆኖ ሳለ፥ ይህን የማይመስል ነገር የሚያጉላላ ጭንቅላቴ እውነቱን ማመሳከር እንዴት ያቅተዋል?" ብዬ እራሴን በትዝብት ጠየቅሁ።

ከሰማዩ ብርሃን ጋር የሰው ቅርጽ እንዲፈጠር የሚያደርግ አካላዊ ክስተት ሊኖር ስለመቻሉ ጉዳይ ሳይንሳዊ ገለጻ ለማግኘት ባለመቻሌ፥ እራሴኑ ባለ ቅዠታዊ አስተሳሰብ ከማድረግ በስተቀር ሌላ አማራጭ በማጣቴ እስካሁን ድረስ ዝም አልኩ፤ እንዲህም እያሰብኩ፡- ለሰው (ለግለሰብ) ማንኛውም የሚታሰበው፥ ለዛ ሰው እውነት ቢሆንለት ወይንም ቢመስለው፥ ለዛ ሰው ነው እንጂ አይሆንም ለሌላ። ታዲያ፥ "እንዲህ አየሁ፥ ይህ ተገለጠልኝ..." የሚል ሰው፥ እንዳው ለወሬ ብቻ መሆኑንም እያሳወቀ ቢሆን፥ ወይንም ይህ አይምሮአችን የሚጫወትብንን የማስመሰል ጨዋታ ለመግለጽ ቢሆን ነው ደጉ።

በዛን ሌሊት ያየሁትን ረስቼው ነበር፤ ለመነገርም ያልበቃ - ኢምንት ጉዳይ ነው ብሎ ማለፍም ይቻላል። ሆኖም፥ የሰው ልጅ ውስጣዊ እውነት የሚገለጽበት ጊዜ መኖሩን፥ እግዚአብሔር ምን ጊዜም ከኛ ጋር መሆኑን፥ ኃጢአተኞች ብንሆንም - ባንሆንም፥ እግዚአብሔርን የካድን ኮሙኒስቶች ብንሆንም፤ የእግዚአብሔር መንፈስ የማይለቀን መሆኑን (የእግዚአብሔር መንፈስ ምን ጊዜም በውስጣችን መኖሩን) እርግጠኛ ስለሆንኩና ይህንኑ ለመግለጽ ስል ለመናገር ደፈርኩ። ብዙ የተደበቁ እውነቶችን በምጽፋቸው መጻሕፍት ሁሉ እንመርምር ከተባለ፥ አንባብያንም በራሳቸው ሕይወት ውስጥ፥ ይህን እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ሊያጋጥሟቸው ስለሚችሉ፥ በውስጠ አይምሮ ግንዛቤያችን እያሰላሰልን እውነቱን ብቻ እንድናቆይ ብዬ ነው።

ሌሊት የለፈለፍኩትንም፥ "አንተ እንደዚህ የተጣራ ንግግር ከየት ልታመጣ ቻልክ? ሌላ ሰው መሆን አለበት የተናገረው፤ ወይንም እኛ የማናውቀው ሰው በውስጥህ ደብቀህ እንደሆን ንገረን፤" ብለው ቀለዱብኝ ጓደኞቼ። እኔም የራሴ ሁለት ሰው መሆን ዘወትር የማይገባኝ ጉዳይ በመሆኑ አሁንም ከዝምታ የተሻለ አማራጭ አላገኘሁምና፥ ጭጭ አልኩ። ሁለቱንም ሳዛምደው፥ ምናልባት ሁለት ሰው በመሆኔ፥

ሳላስበው አንደኛው እኔ ክርስቶስን አይቶትስ እንደሆን እያልኩ አሁንም ትንሽ ትንሽ እጠራጠራለሁ።

አዎ! ሁላችንም ሁለት - ሁለት ሆነን ተፈጥረን ሳለ፥ አንደኛው ተፈጥሮአችን ከአካባቢው (ከምድራዊነታችን) ጋር የተዛመደ ስለሆነ በደንብ እናውቀዋለን፤ ሁለተኛው ግን ከዚህ ከአካላዊ (ሥጋዊ) አለም ጭራሽ የተለየ በመሆኑ እምብዛም አይታወቀንም። ነገር ግን አልፎ - አልፎ ምክር ሲሰጠን ወይም ገደል ውስጥ ሲከተን እናውቀዋለን። "አለ፥ ይታያል፥ ሆኗል" የምንላቸው ጉዳዮች፥ "የለም፥ አይታይም፥ አልሆነም" ከምንላቸው ጉዳዮች የማይተናነሱ መሆናቸውን በውስጠ ልቦናችን ስለምናውቅ፥ "ግን እኛ በምን አይነት አለም ውስጥ ነው የምንኖረው?" እያልን እራሳችንን መጠየቃችን አልቀረም።

ይህን በዚህ እንግታውና ወደ ቀድሞ ታሪካችን እንመለስ። ከተጠቀሰው አይዲያሊስት አስተሳሰብ መላቀቅ እና በማርክስና ሌኒን ፍልስፍና እራሴን ማጠናከር፥ ለወደፊት ሕይወቴን በመስዋእትነት ለማቀርብለት ሰፊ ሕዝብ አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን በመረዳት፥ አላማዬን ብቻ እየተመለከትሁ ኑሮዬን አስተካከልኩ።

በአገራችን የአብዮት ፍንዳታና የመንግሥት ለውጥ ሲመጣ፥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፥ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፥ የኢትዮጵያ ኮሙኒስትት ፓርቲ (ኢኮፓ)፥ የኢትዮጵያ ጭቁን አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት)፥ ማርክሲስት ሌኒኒስት አብዮታዊ ድርጅት (ማሌሪድ) የተባሉት ሁሉ ከፍተኛ ተሳትፎ ያሳዩበት ዘመን ነበር (ከ1966 ጀምሮ)።

በወቅቱ ሶሻሊስቶች ነን የምንል ወጣቶች ከሩቅ እንለያለን። ገንዘብ አለማጠራቀም፥ ሃብትና ንብረት አለመያዝ፥ በአጠቃላይ ለራስ አለማሰብና በአለባበስም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ ድሃውንና ሰፊውን ሕዝብ መምሰል የኛ ምልክት ነበር። ጢማም የሆኑት፥ ጭንቀትና ሃሳብ ሲገባቸው፥ ካለማቋረጥ ጢማቸውን ይጎትታሉ፣ ባለ ጎፈሬዎቹ ደግሞ፥ ከጆሮአቸው ሥር ጥቂት ጠጉሮችን ካለማቋረጥ ይገምዳሉ፡ ይህንን ይመስል ነበር የኛ በጭንቀት የተከሰት ውጪያዊ ምልክት።

እንደኔ አርቆ ማሰብ የተሳናቸው ደግሞ፥ ለገዛ ቤተሰብ ማሰብና ለራስ ማሰብ፥ ባጠቃላይ ለሰፊው ሕዝብ ከማሰብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ባለመገንዘብ፥ ራሳቸውንና ዘመዶቻቸውን መርዳትን ረስተውታል። ግን ወቅቱ ይህን ሁሉ ለማሰላሰል ፋታ የሚሰጥ አልነበረምና፤ ሶሻሊዝምን ስንሰብክ አለምን ንቆ እንደመነኮሰ ባህታዊ መስለን ነበር።

ኢሕአፓዎች በውጪያዊ ጠባያቸው የሚለዩበትን ፍንጭ ሰጠን እንጂ፥ እጅግ የሚያስገርመው ግን፥ በማንኛውም ጊዜ የአብዛኛዎቹ ተመሳሳይ ውስጣዊ

ጠባያቸው ነው። የሰውን ልጅ ውስጣዊ ጠባይ ወደ አንድ ርህሩህ ለሰውና ለምድሪቱ፥ ወይንም ለአገሩና ለሕዝቡ የሚያስብ የሚያደርግ ርዕዮት መታጣቱ፥ ወይንም የሰው ልጅ ጠባይ በርዕዮተ አለም አይነቶች የማይበገር (ሊለወጥ የማይችል መሆኑ) "ሚዳቋ እዚያ ቅዝምዝም እዚያ" አደረገብን።

አብዮታዊ ቅስቀሳ ማካሄድ በጠመንጃ ከመዋጋት አያንስምና፥ እንደ እኔ ዝምተኛ የነበሩ ሁሉ እንደበታቸው በድንገት ተከፍቶላቸው ለፍላፊዎች የሆኑበት ዘመን ነበር። እኔም የኢሕአፓን ጽሑፎች እያነበብሁ፥ ከኢሕአፓ የፖለቲካ አስተሳሰብ ጎን ለጎን በመሆን፥ ጭቁን ሕዝብ በተገኘበት ሥፍራ ሁሉ እየተዘዋወርኩ ጥሩ ታናጋሪ ወጥቶኛል። እህ! ተናጋሪ (ቀስቃሽ) ከተባለስ፥ እነ እገሌን፥ እነ እገሌን (ስንቱን - ስንቱን! ኸረ ስንቱን!) ማን ይሆን እነርሱን አስታውሶ ስለነርሱ የሚጽፍላቸው?

ግን ያ የተተካው የወታደር መንግሥት እያየለ ሲሄድ፥ የተቃውሞ ፖለቲካን የተናገረ ጸረ አብዮያዊ ቅስቃሳ ያካሂዳል እየተባለ ይታሰር ጀመር፤ ቀጥሎም መግደል ተጀመረ። በዚህን ጊዜ በህቡዕ (በድብቅ) ተደራጅቶ ከመታገል በስተቀር ሌላ አማራጭ ጠፋ።

## <u>የፓርቲ ሕዋስ ምሥረታ</u>

ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ሁለቱ የሥራ ባልደረቦቼ (ደረጀ እና ኃይሉ ) እኔን አስተማሩኝ፥ በሶሻሊስትም ጎዳና መሩኝ እንጂ፥ ለማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አላጨኝም ነበር። እንዳውም ትንሽ ቆይቶ ኃይሉ ከፎቅ ተጥሎ ተገሏል። ደረጀ ግን ይሙት ይኑር አላውቅም።

በዛን የአብዮት ወቅት አዲስ አበባ ቤት ተከራይቼ የምኖረው ታደሰ ከተባለው ጓደኛዬ ጋር ነበር። ታደሰ በጣም ጥሩ ሰው ነው፣ እኔና ታደሰ ተቀራራቢ ርዕዮት አለን፤ በብዙ ነገር እንስማማለን። ታደሰ ሚዛናዊ ነው እንጂ ወላዋይ አይደለም። እኔና እሱን የሚለየን ነገር ቢኖር፥ እኔ ለማምንበት ነገር ቶሎ ብዬ እርምጃ መውሰድ እፈልጋለሁ፤ እርሱ ግን የራሱን ፍላጎት በማያስጠብቅ ጉዳይ ላይ ፈጣን እርምጃ መውሰድ ካለመፈለጉም በላይ፥ ከበድ ያሉ ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ ያዳግተዋል።

ከታደሰ እኩል የማቀርበው አዲስ አበባ ተወልዶ ያደገ፥ ኢትዮጵያዊ ኤርትራዊ ጓደኛዬ ተክሌ ይባላል። እኔና ተክሌ በጣም እንዋደዳለን፤ በአስተሳሰብም በጣም ስለምንቀራረብ፥ ከታደሰ ይልቅ ብዙውን ጊዜ የማሳልፈው ከተክሌ ጋር ነበር።

የአብዮቱ እንቅስቃሴ እየተፋፋመ ሲሄድ፥ የሰው ሁሉ መነጋገሪያ የሆነው በየቀኑ የሚከሰተው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሆነ። ባንድ በኩል የደርግ መንግሥት የንጉሣዊ ስርአትን በመገርሰስ፥ በምትኩ ሶሻሊስት የሚመስሉ እንቅስቃሴዎችን ያካሂዳል። በሌላም በኩል ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች እንደየአመለካከቶቻቸው "ይህ መንገድ ይሻላል፥ ይኸኛው አያዋጣም.." እያሉ፥ ደርግን ቀርበው የሚያማክሩ፥ ከደርግም ርቀው የራሳቸውን አጀንዳ የሚያራምዱ ነበሩ።

እኔና ተከሌ "የሁሉንም ፖለቲካዊ አመለካከት እያጠናን፥ ለሰፊው ሕዝብ የሚጠቅመው የትኛው ነው?" ብሎ መምረጥና ወዳንዱ ድርጅት መጠጋት፥ ከተቻለም መሳተፍ አስፈላጊ መሆኑን አምነንበታል። ታደሰ ግን እንዲሁ ለወሬ ያህል መረጃዎችን በማሰባሰብ ከኛ ጋር ይሳተፋል እንጂ፥ ምንም አይነት አቋም የሚወስድ ሰው አይደለም።

በድርጅቶቹ መካከል ቅራኔዎች እየተባባሱ ሄዱ። ኢሕአፓም በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ብዙ አባላትን እፍርቶ፥ እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ፥ የፖለቲካ አቋሙን የሚያንጸባርቁ አብዮታዊ ቅስቀሳዎች፥ በጽሑፍ (በዲሞክራሲያ)፥ ለሕዝቡ እንዲዳረስ አደረገ።

በዛን ወቅት ሁለቱ ታላላቅ ተቀናቃኝ ፓርቲዎች፥ መኢሶን እና እሕአፓ ብቻ ነበሩ። በሁለቱ መካከል የነበረውን ተቀራራቢ የሚመስል፥ ግን ጠለቅ ብሎ ለተመለከተው ተፃራሪ የሆኑ ርዕዮቶች በደንብ ለመረዳትና ለማወቅ፥ የሁለቱን የፖለቲካ አጀንዳ መመልከት ብቻ ሳይሆን፥ ሌሎች አገሮች ያለፉበትን አብዮታዊ ጉዞ ማጥናት እና ካገራችን ሁኔታዎች ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል። የሁለቱን ፓርቲዎች ልዩነቶቻቸውን በደንብ ከተረዱ በኋላ ለሰፊው ሕዝብ የወደፊት ዕድል የሚጠቅመውንና የተሻለውን፥ ከሁለቱ አንዱ ለኢትዮጵያችን የተሻለውን በመምረጥ፥ ወዳንዱ ተጠግቶ በጋራ መሳተፍ፥ በወቅቱ የነበርን የብዙዎቻችን ወጣቶች ዝንባሌ ነበር።

ስለዚህ፥ እንዲሁ በየመንገዱና በየቡና ቤቱ የምናወራውን ወሬ አቅጣጫ ለማስያዝ በሃሳብ የምንገናኝ ጓደኞች፥ በአንዳንድ አመቺ ሥፍራዎች ሰብሰብ እያልን መወያየት ጀምረናል። እኔና ታደሰ የምንኖርበት ግን፥ በተለያዩ ምክንያቶች (የታደሰም አቋም አለመውሰድ ተጨምሮ) ለዚህ አመቺ አልሆነም። ሰው ቤታችን ቢመጣ፥ ወይንም ከታደሰ ጋር ቡና ለመጠጣት ወጣ ብንል፥ ሁሉም ነገር በታደሰ ቀልድ፥ ሳቅና ጨዋታ ዙሪያ እየሆነ፥ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ተሳታፊዎቻቸው ከደረሱበት ለመድረስ አዳጋች ሆነ።

ከእለታት በአንድ ቀን፥ እኔን በጣም የሚቀርበኝ አንድ ሻምበል፥ "ና ቡና ልጋብዝህ፥" ብሎ ወዳንድ ቡና ቤት አመራን። ከዚያም ቢራ እየጠጣን የወቅቱን ጥያቄዎች ሊፈቱ በሚችሉ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ከተወያየን በኋላ ሻምበሉ "የዚህን አምባገነን ፋሺስታዊ የወታደር መንግሥት ገርስሶ በምትኩ "ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ለመመሥረት መተባበር አለብን..." በማለት፥ በተለይ እኔ ይህንን ጉዳይ በጣም እንዳስብበትና እንድሳተፍ አጥብቆ መከረኝ፥ "ባሁኑ ወቅት፥ ይህንን የንኡስ ከበርቴ ጠባይህን ትተህ ከሰፊው ሕዝብ ጎን ካልተሳተፍክ፥ ያንተ አርቆ አሳቢነትና ተቆርቋሪነት ምንድነው?" አለኝ።

ሻምበሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ስለነበርና ውሎውም ከተማሪዎች ጋር ስለነበር፥ እርሱን የደርግ አባል ይሆናል ብሎ የሚጠረጥር አልነበረም። እንዳውም ብዙዎቻችን፥ በርሱ ተናጋሪነት አንድ ቀን ይይዙትና ያስሩታል ብለን እንፈራ ነበር።

አልቀረለትም፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ፥ ያ ሻምበል እጅጉን የሚያፈቅራትን ሚስቱንና ሁለት ሴት ልጆቹን ትቶ፥ ደርግን እየተራገመና እየተሳደበ፥ ከወህኒ ቤት ተወረወረ። ብዙም ሳይቆይ ተገደለ። የብዙዎቻችን ጓደኛ የሆነ፥ አንድ ለአገሩ ተቆርቋሪ ጀግና፥ ገና በጅምሩ ቶሎ ተቀጨ፤ ያሳዝናል።

የኢሕአፓ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይወሰን፥ በየከተማዎችና ገጠሮች ሁሉ ተዳረሰ።

ከእለታት በአንድ ቀን፥ ተክሌ ቀርቦ አነጋገረኝ። "እኔና አንተ እስከ መቼ ነው ገለልተኞች የምንሆነው? ሁለታችንም ኢሕአፓን እንደግፋለን፤ ለምን ተሳታፊዎች አንሆንም?" በዚህን ጊዜ የሻምበሉ ምክርና ተግሳፅ ከልቤ ሰርጎ ገባና "አዎ! ልክ ነህ፤ ...እ..እ...ይሰማኛል፤... ግን ይህ እንዴት ይቻላል፥ የሚመለምለን ሳይኖር? ለመመልመል ደግሞ ሰብሰብ እያሉ ጥናቶችና ውይይቶችን ማካሄድ ያስፈልጋል። እንደምታውቀው፥ በዚህ ሃሳብ ታደሰ አይስማማም፤ ቤቱም አመቺ አይደለም" አልኩ።

ተክሌም ሳቅ ብሎ "እህ!..አንዳንድ ጊዜ እኮ! ይህ ለውጥ ሲመጣና ሰው ሁሉ ስለ ትግል ሲያወራ፥ ከቀን ወደቀን በታደሰ ዙሪያ የሚታዩ ግለሰቦች እየተቀየሩ፥ ከራሳቸው የቀን ተቀን ኑሮ አልፈው፥ ለሰፊው ሕዝብ የማያስቡ፥ እልም ያሉ ንኡስ ከበርቴዎች እየሆኑ ነው። ታዲያ አንተም ከነሱ ተደምረህ እስከመቼ?... እኔ ሳውቅህ፥ አንተ ለየት ያልክ ነህ፤ እስከመቼ ከማይመስሉህ ጋር ጊዜህን ታጠፋለህ? ውጣና ሌላ ቤት ተከራይ፤ ይህ ነው መፍትሄው፤ አይመስልህም?" አለኝ።

እኔም "ይመስለኛል፤ ግን የት ነው የምከራየው? በየጊዜው ለመሰባሰብ የሚያመች ሥፍራ ታገኛለህ?" አልኩት። እርሱም "ይህንን በኔ ተወው፥ በአንድ ሳምንት ውስጥ ቆንጆ ቤት ፍልጌ አግኝልሃለሁ" አለኝ።

ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተክሌ መጣ። “ናና ቤቱን እንየው” አለኝ። ቤቱን ሳየው ወደድኩት። በዛኑ ለት ተፈራርሜ በሚቀጥለው ቀን ልብሶቼና መጻሕፍቶቼን ይዤ ወጣሁ፣ ለታደሰ ሳልነግረው።

ታደሰ እጅጉን ተቆጣ። እርሱን ያሳዘነውና ያናደደው፥ ለምን ለኔ ሳይነገረኝ ወጣ ብሎ ነው። ጉዳዩን እንደዚህ በዝርዝር መናገር የማይቻልበት ወቅት ስለነበረ፥ ሁሉንም እንደ ቀላል ነገር በማድበስበስ እና በማሳሳቅ “በቃ ይቅርታ አድርግልኝ” ብዬው ነው የተለየሁት። ታደሰ አሁን ይህንን ጽሑፍ ሲያነብ ነው የሚገባው።

በሃሳብ የምንቀራረብ ከአዲሱ ቤት መሰባሰብና መወያየት ጀመርን። ስንጀምር አልፎ አልፎ ከሚመጡት ጋር፥ በጠቅላላ ወደ አስር እንጠጋለን። የሚበተኑ ጽሑፎችን ከያቅጣጫው እያመጣን በተለያዩ ጊዜያት ከአራት እስከ ሰባት እየሆንን እናነባለን፤ እንወያያለን፤ አልፎ አልፎም የሶሻሊስት ጽሑፎችን እናነባለን።

ትግሉ እየተባባሰ ሲሄድ፥ በመካከላችን የነበረም ጥቃቅን የርዕዮት ልዩነት እየጎላ ሄደ። ቀስ በቀስ ቁጥራችን መነመነ። ሆኖም የኢሕአፓን አመለካከት ያልለቀቅን እኔ፥ ተክሌ፥ አሰፋና መሃመድ ብቻ ነበርን።

መሃመድ ብዙ የማይናገር ከመሆኑም በላይ፥ አልፎ አልፎ ብቻ ነበር ከኛ ጋር የሚገናኝ። ከጊዜ በኋላ፥ ትግሉ እየተፋፋመ ሲሄድ፥ ግድያዎችም ሲባባሱ፥ ከዚያ ቤት መቆየት አስጊ ሆነና፥ እንደገና ሌላ ቤት ቀየርኩ። ካዲሱ ቤት የምንገናኝ አራታችን ብቻ ሆን።

እኛን ቀርቦ የሚመለምለን ጠፋ። በተለይ እኔና ተክሌ “እስከመቼ ነው ከትግሉ ተገልለን የምንቀመጥ?” እያልን ተበሳጨን። ከአራታችን ውጪም እኛ በፖለቲካ አቋማቸው የምናውቃቸው “ኢሕአፓ ለምን አይመለከተንም፤ አብረን በቆራጥነት እንዳንታገል” እያሉ የተጨነቁም ነበሩ።

ከእለታት በአንድ ቀን አራታችን ብቻ ከኔ ቤት እየተገናኘን ቋሚ ጥናት እንድንጀምር መሃመድ አሳሰበ። በዚሁም መሠረት እኔ፥ ተክሌና አሰፋ ከኔ ቤት ተገናኝተን፥ መሃመድን ስንጠባበቅ፥ መሃመድ ትንሽ ዘግየት ብሎ ከአንድ እኛ ከማናውቀው ሰው ጋር መጣ። መሃመድ የዚህ ግለሰብ ከኛ ጋር መሳተፍ ለበጎ ስለሆነ፥ በቅድሚያ የኛን ፈቃድ ጠየቀ። እኛም መሃመድን በመተማመን ብቻ “እሺ” አልን።

ግለሰቡ ግርማ ይባላል፤ ረጋ ያለና አስተዋይ ነው። የፖለቲካ ብስለቱና ስለ ሶሻሊዝም ያለው እውቀት ካነጋገሩ ያስታውቃል። አልፎ አልፎ አባል ያልሆነ የማያውቀውን በኢሕአፓ ድርጅት ውስጥ ስለሚከናወን ጉዳይ ሲያሳውቀን፥ በተዘዋዋሪ ከላይ (ከበላይ አካል) በተልእኮ ከውስጣችን የገባ መሆኑ ያስታውቅበታል።

ስብሰባውን ስንጀምር እርሱ እንደመሪያችን እየሆነ፥ ማድረግ ያለብንን ይነግረን ጀመር። ከሁሉ አስቀድመን የሶሻሊስትን ቲዎሪ በደንብ እንድናውቅ፥ የሁለቱን መጻሕፍት (Historical Materialism & Dialectical Materialism) ይዘት በሚገባ ስንወያይ አንድ ወር አለፈ። ቀጥሎም በድርጅቶች መካከል ያለውን ቅራኔና የኢሕአፓ አቋም ከሌሎቹ እንዴት እንደሚለይ፥ ጽሑፎችን ሁሉ እያነበብን ተወያየን። በሦስተኛው ወር ላይ ያተኮርነው በወቅታዊ ጉዳዮች ላይና በኢሕአፓ እርምጃዎች ዙሪያ ነበር።

በዚህን ጊዜ ሁሉ፥ ግርማ ከጥውም ልሳኑ ጋር በአስተሳሰቡ የበሰለ፥ የፖለቲካ እውቀቱም ከሌሎቻችን የላቀ ነው። ግን ሁላችንንም በጥሞና እያዳመጠ፥ የሁላችንንም አመለካከት የሚያደንቅ፥ በተለይ በኔ በኩል የሚሰነዘሩ አሳቦችን የሚወዳቸው መሆኑን ይነግረን ነበር።

ከሦስት ወራት በኋላ ግርማ የምሥራች ይዞልን መጣ (ለያንዳንዳችን ከፓርቲው ጋር የሚያገናኝ ኮድ)። እኔ እና አሰፋ በፓርቲው መዋቅር ውስጥ ስንገባ፥ መሃመድና ተክሌ በወጣቶች ክንፍ ገቡ። ሁላችንም በየሥራችን ተሰማራን። እኔም ከባንክ የነበረኝን ገንዘብ ሁሉ አውጥቼ ግርማ ለፓርቲው እንዲሰጥልኝ ነግሬ ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበትኩት። ግርማ አሁንም በሕይወት ያለ ይመስለኛል፤ ግን እርግጠኛ አይደለሁም።

## ድርጅታዊ ሥራዎች

በስሜት ተገፋፍቼ ሳይሆን፥ በአስተሳሰብ (በርዕዮተ አለም አመለካከት) የኔ ዝንባሌ ወደ ኢሕአፓ ተጠግቶ፥ እዚህ ድርጅት ውስጥ ለመግባት አስፈላጊ የሆኑትን የሕቡእ ጥናቶች ከጨረስኩና ፈተናዎችንም ካለፍኩ በኋላ የፓርቲ አባል ለመባል በቅቼ፥ ከበላይ አካል የሚተላለፍልኝን ድርጅታዊ ሥራዎች መሥራት ጀምሬአለሁ። ሰው የሚፈልገውን ሲያገኝ ጥሩ ነው (ደስ ይላል)።

በሕቡዕ መታገል ማለት አብዛኛውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ በድብቅ ማከናወን ስለሆነ፥ የሚያውቁኝ ሁሉ እስኪረሱኝ ድረስ፥ በልዩ ልዩ የፓርቲው የፖለቲካ አውታሮች ውስጥ በመሳተፍ በህቡዕ ታግያለሁ። ሰው የሚፈልገውን ሥራ ሲሠራ ጥሩ ነው (ደስ ይላል)።

የኮሚቴ ውይይቶች በምናደርግበት ወቅት፥ በዚያን ጊዜ የሰው ልጅ መመዘኛያና መለኪያ አብዮታዊ አመለካከቱ ስለነበር፥ ከብዙ ጓዶች ጋር ተዋወቅሁ። ከነኚህም መካከል በኋላ ሚስቴ የሆነችው ኮከቤ ትገኝበታለች።

ከቀን ወደ ቀን የሚፈጠረው ሁኔታ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ቢሆን ፋታ የሚሰጥ ሆኖ አልተገኘምና፤ ሁላችንም በትግል አለም ተጠምደን ለአንዲት ቅጽበት ታህል እንኳን አለማዊ ኑሮ ስለማያሳስበን፥ እኔ ኮከቤን በጓዳዊ ስሜት ብቻ ነበር የማውቃት፤ እርሷም እንዲሁ።

በቀድሞው "ሰላማዊ" ኑሮ ምትክ እጅግ አስከፊ ኑሮ ሲተካ፥ በአንጻሩም ፓርቲዎችና ድርጅቶች በርዕዮተ አለምም ሆነ በእንቅስቃሴ እየተጠናከሩ ሲሄዱ፥ የእኔ ኑሮ መልክ እየያዘ መጣ። ለመኖሬ ትርጉም አገኘሁለትና፤ ደስ የሚል ሕይወት መኖር ጀመርኩ። የጥናት ህዋሶችንም በመመሥረትና የፓርቲ አውታሮችን በመዘርጋት በኩል ብዙ - ብዙ አገለገልኩ። አዎ! ደስ እያለኝም ወደ ሞት ሊያመራ የሚችል የበላይ አካል ትእዛዞችን ሁሉ ከመፈጸም አልቦዘንኩም። የፕሮፓጋንዳ ጽሑፎችንም[2] እስከማዘጋጀት ደረጃ ደርሼ ነበረ።

በኢሕአፓ በኩል የተፈጸመ ታሪክ ተወርቶም አያልቅ። ግን ባጭሩ፡- ብዙ ሰላማዊ ሰልፎች ተደረጉና፤.. ብዙ ወጣቶች አለቁና፤.. ከብዙ የጽሑፍና የንግግር ፕሮፓጋንዳዎች (ቅስቀሳዎች)፥ ከአንዳንድ የግለሰብ ግድያዎችም በኋላ.. በኢሕአፓ በኩል የተሞከረው የመንግሥት ፍንቀላ ሙከራ ሳይሳካ መቅረቱ አንድ የኢሕአፓ ውድቀት መከሰቻ ሆነብን[3]።

የአገር መሪ በተባለው ሰውዬ ላይ የተቃጣው የግድያ ሙከራ ውጤት ግለሰቡን በሥጋ ከማቁሰል በስተቀር፥ "ደም የሚመስል ከበድ - ጠቆር ያለ መንፈሱን" ከምንጊዜውም የበለጠ አኮሳተረው (መራራው ሃሞቱ የበለጠ መራራ ሆነ)።

የመንግሥት ተባባሪዎች ሁሉ የቀይ ሽብር በሚል መጠሪያ በአንድነት ትግላቸውን በማቀነባበር፥ በኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎቻቸው ላይ ዘመቱባቸው። ግድያ በያለበት ተጧጧፈ። ለቀበሌ የአብዮት ጠባቂዎች የመግደል መብት ተሰጣቸው። ከእነኚህም መካከል የእንስሳነት ጠባያቸው ያመዘነባቸው ጨካኞች የሰው ሚስት መቀማት፥ ገንዘብ ካላቸው ላይ፡- እፈታልሻለሁ (እፈታልሃለሁ) እያሉ ጉቦ መቀበል፥ አሰቃይቶ መግደል፥ ባጠቃላይ ለመስማት የሚዘገንን ግፍ መፈጸም የወቅቱ የአብዮታዊነት መለኪያ ሆኖ ነበር። ከነኚህ ግፈኞች መካከል፥ በነፍስ ወከፍ (እያንዳንዳቸው)፥ መቶና ሁለት መቶ የገደሉም ነበሩ።

---

2 ከመንደር ያለሽው - በየጓዳው የተደበቅሺው ምሥጢሬ፥ ከቶም ፈልጌ ማላገኝሽ ትዝታዬ...።

3 እህ! ፍቅርዬ! በስምህ ፍቅርን ከጉያህ፥ መዘርጋትንም በጉልበትህ ተማምነህ፤ ከካናዳ ምድር ወጣህና መጣህ ወደ ቤትህ፤ ፍቅር - ሰላም ጥሞህ። የስሜቶችህ ግለት ካጉል ሥፍራ ጣለህ።

ወጣቶችን እየገደሉ መንገድ ላይ በመጣልና በመተው ተመልካችን በፍርኃት ማሸበር እንደ አንድ የስነ አይምሮ ጦርነት ተቆጠረ። በየከተማው የነበሩ የኢሕአፓ የጦር ክፍል አባሎች በክላሺን ጠብ መንጃያ እየተጠቀጠቁ ረገፉ (እነርሱም አርግፈዋል)። ሌሎችም ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ በመትረየስ ተረፈረፉ። ይህ በጠቅላላ ኢትዮጵያ የተፈጸመ ግፍ ሲሆን፥ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ በአንድ ሳምንት ውስጥ ብቻ ከሁለት ሺህ[4] የሚበልጡ ወጣቶች የተገደሉበት ጊዜም ነበር።

## <u>የኢሕአፓ መከፈል - የአንጃዎች መፈጠር</u>

የኢሕአፓ አባላትን ሁለት ቦታ በመከፈል ሲያጨቃጭቅ የቆየ የአመለካከት ልዩነት በገሃድ ወጣ (አንጃ ይባላል - ተቃዋሚ - ተገንጣይ ማለት ነው)። ይህን የአመለካከት ልዩነት የሚገልጹ ዘገባዎች ከፓርቲው ይደርሰኝ ስለነበር፥ እውነት መስሎኝ የነበረ ሁሉ አጠራጠረኝ (አንድ ሰው ከሁለት ቢሰነጠቅ ሰው እንደማይሆን፥ ይህም ፓርቲ ከሁለት ቦታ ተሰንጥቆ ፓርቲ ሊሆን እንደማይችል፥ ውስጣዊ ስሜቴ ነገረኝ)። እኔ ብቻ ሳልሆን፥ እንዲህ አይነቱ መጠራጠር በፓርቲ አባላት መካከል ተስፋፋ። ፓርቲውም ከሁለት ተከፈለና ተገንጣዮች የራሳቸውን የተገንጣይ ክፍል (አንጃ) ሲያጠናክሩ፥ "ምድራዊ እውነታዎች" ሰይጣናዊ መልካቸውን በቅድሚያ ለኛ ለአባሎች ነበር ያሳዩንና ያስደነገጡን።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ (አይ ያ ጊዜ!) የፓርቲው አካሄድ የተሰነካከለና የተደነቃቀፈ፥ የሚወሰደው እርምጃ ሁሉ ባጭሩ እየተቀጨ የሚከሽፍ ሆነ። በያለበት የፓርቲ አባላት እየተገደሉ፥ ምንም መሥራት እስኪያቅት ድረስ ተደረሰ። በጊዜው የነበረ "ጎህ" ተብሎ የ<u>ሚጠ</u>ራ መጽሔት ስለ ኢሕአፓ አቃቂር ሲያወጣ እንዲህ አለ፡- "ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ፥ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ"። ፓርቲውን እንዲህ እንደ ሙቀጫ እንዲንከባለል ያደረገው የጠላትን ኃይል በትክክል መመዘን አለመቻልና አከራሪነት ሲሆን፥ በጎን ደግሞ የአንጃዎች መፈጠር ነበረ።

ሀ እና ለ ተብለው የሚጠሩ፥ በማንኛችንም ዘንድ በታጋይነታቸው ስማቸው የገነነ (ብዙ የተጻፈላቸው)፥ ሁለት አብዮታውያን ግለ ሰቦች የፓርቲው መስራቾች እንዳልሆኑ ሁሉ፥ በቀውጢ ቀን በተገንጣይነት (በአንጃነት) ስማቸው በተጠራ ጊዜ፥ የአብዛኛዎቻችን የፓርቲ አባላት ቅስም ከሁለት ተሰነጠቀ።

የፓርቲው መሥራችና መሪ ከነበረው ሀ ተብሎ ከሚጠራው ቀጥሎ ፓርቲው የሚመራው "ደብተራ" ተብሎ በሚጠራ ግለሰብ ነበር። ደብተራው ከህጻንነት ጀምሮ

---

[4] ይህ ቁጥር የዚህ መጽሐፍ ደራሲ በግሉ አስልቶ ያገኘው ነው።

ከቤተ ክርስቲያን ያደገ በመሆኑ፥ ትሁትነት እና ደግነት የተዋሃደው እጅግ ቀልደኛና ተጫዋች ሰው ነበር። ደብተራው የአማርኛው ጥራትና የአነጋገሩ ስልት፥ የእውቀቱ ብዛት እና ወሬው ሁሉ፥ ሲናገር ለሚሰማው፥ ምነው እኔም ከቤተ ክርስቲያን ባደግሁ ያሰኛል። ቀልዱን ኩምክናውን ከቁም ነገር ያዛመደ ደብተራ ስለነበረ፥ የሚወደውና አጃቢው ብዙ ነበር። ያን ሁሉ የቤተ ክርስቲያን እውቀት (ቅኔ፥ ዜማ፥...ወ.ዘ.ተ...) ወደ አብዮት ቀይሮት ኢሕአፓን ሲመራ በነበረበት ወቅት፥ ፓርቲያችን ከምንጊዜውም የበለጠ ምርር - ክርር ያለ ሆነ።

## ታላቁ ውሳጣዊ የፓርቲ ውዝግብ

ፓርቲው ደርግን እንደ ፋሺስት ሲቆጥረው፥ ሀ እና ለ ደግሞ (መኢሶኖችን ተከትለው)፥ ደርግ ፋሺስታዊ ድርጊትን ቢፈጽም፥ ፋሺስታዊ ድርጊትን የሚፈጽም መንግሥት ይባላል እንጂ፥ ፋሺስት አያሰኘውም። ደርግ የፊውዶ ካፒታሊስት ስርዓት የፈጠረው መንግሥት በመሆኑ፥ በጠባዩ በከፍተኛ ደረጃ ከካፒታሊስት ስርዓት እንደሚመነጭ (ጀርመን አገር እንደተፈጠረው) ፋሺስት መቆጠር የለበትም። ስለዚህ፥ ደርግን ከፋሺስታዊ ድርጊቶቹ እንዲላቀቅ ማድረግ፥ አብሮ መሥራትም ይቻላል ባዮች ነበሩ። በዚህና በሌሎች ጥቃቅን አስተሳሰቦች ውስጣዊ ቅራኔዎች ተስፋፉ። ለነርሱ አልታያቸውም ይሆናል እንጂ፥ ከሰፊው ሕዝብ አንጻር፥ በሁለቱም ወገን የሚሰነዘሩ ፍልስፍናዊ አመለካከታቸው ወደ ጸጉር ስንጠቃ ነበር የመራቸው።

ሀ እና ለ "ድርጅታዊ ነጻነታችንን ሳናጣ ከደርግ ጋር መሥራት እንችላለን" በማለት ከዋናው ፓርቲ ተገንጥለው የራሳቸውን እርምጃ መውሰድ ጀመሩ። ድርጅታዊ ነጻነታችንን ሳናጣ ሲሉ፥ ባንድ በኩል በአብዮታዊ ጦር ደርግን ስንወጋ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራን አብረን እየሰራን፥ ለሕዝብ የማይጠቅመውንና የሚጎዳውን ደግሞ ለማሻሻልና ለመለወጥ፥ በጦር ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን ማለታቸው ነው።

በደብተራው የሚመራው ፓርቲ ግን "ጎኑን እየተወጋ በእጆቹ የሚያቅፍ መንግሥት ምን አይነት ሞኝ ቢሆን ነው? ይህስ ለጠላት እጅ ከመስጠት ተለይቶ አይታይም.." በማለት የ ሀ እና ለን አስተሳሰብ አልተቀበሉትም።

አንጃዎች (ሀ እና ለ) "ጨካኙ መንግሥት በየቀኑ እንዳይጨርሰን አንድ መከላከያ ዘዴ ማበጀት ይገባናል። እኛም በበኩላችን ረጋ ብለን የጊዜውን ሁኔታና ትግሉን እናቀናጀው እንጂ፥ አባላቱን በየቀኑ ከማያስፈልግ አደጋ ውስጥ እየከተትን የገዛ ኃይላችንን ማዳከም አይገባም..." በማለት ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ።

ፓርቲው በጭፍኑ የወደፊቱን ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሲመለከት፤ አንጃዎች ደግሞ፥ ያም ቢሆን አላስፈላጊ ግድያዎችንም በመቀነስ መሆን አለበት ባዮች ነበሩ።

አንጃዎች "ይህ እኛ በማካሄድ ላይ ያለነው ትግል፥ አዝማሚያው ወደ ተናጠል ትግል የሚያመራ በመሆኑ፥ ግቡ የግለሰብ ግድያ[5] ብቻ ሆኖ ይቀራል እንጂ፥ አብዮታዊ ሆኖ መሠረታዊ ለውጥን አያመጣም። እንዲህ አይነቱ አሠራር እራሳችን ከማስጨረስ በስተቀር የትም አያደርሰንም። መፈንቅለ መንግሥተኝነትም የቆምንለት አላማና የመጨረሻ ግባችን ስላልሆነ፥ በተራዘመ ጦርነት (protracted war) ሠፊውን ሕዝብ ለሕዝባዊ ሥልጣን ማዘጋጀት ነው ያለብን። በግለሰብ ግድያ ብቻ የትም መድረስ አለመቻላችንን ብናውቅና፥ ዘላቂ ታክቲክና እስትራተጂ ብንቀይስ ይሻለናል።" ብለው መከሩ።

ደብተራውና ተከታዮቹ ሁሉ አንጃዎችን፥ ከመሠረታዊ አመለካከታችው በመነሳት፥ ከመኢሶን መደቧቸው። ጥንትም መኢሶኖች ከኢሕአፓ የተለዩት የወታደራዊውን መንግሥት (ደርግን) እንደ ጊዜያዊ መንግሥት ስለተቀበሉት ነበር። በእውነትም አንጃዎች፥ በዚሁ ግልባጭ አስተሳሰባቸው ወደ መኢሶን አዘንብለዋል። የዋናው (ያልተገነጠለው) የኢሕአፓ አቋም ግን "ይህ የወታደሮች መንግሥት በጠባዩ አምባ ገነን ስለሆነ፥ በራሱ ሥልጣን ጨብጦ ሌላውን ተቃዋሚ ኃይል ያጠፋል እንጂ፥ ሕዝባዊ ተወካዮችን ሁሉ በማቀፍ የሕዝባዊነት ተቋም ሊኖረው አይችልም። ስለዚህ እንደ ጊዜያዊ መንግሥት ልንቀበለው አይገባም። ወቅታዊ ትግላችን ሰፊውን ሕዝብ ለሚያቅፍ ለእውነተኛ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት (የሽግግር መንግሥት ማለት ነው) መሆን አለበት። ከዚያ በኋላ የሚፈጠረው መንግሥት ሰፊው ሕዝብ በሚኖረው ንቃትና አብዮታዊ ትግል ይወሰናል.." የሚል ነበር። በዚህ መሠረታዊ አመለካከት አንጻር፥ ፓርቲውና ተገንጣዮች (አንጃዎች) ሊስማሙ አልቻሉም።

ኢሕአፓ "ሕዝቡ በጊዜያዊ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ይደራጅ" ያለው በጊዜያዊ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሰፊው ሕዝብ አይምሮና አንደበት እንዲከፍትለትና በነፃነት እንዲነጋገር፥ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን ራሱ እንዲለማመድና የገዛ ኑሮውን እራሱ እንዲቀይስ ነበር።

በቅድሚያ "ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት - ለሽግግር መንግሥት" መታገል ያስፈልጋል የተባለውም፥ የወደፊቱን ዘላቂ መንግሥት ሕዝቡ እንዲቀይስ በማሰብ፥ ገና ከጅምሩ ሥልጣን የሕዝብ መሆኑ በግልጥ ታዋቂ ከሆነ በኋላ፥ በሕዝቦች ሁሉ

[5] (putshism)

ተሳታፊነት - ካለ አምባገነናዊነት “ሕዝባዊ መንግሥት”ን ለመመሥረት እንዲቻል ለማድረግ ነበር።

የኢሕአፓዎች አላማ፥ ደርግ (ወታደራዊው መንግሥት) በጉልበቱ የያዘውን ሥልጣን፥ ተራማጅ ኃይላት ባላቸው ኃይል ሁሉ ተጠቅመው፥ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ፥ በእርግጥ ሕዝቦችን የሚወክሉ፥ ሕዝቦችን በጊዜያዊነት መርተው ለዘለቄታው “ሕዝባዊ መንግሥት” ማዘጋጀት ነበር፤ ወታደራዊው መንግሥት ራሱን ጊዜያዊ ብሎ ቢጠራም፥ ሕዝቡን ስለማይወክል፥ ይህንን ማድረግ አይችልምና። ኢሕአፓዎች ለዚህ ቅን አላማ ሲሉ ነበር በሕዝቦች ፊት የተጋረጠውን ወታደር ሥልጣኑን ለሕዝብ እንዲያስረክብ የጠየቁት (የታገሉት)። ይህንን ነው በቁንጽሉ፥ አንጃዎች “መፈንቅለ መንግሥተኝነት” ነው ያሉት።

ግን እዚህ ላይ ለአንባቢ ግልጽ መሆን ያለበት፥ ዋናው ፓርቲ (ያልተገነጠለው) እንዳስቀመጠው አልነበረም የአንጃዎች አስተሳሰብ።

የአንጃዎች “ሕዝባዊ መንግሥት”ና የመኢሶኖች “ሕዝባዊ መንግሥት” በፍልስፍናውና በይዘቱ የተራራቀ ነበር። መኢሶኖች፥ “በዚህ ወታደራዊ መንግሥት እኛ ገብተን አብረን ከሠራን፥ እንደ “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት” ይቆጠራልና፤ ቀስ በቀስ እኛው ሕዝቡ ሥልጣን እንዲጨብጥ እናደርገዋለን..” ባዮች ነበሩ (ብዙ ቢባልም ከዚህ አባባል አይወጣም)።

የአንጃዎች “ሕዝባዊ መንግሥት” ግን ከዚህ እጅጉን ይለያል። እነርሱ፥ ለሥልጣን ሳይስገበገቡ “ሕዝባዊ መንግሥት”ን በቀስታ ለመመሥረት ነበር ሃሳባቸው። እንዲህም ሲሉ አስቀምጠውታል፥ “እውነተኛ ሕዝባዊ መንግሥት ሥልጣን ላይ ጉብ ካሉ በኋላ አይደለም የሚመጣው፤ ብዙ መስዋእትነትን ይጠይቃል። ምንም ያህል ጊዜ ቢፈጅ፥ ሕዝቡን “ለተራዘመ ጦርነት” (protracted war) አስታጥቆ ሕዝቡ ራሱ በራሱ ሥልጣን እንዲጨብጥ መታገል ይገባል። ይህንንም ለማድረግ፥ ሕዝቡ ዲሞክራሲን እንዲያውቅና፥ እራሱን በራሱ ማስተዳደርን እንዲለማመድ፥ አብዮታችን ቀስ በቀስ ከገጠር ወደ ትናንሽ ከተሞች እየገባ በትጥቅ ትግል አካባቢውን ነፃ ሲያወጣና ሥልጣን እየጨበ፥ እራሱን በራሱ ማስተዳደር ሲጀምር፥ ይህም ክስተት ቀስ ቀስ እያለ ጠቅላላ አገሪቱን ሲያዳርስ፥ የዚያን ጊዜ አሮጌው ስርአት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይደመሰሳል፤ የዛን ጊዜ ሕዝቡ ራሱ ባስገኘው ድል ሥልጣን ይጨብጣል፤ ያን ጊዜ ነው “ሕዝባዊ መንግሥት” የሚባለው።”

ግን አሁንም ለአንባቢ ግልጽ መሆን ያለበት፥ ዋናው ፓርቲ የአንጃዎችን “የሕዝባዊ መንግሥት” አመሠራረት ጉዳይ በቀላሉ አልነበረም የተመለከተውም።

"ፓርቲው አያሌ ቅስቀሳዎችን ከከተማ እስከ ገጠሩ ድረስ በሚያካሄድበት ወቅት፥ በአንፃሩም የደርግ መንግሥት ሕዝቡን አፍኖ ሲይዝ፥ በእርግጥ የኢሕአፓ ቅስቀሳና የወቅቱ ሁኔታ ሕዝቡን አላነቃውም ወይ? ለተሻለ ለውጥ አላዘጋጀውም ወይ? ለጥቂት ጊዜ በዚሁ ቢቀጥል፥ የተራዘመ ጦርነት ያስፈልገዋል ወይ?

አንጃዎች "ምንም ያህል ጊዜ ቢፈጅ፥ ሕዝቡን በቻይና የተካሄደውን አይነት ለተራዘመ ጦርነት (protracted war) አስታጥቆ ሕዝቡ ራሱ በራሱ ሥልጣን እንዲጭብጥ ማድረግ ነው" ይላሉ። ግን ይህ ካገራችን ሁኔታ ጋር አይሄድም። ዛሬም ሆነ ለወደፊት፥ እኛ ከቻይና የተለየን ሕዝቦች ነን፥ ባሁኑ ጊዜ የሕዝባችንም ንቃተ ሕሊና ከዚያ አልፎ ሄዷል። ይልቅስ "በጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" የሕዝቦች መደራጀት ከቀጠለ፥ ካለ "የተራዘመ ጦርነት" ሕዝባዊ መንግሥትን መመሥረት ይቻላል ባይ ነው ኢሕአፓ።

በዚህ ጉዳይ ላይ መኢሶኖችም ይስማማሉ። እነርሱ ግን ደርግን እንደ ጊዚያዊ መንግሥት ቆጠሩት (የእነርሱ ከደርግ ጋር መሥራት ደርግን እንደ ጊዜያዊ መንግሥት የሚያስቆጥረው መሰላቸው)። ታላቅ የፖለቲካ ቀውስ።

አንጃዎች ከተጠቀሰው መሠረታዊ የፖለቲካ መነሻቸው ተነስተው የፓርቲውን ጊዜያዊ አቋም ሲተቹ፥ ፓርቲው ከጊዜ ወደጊዜ በግትርነት እየተንገታገተ በራሱና በሕዝቡ ላይ አላስፈላጊ ጥፋቶችን ማስከተሉን በመመልከት ነበር።

የፓርቲው ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ደርግን በቶሎ መደምሰስን ይጠይቃል። ደርግ ደግሞ ከመኢሶኖችና ከሌሎችም ጋር አብሮ ቶሎ የማይደመሰስ ሆነ። "ታዲያ በመሃል ወጣቱ ይለቅ ወይ?" ባዮች ነበሩ አንጃዎች። ከዚህም በመነሳት ነበር ፓርቲው ቆም ብሎ እንዲያስብ የጠየቁት። ከዚህም የተነሳ ነበር "የሕዝባዊ መንግሥትን" እስትራተጂ የተለሙት። አለዚያማ በመካከላቸው የፖለቲካ ቀውስ እስኪገባና ሥር እስኪሰድ ድረስ አንድ ነበሩ።

ባጭሩ፥ የፓርቲው ዋነኛ ትግል ደርግን መደምሰስና "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትን" በመመሥረት ላይ ያተኮረ ሲሆን፥ የአንጃዎች ዋነኛ ትግል ደግሞ ከላይ ለተጠቀሰው የ"ተራዘመ ጦርነት" ብሎም ለመጨረሺያው "ሕዝባዊ መንግሥት" ነበር።

ፓርቲው በመጣላት ፋንታ መስማማትን የሚፈልግ ቢሆን ኖሮ፥ እንደምንም ብሎ አንጃዎችንና ተከታዮቻቸውን ከጉያው ባያስወጣ ኖሮ፥ ያ ኢሕአፓ የተባለ ታላቅ ኃይል እስከ ዛሬ ባልጠፋ ነበር። ግን ማን የሁለቱን እውነት ያስታርቅ?

የአንጃዎች ወቅታዊ ችግሮችን በመፍታት "ወደፊት ሊያራምድ የሚችል" የሚመስል የፖለቲካ እስትራተጂና ታክቲክ ትንተና፥ እንዲሁም የዋናው ፓርቲው ከወቅታዊ ችግሮች ባሻገር፥ በመረረና በከረረ አብዮታዊ ትግል ወደፊት መራመድ

የሚቻል የሚመስል የፖለቲካ እስትራተጂና ታክቲክ ትንተና መካከል ሲካሄድ በቆየ ንትርክ ምክንያት፥ የፓርቲው መሠረት የሆነው የአባላት መንፈስ ተበረዘ። ከሁለቱም አቅጣጫ በሚሰነዘሩ ሠፊና ጥልቅ በሆነው የፖለቲካ ትንተናቸው፥ በአባላቱ መካከል የፓርቲውን አቋም አጠያያቂ አደረጉት። ታላቅ የፖለቲካ ቀውስ ተከሰተ።

በደብተራው የሚመራው ፓርቲ፥ "ትግል ካልመረረ፥ ካልከረረ፥ ምኑን ትግል ሆነ?" በሚል መርሆ መሠረት፥ ከቀድሞው አቋሙ ትንሽም ፈቀቅ (ፍንክች) የማይል ሆነና፥ በአንጃዎች ላይ ተቃውሞውን በማስተጋባት፥ የራሱን የማያወላዳ አመለካከቱን አጠናከረ። በፓርቲውና በአንጃዎች መካከል የተፈጠረው ጭቅጭቅ በጣም ተካረረ።

ፓርቲው ተገንጣዮችን በማቀፍ አብሮ መሥራት ስላልቻለ፥ ሀ እና ለን በአንጃ ፈጣሪነት ከፓርቲው አስወገዳቸው። ሀ እና ለ ግን በውስጣዊ ትግል የፓርቲውን አመለካከት ለውጠው፥ አብሮ መዝለቅ (አብሮ መታገል) የሚቻላቸው መስሏቸው እንደነበር ካቀረቡት ዘገባ መረዳት ይቻል ነበር፤ ግን ይህ አልሆነም። አለመሆኑ ሲገባቸው ይሆናል፤ አንጃዎች አመረሩ። ከዋናው አብዮታዊ ትግል ይልቅ የእርስ በርስ ትግሉ ላይ አተኮሩ።

እንዲህ ከሁለት በተከፈለው የውስጥ ፓርቲ ጭቅጭቅ የተነሳ፥ ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚጎዳ ባለማሰብ፥ አንዱ ሌላውን በጠላትነት መውጋትን መረጠ። "አብዮታችንም ከገጠር ወደ ከተማ እንጂ፥ ከከተማ ወደ ገጠር መሄድ የለበትም" በማለት አንጃዎች ለተራዘመ ጦርነት በበኩላቸው ሲዘጋጁ፥ የፓርቲውን የጦር ክፍል መደበኛ ሥራውን እንዳይሠራ ያሰናከሉት ጀመር[6]።

ይህ በዚህ እንዳለ፥ የሱማሌ ጦርነት ተጀመረ። ፓርቲው በሱማሌ ጦርነት ጉዳይ ላይ፥ "ሁለቱም ፋሺስቶች ስለሆኑ፥ ሁለቱንም እንዋጋለን፤" የሚል ለአባላቱ ግልጽ ያልሆነ መመሪያ አወጣ። አሁንም ፓርቲው በመሠረታዊ አቋሙ ላይ የጸና በመሆኑ፥ ሁለቱም ፋሺስቶች ናቸው አለ እንጂ፥ የሱማሌን ጦር የመደገፍ ዝንባሌ አልነበረውም። ሁለቱም ፋሺስቶች ናቸው ሲል ደግሞ፥ ሁለቱም የሕዝቦች ጠላቶች መሆናቸውንና፥ ገና ለገና የውጪ ጠላት መጣብን በማለት ስንደናገጥ፥ የቆምንለትን ትግል እንዳንረሳ በማሰብ ነበር። የዚህም የቆምንለት ትግል አላማ፥ በሕዝቦች የተቀነባበር ሕዝባዊ አመጽ (በገጠር እንዲሁም በከተማ) ይህንን ፋሺስታዊ መንግሥት ገርስሶ፥ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት ስለሆነ፥ ጓዶች በግርግር የቆሙለትን አላማ ስተው እንዳይወናበዱ፥ የኢሕአፓ የበላይ አካላት መልእክታቸውን ለበታች አካላት አስተላልፈዋል።

---

[6] የዛን ጊዜ "ሀ" ተብሎ የሚጠራው የአንጃ መሪ ነበር የጦር ክፍሉ ኃላፊ።

ነገር ግን ከፉ ወሬን ለሚበትን እርኩስ መንፈስ ትንሿ ቀዳዳ ትበቃለችና፤ ሀ እና ለ "የውጪ ጠላት አገርን ሲወር እንዴት ዝም ይባላል?" በማለትና ነገር በማጋነን ኢሕአፓን ማስጠላት ጀመሩ። "ይልቅስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት እንዲህ በተደፈረበት በአሁኑ ወቅት ከማንም ጋር ያለንን ልዩነት ትተን አገራችንን ከወራሪ ጠላት መከላከል ይገባናል እንጂ፥ ገለልተኛ አቋም መውሰድ ተገቢ ነውን?" በማለት ኢሕአፓን የኢትዮጵያ ጠላት አስመስለው፥ እነርሱ በሱማሌ ጦርነት ላይ የያዙትን ጥርት ያለ አቋም አስተጋቡ። መቼም አንጃዎች ነገሮችን ሲያብራሩ የጊዜውን ሁኔታ እያስታከኩ ስለሆነ፥ የኢሕአፓን ደካማ ጎኖች ተጠቀሙበት። ነገር በማጋነን፥ የራሳቸውንም አቋም ግልጥልጥ አድርገው ስለነበር፥ እነርሱን የሚሰሙ በረከቱ።

የፓርቲውን ጥልቅ ፍልስፍና መረዳት ቀላል አልነበረም። እስከዛሬ ድረስ በፓርቲው ላይ ትችት የበረከተው፤ ጥልቅ ፍልስፍናውን ባለመረዳት ነበር። ይልቁንም በፓርቲው ውስጥ ምንም ተሳትፎ ያልነበራቸውና በውስጥ ትግል የነበረውን ልዩነት ያልደረሱበት (ያላወቁ) ጥራዝ ነጠቆች፥ ከልብ የደከሙላትን - የደሙላትን - የሞቱላትን ጀግኖች እያጥላሉ፥ እነርሱን ልክ እንደ አገር ጠላት - አናርኪስት መቁጠራቸው እጅጉን የሚያሳዝን ጉዳይ ነው።

ለሥልጣን የተሽቀዳደመ ማነው? የኢትዮጵያን አብዮት መልክ ያሳጣውስ ማነው? አንጃዎች በጎን ፓርቲውን የኢትዮጵያ ጠላት የማስመሰል ፕሮፓጋንዳቸውን ቀጠሉ፤ በመጠኑም ቢሆን ተሳክቶላቸዋል።

በተፈጠረው የውስጥ ትግል ምክንያት፥ በፓርቲው ውስጥ የተከሰተ የአመለካከት ልዩነት የአባላቱን የትግል መንፈስ አዳከመው፤ የትኩስ አብዮታዊ አባላትን ተስፋ አጣመመው፤ ቀና አስተሳሰባቸውን መረዘው፤ ርዕዮተ አለማቸውን አጨለመው፤ ስሜታቸውን ሁሉ በጠበጠው፤ ሃሞታቸውንም አፈሰሰው። በዚሁ ልዩነት ምክንያት ብቻ የፓርቲውን ሥራ በትክክል መሥራት፥ ከበላይ አካል የሚመጣውንም ወደታች ማስተላለፍ አስቸገረ።

ከሱማሌ ጦርነት በኋላ አንጃዎች የፓርቲ አባላትን ለመንግሥት እያጋለጡ ማስጨረስ ጀመሩ። አንጃዎች በመንግሥት ከፍተኛ ሥፍራ እየተሰጣቸው ከደርግ ጋር እጅና ጓንት ሆኑ። የፓርቲውን የአሰራር መዋቅር (እስትረክቸር) በውስጡ የተካተቱትንም አባላት የስም ዝርዝር አሳልፈው ሰጡ። በየከፍተኛውና በየቀበሌው በመሠማራት አባላትን በየስማቸው እየጠሩ አሳሰሩ፤ አስገደሉ።

**<u>ትችቶች በኢሕአፓዎች ላይ</u>**

ከተጠቀሰው አርእስት ወጣ ብሎም ቢሆን፥ ሳይረሳ፥ ስለጊዜው ተቺዎች፥ እነርሱም የነገዎቹ ተተቺዎች ከመሆን እንደማያመልጡ ማሳሰብ ግድ ይላል። የዘመኑ ተቺዎች፥ ያገር ተቆርቋሪዎች፥ እውነተኛ ታጋዮች በመምሰል፥ በተለያዩ መድረኮች ላይ በመውጣት፥ "ከጥንቱም ኢሕአፓ የሻቢያ ቅጥረኛ እንጂ፥ ለሰፊው ሕዝብ የቆመ፥ የእውነተኛ ታጋይ ድርጅት አልነበረም....." እያሉ ይተቻሉ።

በመጠኑም ቢሆን ስለዚህ ኢሕአፓ የተሰኘ ፓርቲ ጥሩና መጥፎ ጎኑ ለመግለጽ ሞክሬአለሁ። አንዳንድ ጊዜ ትችቶች መረን የለቀቁ (አጉል አሉባልታዎች) ይሆኑና ያናድዳሉ። አልፎ አልፎ የኢሕአፓ ፓርቲ አባል ካልነበሩ ግለሰቦች የምንሰማቸው ትችቶች፥ ከመሠረቱ ከኢሕአፓ ጠላቶች፥ ወይንም ተቀናቃኝ ኃይላት የመነጩ መሆናቸውን ሳይገነዘቡ፥ በተደጋጋሚ የሚሰሟቸውን፥ "ኢሕአፓዎች የአገር ጠላቶች፥ አናርኪስቶች፥ ቅጥረኞች ናቸው (ነበሩ)" እያሉ የሚያናፍሱት የሃሰት ፕሮፓጋንዳዎች መሆናቸውን አንባቢ ያስተውል።

ዋናው ፓርቲም ቢሆን፥ አንጃዎችም ቢሆኑ፥ በእውነት ከልባቸው ታገሉ እንጂ ቅጥረኞች፥ የሕዝብ ጠላቶች አልነበሩም። የፖለቲካው ፍልስፍና በዝቶ ነው ያደናቆረን። የጊዜውም ሁኔታ ከማንኛውም የፖለቲካ ፍልስፍና በላይ ሆነና፥ በሰው እውቀት የማይፈታ ሆኖብን ነው ከዚህ ያደረስን። ነገሮችን ሳያውቁና ሳያገናዝቡ፥ ከውጪ ሆኖ በማስተዋል ብቻ፥ ለትችት መሽቀዳደም ፋይዳ የለውም። ይልቅስ ተቺዎች ከትችቶቻቸው በማስቀደም የኢሕአፓን ርዕዮት ይመርምሩ፤ ቀጥሎም እነርሱን ራሳቸውን የኢሕአፓ አባል ከነበሩት ጋር (ተሳትፎአቸውን ሁሉ) አወዳድረው ይመልከቱት። በእርግጥ ከውጪ ሆኖና ከውስጥ ሆኖ መመልከት የተለያየ ሊሆን ይችላል። ሆኖም፥ መሠረተ ቢስ ከሆኑ ትችቶች ይልቅ፥ ትክክለኛ መረጃዎችን የተከተሉ - በእውነቶችና በእውቀቶች ላይ የቆሙ ትችቶች ናቸው ወደፊት የሚያራምዱት።

ሰዎች ሁሉ ከግላዊ ስሜቶቻቸው ሁሉ ባሻገር (ፖለቲከኞችም ከፖለቲካ ግቦቻችን ባሻገር) እውነቱን እውነት፥ ውሸቱን ውሸት ማለትን ቢደፍሩ፥ ብዙ ችግሮች በተቃለሉ። በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቶቻችን መካከል እውነት የሚመስሉ ውሸቶች (እንዲሁም ቅልጥጥ ያሉ ውሸቶች) እየተሰገሰጉ ነው ሰላም ያጣነው።

ውሸትም እውነትም አንዱ አንዱን ሳያውቀው፥
ጊዜ ነው መስተዋት ገላልጦ 'ሚያሳየው፤
ውሸት ሲሽማቀቅ ጊዜ ሲያሳፍረው፥

እውነት ግን ቦግ ይላል፥ ጊዜ ሲያሞግሰው።

ከእውቀቶችም መካከል ጥላቻና መከፋፈልን በሚያመጡት ላይ ማተኮር ወደኋላ ያስቀረናል። ለሕዝቦች ፍቅር እና አንድነት የሚጠቅሙትን እውቀቶች ማዳበር ነው ወደፊት የሚያራምደን።

ዘርፈ ብዙ እውቀቶችን ተሸከመውት ዝም ማለትን የመረጡ፥ ከእውቀቶች መካከል እውነተኛውን (ጠቃሚውን - ለሕዝቦች ፍቅርን እና አንድነትን የሚያመጣውን) ለይተው ባለማወቃቸው ይሆናል። ሕዝቦችን ከሚለያይና ከሚከፋፍል እውቀት ድንቁርና ይሻላል። መማርና መወቅ ጥሩ ሆኖ ሳለ፥ ከሁሉም የተሻለው ግን ጥበብ ነው። ጥበብ በመማርና በማወቅ ሊገኝ ቢችልም፥ መማርና ማወቅ ግን ብቻውን ጥበብን አያስገኝም። እኛ የደማነው - የሞትነው የአገር ጠላት ሆነን እንዳልሆነ ተገንዝቦ፥ ከአጉል (በታኝ) ትችት መቆጠቡ በተሻለ።

## <u>የኢሕአፓ መዋቅር መመታት እና ውጤቱ</u>

አንጃዎች በተፈጠሩ በጥቂት ወራት ውስጥ፥ በዋነኛነት ሲታገል የነበረው የተቃዋሚው የኢሕአፓ ኃይል እጅጉን ተዳከመ፤ የመንግሥት ኃይልም ከአባሪ ኃይላት ጋር እጅጉን ተጠናከረ። በመንግሥት ካድሬዎችና በአንጃዎች እገዛ፥ በየቀበሌው የኢሕአፓ ተከታዮች የሆኑትን ሁሉ ማሰር ተጀመረ።

የፓርቲው መሠረታዊ ተቋም ባልተነካበት ወቅት፥ እኔ ከዲሞክራሲያዊ ግንባር አባላት ጋር እንድሠራ ታዝዤ ነበር። የዲሞክራሲያዊ ግንባር ዋና አላማ፥ ዲሞክራሲያዊ ዝንባሌ ያለው ሰፊው ሕዝብ ለሕዝባዊ አመጽ በሚነሳበት ወቅት (መብትና ፍትህ ማጣት፥ መታሰርና መገደል ሲበዛበት፥ ሲመረውና ሲቸግረው መነሳቱ ስለማይቀር)፥ የትግሉ አቅጣጫ፥ ያንን ቋፍ ላይ ያለውን ፋሺስታዊውን የደርግ መንግሥት ለመጣል በሚያስችል መንገድ ትግሉን ማቀነባበርና መምራት ነበር። ይህንን የፓርቲውን አላማ ወደ ሰፊው ሕዝብ ሰርጎ እንዲገባ ለማድረግ ነበር፥ አንዳንድ የፓርቲው አባላት በየዲሞክራሲያዊ ግንባሮች እንድንገባ የተደረገው።

በአንጃዎች እርዳታ የፓርቲው መዋቅር በመንግሥት እጅ ገባ። የወጣቶች ክንፍና የዲሞክራሲያዊ ግንባር በቅድሚያ ተመታ። እኔም በዛን ወቅት በዲሞክራሲያዊ ግንባር ተሳትፎ ስለነበር፥ ቀበሌዎች ከቤቴ መጥተው እንደሚወስዱኝ እርግጠኛ ነበርኩና፥ ሌላ ክፉ ነገር ሳይመጣ ተዘጋጅቼ ጠበቁኳቸው። ቤቴን አንኳኩተው ሲገቡም ቶሎ ብዬ ከፈትኩ። ከሊቀመንበሩ ጋር አልፎ አልፎ ከአንድ ቢራና አረቄ መቃመሺያ ሥፍራ ስለምንገናኝ በተለይ የኔ “ጸረ አብዮተኛ” መሆን እጅጉን ነበር ያስቆጣው። ልክ በሩ ሲከፈትና ፊቱ ድቅን ስል በዛ ደንዳና መዳፉ አንዴ ፊቴን

ሲመርግብኝ ከአንድ የአብዮት ጠባቂ ላይ ወደቅሁ። “በሉ ውሰዱት ብሎ አዘዘ።” እያዳፉ ወስደው ከቀበሌው እስር ቤት፥ ከኔ በድሜ ከሚያንንሱ ወጣቶች ጋር ደባለቁኝና ከዚያ ሰነበትኩ።

ከእለታት በአንድ ቀን፥ የታሰርኩበት የቀበሌው ዋነኛ ካድሬ፥ ከእስረኞቹ መካከል እኔን ብቻ ነጥሎ አወጣኝ። “ና! ለከባድ ጉዳይ ትፈለጋለህ” ብሎ ከቢሮው አስገባኝ። እኔም “የፓርቲ አባል መሆኔ ስለተነቃብኝ ሊገለኝ መሆን አለበት” በማለት እራሴን ለሞት ማዘጋጀት ጀመርኩ። ወዲያውም ለካድሬዎች ብቻ የተዘጋጀ ጃኬት አምጥቶ “በል ይሄንን ልበስ” አለኝ። እኔም ለተጠየቅሁት ሁሉ ተባባሪ በመምሰል “እሺ” አልኩና ጃኬቱን ለብሼ እሱኑ መሰልኩለት።

በዛን ወቅት፥ “ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች” የተሰኙ፥ በየመሥሪያ ቤቱ በዝቅተኛ ደምወዝ የሚስተዳደሩ (ተላላኪዎችና ዝቅተኛ የቢሮ ሠራተኞች)፥ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ከጨበጡ ጋር ሆነው የሶሻሊስት የፖለቲካ ትምህርት ይሰጣቸው ነበር። ከነኚህም መካከል፥ በአብዮታዊ ካድሬነት ተመርቀው፥ “ለአብዮት መከላከያ - መጠበቂያ” የተሰኘ ሽጉጥ እየተሰጣቸው ወደ መደበኛ ሥራቸው የተመለሱ “እኛስ በአብዮታዊነታችን ምን እንሥራ? እንዴትስ በመንግሥታችንና በአገራችን የተነሳውን ጠላት እንከላከል” በማለት በየመሥሪያ ቤቱ አላስፈላጊ ሁከት ሲፈጥሩ ቆይተዋል። እኔ ከምሠራበት መሥሪያ ቤትም እንዲሁ።

የቀበሌው ካድሬ “በል ተዘጋጅ፤ ዛሬ አንተ ወደምትሠራበት - መሥሪያ ቤትህ ሄደን ጸረ አብዮተኞችን ሁሉ እየፈነቃቀልን እናወጣቸዋለን” አለኝ። ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባኝም። ከውጪ ወደተዘጋጀልን መኪና ገባንና ወደ መሥሪያ ቤቴ አመራን። ልክ እንደደረስን የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ሁሉ ከውጪ ቆመው እኛን ይጠባበቃሉ። እኛ ከመምጣታችን በፊት ግን፥ እነኛ “ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች” የጊዜው ካድሬዎች፥ “ጸረ አብዮተኞች” ያሏቸውን ሁሉ ለብቻ ለይተው ወደ እስር እንዲጓዙ ወስነውባቸዋል። እንግዲህ የኔ ከዚያ ሥፍራ መገኘት፡- አንድም “ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች” ለይተው ያወጧቸውን “ጸረ አብዮተኞች” የተባሉትን በኢሕአፓ በኩል ያላቸውን ተሳትፎ እንዳረጋግጥላቸው ሲሆን፥ በተለይ ያልተጠቆመባቸው የኢሕአፓ አባላት ካሉ ደግሞ፥ ወዲያውኑ እየጠቆምኩ እንዳወጣ ነበር። ይህንን ጉዳይ ለማጠናከር ሲል የቀበሌው ሊቀመንበር በጣም ይገፋፋኝ ጀመር። “ሲጋራ ልስጥህ? ሽጉጥ መታጠቅ ፈለግህ? በል ቀኑ ሳይመሽ በቶሎ አውጣ” ይለኛል።

በኔ መሥሪያ ቤት ውስጥ በወጣት ክንፍ እንዲሁም በፓርቲው የታቀፉ ብዙዎች ነበሩ። ግን በዚያን ወቅት የታሰርኩት እኔ ብቻ ነበርኩ። በፓርቲ ሕዋስ

በማቀፍና በሌሎችም ሥራዎች ከፓርቲው ጋር ንክክ የነበራቸውን ከሞላ ጎደል ሁሉንም አውቃቸዋለሁ። ከሩቅ ቆሜ ሳያቸው "ካሁን ካሁን ያጋልጠናል" እያሉ የፈሩም ይኖራሉ። እንዳው መተያየት ብቻ ሆነ። "ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች" እነርሱን ጠቁመው ለማውጣት የሚያስችል ብቃት አልነበራቸውም (የፓርቲው አሠራር የረቀቀ ስለነበር)። እንዳው ካድሬ በመባላቸውም በሠራተኛው ሁሉ ላይ ያላቸውን ሥልጣን ለማሳየትና ለማስፈራራት፥ ተጣልተዋቸው የነበሩትንም ሁሉ "ጸረ አብዮተኞች" እያሉ፥ በቂም በበቀል ሊያንገላቷቸው ፈልገው ነው እንጂ፥ እነርሱ ከፓርቲው ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉትን ግለሰቦች ለይተው የማውጣት ችሎታ የላቸውም።

የቀበሌው ካድሬ "በል እንጂ፥ መሸብን እኮ! አታወጣም እንዴ?" አለኝ በቁጣ፥ እንደማስፈራራትም ብሎ። እኔም "ምንድነው የማወጣው?" አልኩት። "አሁን ከዚህ ሁሉ ሕዝብ መካከል የኢሕአፓ አባል ይጠፋል? በል ጠቁም፤ አለዚያ ትቀምሳታለህ" ብሎ በድጋሜ አስፈራራኝ። እኔም ፍርጥም ብዬ "ከዚህ ሁሉ ሕዝብ መካከል የኢሕአፓ አባል ይጠፋል ማለት እንዴት ይቻለኛል? ነገር ግን አንተም እንደምታውቀው፥ በቀበሌ ተጠቁሞብኝ ነው የታሰርኩት። በዲሞክራሲያዊ ግንባር ተሳታፊነቴ ተይዤ ታሰርኩ። የማውቀውን ሁሉ በዚያ ተናግሬአለሁ። ከመሥሪያ ቤቴ ሠራተኞች ጋር ንኪኪ ቢኖረኝ ኖሮ እጠቁምልህ ነበር። እኔ ከዚህ በላይ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም" በማለት ስናገር የአመነኝ ይመስለኛል።

"ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች" ከኛ ለመስማት እየተጣደፉ ቀረቡን፤ ካድሬውም ቆጣ ብሎ "በሉ የተጠቆሙትን አምጧቸው" አለ። እነርሱኑ አምጥተው ሦስቱን እኔ ካለሁበት መኪና አስገቧቸው። ሌሎቹ ሁለቱ በሌላ መኪና ገቡ። ሁሉንም በደንብ ስለማውቃቸው፥ አንዳቸውም በኢሕአፓ ውስጥ እንዳልሠሩ እርግጠኛ ነበርኩ።

እኔ ካለሁበት የገቡት ሴቶች ናቸው። ልክ እንደገቡ ማልቀስ ጀመሩ። ሁለቱ ይንሰቀሰቃሉ፥ አንደኛዋ "አሁን ምን ባጠፋሁ፥ ምንስ ስሠራ ተገኘቴ! እያለች" ትጮሃለች። ካድሬውም ቆጣ ብሎ "ዝም በሉ፤ የሠራችሁትን መቼ አጣችሁት?" አለ።

ካድሬው ወደኔ ፊቱን ዞር አደረገ፤ እኔና እርሱን አንድ የፖለቲካ መሥመር ተከታዮች በማስመሰል። ቀስ ብሎም "እንግዲህ እነኚህ ናቸው በኢሕአፓ ተሳትፈዋል የተባሉት። ስለነኚህስ ምን የምታውቀው አለህ?" አለኝ። እኔም "በእውነት ስለእውነት እኔ እነኚህን የማውቀው በመሥሪያ ቤት በሥራ ጉዳይ ብቻ ነው እንጂ፥ ከዛ ውጪ የሚሠሩትን አላውቅም" አልኩት። "እሺ አንተ አታውቅም። ግን የሚያዋጣቸው በቶሎ

ቢያጋልጡ መሆኑን፥ አለዚያ የሚያስከተለውን ፍዳ አብራርተህ ንገራቸው” አለኝ። እኔም “እሺ” አልኩና ማባበል ጀመርኩ።

“እንግዲህ የሚያዋጣችሁን ስነግራችሁ በደንብ ስሙኝ፡- እኔ በቀበሌ ተጠቁሞብኝ በሠራሁት ታሠርኩ። የሠራሁትንም ሁሉ ተናገርኩ። እኔ ከናንተ ጋር ከመሥሪያ ቤት ሥራ ውጪ ምንም ግንኙነት ስለሌለኝ፥ እናንተ በኢሕአፓ የሠራችሁትን ያልሰራችሁትን ላውቅ አልችልም። እናንተ የሠራችሁትን እውነቱን ብቻ ተናገሩ፤ ምንም አትሆኑም። ግን ገና ለገና በነፃ እንለቀቃለን ብላችሁ የማታውቁትን ሁሉ ብትቀባጥሩ ወዮላችሁ፤ ዋ! መገረፍ ብቻ አይደለም፤ ከዛው ከስር ቤት ትማቅቃላችሁ።” እነርሱም እንዲህ ስመከራቸው ሰሙኝና ትንሽ ተረጋጉ።

ከቀበሌው እስር ቤት ደረስን፤ ካድሬው ሁሉንም ወዲያው ወደቢሮው እየወሰደ አነጋገራቸው። በኢሕአፓ ምንም ተሳትፎ ስላልተገኘባቸው ከጥቂት ቀናት በኋላ ተለቀቁ።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ የዋናው ፓርቲ መዋቅር አልተመታም ነበር። ግን የመንግሥት ኃይል እጅጉን አይሎ ስለነበርና፥ በከተማው ውስጥ እንደልብ መንቀሳቀስ ስላስቸገረ፥ ሁሉም ራሱን ለማዳን ነበር የሚሯሯጠው። የፓርቲ አባላት ከተያዙ ወዲያው ይገደላሉ።

በዚሁ የቀበሌ እስር ቤት ሁለት ወር ሊሞላኝ ሲል፥ እንደኔ የተጋለጡበትን ብቻ ተናግረው፥ ያላጋለጡትን ደብቀው የተደበቁ፥ በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፉ የኢሕአፓ አባላት መኖራቸውን ተጠራጠርኩ። ቀስ ቀስ እያልኩ፥ ፊታቸው ላይ ጭንቀት የሚታይባቸውን እየለየሁ ወሬ መልቀም ጀመርኩ። ከነኚህ ተጨናቂዎች መካከል አንዱ ቀስ ብሎ ሹክ አለለኝ። እዛው እስር ቤት እንዳለሁና ለመፈታት ጥቂት ቀን ሲቀረኝ፥ ሌሎች ከኔ ጋር ይሠሩ የነበሩ የፓርቲው አባላት ሌላ ቀበሌ መታሠራቸውን በድብቅ ነገረኝ። ከእስር ቤት ሳልወጣ ይህ በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፍኩበትን አለማጋለጤ ቢታወቅ የሚገድሉኝ ስለሆነ፥ ባጋልጥም መገደሌ ስለማይቀር፥ በውስጣዊ ፍርኃትና ጭንቀት ተጠመድኩ።

ተመስገን። ምንም ሳልጠረጠርና እንዳጋልጥም ሳልጠየቅ በሁለት ወር እስር ብቻ ተገላገልኩ። በዚያን ወራት ውስጥ የመታሰር ጽዋ ያልደረሳቸው የዋናው ፓርቲ አባላት በከተማም ሆነ በገጠር ድምጻቸውን በማጥፋት፥ ፓርቲውን እንደገና ለማደራጀት ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉበት ወቅት ነበር። ከእስር ቤት ከተፈታሁ በኋላ መሄጃ አጣሁ። ተመልሼ ቀበሌ ብቀመጥ ይይዙኛል፤ ይዘውም ይገድሉኛል ብዬ መደበቅ ጀመርኩ። ተደብቄም ሁለት ሃሳቦች በጭንቅላቴ ይመላለሱ ጀመር። የኸውም፡-

አብረውኝ ይሠሩ ከነበሩትና ከታሰሩት ጋር ሌላ እስር ቤት መቀላቀልና እንደነርሱው ኃጢአቴን ተናዝዤ መቆየት፤ የሚከተለኝንም የመዳን ወይም የሞት ጽዋ መጠባበቅ፤

ሌላውም አማራጭ፡- የጀመርኩትን አብዮት ዳር ማድረስ ስለሆነ፥ እንደገና ለመደራጀት ከፍተኛ ጥረት ከሚያደርጉ ጓዶች ጋር በመሆን፥ ለአዲስ ትግል መዘጋጀት።

ከእስር ቤት ወጥቼ ትንሽ ቀናት እንደቆየሁ፥ የፓርቲ ኮሚቴአችን አገናኝ (የበላይ አካል) ስለኔ በሌላ የፓርቲው አካል ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ስለመሳተፌ እንደተናገረ በድብቅ ሰማሁ። ደግነቱ ይህ ግለሰብ የፓርቲ መጠሪያ ስሜን እንጂ፥ እውነተኛ ስሜን አያውቅም ነበር። ግለሰቡ አቅመ ደካማ ስለነበር በቅጥቀጣ ብዛት ሞተ (አዝናለሁ)።

ከኔ ጋር ለጥቂት ቀናት የሠራች፥ ከግለሰቡ በላይ የ RC (Regional Comitee) አባል የነበረችዋን፥ ሊይዟት ሲሉ የራሷን ሕይወት በገዛ ራሷ አጠፋች። ይህቺ ሴት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ጥሩ ሥራ የነበራት፥ ከቁንጅናዋ ጋር ፈገግታ የማይለያት ምሁር ነበረች፤ በህቡዕ ስትታገል ብዙ ጊዜ ቆየችና፥ ገና ከአፈጣጠሯ ለአብዮት የተሰጠች ደናግል (መነኩሴ) መስላለች።

አዬ! አንቺ ቆንጆ ሴት፥ ለአብዮት ብለሽ የተከበረ ሥራሽን ለቀሽ፥
ነጠላሽን ተከናንበሽ፥ የቤት ሠራተኛ መስለሽ፥
ስትመሪ፥ ስታስተምሪ -
የዲሞክራሲያ መጽሔታችንን በጡቶችሽ ማሃል፥
ጽሑፎችን በጉያሽ እየወሸቅሽ፤
በህቡዕ ስታደራጂ፥ ከአንድ አባል ወደ ሌላው ስትመላለሺ፥
ቀኑን ሙሉ ስትደክሚ፥ ሳይነቃብሽ ብዙ - ብዙ ሠርተሽ፥
ለአገርሽ፥ ለወገኖችሽ ብለሽ፥
እውነቶችሽን እንቅ አድርገሽ ይዘሽ፥
መንፈሴንስ ከጓዶቼ አልለይም ብለሽ፥
ከራስሽ ተለየሽ - በፈቃድሽ።
በሥራ ብዛት ብርር ያሉ - ፍዝዝ ያሉ አይኖችሽ፥
ድክም ያለው ሰውነትሽ፥ ለደርጎች በድን ሆኖ ወደቀልሽ - ገላገለሽ።
  እንደ ኅበዛዝት የኢሕአፓ ሰዎች፥

እጅ ላለመስጠት ራሷን የለየች፤

መንፈሷን እንዳይወስዱ ሥጋዋን የተካች፥

ዛሬም ይህች ሴት አለች።

ምርጫዋን አስተካክላ ሰማይ የወጣች ሴት፥

"በአውራ ጎዳና" የሚመላለሱትን የምትመለከት፥

ትላንት የነበረች፥ ዛሬና ወደፊት የምትኖር፥ በመንፈስ የማትሞት፥

ያውና መሰሏ ደጉ ሰው/ደጓ ሴት - ሕያው ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት።

ከጥንት ጀምሮ ካላግባብ የተገደሉ የኢትዮጵያኖች መንፈስ በሙሉ በየመንገዱ "በየአውራ ጎዳናው" ይመላለሳል፤ ቁልጭ ያለ እውነት በኢትዮጵያ እስኪመጣ ድረስ ይጮሃል፤ ይዘምራል። ኢሕአፓዎችና ሌሎችም የራሳቸው እየመሰላቸው የዘመሩት መዝሙር በራዲዎ ሲዘመር በየመንገዱ ይሰማል። ታጋይ የተባለው ቃል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲታገሉ ሕይወታቸውን ያጡትን ሁሉ የሚያጠቃልል ከሆነ፥ ይህ አብዮታዊ መዝሙር ለማንኛውም ታጋይ የሚገባ ነው።

እንዲህ አለች ሙታን ተራማጅ፥ እንዲህ አለች እርሱም እንዲህ አለ፤

መች ሞቱና ሞቱ ተባለ።

የታጋይ ድምጽ ይጮሃል፥ ይጮሃል ከመቃብር፥

ተከቶን ታጋይ ያልፋል፥ ትግላችን ይቀጥላል።..

ሌሎች በጎን (በስነጽሑፍ ኮሚቴ) አብረውኝ ይሠሩ የነበሩት ግን እንዳልታሰሩ ሰማሁ፤ ይኑሩ ይሙቱ እስካሁን አላወቅሁም። እኔም የማደርገው ጠፍቶኝ ብቻዬን መንከራተት ሆነ ሥራዬ። የጀመርኩትን ትግል በፈቃዴ መግታት ኃጢአት መስሎ ታየኝ። ፓርቲው እንደገና ለመደራጀት በሚያደርገው ከፍተኛ ጥረት መሳተፍ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መስሎ ታየኝ።

ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ፥ ፓርቲው ልብ ገዝቶ የተቀሩትን አባላት የገጠሩ ትግል ወዳለበት ሥፍራ ይሰበስብ ይሆናል የሚል ተስፋ አደረብኝ። ምንም እንኳን በወቅቱ ፓርቲው የሚወስዳቸው እርምጃዎች ስህተቶች እንዳሉበት ቢገባኝም፥ እነኚህ መለስተኛ (የታክቲክ) እንጂ መሠረታዊ (የእስትራተጂ) ስህተቶች ስላልሆኑ፥ አስፈላጊ እርማቶችን ማድረግ ይቻላል በማለት፥ ቃል ኪዳን የገባሁለትን ፓርቲ እንደገና በትኩስ ኃይል ለማገልገል ቆርጬ ተነሳሁ።

ምንም እንኳን የፓርቲውና  የኔ አመለካከት ሙሉ በሙሉ የማይጣጣም ቢሆንም፥ ምናልባት ይህ ጊዜያዊ እንጂ ዘለቄታዊ ስላልሆነ፥ የጀመርኩትን ትግል ለዚህ ብዬ ማቋረጥ የለብኝም ብዬ ወሰንኩ።

አንጃ ፈጣሪዎቹ (ሀ እና ለ) የሚሉትን አይነት የተራዘመ ትግል ባይሆንም፥ የፓርቲውን መመሪያ በመከተል፥ የማያቋርጥ ትግል ለመጀመር ምኞታዋ ተስፋ አደረብኝ። ውስጣዊ የፓርቲ ትግል ማካሄድ ካስፈለገም፥ ለዚህም ቢሆን ዝግጁ ሆኜ የመገኘት ኃላፊነት እንዳለብኝ ሆኖ ተሰማኝ።

## <u>ከመድህን ጋር በመርካቶ</u>

በአይምሮዬ ለብዙ ቀናትና ሰዓታት አውጠንጥኜ፥ በቁርጠኝነት ከዋናው ፓርቲ ጋር ለመገናኘትና ለመሥራት ቆረጥሁ። ይህንኑ ሃሳብ በሥራ ለመተርጎም፥ ከፓርቲው ጋር የሚያገናኝ (ኮንታክት) ፍለጋ ከተማውን ማሰስ ጀመርኩ። መጀመሪያ ካዛንቺስ አካባቢ ፍለጋውን ቀጠልኩ፤ ምንም የፓርቲው የሚመስል ሰው አጣሁ። ወደ ፒያሳ ወጣሁ፤ ሰው ጠፋ።

ከብዙ የፓርቲ አባል ፍለጋ በኋላ፥ ከእለታት አንድ ቀን (እሮብ ለት)፥ ልክ የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት፥ ወደ መርካቶ በሚያወጣው መንገድ ላይ፥ አንድ ጓደኛዬ - ጓድ መድህን - ወደ ታች - ወደ ሜክሲኮ አደባባይ ሲኳትን አገኘሁት። አንድ ጓደኛ  ጓድ ሊሆን የሚችል መሠረታዊ አስተሳሰቡና የፖለቲካ ተቋሙ ሲታወቅ ነው። ከመድህን ጋር  በጓደኝነት ስለምንተዋወቅና አስተሳሰቡንም ስለምረዳ ነው በጓድነት የቀረብሁት።

ከጓዱ ጋር ሰላምታ ተለዋወጥንና ከአንድ ቡና ቤት ገባን። ቡና አዘዝንና እየተጎነጨን ለጥቂት ጊዜ ያህል ዝም - ዝም ተባባልን። ትንሽ ቆይቶ መንፈሶቻችን እርስ በርስ የተነጋገሩ ይመስል፥ በገጽታዎቻችን ከሚታየው ጭንቀት ሁሉ ባሻገር፥ አንዱ የሌላውን ጭንቅላት አነበበ። ካለ ምንም ንግግር፥ እንዲያው በመተያየት ብቻ፥ መድህን የኔን አንጃ አለመሆን እንደተረዳ ገመትሁ። እኔም መድህን የፓርቲው እንጂ የአንጃ ደጋፊ አለመሆኑ ቶሎ ገባኝ።

ወዲያው “አይዞህ! አለን እኮ! ሞተን አላለቅንም እኮ!” አለኝ። ቀጥሎም “ሀ እና ለ አሁንም በደብረ ብርሃን አካባቢ እያስቸገሩ ናቸው። ፓርቲአችን በአዲስ አበባ አካባቢ የተጎዳ ቢሆንም፥ አሁንም በገጠሩ እንደተጠናከረ ነው ያለው። እዚህ መንቀሳቀስ ቢያቅተንም ጫካ ገብተን ከሰፊው ባላገር ጋር እንቀላቀላለን፤ አይዞህ! አይዞን!” አለ፤ በግድ ፈገግ ለማለትም እየታገለ።

መድህን ይህን ሲናገር፥ በአይምሮዬ የነበረው ጭንቀት እልም ብሎ ጠፋ። የኔ ፊት ፈገግ ሲልና እርሱም ሳቅ ሲል፥ ለሁለታችንም ለሰው የማይታይ ጸጋ ከሰማይ የወረደ ይመስል ነበር (ፊቴን ወደ ግራ ዞር ሳደርግ በመስተዋቱ ውስጥ፥ ከመንገዱ ባሻገር፥ ከአጥሩ ዙሪያ ድሆች የተኮለኮሉበት፥ ያው የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ነው ጎላ ብሎ የሚታየኝ የነበረ፤ ግን ይህንን የምጽፍ እኔ - የዛን ጊዜ በእውነት ስለራሴው ችግር እንጂ ስለ ሌላ ነገር አላሰብኩም፥ በጭንቀቴ ውስጥ የተቀረጹ "ነገሮች" ቢኖሩም - "አይ! አይደለም! መድህን ነው መድህኔ።")።

እኔም እንዲህ አልኩ "ከእንግዲህ አጥብቄ የምይዘው ጓደኛም ጓድም የሆንከውን አንተን ካገኘሁ ነፍስ እንደዘራሁ ነው የምቆጥረው።"

አንዳንድ መረጃዎች ከተለዋወጥን በኋላ፥ በሌላ ቀን (ቅዳሜ) መሃል መርካቶ ለመገናኘት ተስማምተን ተለያየን። በዘመድና በጓደኛ ቤት እያፈራረቅሁ ስደበቅ ቆይቼ ሳለሁ፥ የቀጠሮው ቀን እስኪደርስ ድረስ አንዱ ቀን እንደ አንድ ወር ሆነብኝ። ወቅቱ ሳያጋልጡ በየቤት የተደበቁ "ጸረ አብዮተኞች" የሚታደኑበት ወቅት ነበር።

የወደፊቱ ታውቆት እንደፈራ ሰው ሃሳብ የገባኝ መሆኑ ከፊቴ ላይ ቢነበብም፥ በደርግ ጥይት ከመገደል የሚያድነኝን የማውቅ እኔው ነኝ እንጂ ሌላ ማንም ሰው እንዳልሆነ አውቄአለሁ፤ መስሎኛል። ለኔ የሚመክረኝ እኔ ሳለልኝ፥ ለኔ እኔው ከጎኔ የሚነገረኝን ብቻ የምሰማ ሆኛለሁና፤ ከማንም ሰው ምክርና ሃሳብ ለመውሰድ አልፈለግሁም።

የቀጠሮው ቀን ሲደርስ፥ ለመጥፋት መነሳቴን ማንም ሳያውቅ፥ የአገር ድንበር ለማስከበር ወደ ግዳጅ እንደሚሄድ እንደ አንድ ቆራጥ ወታደር ሆኜ፥ ለማያቋርጥ ትግል ወደ መርካቶ አመራሁ። ለመልመድ አስቸጋሪ የሆነውን የመርካቶ መንገድ ሀ ብዬ ለማጥናት ተዘጋጀሁ። የመድህን ቤት መርካቶ መሃሉ ላይ ስለነበር፥ መንገዱንና የቤቱን አካባቢ አጠናሁ። ከጫካ ወጥታ ከተማ እንደገባች ዝንጀሮ ሆንኩና መርካቶ ውስጥ ስምጥ አልኩ።

በቀጠሮውም ሰዓት ከተቃጠርንበት ሥፍራ ተገናኘን። መድህን ሕጋዊ ስለነበር፥ በፓርቲው ውስጥ ጓዶችን ወደ ባላገር ለማሸጋገር ይጥር ነበር። እኔን በየቀኑ በማግኘት፥ ባላገር የምገባበትን ቀን በተስፋ እንድጠባበቅ ይመክረኝ ጀመር። መድህን ከሥራ እስኪመጣ ድረስ ቀኑ እየረዘመብኝ፥ በየቀኑ በተስፋ ብቻ መኖር ጀመርኩ። የዛሬው ተስፋ ወደ ነገ፥ የነገው ደግሞ ወደሚቀጥለው ቀን እየተላለፈ፥ ነገዎች እየበዙ ሲመጡ ጊዜ፥ ሌሎች አላስፈላጊ ሃሳቦች በጭንቅላቴ ይንገዋለሉ ጀመር።

የፓርቲው ከፍተኛ አካላት እኔን "ይህ ሰው የንኡስ ከበርቴነት ጠባይ ስለሚኖረው ለአብዮታዊ ትግል ብቁ አይሆንም...." የሚሉኝ እየመሰለኝ፥ ያሰብኩት

ረጅም የትግል ጉዞና መስዋእትነት እንዳይከሽፍብኝ የምፈራ ሆንኩና፥ ይህንኑ ፍርኃቴን ለመድህን ገለጽኩለት። እርሱም እንዲህ አይነቱን አስተሳሰብ ከጭንቅላቴ እንዳወጣ መከረኝ።

ባሁኑ ወቅት አባላቱን የመንከባከብ ኃላፊነት ጉዳይ ፓርቲው በከፍተኛ ደረጃ የሚመለከተው መሆኑን በመግለጽ አጽናናኝ። እንዲሁም፥ "ካንተ ጋር የሚሄድ ሌላ ካንተ የበለጠ የተጋለጠ (የተበላ) ጓድ አለ፤ ከርሱ ጋር ስለማስተዋውቅህ ነገ በዚህ ቡና ቤት እንገናኝ" ብሎኝ ተለያየን።

## <u>ከአሻግሬ ጋር በመርካቶ</u>

በነጋታው መድህን ከጓድ አሻግሬ ጋር አስተዋወቀኝ። አሻግሬን ቀደም ብዬ አላውቀውም ነበር። ግን ብዙም ጊዜ ሳይፈጅ ጥሩ ጓደኛ ሆነኝና በየቀኑ ከመሃል መርካቶ ሻይ ቤቶች መገናኘት ጀመርን። ካነጋገሩና ከሁኔታው ቆራጥ ጀግና ይመስላል። እንደማንኛችንም ካለ ጠብ መንጃ (ወይም ካለ ሽጉጥ) በጦርነት ውስጥ ያለን የኢሕአፓ የሃሳብ ወታደሮች ሁሉ፥ አሻግሬም በፍርኃትና በጀግንነት መካከል የተጠመደ ነበር። ከኔ የበለጠ አካባቢውን በቁጥጥሩ ያደረገ ይመስላል። ቀልድና ጨዋታ ያውቅበታል፤ አጠር አጠር ያሉ ጨዋታዎችን እየለዋወጠ ሲያመጣ፥ እራሱን በቀላሉ ከድብርት ማውጣት የሚችል መሆኑ ያስታውቃል። እኔ ግን ኑሮን የጀመርኩት አብዮት ከፈነዳ በኋላ ይመስል፥ ከጊዜው ሁኔታ የሚዛመድ ወሬ ካልሆነ በስተቀር፥ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ስላለፈው ጥሩም ሆነ መጥፎ ጊዜ ማውራት አያሰኘኝም። አንዳንድ ጊዜ የኔ ዝምታ እንደሰለቸው ከፊቱ ሳነብ፥ እጅግ አስደናቂ የሆኑ ህልሞቼን አወራለታለሁ። እርሱም በተመስጦ ከሰማ በኋላ፥ ልክ ሲኒማ ቤት ገብቶ እንደ ወጣ ሰው ይሆንና በመገረም፥ ምን ይሆን ፍቺው? ብሎ ዝም ይላል። እኔም "በል ለፍቺው ሌላ ቀን" እለዋለሁ።

አሻግሬ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚፈለግና እኔም በተቻለ መጠን ይህን ግለ ሰብ እንዳይጋለጥ ለመሸፋፈን መጣር እንዳለብኝ በመድህን በኩል ስለተነገረኝ፥ ጉዳዩ ባይገባኝም፥ ለዚህ ግለሰብ አስብለት ነበር።

ከአሻግሬ ጋር ዘወትር ጧት ጧት ብቻ ነበር የምንገናኘው። የምሳ ሰዓት ሲደርስ ጥፍት ይላል። እኔም ከምሳ ሰዓት ጀምሮ እስኪመሽና መድህንን እስካገኘው ድረስ፥ መርካቶን ማሰስ መደበኛ ሥራዬ ሆነ። በደርግ "አብዮት" ካለ ሥራ መንገላወድ ወይንም ባንድ ሥፍራ መቆም ስለማይቻል፥ አውቆ አበድ መስሎ ሮጥ - ሮጥ እያሉ መራመድ፤ አለዚያም፥ የቀን ተቀን ኑሮውን ለሚሟላት እንደሚሯሯጥ ነጋዴ ጣደፍ - ጣደፍ ማለትና መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ማንም ሰው በመንገድ ላይ ሲሄድ አብዮታዊ

ካድሬ በመምሰል፥ ግንባርን ኮስተር አድርጎ፥ ደረትን ነፍቶ፥ ትምክህት በተሞላበት መንፈስ፥ ገልመጥ - ገልመጥ እያለ መራመድ ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ፥ ከቡና ቤት ቡና ቤት፥ ከጠላ ቤት ጠላ ቤት እየዞሩ መጎለትና ጊዜ ማጥፋት ነበር የተቀረው አማራጭ።

ከመድህን ጋር ስንገናኝ የምንጨዋወተው የጊዜውን ሁኔታ የሚመለከት ጉዳይ ብቻ ስለነበር፥ እርሱን በየቀኑ ሳገኘው ከመጠን በላይ ደስ ይለኛል። መድህንና አሻግሬ በማይኖሩበት ወቅት፥ በየቀኑ ሻይ ቤትና ጠላ ቤት እየተመላለሱ ጊዜን መፍጀት እየሰለቸኝ መጣ። ይህም ምናልባት የንኡስ ከበርቴነት ጠባዬ እያቅበጠበጠኝ ይሆናል በማለት ያለኝን ትእግስት ላለመጨረስ ስል እራሴን አጽናናለሁ።

አሻግሬ መድህንን ሊያገኘው ስለማይችል (ስለማይፈቀድለት)፥ የአሻግሬ ተስፋ (ኮንታክት - አገናኝ) እኔው ብቻ ነበርኩ። እኔን ካላገኘ ከፓርቲው ጋር ያለውን ግንኙነት ለመቀጠል ቀላል አይሆንለትምና፤ በመድህን በኩል የቀረበ ተስፋ መኖሩን በየቀኑ ስንገናኝ ይጠይቀኛል።

ከእለታት አንድ ቀን፥ መድህን ከበላይ አካል ጋር በመነጋገር ስለገጠሩ ጉዞአችን አንዳንድ ዝግጅቶች እያደረገ መሆኑን በመግለጽ እንዲህ አለ፡-

“እንግዲህ ለሁለታችሁም የቀበሌ የፈቃድ ወረቀት ለማውጣት መሯሯጥ ይኖርብኛል። ይህ የፈቃድ ወረቀት ከተገኘ በኋላ ነው ኮዱ (የምሥጢር ቃል) የሚዘጋጅ። ሁሉም በቶሎ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ባሁኑ ጊዜ ቀላል እንደማይሆን ሊገባህ ይችላል። የተቻለኝን አደርጋለሁ፤ አይዞህ በርታ።” መድህን ይህንን ብቻ ተናግሮ ቶሎ ተለየኝ።

በነጋታው ጧት ይህንን የምስራች ለአሻግሬ ነገርኩትና በጣም ደስ ተሰኘ። ከአንድ ሳምንት በኋላ መድህን ሌላ የምሥራች ይዞልኝ መጣ። “መልካም ዜና ይዤልህ መጥቻለሁ” ሲለኝ፥ የደስታ ኮረንቲ ሰውነቴን ወረረው። ከዛም ገልመጥ - ገልመጥ እያለ በሹክሹክታ እንዲህ አለ፡-

“ከእንግዲህ አንተና ጓዱ የኮረም ሰዎች ናችሁ። ከዚህ የምትቆርጡት የአውቶቡስ ቲኬት እስከ ኮረም ድረስ ሲሆን፥ እናንተ ግን እዛ ሳትደርሱ፤ ቆቦ የሚባል ሥፍራ ትወርዳላችሁ። አውቶቡሱ ከአዲስ አበባ ተነስቶ፥ ደሴንና ወልድያን አቋርጦ፥ ራያና አዘቦ በሚደርስበት ወቅት፥ ቆቦ የሚባል ከተማ ይቆማል። እናንተም ከዛ ወርዳችሁ ከሆቴሉ አጠገብ ትቆማላችሁ (ያለው ሆቴል አንድ ብቻ ነው)። ከመንገዱ ዳር አንድ ባላገር እግሩን አጣምሮ፥ ነጠላ በራሱ ላይ ጣል አድርጎ፥ በትር ተመርኩዞ፥ ቆሞ ታገኛላችሁ። ከሁለት አንዳችሁ፥ እንበል አንተ፥ ጤና ይስጥልኝ ስትለው፥ ሰላምና ጤንነት ይስጥዎት ይልሃል። ከዛም፥ ይህ መንገድ የት ያደርሳል ስትለው፥ ቀይ መስቀል

ይልሃል። በዚህን ጊዜ እኛው ነን ትሉትና ባላገሩ እየመራ ያደርሳችኋል።" አለ ጓድ መድህን፥ ፍቅርና እንክብካቤ በተሞላ አንደበቱ።

እንዲሁም በድጋሚ "ከእንግዲህ ይህን ያልኩህን እንዳትረሳ፤ እስቲ ያልኩህን መልሰህ ንገረኝ" አለ። እኔም በትክክል ከነገርኩት በኋላ፥ "ከእንግዲህ ይህ በአይምሮ የሚያዝ፥ በልብ የሚጻፍ እንጂ፥ በወረቀት የሚጻፍ አይደለም። ስለዚህ አደራህን እንዳትረሳ" ሲለኝ፥ እኔም ብዙ - ብዙ ኮዶችን በመቀበልና በማስተላለፍ የሠለጠንኩበት ጉዳይ እንዳልሆነ ሁሉ፥ በሙሉ ልቤ "እሺ" አልኩትና ተለያየን።

በማግስቱ ይህንን ታላቅ ዜና ለማብሰር ወደ ተለመደው ሻይ ቤት አመራሁ። የምስራቹን ለአሻግሬ በሹክሹክታ ስነግረው፥ ልክ በገንዘቤ ነፍስ ገዝቼ የሰጠሁት ይመስል እጅግ ደስ አለው። እኔም "ከነገ ወዲያ ወደ ኮረም ለመሄድ የአውቶቡሱን ቲኬት ነገ መቁረጥ አለብኝ" በል እንግዲህ ቲኬቱን ቆርጬ ስለምመጣ ነገ በአምስት ሰዓት እዚሁ ስፍራ እንገናኝ" አልኩትና ተለያየን።

የኮረም አውቶቡስ የሚነሳው ከጧቱ ሦስት ሰዓት ነው። ቲኬቱን ቶሎ መቁረጥ ይሻላል ብዬ፥ በማግስቱ፥ ገና ሳይነጋ በመነሳት፥ ከሥፍራው ስደርስ ከምሽቱ 12 ሰዓት (ወይንም ከጧቱ 6:00 A.M.) እንኳን አልደረሰም። ከኔ በፊት አንድም ሰው ይገኛል ብዬ አካሰብኩም ነበር። ዳሩ ግን ከኔ በኋላ መጥቶ የሚሰለፍ ሰው ጠፋ።

ከኔ ፊት የተሰለፈውን ሰው ስለ ሰልፉ መርዘም እያጋነንኩ ላናግረው ስሞክር፥ "እባክህ ቀልዱን ተወው፤ እኔ ካንተ አንድ ሰዓት በፊት መጥቼ፥ ካላንተ የቀደምኩት ሰው የለኝም" አለ። በዚህን ጊዜ ፍርኃትና ድንጋጤ አደረብኝ። እንደ ምንም ሦስት ሰዓት ደረሰና ቲኬት መቁረጥ ተጀመረ። ልክ የሰልፉ አጋማሽ ላይ እንደተደረሰ፥ "ቲኬቱ ስላለቀ ነገ ተመለሱ" ተባለ።

ይህንን አሳዛኝ ሁኔታ ለሁለቱ ጓዶች እንዴት አድርጌ እንደምነግራቸው ነው ግራ የገባኝ። አውቄ ያደረግሁት ወይም ንዝህላልነት ያስመስልብኛል በማለት እጅግ ተጨነቅሁ። መድህን እኔን በአንጃነት ይጠራጠረኝ ይሆናል በማለትም የሃሳብ ጭንቀት ያዘኝ።

አምስት ሰዓት ላይ ከአሻግሬ ጋር ሻይ ቤት ተገናኘን። ሁኔታውን ሳስረዳው ለጊዜው ክው ብሎ ደነገጠ። ግን ደግነቱ፥ ለሚቀጥለው የተቻለኝን እንዳደርግ አደፋፈረኝ እንጂ፥ እኔን እንደ ጥፋተኛ አልተመለከተኝም። እንደወትሮው የመሄጃው ሰዓት ሲደርስ በቅሬታና በሃዘን ተለየኝ።

ማታ ሲሆን መድህን አገኘሁትና ለርሱም እንዲሁ ስለ ሁኔታው አለመሳካት አስረዳሁት። ጓዱም "የሚያሳስበው የኮዱ ጉዳይ ነው እንጂ፥ የቀበሌውን ወረቀት

እንኳን ለሌላ ጊዜም መጠቀም ይቻላል” አለና፥ ለሚቀጥለው እንድጠነቀቅ መከሮኝ፥ እርሱም በሃዘን ተለየኝ።

ሳምንታት አለፉ፤ ኮዱን በድጋሜ ሠርቶ ማስተላለፍ እጅግ ከባድ ነው የሚሆን። መድህን ካለ ወትሮው ተስፋ የመቁረጥ ምልክት ይታይበት ጀመር። እርሱም “አንጃዎች ጓዶቻችንን ከመንገድ እየጠለፉ ለደርግ ማስረከብ ጀምረዋል፤ እኔም ራሴ በመሥሪያ ቤት አካባቢ ጥቆማ ሳይደርስብኝ አይቀርም” ብሎ ሲነግረኝ፤ የርሱ ተስፋ መቁረጥ ወደኔም ይዛመት ዘንድ ግዴታ ሆነና አይምሮዬን በጠበጠው።

ብዙ ቀናት አለፉ፤ መድህን በየቀኑ አልገኝ አለ፤ በእጄ የነበረ ገንዘብ መነመነ። በየቀኑ ለጠላና ለሻይ የማወጣውን ገንዘብ በቁጠባ መያዝ ጀመርኩ። ከጊዜ በኋላ ለአልቤርጎ የሚሆን ገንዘብ አጣሁና በድንገት የማላውቀውና ያልተለማመድኩት ችግር ውስጥ ገባሁ። ጨለማን ተገን አድርጎ፥ ግርግዳን ተደግፎ መተኛት ሊመጣ ሆነ። እንግዲህ ያለው አማራጭ ይኸው ከሆነ፥ ማን ይፈራዋል። ለኔም ጥሩ ነው፤ የጫካውን ኑሮዬን እለማመድበታለሁ አልኩ።

በዚያው ሰሞን፥ ለማደሪያ ጸጥ ያለ ሥፍራ ስፈልግ አምሽቼ፥ ጨለምለም ያለና ገላጣ ሥፍራ አገኘሁ። ስዞር ውዬ፥ ሰውነቴ ዝሎ፥ እንቅልፍም አስቸግሮኝ ነበረና፥ ቶሎ ብዬ ጨለምለም ካለው ስፍራ ሰውነቴን ጣልኩትና ኩርምት ብዬ ተኛሁ።

ትንሽ እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረገኝ ውሾች መጥተው ከበቡኝ። አሁን ብድግ ብዬ ተነስቼ ብሄድ ግማሽ ጎኔን ቦጭቀው፥ የተቀረውን ግማሽ ጎኔን ለቀበሌ ዘበኞች ይሰጡታል በማለት፥ ቀረብ ሲሉኝና ሲያሸቱኝ ትንፋሼን ያዝ በማድረግ ልክ እንደ ሞተ ሰው ሆንኩባቸው። በቁጥር ሰባት የሚሆኑ ውሾች እያንዳንዳቸው በየተራ እየዞሩ አሸተቱኝ። ነፍስ እንዳለኝ የገባቸው አልመሰለኝም፤ ሞቷል ብለውም ሳያዝኑልኝ አልቀረም። ተጠራጣሪ የሆኑ ሁለት ውሾች ብቻ በመደጋገም እየመጡ ይመረምሩኝ ጀመር፤ የሚያውቁኝ መሆኑን ለማጣራት ይመስላል። በመጨረሻም “ይህን ሰው አናውቀውም፤ ግን ሞቷል፥ ወይንም ማደሪያ ያጣ ድሃ ይሆናል” ብለው በማዘን ሁሉም ጥለውኝ ሄዱ። አልፎ አልፎ እንዳይመጡብኝ በአይኔ እየቃኘሁ፥ ከእንቅልፍ ጋር ትግል ጀመርኩ። ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ሲሆን እነሱም እንቅልፋቸው መጣና ሁሉም በየተራ ተኙ።

ውሾች ምስኪኖች ናቸው። እነርሱስ ከጊዜያዊ አለመስማማት የተነሳ እርስ በርሳቸው ትንሽ - ትንሽ ይጣላሉ። ግን ወዲያው ይታረቁና አብረው ይተኛሉ፤ የእኛ የሰው ልጆች ጠብ ግን ንዝንዝ ያለ፤ .... መጨረሻ የሌለው።

እንደ ምንም ትንሽ እንቅልፍ ሸለብ አደረገኝ፤ ግን ወዲያው ብንን አልኩ። በዚህን ጊዜ ቀና ብዬ ወደ ሰማይ በግማሽ በማንጋጠጥ ተመለከትሁ። እግዚአብሔር ኮሙኒስትቶችን ባያይ ከዋክብት አፈጠጡብኝ። ቦግ ቦግ ብለው ወደ መሬት ለመውረድ የተዘጋጁ ይመስላል። ባንድ በኩል "እኛም አለንልህ እኮ! አይዞህ አትፍራ..." በሌላ በኩል ደግሞ "መጣን አንጠልጥለን ልንወስድህ.." የሚሉኝ ይመስለኛል። "ሁለቱም ለኔ ቆንጆ ነው፤ ያሻችሁን አድርጉኝ እባካችሁ!" እያልኩ ቁንጅናቸውንም በልቤ ሳደንቅላቸው፥ እነርሱ እየሰደቁ (በደስታ እየፈነደቁ) እኔንም ከነርሱ ደስታ ያካፈሉኝ ይመስለኛል።

የማላየው የሰማይ ክፍል በዙሪያዬ በከበቡኝ የቤቶች ጣሪያዎች ስለተሸፈነና የማየው የሰማይ ክፍል የተወሰነ ሆኖ፥ እነኛ የማያቸው ከዋክብት ከላይ ሆነው ይህ ነው የማይባል ደስታ፥ የናፍቆት ሰቀቀን እና ተስፋ የተቀላቀለበት ስሜት (የገጠር ትግል፥ ደርግን አሽቀንጥሮ መጣል፥ ሥልጣን ለሕዝብ መስጠት፥ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ስርዓትን መመሥረት...) አፈሰሱብኝ (ለማንም ደስታን የሚሰጥ እርሱም ያገኛልና ነው?)።

ከሚታሰበኝ ስሜት ጋር የተቀላቀለው ወቅታዊ ችግር ቀሰቀሰኝና "በሉ ላርቤርጎ የሚሆን ገንዘብ ወርውሩልኝ አልኳቸው።" እነርሱም "ከሰማይ ቤት ገንዘብ አለ ብሎ የነገረህ ማነው? አንተ ባለጌ! በል ተነስ! አይዲያሊስትነት ያልተላቀቀህ ግማሽ ኮሙኒስት! ተነስ! ይልቅስ ሳይነጋና፥ ውሾቹ ከእንቅልፋቸው ሳይቀሰቀሱ ሹልክ ብለህ ከዚህ ጥፋ!..." የሚል መልእክት ካንዷ ኮከብ የደረሰኝ ይመስል፥ ድምጼን በማጠፋት እኔም ባራት እግሬ፥ ውሻ መስዬ፥ ሹልክ ብዬ ጠፋሁባቸው።

የዛሬውስ በዚህ አለፈ፤ የነገውስ? እንደተለመደው አሻግሬን ወደማገኝበት ሻይ ቤት ሄድኩ። ምናልባት አሻግሬ ገንዘብ ይኖረው እንደሆን በማለት፥ ሻይ ቤት ስንገናኝ፥ ከውሻ ጋር ማደሬን ሳይሆን የገንዘብ እጥረት እያሳሰበኝ መምጣቱን ነገርኩት። እርሱም "ስለ ገንዘብ አታስብ፤ አንዳንድ እቃዎች (እንደ ሙዚቃ ማጫወቻ የመሳሰሉ) አሉኝ፤ እነርሱን በርካሽ እሸጥና እንካፈካለን። አንተ ብቻ በርታልኝ፤ እንደምታውቀው ብዙ መጋለጥ የለብኝም። ካንተ በስተቀር ሌላ ማንንም የበላይ አካል ማግኘት አልችልም" ብሎ፥ የአንድ ቀን አልቤርጎ ማደርያ ሰጥቶኝ ተለየኝ።

በማግሥቱ አሻግሬ መልኩ ሁሉ ተለዋውጦ፥ ሌላ ሰው መስሎ መጣ። እርሱ መሆኑን ያወቅሁት ሲጨብጠኝና ሲያነጋግረኝ ብቻ ነበር። ትላንት በሰጠኝ ተስፋ መሠረት ገንዘቡን በጄ አስጨበጠኝ። "ይህን ሁሉ ገንዘብ ከየት አመጣኸው?" ስለው ደንገጥ ብሎ ዝም አለ። እኔም ከዋክብቶቹን "በሉ ላርቤርጎ የሚሆን ገንዘብ ወርውሩልኝ" ያልኳቸው ትዝ አለኝና፥ ለጊዜው ማንን ማመስገን እንደሚገባኝ ሳላውቅ

ቀርቼ ጭጭ አልኩ። ትንሽ ቆይቼ እንዳላመሰገንኩት ትዝ አለኝና፥ "አሻግሬ በጣም ነው የማመሰግንህ፤ በነፍሴ ደረስክልኝ እኮ!" አልኩት።

አሻግሬም "ይኸውልህ ጓድ፥ ስሜና ፎቶግራፌ በጋዜጣ ወጥቷል፤ በጥብቅ እፈለጋለሁ" አለ። ጋዜጣውንም ከኪሱ አወጣና አሳየኝ። ከአይኖቹ በስተቀር፥ አሁን የማየው አሻግሬ ጋዜጣው ላይ ካለው ይለያል።

"እንዴት ነው ሌላ ሰው አልመስልም?" አለ፤ የኔን መልስ በጉጉት የሚጠባበቅ በመምሰል። እኔም በደንብ አስተዋልኩትና፤ "አዎን! ጭራሽ ሌላ ሰው ነው የምትመስለው" አልኩት። እርሱም፡- "ይኸውልህ! ጸጉር በመላጨት ብቻ ሌላ ሰው መምሰል ይቻላል። ካወቅህበት፥ አለባበስ፥ መነጽር፥ ኮፍያ፥ አካሄድ፥ ወ.ዘ.ተ...አንተነትህን ይደብቁልሃል፤" አለኝና ቀጠል በማድረግ፡- "ቅድም ወደዚህ ስመጣ፥ አንድ የሚያውቀኝ ሰውዬ ከፊት ለፊቴ ድቅን አለብኝ። እኔም አይኖቼን በማንሸዋረር ስገላምጠው ጊዜ፥ እንደማፈር ብሎ ሄደ" አለኝ። እኔም በአድናቆት "ይገርማል" አልኩ። እርሱም ቀጠል አድርጎ፡-

"ከእንግዲህ እኔና አንተን አንዳንድ ያልታሰበ አደጋ ሊያጋጥመን ይችላል፤ ሆኖም ከአደጋ ለመዳን ጭንቅላታችንን በፍጥነት ማሠራት ይኖርብናል። ተስፋ መቁረጥ እራስን እንደ መግደል፤ ቃል የገባንለትን ሠፊውን ሕዝብም እንደ መካድ ይቆጠራል" አለኝ።

እኔም "ከምግብ የበለጠ የሚርበኝ፥ ከመጠጥ የበለጠ የሚጠማኝ፥ ከጓዶች ጋር በአንድነት እየታገሉ ሠፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ጨቋኝ መንግሥት ነፃ ማውጣት ስለሆነ፥ ይህን አላማዬን ከግብ ለማድረስ በምታገልበት ወቅት ሕይወቴ ብታልፍ፥ አብዮታዊ ግዴታዬን እንደተወጣሁ ነው የምቆጥረው። ስለዚህ ተስፋ መቁረጥ ከኔ ዘንድ ሥፍራ የለውም፤ ሞትም ቢመጣ አልፈራውም" አልኩት።

የዛን ለት ብቻ ከአሻግሬ ጋር ቀኑን ሙሉ አብረን ዋልን። ለመሸሸጊያ ያመቻል ብዬ የማስበውን፥ መታወቂያ የማይጠየቅበትን አልቤርጎ ጠየቀኝና፥ መሸትሸት ሲል ወደማውቀው አልቤርጎ አመራን፤ ባለ ሁለት አልጋ ክፍል ተከራየንና ገባን። የዛን እለት ብዙ አወራን፤ በመካከላችን ያለውን አንዳንድ የስሜታዊ አመለካከት፥ ልዩነቶቻችንም ሳንደብቅ ተነጋገርን።

ስለ አንዳንድ የፓርቲያችን ታክቲክና እስትራተጂ (የወደፊት አላማዎችና እቅዶች) በሰፊው ስንነጋገር፥ "እኔ እንደ አንጃዎች አላስብም፤ ሆኖም በወጣቶች እልቂት ትይዩ የኛን ትግል ስመለከት፥ ታክቲክና እስትራተጂአችንን (የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዳችንን) ለማጣጣም አንዳንድ ለውጦች ማድረግ የሚኖርብን ይመስለኛል" አልኩት። እርሱም በመሠረተ ሃሳቡ ተስማማ፤ ግን በንግግሬ ውስጥ

አንዳንድ "ተመጻዳቂ ርህራሄ" የሚከሰት መሆኑን እና ይህም ለወቅታዊ ችግሮቻችን የበለጠ ችግር የሚጋብዝ መሆኑን አስረዳኝ።

"እርግጥ እኛ ኮሙኒስቶች ርህሩሆች ነን፤ በተፈጥሮ ለሰው የመራራት ዝንባሌአችንም ነው ኮሙኒስቶች እንድንሆን የገፋፋን። ዳሩ ግን የአብዮቱ ሂደት ያስከተለውን አስከፊ ሁኔታ እየተመለከቱ፥ በግብታዊነት ርህራሄ መጠመድ፥ ለትግላችን እንቅፋትን ሊፈጥር ይችላል። ሰው ሲገደል፥ ሰው ሲበደል አንወድም። የትግላችን መነሻ ምክንያት ይኸው ሲሆን፥ መጨረሻያውም የሰዎችን በደል ማቆም ነው። ስለዚህ፥ ባንተ በግልህ ለትግላችን ማድረግ የምትችለውን ብቻ አስብ እንጂ፥ በዚህ ባለንበት ሁኔታ፥ በቁንጽል ለዚህም ለዛም አስበንና ተጨንቀን አንችለውም፤ ከግባችንም እንዳንደርስ እንቅፋት ይሆንብናል" በማለት መከረኝ።

እኔም አጀቼን ጭብጥ በማድረግ "የወጣቶች መስዋእትነት፥ በየመንገዱ ኮለል ብሎ መሬት የሰረገው ደም፥...እህ! የሁላችንም ትግል ካለ ውጤት አይቀርም! ካለ ውጤት አይቀርም!" ብዬ ጭጭ አልኩ።

ስለ ውስጣዊ ችግሮቻችን ብዙ በመወያየት እራሳችንን ድክም ካደረግን በኋላ፥ "የአንጃዎችና የፓርቲያችን የተራራቁ አመለካከቶች በአንድ አቅጣጫ ቢነፅሩ ኖሮ፥ እኛም ከዚህ ባልደረስን ነበር...." እያልን በማላዘን ወደ እንቅልፋችን ተሸጋገርን።

በማግስቱ ጧት ተነስተን፥ ቁርስም ሳናደርግ፥ በቀጠሮ ተለያየን። እኔ ግን ብዙ -ብዙ ሃሳቦችን በጭንቅላቴ ማጉላላትና ማብላላት ጀመርኩ። በውስጤ የጋየውን ስሜት መቆጣጠር አላስችል አለኝና አንድ ባለ ብዙ ወረቀት ደብተር ከነ መጻፍያው (እስክሪፕቶ) ገዛሁና፥ በኢሕአፓነት ተሰጥቶኝ የነበረ የመጻፍ ሥራዬን በልዩ መልኩ ተያያዝኩት።

"ታማኝ ሰው ታማኝነቱንም ራሱ ካልገለጸ፥ ማን ይረዳዋል?" በማለት የሃሳቦቼ ግፊት "ቶሎ ቶሎ በል" የሚለኝ እየመሰለኝ ስጽፍ፥ ጽሑፉ የማያቋርጥ ሆነ።

በገባሁበት ጠላ ቤትና ሻይ ቤት መጻፍ ብቻ ሆነ ሥራዬ። ግን፥ "በኢሕአፓነት የተሰጠኝ የጽሑፍ ሥራ አላማው የመንደር ሰዎችን ወደ ኢሕአፓ ለመቀስቀስ ነበር፤ የዚህኛው አላማ ደግሞ፥ ኢሕአፓን ወደኔ ለመሳብ ነው እንዴ?...ባይሆንም፥ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ኃጢአትን ተናዞ፥ ንስሐ ገብቶ እንደመሆኑ መጠን፥ ወደ ትጥቅ ትግል የሚገባውም በሆድ ውስጥ ያለውን ተናዞ መሆን አለበት" በሚል ስሜት፥ ስለራሴ አቋምና ስለ ኢሕአፓ የሚሰማኝን ሁሉ ፍርጥርጥ አድርጌ ጻፍኩ። በጽሑፌ ውስጥ በተደጋጋሚ ለኢሕአፓ ያለኝን ታላቅ እምነትና ለገጠሩ ትግል ያለኝን ከፍተኛ የሞራል ዝግጅት ገለጽኩ። በስነ ስርዓቶች (ዲሲፕሊን) በኩልም፥ ከሥጋዊ ፍትወት ሁሉ የተቆጠብኩ እንጂ፥ ያካባቢዬ ሁኔታ

አዘናግቶኝ አላማዬን የምስት አለመሆኔን አረጋገጥኩ። በርዕዮተ አለም የበሰልኩ፥ በሞራል የጠነከርኩ መሆኔን ዘረዘርኩ። በመጨረሻ.ያም፥ በደርግ የተቀናጀውን የሰዎች እልቂት ዘመቻ እንደ እኔ ያለ ቆራጥ ወደ ባላገር ሄዶ በትጥቅ ትግል ካልተጋተረው በስተቀር፥ እስካሁን ያደረግነው ትግል ውጤት አልባ እንደሚሆን አሳሰብኩ። የጽሑፉ ስሜት "እባካችሁ ወደ ገጠሩ ውሰዱኝና ካናንተው ጋር ልቀላቀል" የሚል የልመና ጥሪ ይመስላል።

በሌላ ቀን መድህን ከተቃጠርንበት ቡና ቤት አገኘሁት። ወዲያውም "ይህንን ጽሑፍ እቤትህ ውሰድና አንብበው፤ ካነበብህ በኋላ ለበላይ አካል አስተላልፈው ወይንም አቃጥለው" አልኩት።

በሁለተኛው ቀን እንዲሁ ከመድህን ጋር ሌላ ቡና ቤት ተገናኘን። "ጽሑፉን አነበብከው ወይ? ስለ ጽሑፉ ምን ተረዳህ?" ብዬ ብጠይቀው፥ ካለ መልስ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለ። እንደገና ጠየቅሁት፤ እርሱም፡- ሁላችንም የገባንበትን ግራ የተጋባ ሁኔታ በተለያየ መንገድ መግለጼን እና የራሴኑ ጭንቀት የሚያንጸባርቅ ጽሑፍ መሆኑን፤ ይህም ባሁኑ ጊዜ ለማንም የማይጠቅም መሆኑን በማስረዳት፥ ጽሑፉን አንብቦ ከጨረሰ በኋላ እንዳቃጠለው ነገረኝ።

መድህን ሃሳቤን ሁሉ የተረዳልኝ መሆኑን እና ኮዱ በሁለት ቀን ውስጥ ተዘጋጅቶ እንደሚደርሰን በማብሰር፥ "አይዞህ - አይዞህ" እያለ አደፋፈረኝ። በዚህን ጊዜ ቀለል አለኝና ተዝናናሁ፤ ኃጢአትን ከመናዘዝ በኋላ የሚመጣ የምህረት ምልክት ይመስላል።

በነጋታው አዲሱን ዜና ለአሻግሬ ነገርኩት። እርሱም በጣም ደስ ብሎት አቀፈኝ። እኔም "ቆይ እስቲ፤ ሁሉ ነገር ሲሳካልን እዛው ጫካ እንተቃቀፋለን" አልኩት። እርሱም "ጓዴ እንደምታውቀው አውቶቡስ ጣቢያ ሄጄ ቲኬት መቁረጥ አልችልም፤ አሁንም ተስፋዬ ባንተ ላይ ስለሆነ በርታልኝ" በማለት፥ የመጠራጠር ምልክት አሳይቶ ተሰናበተኝ።

ከመድህን ጋር በቀጠሮው ሰዓት ተገናኘን፤ ኮዱን ይዞልኝ መጥቷል። ይህ ኮድ ከበፊቱ የሚለየው ቀይ መስቀል በጥቁር መስቀል መተካቱ ነው። በልቤ "ይህስ ቀላል ነው" አልኩና መድህን ጣደፍ - ጣደፍ ብሎ ስለነበር፥ ብዙ ሳናወራ ካለወትሮው ቶሎ ተለያየን።

እኔም ወዲያው እዛው አውቶቡስ ጣቢያ ለማደር እየተጣደፍኩ ሄድኩ። ከቲኬት መቁረጫው ሁለት ሜትር ያህል ራቅ ብዬ ቁጭ አልኩ። ወዲያው አንድ ድሃ መሳይ ወደ ቲኬት መቁረጫው ሲጠጋ አየሁት። አካሄዱ ስላላማረኝ፥ ቶሎ ብዬ ቀደምኩትና ከቲኬቱ መቁረጫ መስኮት ሥር፥ ከግርግዳው በስተቀር ማንም

እንዳይቀድመኝ አድርጌ ቁጭ አልኩ። እርሱም በንዴት "ሁለተኛነቴን ማን ይነፍገኛል!" በማለት፥ ከጎኔ ተጠግቶ ተቀመጠ። ትንሽ ቆይቶ ሌላ ሰው መጣ፤ አንድ አንድ እያለ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ላይ የቲኬት ገዢዎች (ብዙዎቹ ተከፍሏቸው ቲኬቱን እንዲገዙ የተላኩ የኔ ብጤዎች ናቸው) መቀመጥና የመኝታ ሰልፉ ተገባደደ።

ከምሽቱ 11 ሰዓት (5:00 AM) ላይ፥ እንደ ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ብድግ - ብድግ ማለት ተጀመረ። እስከ ጧቱ ሦስት ሰዓት ድረስ ቆምን፤ አንድም ሰው በሰልፉ አንደኝነቴን የተዳፈረ ሳይኖር። ሦስት ሰዓት ተሩብ ሲሆን የቲኬት መቁረጫው መስኮት ተከፈተ። ከውስጥ ቲኬት ቆራጩ ጎረምሳ እጁን አሾልኮ የያዝኩትን ገንዘብ ተቀበለኝ። ለኔና ለአሻግሬ ሁለት ቲኬቶች በመግዛት ቲኬቶቹን በእጄ እንደጨበጥኩ፥ የአውቶቡስ ጣቢያው ድንገት በወታደሮች ተከበበ።

በአንጃዎች ጠቋሚነት፥ ከዛ ሁሉ ሕዝብ እኔን ብቻ መንጥቀው ለመውሰድ የመጡ መሰለኝና በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ። እግሮቼ ቀጥቀጥ - ቀጥቀጥ ማለት ጀመሩ። ሮጬ የማመልጥበት ስለሌለ፥ "አልሳሳም ለነፍሴ፤ የትግሉ ነው ሕይወቴ" የሚለውን የኢሕአፓ መዝሙር በልቤ መዘመር ጀመርኩ።

"ለዘመናት በጭቆና ማጥ፥

በግፍ ሰንሰለት ታስሬ፥

ሙብቴን ላስከብር፥

ጨቋኙን ልሽር፥

ተነስቻለሁ ዛሬ።

ይኸው ታጥቂአለሁ ዛሬ፤

ባንድ እንደሚነሳ፥

ጭቁን ሕዝብ ሁሉ፥

ለማያጠራጥር ድሉ፥

ፍጹም ነው እምነቴ፥

የትግሉ ነው ሕይወቴ፥

ልጓዝ በድል ጎዳና፥

በተሰዉት ጓዶች ፋና፥........."

አልጨረስኩትም። በልቤ ስዘምር ካለሁበት ቆሜ ቀረሁ። ወዲያው አንድ የሚሊታሪ ካድሬ የሚከተለውን መግለጫ ሰጠ።

“ከዛሬ ጀምሮ፥ ላልተወሰነ ቀን፥ የማመላለሺያ አውቶብሶች በጠቅላላ፥ ለአብዮታዊ ግዳጅ - ለአብዮታዊ ወታደሮች ወደ ሰሜኑ ጦር ማጓጓዣ ስለሚውሉ፥ አብዮታዊ ይቅርታን እየጠየቅን እናሰናብታችኋለን።”

ወታደሮቹ እኔን ለመያዝ አለመምጣታቸው ደስ ሲለኝ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የአዲስ ሕይወት ጎዳና የሚከፍትልኝን አውቶቡስ በማጣቴ ጥልቅ ሃዘን ተሰማኝ። ይህ በሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ውስጥ መዋጥ እኔነቴን ያሳጣኛል፥ ፈሪም ያስመስለኛል በማለት፥ ቶሎ ብዬ ወደ ጊዜያዊው እውነታ ውስጥ ገባሁና የዛሬውን አሳዛኝ ዜና ለማርዳት ወደ ተለመደው ሻይ ቤት ገሰገስኩ። እንደ ደረስኩም አሻግሬ “ቲኬቱስ” አለኝ፤ አሳየሁት። ፈገግ ብሎ ሊስመኝ ሲል፥ አውቶቡሳቻንን በወታደራዊ ግዳጅ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀማን መሆኑን ነገርኩት።

አሻግሬም ሰውነቱ ጭምድድ ሲልና ሲያዝን ሳየው፥ ምነው ባልተፈጠርኩ አሰኘኝ። እኛ ኮሙኒስትቶች፡- ይህስ ከላይ (ከእግዚአብሔር) የመጣ ማለትን አንወድምና፤ መጥፎ አጋጣሚ እያልን ብቻ ተራገምን። ትንሽ ቆይቶ፥ ቀልጣፋው አሻግሬ ስለ ወደፊቱ ማሰብ ጀመረ። እኔ ደግሞ ስለ መጀመሪያው አውቶቡስ አለመሳካት እራሴን እየወቀስኩ አላዘንኩ።

“ከእንግዲህ ምንድነው ያለን አማራጭ?” አለ አሻግሬ። እኔም “በእግር መሄድ ወይም ሌላ ኮድ መጠበቅ ነዋ!” አልኩት። ሁለቱም እንደ ሰማይ ሩቅ መስሎ ታየን። የተዘጋጀልን የቀበሌ ወረቀትም አገልግሎቱን የሚጨርስበት ቀን ቀርቧል። ለማንኛውም የበላይ አካል የሚለውን እንስማ በሚል ሃሳብ ተስማምተን ተለያየን።

መሸት ሲል፥ መድህንን አገኘሁት። በዛሬው ለት የተፈጠረውን ስነግረው በጣም አዘነ። “ያጋጣሚዎች መደራረብ እኛን ችግር ላይ ሲጥለን፥ አንጃዎች ደግሞ ከደርግ ጋር በመሆን ፓርቲአችንን ለማዳከም ሲታገሉ፥ ሌላ ኮድ ለማዘጋጀት ምን ያህል እንደሚያስቸግር በቀላሉ ሊገባህ ይችላል! አይደለም? ካሁን በፊት እንደነገርኩህ፥ በመሥሪያ ቤት ጥቆማ ተካሂዶ አንዳንድ ግለሰቦች ተይዘዋል። ይህንኑ ጉዳይ ለበላይ አካል አሳውቄ፥ ለኔ ደግሞ አማራጭ እስኪገኝልኝ ድረስ እኔም እንዳንተ አንደር ግራውንድ (ራስን ከሕጋዊ ሰዎች በመሰወር መደበቅ) መግባት ይኖርብኛል፤ እስከዛውም ካልተበላሁ (ካልያዙኝ) ነው” አለኝ መድህን። እኔም በልቤ “ወይ ጉድ! በችግር ላይ ችግር ሲደራረብ፥ መጨረሻው ምን ይሆን?” አልኩ።

መድህን በመቀጠል “ከእንግዲህ እኔ ኮንታክት (አገናኝ) ልሆንህ የምችል አይመስለኝም። ነገ ማታ ከዚህ ሥፍራ መጥተህ ባታገኘኝ፥ ችግር ውስጥ መግባቴን ትረዳዋለህ። ይህንን ስልህ፥ ሁኔታው ወደዛ እየገፋፋኝ መሆኑን ስለተረዳሁት ነው። በተቻለኝ መጠን ላለመያዝ እጥራለሁ። የበላይ አካል ይህንን የኔን እና የናንተንም

ጉዳይ ያውቃል። እኔ ብያዝ ወይንም ብሰወር እንኳን፥ የኔ ኮንታክት (አገናኝ) በእኔ ፋንታ ያገኛችኋል። ስለዚሁ ጉዳይ ቀደም ብዬ ከበላይ አካል ጋር ተነጋግሬ ስለነበረ፥ ከእኔ አገናኝ ጋር የምትለዋወጡበት ኮድ (የምስጢር ቃል) ተሰርቶላችኋል። ስለዚህ ወደዚሁ ሥፍራ እንዲመጣ እነግረዋለሁ። ምልክቱም እንደሚከተለው ነው፡-

ልክ ከቀኑ 12 ሰዓት (6 : 00 PM) ሲሆን፥ ከዚሁ ቡና ቤት ፊት ለፊት፥ ከመንገዱ በስተ ሰሜን በኩል፥ ጓዱ በቀኝ እጁ የጋዜጣ ጥቅል ይዞ፥ በጋዜጣው ግራ እጁን እየመታ ይቆማል። አንተም "ሰዎቹ አለፉ ወይ?" ስትለው፥ እርሱ ደግሞ "በባቡር ተሳፍረው ሄደዋል" ይልሃል። ይህ አንድም የምትለዋወጡበት ኮድ (የምስጢር ቃል) ነው፤ አንድም የኔን መያዝ የሚያነግርህ ነው።"

መድህን ይህንን ሲናገር ድንግጥ አልኩ። "እንዴ!..." አልኩ በልቤ፤ "መድህን እጁን ሊሰጥ ነው እንዴ? እርሱም እንደ አንጃዎች?" በማለት፥ በፊቴ ላይ ጥቁር ጉም ሽው ሲል ተመለከተ መድህን።

እንኳን የፊቴን የጭንቅላቴንም የሚያነበው መድህን ነገሩ ገብቶት "አይዞህ፥ እንዴ አይዞህ! ካልተያዝኩ እኔኑ ነው እኮ ከዚሁ ሥፍራ የምታገኘኝ። ስታውቀኝ? እኔ እጄን የምሰጥ እመስልሃለሁ? ተለውጬ አንጃ የሆንኩ መሰለህ? ኮዱን የሰጠሁህ ድንገት ከተያዝኩ ለናንተ ለራሳችሁ፥ ለፓርቲውና ለቆምንለት ሕዝብም ሁለት ነፍስ ላትርፍ ብዬ፤ የሁኔታውንም አዝማሚያ ስመለከት፥ ምናልባት ያለኝ ቀን ዛሬ ብቻ ሊሆን ሰለሚችል ነው። ምን ላድርግ? ተታኩሼ እንዳልሞት እንኳን ጠብ መንጃያ የለኝ፤ ሽጉጥ የለኝ.." አለ በቅሬታ።

እኔም "አይ አይደለም፤ እንዳው የወደፊቱን እያሰላሰልኩ ነው ሃዘን የገባኝ። አይዞህ፥ የሆነው ይሆናል" አልኩ በትካዜ።

መድህን "በል እንግዲህ ብዙ ማውራት አልችልም። እስከዚህ የደከምኩላችሁ በትግላችን አንፃር፥ የኔም የናንተም ነፍስ አንድ ናት ብዬ ነው። እና ያልኩህን ካለመጠራጠር አድርግ። በነገርኩህ መሠረት - ከቡና ቤት ፊት ለፊት፥ ከመንገዱ በስተ ሰሜን በኩል፥ ጓዱ በቀኝ እጁ የጋዜጣ ጥቅል ይዞ ስታይና ኮዱን ከተለዋወጣችሁ በኋላ፥ ምን ማድረግ እንደሚቻል ከጓዱ ጋር ትወያያላችሁ።" በማለት ጥልቅ በሆነ ቅሬታና ሃዘን በተቀላቀለበት ስሜት የመጨረሻ መልእክቱን አስተላልፎ ተለየኝ።

መድህን ጥሩ ጓደኛዬ ነበር። እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን እንዳልለው ኮሙኒስትት ነኝ። "አጋጣሚዎች ተስተካክለው፥ ከአቸናፊው ሠፊ ሕዝብ ጋር በሰላም ይግጠመን" አልኩ፤ በመረረና በተዳከመ ድምጽ። ከዛም ተሳሳምንና ተለያየን።

በማግስቱ፥ ልክ 12 ሰዓት (6፡00 PM) ሲሆን፥ የተባለው ጓድ ኮዱን እየሠራ ቆሞ አገኘሁትና፥ ኮዱን ከተለዋወጥን በኋላ ንግግር ጀመርን።

ይህ ጓድ (ጸጋዬ) በተክለ ሰውነቱ፥ በአለባበሱና በሁኔታው ሁሉ እንደጠበቅሁት ሆኖ አላገኘሁትም። እኔ የማውቃቸው የበላይ አካላት በብዛት በትምህርት የመጠቁ ናቸው። ይኸኛው ግን እንደነሱ አይመስልም። ጸጋዬ በሰውነቱ ኮሳሳ፥ አለባበሱም እንደ ድሆች ስለሆነ፥ "ሕጋዊ" አለመሆኑ ያስታውቃል። ሆኖም፥ ይህ ጓድ ቀልጠፍ - ቀልጠፍ የሚል፥ ባላገርና ከተማ የሚመላለስ የመርካቶ ሰው ሳይሆን አይቀርም። አካባቢውን ሁሉ በቁጥጥሩ ያደረገ መሆኑ ከሁኔታው ያስታውቃል።

ኮዱን ከተለዋወጥን በኋላ፥ ጓድ ጸጋዬ እንዲህ አለ፤ "ከእንግዲህ ባጭር ጊዜ ውስጥ ይሳካል ብዬ ተስፋ አልሰጥህም፤ ያለህ እድል በትእግስት መጠበቅ ብቻ ነው፤ እኔን እንደ ጓዱ በየቀኑ ልታገኘኝ አትችልም። ቀጠሮም ልሰጥህ ያስቸግረኛል፤ ስለዚህ ዘወትር በዚህ ሰዓት አካባቢ፥ እዚሁ ሥፍራ ፈልገኝ። ካለሁ አለሁ፤ ከሌለሁም የለሁም ማለት ነውና ብዙ አታንዣብብ።"

እኔም "እሺ" አልኩና ስለ መድህን ሁኔታ የሚያውቀው ካለ ብዬ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት። እርሱም "እንጃ! አላወቅሁም፤ ምናልባት ሳያመልጥ አልቀረም፤ ግን እኔ ይህንን በዚህ ሰዓት ማወቅ አልችልም። ወደናንተው ጉዳይ ብናተኩር ይሻላል።" አለ ኮስተር ብሎ። ጸጋዬ ይህን ብቻ ተናግሮ፥ ካጠገቤ ጠፋ።

እኔም "ወይ ጉድ!" አልኩና፥ ወደመሬት አይኖቼን ተክዬ፥ የፍርኃት ሃዘን ተሰማኝና፥ እንደገናም ወደ ሰማይ አንጋጠጥጬ በተስፋ ተዋጥኩና፥ አምላክና አጋጣሚን አንድ ላይ አዋህጄ "ሦስታችንንም ሜዳ ቢያገጣጥመን?" አልኩ።

ከቀን ወደ ቀን አሻግሬን ለጥቂት ደቂቃዎች ከማግኘት በስተቀር ብቸኝነት እያጠቃኝ መጣ። በቀበሌ ውስጥ ካለ ሥራ መቆምና ማንዣበብ መታሰርን የሚያስከትል በመሆኑ፥ ያለው አማራጭ ቀኑን ሙሉ ሲዞሩ መዋል ነው። ይህ ደግሞ ያልተመጣጠነ ምግብ እየተመገበ ለሚኖር ሰው ያደክማል፤ አይቻልም። ጠላ ቤት በመግባትና ከዛ ቁጭ በማለት ነው ጊዜው የሚገፋው።

እንደ ጸጋዬ ቀልጠፍጠፍ የምል፥ የመርካቶ አራዳ ብሆን ኖሮ፥ እስከዛሬ ራሴን ከችግር ማውጣት ይቻለኝ ነበር እያልኩ አስባለሁ። ሰው የራሱን ጠባይ (ተፈጥሮ) በራሱ ይለውጠው ዘንድ እንዴት ይቻለዋል? እንዲህም ሆነ እንዲያ በሕዝቦች መካከል ነው ያለሁት፤ ስለዚህ ራሴን ከራሴ ጋር ሙጭጭ አድርጌ በውስጣዊ ንግግር ብቻ አልወሰን፤ ከሕዝቦችም ጋር ላውራ አልኩ።

ሻይ ቤትና ጠላ ቤት እየገባሁ ከሕዝቦች ጋር አንድ ሁለት ቃል መናገሬ አልቀረም። ነገር ግን፣ እኔ በተፈጥሮዬ ብልጣ ብልጥ ስላልሆንኩ፣ ሦስትና አራት ቃል ከጨመርኩበት፣ የኢሕአፓ ወገን መሆኔን ለመረዳት አያስቸግርም በማለት፣ እራሴን እየደበቅሁ ከራሴ ጋር ብቻ ሳወራ ቀኑ ያልፋል።

አንዳንድ ጊዜ ለምታገለለት ሰፊ ሕዝብ የሚረዳ ሃሳብ አገኝ እንደሆን እያልኩ፣ ወሬ በጥሞና ለማዳመጥ ስሞክር፣ ፖለቲካ መሰል ካልሆነ በስተቀር፣ ወሬ ቶሎ አልገባህ ይለኛል። ሰው ቀልጠፍ - ቀልጠፍ ብሎ ሃሳብ ለሃሳብ ሲለዋወጥ፣ አንዱ ሌላውን ቶሎ - ቶሎ ይረዳዋል። አንዱ ተናግሮ ሳይጨርስ ሌላው ይቀጥላል፤ የመርካቶ ሰዎች የእርስ በርስ የመግባባት ችሎታቸው እጅግ ከፍተኛ ነው። በወቅታዊ ኑሮአቸው ውስጥ ያለውን ጥቃቅን ሃሳቦችን መተረክ ያደጉበት ስለሆነ፣ ሲያወሩ የአማርኛን ቋንቋ ተራቀውበታል። መራቀቅ ብቻ አይደለም፤ ይህ ቋንቋ የተሰጠው ለነርሱ ብቻ ይመስላል። ባይሆንማ ኖሮ ከሚያወሩት ውስጥ ለምን በብዛት አይገባኝም?

ከአንዳንዶቹ የሚሰነዘረውን ጥልቅና የሰላ አስተሳሰብ እኔ በድጋሜ ቀስ እያልኩ ሳመነዥገውና ብዙ ከቆየ በኋላ የወሬው ለዛ ሲገባኝ፣ “እነኚህስ እድል ቢያጋጥማቸው በአለም ከሚታወቁ ሳይንቲስቶችና ፈላስፎች እኩል የሚሆኑ ወይንም የበለጡ ናቸው በእውነት” እላለሁ።

አንዳንድ ጊዜ ያነበብኳቸው የኢሕአፓና የአንጃዎች የልዩነት ዘገባዎች በአይምሮዬ ይመላለሳሉ። በተጨባጩ ሁኔታ አንጃዎች ያቀረቡት ዘገባ ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦችን ያዘለ ስለመሆኑ ልክድ አልቻልኩም። ነገር ማክረር ባይኖር ኖሮ፣ በእነኚህ ጠቃሚ ሃሳቦች መጠቀም ይቻል ነበር።

እውነትም ኢሕአፓ ባለ ሁለት እውነት!! እውነትም ኢሕአፓ ባለ ሁለት እውነት!! ሰው እንዴት ለሁለት እውነት ይከፈላል። አባት በአስቸጋሪ ልጁ እንደሚናደድ፣ ፓርቲውም እንዲሁ በአንጃዎች ላይ አመረረ። ትንሽ እንኳ በጎ መንፈስ ቢኖር ኖሮ፣ የአባትና ልጅ መታረቅ ይህን ያህል አስቸጋሪ አይሆንም ነበር። ፓርቲው ሀ እና ለን በማግለል ፋንታ ለምን መታገስ አቃተው? በግለሰብ ደረጃ የሚወቀስ ማን ይሆን?

ኢሕአፓ የወቅቱንም ተጨባጭ ሁኔታዎች በማስመልከት፣ ሌላ ለየት ያለ ሃሳብ ከገዛ አብራኩ ሲመነጭ፣ በርዕዮተ አለም የከረረ አስተሳሰቡን ገታ ቢያደርግ፤ አንገቱን ዘንበል - ቀለስ አድርጎ፤ በጥሞና የሚያዳምጥ ቢሆን ኖሮ፣ ይህ ሁሉ ችግር አይደርስም ነበረ።

እውነት እና ትህትናን አብሮ ጨብጦ መያዝ የኢሕአፓ መሪ የነበረውን (ደብተራውን) ከመጣበት ከቤተ ክርስቲያን የሚመልሰው መስሎት ይሆን እንዲህ

ያመረረው? አዎ! ትህትና በሃይማኖተኛነት እንጂ በኮሙኒስትነት አይገኝም (ይሆን?)። ፖለቲካ ማለትም የሰዎችን ከፋት በቃላት ሽንገላ ጥሩ የሚያስመሰል ነው እንጂ፥ ፍጹም እውነት ሊሆን አይችልም (ይሆን?)።

የሁለትነት ቀውስ የማይገባበት ሥፍራ የለም፤ ምንም እንኳን ፓርቲው የተሳሳተ መስመር ቢይዝም፥ እስከ መጨረሺያው በውስጥ መታገል ነው እንጂ፥ እርስ በርስ መጣላትና መዋጋት፥ መፈረካከስን፥ መዳከምን፥ ብሎም እራስን ማጥፋትን እንደሚያስከትል እንዴት ፓርቲው (አንጃዎችም) ሊገነዘቡት አልቻሉም? አልገባኝም።

አንጃዎችስ ሠፊውን ሕዝብ በማስቀደም ፋንታ፥ አብረን ስንታገል የቆየናቸውን ጓዶች መግቢያ መውጫ ማሳጣት፥ እንኳን ከሰው ከእንስሳስ የሚጠበቅ ነው ወይ? አልገባኝም።

አንድ ትልቅ መጽሐፍ ከሚወጣው ከሁለቱ (ከኢሕአፓና ከአንጃ) ዘገባዎች (የፖለቲካ ምጥቀትና ፍልስፍና) የሰው ልጅ የማሰብና የእውቀት ደረጃ ጥልቀት ኢትዮጵያኖችን ያኮራል። ግን ከዚህ ሁሉ የተራቀቀ እውቀት ባሻገር፥ የሰው ልጅ የእንስሳነት ጠባይ ተደብቆ ይሆን? የየትኛው እንስሳ ጠባይ ከየትኛው እንስሳ ጠባይ ይሻላል?

አዎ! እስከዛሬ ድረስ በአለም ዙሪያ እንዳየነው ከሆነ፥ አከራካሪውስ በእውቀት መበላለጥ የተነሳ አይደለም፥

አዎ! እስከዛሬ ድረስ በአለም ዙሪያ እንዳየነው ከሆነ፥ አከራካሪውስ በእውነቶችና በውሸቶች መካከል ባለው ልዩነት የተነሳ አይደለም፥

አዎ! እስከዛሬ ድረስ በአለም ዙሪያ እንዳየነው ከሆነ፥ አከራካሪውስ በሰዎች በውስጣቸው ያለ ተፈጥሮ (ልዩ ያልታወቀ ጠባይ) ነው።

የኔም የአስተሳሰብ ዝንባሌዩ በመሀል ተንጠለጠለ። ከግራ ወደ ቀኝ፥ ከቀኝ ወደግራ የሚያናፍሱ ሃሳቦቼ እኔን አንገላቱኝ። ግን ከአንጃዎች የወረስኳቸው አስተሳሰቦች ቢኖሩኝም፥ እስከሞት ድረስ በውስጥ ትግል እታገላለሁ እንጂ፥ ወይንም ትግሉን ትቼ ለጊዜውም ቢሆን ዞር እላለሁ እንጂ፥ የገዛ ጓዶቼን መልሼ አላጠቃም።

አንጃዎች ደርግ የሰጣቸውን ሥራ እርሱ እንደሚፈልገው ከሠሩለት በኋላ፥ ሌላ ሥራ ሊሰጣቸው አልፈለገም። እነርሱ በሥራቸው ሁሉ ደርግን አስደሰቱት፤ እርሱ ግን በሥራቸው አልሸለማቸውም።

አንጃዎች (ምናልባትም የአንድ ግለ ሰብ ድርጊት ይሆናል) ነፍሳችን ይምራታል ብለው (ይሆናል?) በአንድ ጊዜ እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር ከአባላት የተዋጣ የኢሕአፓ ገንዘብ ለደርግ አስረከበዋል። ደርግ ግን ከኔና ከጓዶቼ

የተጠረቃቀመውን ገንዘብ ከኪሱ አስገብቶ አንጃዎችን አላመሰገናቸውም፤ ነፍሳቸውንም አልማረላቸውም። እነርሱኑ አንድ ባንድ መልቀምና መግደል ጀመረ እንጂ።

የደርግ ፋሺስትነት (ወይም ፋሺስታዊነት) የእንስሳነት ጠባዩን በቀላሉ እንዲታይበት አደረገው። ሌሎችም አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች አባሎች ለራሳቸው ሕሊና እንኳን የሚቆጫቸውን ሁሉ  አደረጉ። ሁኔታው ይህን ይመስላል፡

ከእለታት አንድ ቀን፥ አንድ የተራበ አንበሳ አንድ ምስኪን አውሬ ይዞ እየበላ ሳለ፥ በጉሮሮው አጥንት ተቀረቀረበትና ተሰቃየ።

"እባካችሁ ከጉሮሮዬ የተቀረቀረውን አጥንት አውጡልኝ.." ብሎ እያሳዘነ ቢለምን፥ ደፍሮ አንበሳውን ለመርዳት የሚጠጋ ጠፋ። አንበሳው መላ ሲያጣ፥ እንዲህ አለ "በጉሮሮዬ የተቀረቀረ አጥንት አለና፥ ይህን አጥንት ላወጣልኝ ሽልማት እሰጠዋለሁ።"

አሁንም እንስሳት ሁሉ ፈሩ። ግን አንድ የደፈረ ጀፌ አሞራ፥ ሽልማት አገኛለሁ ብሎ፥ ከአንበሳው ጉሮሮው ውስጥ ገባና አጥንቱን አወጣለት።

አሞራውም "አጥንቱን አውጥቼልሃለሁና፤ ሽልማቴን ስጠኝ" ብሎ አንበሳውን ጠየቀው። አንበሳውም "ከአንበሳ ጉሮሮ አጥንት አወጣሁ ብለህ ማውራቱ፤ ይህ ላንተ ትልቅ ሽልማት ስለሆነ፥ ይህንኑ እያወራህ ኑር። ይህ ነው ሽልማትህ፤ በል ሂድ ካጠገቤ ጥፋ ሳልቦጭቅህ!"  ብሎ አባረረው ይባላል።

እንዲያ ነው፤ የማንም ሰው ጠባይ ከመንፈሳዊነቱ ይልቅ ምድራዊነቱ ካመዘነ፥ እንደ እንስሳ ሆኗል ማለት ነው። ሰው እርስ በርሱ ሲባላ፥ የማይጠግበውን የሥጋ ከርሱን ሲሞላ፥ ሞራላዊነቱን ረስቶ፥ እንስሳዊነቱን አጎላ። አዎ! ክፉ ቀን ሲመጣ፥ የረከሰው የሰው ልጅ ጠባይ በገሃድ ይታያል፤ ውሸታምና ከዳተኛም ይበዛል።

በፖለቲካ የተሰማራ ሁሉ፥ አንድ ባንድ፥ በሚከተለው የእንስሳዊነት ጠባዮ ረከሰ፡- ውሸታምነት (እንደ ፖለቲካ ታክቲክ እየተቆጠረ)፥ ራስን ወዳድነት፥ የሥልጣን ጥም፥ ክፋት፥ ውዳሴ ከንቱ፥ ስግብግብነት፥ ትምክህተኛነት፥ እብሪተኛነት፥ ጀብደኝነት..። የሰው ልጅ ይህን ሁሉ አስከፊ ጠባያት ተሸክሞ ሠፊውን ሕዝብ ሊያገለግል እንዴት ይቻለዋል? እንዴት ይቻለዋል? እንዴት ይቻለዋል።

ለነገሩ ከሃይማኖት መጻሕፍት ያላነሰ ሞራል የሚያስተምር፥ የፓርቲ ዲሲፕሊን በሚል በእንግሊዝኛ የተጻፈ፥ እንዲሁም በአማርኛ የተተርጎመ ጽሑፍ ለብዙዎቻችን ተዳርሶ አንብበነዋል። ለነገሩ ይህን የሚከተሉ የኢሕአፓ አባላት በንግግራቸው፥ በጠባያቸውና በተግባራቸው ሁሉ፥ ከአንድ ቄስ ያላነሰ ትህትና ነበር

የሚያሳዩት። እነ ዲሞክራሲያ ሲያስተላልፉ የነበረው መልእክት ከሐዋርያቶች መልእክት በምን ያንስ ነበር? ምን አይነት ሰይጣን መጥቶ ነው የበጠበጠን? መሪዎቻችን እንዴት ከዱን? እንዴት ከዱን።

ሃይማኖተኞች እጹብ ድንቅ ለሆነ፥ ፍጹም እውነት ለነገሠበት አገረ ሕይወት ይታገላሉ። አዎ! አዎን! እኔም ደፋር ነኝና፤ ወደ ባላገር ገብቼ የምታገለው፡- ይህ ትውልድ እውነትን ባያገኝ፥ የኢሕአፓዎች እውነት ለሚቀጥሉት ትውልዶች ተላልፎ፥ በኢትዮጵያ ምድር የኮሙኒስትት ስርዓትን (ምድራዊ አገረ ሕይወትን) እንዲያገኝ ለማድረግ፤ የሰውን ልጅንም መጥፎ ጠባያት ለማጥፋት (ለመቀየር) ነው። አለዚያማ እንዴት ይሆናል? ጥንትስ የፊውዳሎችና የአሪስቶክራቶች ጠባይ አይደለም እንዴ ሠፊውን ሕዝብ መቀመቅ የከተተው? የነርሱ ሆዳምነትና አልጠግብ ባይነት አይደለም እንዴ ሕዝቡን ያደኸየው። የነርሱ ማናለብኝነት አይደለም እንዴ ሰብአዊ መብትን የጣሰው? የነርሱ አምባገነናዊ ጠባይ አይደለም እንዴ? ሕዝቦችን ረግጦ መግዛት፥ ጭቆናና ምድራዊ ስቃይን ሁሉ ያስከተለው።

ይህንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች እንደ ልማዴ ጻፍኩ፤ ብዙ የደረቁ እውነቶቼ እኔን የተለየ ሰው እንዳያስመስሉኝ፤ ምናልባት ወደ ሌላ አለም ከመሸጋገር ተርፌ እዚችው ከቀረሁም ጉዳት ላይ እንዳልወድቅበትም እየፈራሁ ነበር የምጽፈው።

**<u>መለስተኛ ሕመም</u>**

በየቀኑ 12 ሰዓት ሲሆን ጻጋዬን ከተባለው ሥፍራ እየሄድኩ መመልከቴን አላቋረጥኩም። ቀን ቀን በሃሳብ እወጠራለሁ፤ ማታ ማታ ደግሞ በህልምና በቅዠት ሌላ አለም ውስጥ እገባለሁ። በህልሜ የማየውንና በእውን የማየውን ለማስታረቅ አልቻልኩም፤ ጤንነቴም እየታወከ መጣ (ኤጭ)።

አሻግሬም ለጥቂት ቀናት ጠፍቶብኝ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ከተለመደው ሻይ ቤት ተገናኘንና ጨዋታ ጀመርን። ከወትሮው የተለየሁ ሆንኩበት። አትኩሮ እያየኝ፥ አንዳንዴም ጎንተል እያደረገኝ ተጨዋወትን። “ደህና ነህ ወይ?” ይለኛል፤ እኔም “ደህና ነኝ” እለዋለሁ።

እኔ ግን ድምጽ የተባለ ሁሉ አንድ አይነት ሆኖብኛል። የሰዎቹ ጩኸት ከማንኪያዎች፥ ከብርጭቆዎች፥ ከወንበሮችና ሌሎችም የሻይ ቤት ኳኳታዎች ጋር ተደበላልቆ፥ የትኛው የየትኛው ድምጽ መሆኑን መለየት አቅቶኛል። እንደ ወንዝ ጎርፍ ዥው ዥው ይልብኛል። ድምጽ የተባለ ሁሉ እንደ አንድ ከፍተኛ ሞገድ ከፍና ዝቅ ሲል፥ በጠፈር መንኮራኩር የዘለአለማዊ ጉዞ እንደሚጓዝ ሰው የሆንኩ ይመስለኛል።

አሻግሬ ሲያወራ፥ አዎ! አዎ! ማለቱ ሰለቸኝና "ከዚህ እንውጣ!" አልኩት (አሁንም በልቤ ኤጭ እያልኩ)። እንደወጣንም "ጸጋዬን ካገኘሁት ሰንበት ብሏል፤ ምናልባት ዛሬ ማታ ሳላገኘው አልቀርም" አልኩት። እርሱም፤ "እንዴት እርግጠኛ ልትሆን ቻልክ በህልምህ አይተህ ነው?" ብሎ ቀለደና ልንለያይ ስንል "ለመሆኑ ደህና ነህ? እባክህ ንገረኝ?" በማለት አጥብቆ ጠየቀኝ። እኔም "አይዞህ ደህና ነኝ፤ ምን እሆናለሁ ብለህ ነው? ትላንትና በደንብ ስላልተኛሁ ደክሞኝ ነው" አልኩት።

አሁንም በጥርጣሬ መልክ ሲመለከተኝ ጊዜ፥ ፊቴን ኮስተር አድርጌ፥ ክርር ባለ ንግግር "ስማኝ ልንገርህ ወዳጄ ጓዴ" አልኩት።

"እኔኮ አገር ለቆ እንደሚወጣ ተሰናብቼ መርካቶ ስገባ፥ ጓዶቼ በቆራጥነት የታገሉበት ክልል ውስጥ መሆኔን አልረሳም። መርካቶን ነጻ ባናወጣትም፥ በደርግ ቅኝ ግዛት ውስጥ ገና አልገባችም። ይህንን አውቃለሁ፤ በተጨማሪም ተዋድቀው የወደቁት ጓዶቻችን መንፈስ አብሮኝ አለ። በከንቱ የፈሰሰው ደም ይታየኛል፤ የሠፊው ሕዝብ ጩኸት ከሻይ ቤቱ ጩኸት በልጦ ይሰማኛል። የሁላችንም የትግል መንፈስ ወደፊት እንጂ ወደኋላ አያስመለከተኝም። መርካቶም ቀረሁ ወይም ጫካ ገባሁ፤ ይህ መንግሥት ከመለወጡ በፊት የማልመለስ መሆኔን ለራሴ ቃል ኪዳን ገብቼአለሁ። ይህን ቃል ኪዳን እንዳጥፍ የሚያደርገኝ ምንም ምድራዊ ኃይል አይኖርም" አልኩት።

እርሱም ቀበል አደረገና፥ ሳቅ ሳቅ እያለ፥ "እኔኮ ቆራጠኛነትህን በመጠራጠር አልነበረም የጠየቅሁህ፤ ሁኔታህን ስመለከተው የታመምክ መስሎኝ፥ ስለጤንነትህ ጠየቅሁህ እንጂ።"

"ደህና ነኝ" አልኩት። እርሱም "በል በርታ፥ በጸጋዬ በኩል ተስፋ ከመጣ እንድትነግረኝ፥ ከዚሁ ሻይ ቤት ተመልሼ እመጣለሁ" ብሎኝ ተለያየን።

## <u>ሦስተኛው ሙከራ</u>

መሸት ሲል (12 ሰዓት) ጸጋዬን ከዚያው ሥፍራ አገኘሁት፤ እርሱም የቀበሌ ወረቀቱን ለኔና ለአሻግሬ ያዘጋጀ መሆኑን ነገረኝ። ጸጋዬ ካለወትሮው እጅግ ጣደፍ ጣደፍ ብሎ "ኮዱ የተዘጋጀ ስለሆነ፥ ከነገ ወዲያ ሁለታችሁም አውቶቡስ ጣቢያ በመምጣት እዛው እንገናኝ" አለ።

በማግስቱ ይህን የምስራች ለአሻግሬ ነገርኩትና ታላቅ ደስታ ሆነ። በተባለው ቀን ሁለታችንም አውቶብስ ጣቢያ ሄድንና፥ ጸጋዬን ከዚያ ቆሞ እኛን ሲጠብቅ አገኘነው።

ጸጋዬ ሹፌሩንና ረዳት ሹፌሩን (አውቲስታውን) ያውቃቸዋል። በዚያ አካባቢ ጸጋዬን የማያውቅ ሰው የለም፤ ከሁሉም ጋር ያወራል፥ ይቃለዳል (ይጫወታል) ይስቃል፥ ያስቃልም።

ጸጋዬ አውቶቡሱ ውስጥ እንድንገባ ነገረንና ገባን። አውቶብሱ ውስጥ ከገባን በኋላ ስለ ኮዱ ነገረን። ምናልባት ብንቀርና ኮዱን ለደርግ አሳልፈን ብንሰጥ፥ የሚከተለውን ችግር በመመልከት ይሆናል አውቶቡሱ ውስጥ እስክንገባ የጠበቀው ብዬ አሰብኩ። ግን እንዴት ይህን ያህል ሊጠራጠረን ቻለ? ይህን ሁሉ እንዳስብ የሚያደርገኝ አንድም ሁኔታው ሲሆን፥ ሌላም እኔና አሻግሬን በደንብ ስለማያውቀንና ስለማይተማመንብንም ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ።

ጸጋዬ የተጠራጠረው ነገረ ያለ ይመስል “አይዟችሁ! ዛሬ ባይሳካ ነገና ከነገ ወዲያ ሊሳካ ይችላል፤ ከሦስት ቀን በላይ ከሆነ ግን ኮዱ መለወጥ ይኖርበታል።” አለን።

ሹፌሩ የአውቶብሱን ሞተር አስነሳና እርሱ ከውጪ ወጥቶ ቆመ። ጸጋዬም ከዚህ በኋላ እርሱን ማግኘት እንደማይቻል ጠቆም ለማድረግ ሲሞክር “ከዛው ሥፍራ?” አልኩት። እርሱም “ሞክር” ብሎኝ ተለየን።

እኛም የአውቶብሱ ጎማዎች በቶሎ ሥራቸውን እንዲጀምሩ በጉጉት በመጠባበቅ፥ ካሁን አሁን ተነሳ ስንል ጊዜው እጅግ ረዘመብን። ጎን ለጎን ቁጭ ብለን፥ ስለ ወደፊት ትግላችን በድምጽ አልባ ንግግር የምናወራ ይመስላል።

ሹፌሩ አውቶብሱ ውስጥ ገብቶ ራሱን መቀመጫው ላይ በማስተካከል ላይ እንዳለ፥ አንድ ሰው እየሮጠ መጣ። ሹፌሩን ለሁለት ደቂቃዎች ካነጋገረው በኋላ ሄደ። ሹፌሩም ወደ ተሳፋሪዎቹ ዞር በማለትና ሃዘን በተሞላበት አነጋገር እንዲህ አለ፡- “አውቶቡሱ ለአብዮታዊ ግዳጅ የሚፈለግ ስለሆነ፥ በተቻለ ፍጥነት እንድትወጡ ትለመናላችሁ።”

ወዲያውኑ ሁሉም ጭጭ ብሎ፥ ውልቅ ውልቅ እያለ ወጣ። አንድ ያጉረመረመ ወይንም የብስጭት መልክ ያሳየ አልነበረም። እንዲህ አይነት ታዛዥነት (ፍጹም መገዛት) ከየት መጣ? እውነትም የሰውን ልጅ ተፈጠሮ የጠብ መንጃ ኃይል ይለውጠዋል! አልኩ በልቤ።

እኛም ከአውቶቡሱ ወጥተን፥ አይዞህ! አይዞን! ተባባልን። እኔም አሻግሬን ሳጽናና፥ “እንግዲህ አይዞን። ጸጋዬም አይዟችሁ፤ ዛሬ ባይሳካ ነገና ከነገወዲያ ሊሳካ ይችላል” ብሎናል። ያ የፈረደበት የባላገሩ ጓዳችን እስኪያገኘን ድረስ በተባለው ሰዓት በየቀኑ ኮዱን ይሠራል ማለት ነው። እንዲሁ ኮዱን እየሠራ ለስንት ቀናት ይጠብቀናል ማለት ነው? ግፋ ቢል ለሦስት ቀናት እንጂ እኮ ነው። ታዲያ እስከዛ ድረስ አውቶብሱን

የማናገኝ ከሆነስ? ትግላችን ረዥም፤ መንገዱም ጠመዝማዛ ነው። ተስፋ መቁረጥ ለሰው ልጅ ጠንቅ ነው፤ ስለዚህ እንበርታ። እንግዲህ ከዛው ሻይ ቤት በየቀኑ እንገናኝ፤ አንድ ሁለት ቀን ብንቆይም ምንም አይደል" ተባብለን ተለያየን። ከዛም በኋላ እየተገናኘን፥ በየቀኑ የአውቶቡሱን ሁኔታ መከታተል ቀጠልን።

አንድ ሳምንት አለፈ፤ ግን ሁኔታው አልተቀየረም። የኤርትራ ጦርነት ከምን ጊዜውም የበለጠ እየተፋፋመ በመሄዱ፥ አውቶቡስ ማግኘት አልተቻለም።

## ሚሊሺያ

በየቀኑ ከየባላገሩ እየታፈሱ የሚመጡት ወጣቶች "ታጠቅ" የተባለው ጦር ሰፈር ይገቡና ጥቂት ሰልጥነው ወደማያውቁት፥ የሽምቅ ውጊያ ወዳለበት ወደ ኤርትራ በረሃ ይወሰዳሉ፤ "ሚሊሺያ" የሚል ስም እየተሰጣቸው።

ባላገሮች ከሚስቶቻቸው ተለይተው - ከዘመዶቻቸውም ተገንጥለው ከግብርና ሥራ ወደ ውትድርና (ሚሊሺያነት) ሥራ ሲሸጋገሩ፥ "አገራችንን ከውጪ ጠላት እንከላከላለን" በሚል መፈክር ነበር። እህ! ታዲያ የኢትዮጵያችን ታሪክ የሁሉም ዜጎቿ ታሪክ ተደምሮ በጥቅሉ ሲነገር ነው እንጂ፥ የአንድ ንጉሥ ወይም የግለሰብ ታሪክ ብቻውን አይደለም፤ ታዲያ፥ ሁሉም ፖለቲከኛ በሆነበት ምድር፥ ማን ያውራ ስለነርሱ - ከባላገር በግዳጅ ስለሚገቡ "ታጠቅ ሰፈር" ስለሚዘምቱ ከሩቅ አገር።

አውቶቡሱ ውስጥ ሲገቡ፥ ሌሎችም ሲከታተሉ፥ የኤርትራ በረሃም ለነኛው ለባላገሮቹ - ለወጣት ገበሬዎች "የመጨረሺያ ማረፊያ ሥፍራ" ሲሆን፤ ሰው ሁሉ ሲያዝን፥ የእናት፥ የእህት፥ የሚስት ሃዘን ምርር ሲል..።

ከቡሬ - ከቡሬ የኢትዮጵያ ባላገር፥
የታጨህበት ሚሊሺያ፥ የመቃብር ስምህ ወታደር፤
በል ደህና ሁን፥ ካውቶቡሱ ተሳፈር፥
ልትሄድ ነውና ኤርትራ ከሚሉት ከሩቅ አገር፤
ነፃነት ወይንም ሞት ብለው ከተነሱት - ከዘመዶቼ መንደር።
በል ሂዳ! ከዚያ ማዶ ... በጠብ መንጃህ ፍቅርን ዝራ፥
አንዲቷ አገራችን በሕዝቦቿ እንድትኮራ።

ታዲያ፥ ወደ ሰሜን - ሜዳ ሜዳውን፥
እስከ በጎ ምድር፥ ሊማሊሞን ስትሻገር፥
አውቶቡሱ ሲነቀንቅህ፥

ፈሱን ሲፈሳብህ እንዳትቸገር፥
እንካ ወንድሜ ይህችን ፎጣ፥
ሸንጥ አርጋት ከአስቤዛው ሥር።
ወይ ጉድ! ግራ የገባ ነገር፤
ምንም ሳይከብድ አብሮ መኖር፥
ጠብና ጭቅጭቅ እንዳይፈጠር፥
ያገር ሰላም ሊታስከብር፥
ከደቡብ፥ ከምሥራቅ ከመሃል አገር፥
ምሩጥ አንተ ገበሬ - ምሩጥ አንተ ባላገር፥
አንተ ልትዘራ በጠብመንጃ ልዩ ፍቅር!!
መገንጠል - ለብቻ መኖር፥
መድኃኒት ከሆነበት መንደር።
ወንድሜ በል ሂድና ለአገርህ ሙት፥
ይሻል ይሆናል ከመቸገር - አፈር ከመግፋት።
በኛ ልፋትና ጥረት በልጆቿም ብርታት፤
የዲሞክራሲ በር ሲከፈት፥ ኤርትራ ቁንጅናዋ እንዲታይላት፤
“ትልቅ እንጨት” ባንዲራ መትከያ በኢትዮጵያ እንዲጸናላት፤
የነፃነቷ ምልክት እንዲውለበለብላት፥
ሰላሟ በሁላችንም ደም እንዲጠበቅላት።
እህ ወንድሜ!
ካላንተ እኮ አይመጣም ሰላሜ።
ግን ምን ይደረግ? መድኃኒት ሆኖ ከተገኘ፥
ደምህና ደሜ።
እኔስ ካላንተ አይሆንልኝም፤...... አታቅፈኝም መሬት፤
ሞትስ ካልቀረ፥ ፈጥኖ ይምጣልኝ፥
ካንተ ከመለየት።
አዬ! በቃ፥ በቃ! በቃ ሂድ፥
ከቡሬ ሂድ በቃ፥ በቃ ሂድና ሙት፤

ግዳጅህን ፈጽምና ከምድር ተሰናበት፤
አይዞህ አብረን እንገባለን ከሰማይ ቤት፥
ፍጹም ዲሞክራሲ ከሞላበት።

ወንድምዬ ጸልይ፥ እንጸልይ፥ አብሮ እንዲጥለን፥
እንጸልይ ጊዜያዊ መለያየት እንዲሆንልን፤
የፍቅር አምላክ አብሮ እንዲያስኖረን።

ውዴ ፍቅሬ በል ሂድ፥
ውዴ ደህና ሁን፤
በእግዚአብሔር እንጂ በሰው አይሆን!
በእግዚአብሔር እንጂ በሰው አይሆን!
በእግዚአብሔር እንጂ በሰው አይሆን!........።

ስለ ኤርትራ ጉዳይ ኢሕአፓ የሰው ልጆችን ዲሞክራሲያዊ መብት ከግለሰብ እስከ ብሔረሰብ ለማረጋገጥ ሲሞክር "የማንኛውም ብሔር የዲሞክራሲያዊ መብት እስከመገንጠል (መገንጠልንም ጨምሮ) የተጠበቀ ነው" የሚል ፖሊሲ አውጥቶ ነበር። ይህ ፖሊሲ ከውጪ የተቀዳና ለኛ ለኢትዮጵያኖች የማይሆን ነው፥ ይህ ፖሊሲ አገር የሚከፋፍል ገንጣይ ነው የሚሉ ነበሩ፤ አሁንም ይኖራሉ። እነርሱ ግን፥ በግላጭ የማይታየውን፥ በውስጠ ታዋቂነት "አንድነት በእኩልነት" በሚል መርሆ የተነደፈውን የትግል ጉዞ (እስትራተጂና ታክቲክ) - ቀናውንና የሰዎችን ሰብአዊ መብት የማያስደፍረውን ፍቅር፥ ዲሞክራሲና የእኩልነት መንፈስ ያልተለየውን መነሻና መድረሻ አላዩትም።

"የማንኛውም ብሔር የዲሞክራሲያዊ መብት እስከመገንጠል (መገንጠልንም ጨምሮ) የተጠበቀ ነው" ሲባል፤ በቅድሚያ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ይኖራሉ። እነኚህም መስፈርቶች - በሃማኖትና በተለያዩ ስነ ልቦና የሚገናኙ፥ አንድ ቋንቋ የሚናገሩ፥ አንድ ባሕል ያላቸው ሕዝቦች፥ ከሌሎች ተለይተው በአንድ የጂኦግራፊ ክልል ተወስነው በአንድነት ተሰባስበው የሚኖሩበት ሥፍራ ሲኖር ነው። ይህ ሲሟላ፥ በተጠቀሰው የጂኦግራፊ ክልል ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ብሔረሰብ ይባላል፤ የሚኖሩበት አካባቢም ብሔር ይባላል።

በእርግጥ፥ ከደርግ በፊትና በደርግ ጊዜ በኢትዮጵያችን ውስጥ ከላይ የተጠቀሰውን መስፈርት በከፊልም ሆነ በምልአት የሚያሟላ ከኤርትራ በስተቀር ሌላ ማንም አልነበረም። ባሁኑ ጊዜ ግን፥ እነርሱ፥ ጸረ ዲሞክራሲ የሆኑት እውነተኛ አገር

ገንጣዮች፥ እውነተኛ የኢሕአፓና የኢትዮጵያ ጠላቶች ለኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የጂኦግራፊ ክልል እያበጁላቸው ለመገንጠል የሚያበቃውን መስፈርት ሁሉ እያመቻቹላቸው ነው፤ ግን መጥፎ ምኞት አይመቸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ።

ኤርትራን ከኢትዮጵያ ልገንጥል ብሎ የተነሳ፥ ኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጥል እንደ ዋነኛ ፖሊሲው አድርጎ የወሰደ ማን ነበረ? በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ አንቆይበትም። ግን፥ ካሁን በፊት ሚኒሊክና ዮሐንስ ያልተጨቃጨቁበት የመገንጠል ጥያቄ የመጣው መቼ ነው? ለምን? እንዴትስ ተባባሰ? በምን አይነት ዘዴ ነበር የተፈጠረው ችግር የሚፈታው ብሎ ማሰብ ይበጃል።

ዲሞክራሲ ከሰብአዊ መብት ጋር የተያያዘ በመሆኑ፥ "የባል ወይም የሚስት ዲሞክራሲያዊ መብት እስከመፋታት - መፋታትንም ጨምሮ" የተጠበቀ መሆኑን እናውቃለን። ይህ ማለት "ተጣሉ..ተፋቱ" ማለት እንዳልሆነ፥ እንዲጣሉ እንዲፋቱም የሚገፋፋ አይደለም፤ መልካሙን ጎን ለተመለከተው፥ በፍቅር ተዝናንታችሁ ኑሩ ማለት ነው እንጂ። ለመፋታት የሚያበቃ ሁኔታ ከመጣ ግን የመፋታት መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል። ለሰው ልጆች ሁሉ የመግባቢያ ቋንቋን የፈጠረ ቸሩ እግዚአብሔር ይመስገን፤ ሊቃውንት የታሪክ አዋቂዎችና ፖለቲከኞች ከሚያስቡት ሁሉ ባሻገር፥ ይህንን በቀላሉ የሚረዱ የኢትዮጵያና የኤርትራ ልጆች ብዙዎች ናቸው።

እኛ ኢሕአፓዎች (የኤርትራም የኢትዮጵያም ልጆች) ከዚህ ቅን አመለካከት ተነስተን፥ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ሕዝቦች የሚጠቅመውን - ለፍጹም ዲሞክራሲ ታገልን እንጂ፥ አገር ለመገነጣጠል አልነበረም የተነሳነው። ግን፥ ዛሬ ከጉልበት በስተቀር ቀና አስተሳሰብ የሌላቸው ስንኩሎች፥ የኛን ጥሩ መንፈስ፥ ገልብጠው በተቃራኒ ሊጠቀሙበት ደፋ ቀና ይላሉ። እውነታው ግን፥ የመገንጠልን መስፈርት የሚያሟላ ዛሬም ሆነ ለወደፊት በኢትዮጵያችን ሊኖር አይችልም። ስለዚህ፥ ከኢሕአፓ የተወሰደ በግልባጩ አንቀጽ 39 ቢባል (የወያኔው) ለኢትዮጵያችን አይሠራም። በሕዝቦች መካከል የሚኖር የእግዚእብሔር ፍቅር የተጣሉትን ያስታርቃል፤ መልሶም አንድ ያደርጋቸዋል። ኢትዮጵያችንም በነጻነትና በእኩልነት ላይ በታነጸ አንድነት - የሚጠብቃትን የአምላኳን ሰላምና ፍቅርን ይዛ ትዘልቃለች።

አሁንም ቢሆን አሁንም፥
ትግል ካለ ዲሞክራሲ ግብ የለውም፤
ዲሞክራሲያዊ ተቋም የሌለው መገንጠልም፥
የጭቆናን ስርአት መልሶ ከማምጣት አያመልጥም።
ያቺ የነፃነት፥ የፍቅር፥ የሰላም፥ የእኩልነትና የአንድነት ባንዲራ፥

ከመሃል ኢትዮጵያ የተተከለች፥ የምታውለበልብ በኢትዮጵያ ጣራ።

ለአንድ ሕዝብ ታጭታ የተቀመጠች ሙሽራ፥

አሁንም አለች በኢትዮጵያ፥ እንዲሁም በኤርትራ።

ኢጭአት፥ መኢሶን፥ ኢሕአፓ፥ ማሌሪድ፥ ኢኮፓ ብለው፥ የፖለቲካ ብርድልብስ ተከናንበው፥ በሰላም እንዳይኖሩ ተጣልተው፥ መንግሥት(ቱ) ሲከዳቸው፥ የፖለቲካ የብርድ ልብሳቻቸውን እያነሳ ሲጥልባቸው፥ እርቃናቸውን ሲያስቀራቸው.. ..፥ ይህ ገንዘብ ከባንክ እያወጣ፥ ጥይት እያመረተ ብዙ ሰዎችን ያጨራረሰ፥ ይህ አንድ ደመ መራራ ጦረኛ - ይህ ያገር መሪ (አጥፊ)፥ መስሎ መኖር ያቃተውን ደባልቆታል ካፈር።

ከአጠቃላይ የጥሩ አሳቢዎች ጀግኖች ወታደሮች (መኮንኖች፥ ሻለቃዎች፥ ኮለኔሎች፥ ጄኔራሎች) መካከል ለብቻው ተገንጥሎ፥ እነርሱን አስጨርሶ፥ አብዮቱን ለብቻው የመራ እርሱ ነው። አዛውንት፥ ምሁራን፥ ወጣቶችም ተገድለው፥ ሕዝቦች ደህይተው፥ ጦሩ ተቀንሶ፥ የሕዝቦች ቅስም ተሰብሮ፥ አገራችን እንድትዳከም ያደረገ ይህ ወታደር ነው።

ይህ ወታደር ለየት ያለ ሃሳብ ያቀረበውን ሁሉ የሚያዳፍን ወይም የሚደፋ (የሚገድል) በመሆኑ፥ ስለ ጦርነትና ስለ ሰላም የሚያውቅ፥ ስለ አገር ጥበቃና ስለ አንድነት ከአባቱ ከጃንሆይ የተማረ፥ አንድ ጄነራል አማን አምዶም የተባለ ኢትዮጵያዊ ጀግና "ኤርትራን ከእናት አገራቸው ለመገንጠል ጫካ የገቡትን የሸምቅ ተዋጊዎች በሰላም ድርድር ካልሆነ፥ በፊትለፊት ጦርነት ብቻ ብንቀጥል አይረባንም፤ ጦርነቱ ማለቂያ ስለማይኖረው፥ ህዝባችንን በከንቱ እንጨርሳለን፤ ያገራችንም ኢኮኖሚ ስለሚዳከም፥ ለአገር እድገት የምናደርገው ጥረት ስኬት አይኖረውም። ስለዚህ እባካችሁ እንደራደር" ብሎ ሲማጸን፥ ወታደሮች ከቤቱ ሄደው እንዲገድሉት አደረገ። በጄኔራሉ ፋንታ ይህ የጥፋት መላእክተኛ ቢሞትልን ኖሮ፥ የኢትዮጵያ አገራችን መልኳ (የጂኦግራፊ ቅርጿ) እንደ ቀድሞው ይሆን ነበረ።

ኢሕአፓ ይህን ግለሰብ ለመግደል ያደረገው ሙከራ ትክክለኛ እርምጃ ነበር ወይንስ አልነበረም? ቢባል፤ ከ"ቢሆን ኖሮ" ዎች መካከል ይኸኛው አንደኛ ይሆን ነበር። ይህን እና የመሳሰለው ታሪክ ለፖለቲከኞችና ለታሪክ ጸሐፊዎች ይቅርላቸው።

አንድ በጣም የምወደው ቀደም ሲል ተክሌ ብዬ የጠቀስኩት፥ አዲስ አበባ የተወለደ ኤርትራዊ ኢትዮጵያዊ የሆነ የቅርብ ጓደኛዬ፥ የኢሕአፓ የጥናት ህዋስ አብረን ጀምረን ስንጨርስ፥ እኔ የተመደብኩበት የፓርቲ ክፍል ብዙ የማያጋልጥ ሲሆን፥ የእርሱ ግን ብዙ መጋለጥ ካለበት ቀበሌ፥ ያውም ከወጣቶች ክንፍ ውስጥ ነበር። ከወረቀት መበተን እና ሰላማዊ ሰልፎች አልፎ ሽጉጥ በእጁ አልጨበጠም። ግን እርሱ

ትግሪኛ ባይናገር እንኳን ዘመዶቹ ይናገራሉ ብለው፥ የርሱ ጸረ አብዮተኛነት በኢሕአፓነቱና በኤርረትራዊነቱ ሲደመር ከፍተኛውን ሥፍራ ስለያዘ፥ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ በጣም ተጋልጦ ይፈልጉት ስለነበር፥ አልፎ አልፎ ከኔ ቤት እየመጣ ይደበቅ ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን እየተቻኮለ ከቤቴ መጣና፡- “ጓዴ፥ ወንድሜ፥ አዲስ አበባ መኖር አልቻልኩም፤ ፓርቲው ምን ያህል እንደተጋለጥኩ ያውቃል። ግን እንኳን እኔን ይቅርና፥ ከኔ በላይ የተጋለጡትን እነ እገሌን እና እነ እገሌን እንኳን ወደገጠሩ አይልካቸውም። ወደ አስመራ ልሂድና ካጎቴ ጋር ለአንድ ወር ያህል ልሰወር። መሳፈሪያ ገንዘብ ስጠኝና አሰናብተኝ፤ ሁኔታዎች ሲረጋጉ እመለሳለሁ...” አለኝ።

እኔም “ቅር አትሂድ..” እያልኩ ባሳንፈው፥ እዚሁ ሙት ማለት መሆኑ ገብቶኛል። ሆኖም፥ “ግን አስመራም ቢሆን እኮ ግድያ የሚፋፋምበት፥ በየመንገዱ የደርግ ወታደሮች የሚቆጣጠሩት ሥፍራ ነው፤ እዛስ ብትሄድ፥ ነፍስህን ስለማትረፍህ ምን ዋስትና አለህ?” አልኩት። እርሱም፥ “አንዴ አጎቴ ቤት ውስጥ ከገባሁ ከዛ አልወጣም። መቼም ለጊዜውም ቢሆን ከሚያሳድዱኝ ገለል ማለት ፈልጌ እንጂ፥ ከትግሉ መሸሽን መርጬ እንዳልሆነ ይገባሃል” አለ።

ለተክሌ ገንዘብ ሰጠሁትና በልቅሶ ተለያየን። በዛን ጊዜ አስመራ ውስጥ ከሽማግሌና ከአሮጊት ወይንም ከሕጻናትና ትናንሽ ልጆች በስተቀር፥ ጎረምሳ ከውጪ አይታይም ነበር። የደርግ ወታደሮች ወጣት የሆነ በአስመራ መንገድ ላይ ከታየ፥ ለጸረ አብዮት እንቅስቃሴ የሚያካሄድ እየመሰላቸው ይገድላሉ ወይንም ያስራሉ። በዚህም ምክንያት፥ በከተማ ብቻ ሳይሆን በየባላገሩ ያለ ወጣት ሁሉ የገዛ ነፍሱን ለማዳን ሲል ከነፃ አውጪዎች ጋር እንዲቀላቀል ይገደዳል። የኔ ጓደኛ በሄደ በሁለት ሳምንት ውስጥ፥ ድንገት ካጎቱ ቤት ወጣ ብሎ መንገድ ሲሻገር ወታሮች አይተው ገደሉት። (ነፍሱን ይማራት)።

በዚህ በአንድ ምስኪን፥ በሌሎችም ኤርትራዊ በመሆናቸው ብቻ የተገደሉ ኤርትራውያን - ኢትዮጵያዋያን ፋንታ፥ ያ የጥፋት መካእከተኛ ቢሞትልን ኖሮ፥ የኢትዮጵያ አገራችን መልኳ (የጂኦግራፊ ቅርጿ) እንደ ቀድሞው ይሆን ነበረ፤ ወይንም የተገንጣዮቹ ቁጥር ይቀንስ ነበር።

ኤርትራዊ/ኢትዮጵያዊ ወጣቶችን ሁሉ “ሂዱ፤ ጫካ ግቡና ውጉኝ፤ ከተቻላችሁስ መንግሥታዊ ስልጣኔን ከኔ ፈልቅቃችሁ ትወስዳላችሁ፤ ከዛ በኋላ ነፃ ትወጣላችሁ.....” በሚል የሰካራም ጉልበተኛ ድንፋታ (ርዕዮተ ሰይጣን) ተመርታ አገራችን ተከፋፈለች።

ተነግሮ የማያልቅ ብዙ ትእይንት ከተፈጸመባት አገራችን መካከል፥ ጎላ ጎላ ያለውን እንኳን ቢጽፉት የወደፊቱ ትውልድ ጠቃሚ ትምህርት ያገኝበት ይሆናል።

**<u>የብቸኛ ትግል</u>**

ወደ ቀድሞው ነገራችን እንመለስና፥ ስለራሴው ሁኔታ ላውራ። በዚህ አለም የሚከናወነው ሁሉ (ወይንም እኔ የምወስደው እርምጃ) እኔን ከተሳታፊነት አገልሎ፥ የተለየሁ አድርጎ አስቀመጠኝ፤ ከማውቃቸው ሁሉ ለየኝ። ወይ ከኢሕአፓ፥ ወይ ከተቀረው ሰው ሳልሆን በመሃል የቁም እስረኛ ሆንኩ።

የብቸኛ ትግል ማለት ምንድነው? ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ከአይምሮ ውስጥ ኢያሰላሰሉ ማሰብና መጨነቅ ማለት ነው?

ዙሪያዬ ጨለማ ባይሆን ኖሮ፥ በፖለቲካና በፍልስፍና መካከል ጣልቃ የሚገባ ሃይማኖታዊ መሰል ቀና አስተሳሰብ በውስጤ እንዳለ አውቃለሁ። እንዳውም ሰውን ሙሉ የሚያሰኘው ይኸው ይመስለኛል። ግን ትንሽ ዞር ብሎብኛል፤ በዛ የመርካቶ ግርግር መካከል፥ የሰውና የሌላውን ጩኸት መለየት አቅቶኛል።

በንድ በኩል፥ “የመርካቶ ሕዝብ ምን አይነት ጆሮ ቢኖረው ነው በዚህ ሁሉ ጩኸት መካከል የሰው የሆነውን ጩኸት አጣርቶ የሚሰማ?” እላለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ የኔ ጥንካሬ ማጣት፥ ባካባቢዬ ከማየው ሰው ሁሉ ያሳነሰኝ እየመሰለኝ፥ በራሴ አዝናለሁ።

ጆሮዬስ ከዳኝ፤ ግን የጆሮዬ መከዳት ለሃሳቦቼ ጥንካሬ የሰጠው እየመሰለኝ፥ ጽሑፎቼን ቀጠልኩ፤ ጠላ ቤት እየገባሁ መጻፍ ሆነ ሥራዬ። ሃሳብ ሲበራከትና ሲጽፉት ቀለል - ደስ ይላል። ግን ይህ ጽሑፍ የት ይደርስ ይሆን?

የሰውነቴ አካል የሆነው ልብሴ፡- አንድ ሰማያዊ ሸሚዝ፥ ጠቆር ያለ ሱፍ ኮት፥ ቡናማ ሱሪ እና ጥቁር የቆዳ ጫማ፤ የጠቅላላ ኪሶቼ ቁጥር አስር፤ ሻይ ቤት ገብቼ ገንዘብ ለመክፈል አስሩን ኪሶቼን አስር ጊዜ መዳበስ የተለመደው ጠባዬ። ኪሶቼን በየጊዜው ስደባብስ የተገዙትን የአውቶቡስ ቲኬቶች አውጥቼ ጥያቸው ይሆን? በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ማለት ይህ እኮ ነው። ችግር ሲመጣ ይደራረባል። በኪሴ የቀሩኝን ብሮች ደጋግሜ ከቆጠርኩ በኋላ፥ ለሁለት ቲኬት መግዢያ የሚሆን ገንዘብ (23 ብር ነው) በአንዱ ኪሴ አስቀምጫለሁ።

መቸገሬን አይቶ ሥጋ የተባለ ከሰውነቴ ጠፍቶ አጥንቴን ስለቀረሁ፤ ተወዛዋዥ አጽም መሰልኩ። ጉልበት ሊከዳኝ ነው፤ ትንሽ ስሄድ ይደክመኝ ጀመር። ከጆሮዬ ቀጥሎ እግሮቼም ሊከዱኝ ነው መሰለኝ። አቅጣጫን የሚያሳውቅ የአይምሮዬ

ክፍል ድንገት ሳይዘጋ አልቀረም፤ መንገድ ይጠፉኝ ጀመር። ቡና ቤቶቹ ሁሉ አንድ አይነት ሆኑብኝ።

ቀደም ብሎ ድምጽ ሁሉ አንድ አይነት ሆነብኝ፤ አሁን ደግሞ በአይን የሚታይ ሁሉ አንድ አይነት እየሆንብኝ ነው። ሌላ አገር ውስጥ ያለሁ መሰለኝ። ብሄድ ብሄድ አንድ የምለየው መንገድ፥ አንድ የማስታውሰው ቡና ቤት አጣሁ። ከእንግዲህ ማንንም ላላገኝ ነው ብዬ ተበሳጨሁ። ለመሆኑ የመርካቶ መንገዶች እንዲጠፉኝ ያደረገ የአይምሮዬ መድከም ይሆን? ወይንስ የሞራሌ መላሸቅ።

አሻግሬ ካጠገቤ ጠፋ፤ ወይ ፈልጌ አላገኘሁት፤ ወይ ፈልጎ አላገኘኝ። ጸጋዬንም ለማግኘት ሞከርኩ እርሱ ባገር የለም። መድህን ጠፍቷል። ሁለቱን (እሻግሬንና ጸጋዬን) ለማግኘት ካልቻልኩ፥ አውቄ የጠፋሁባቸው ይመስላቸው ይሆን? ጸጋዬን ለማግኘት ካልቻልኩ ለአሻግሬ አልጠቅመውም። ግን ጸጋዬን እንኳን ባጣ አሻግሬን ባገኘውና፥ ሃሳብ ለሃሳብ ብንለዋወጥ ጥሩ ነበር።

በሄድኩበት የቀበሌ ዘበኞች ይከታተሉኝ፥ ሁኔታዎችም ተስፋ እንድቆርጥ ያስገድዱኝ ጀመር። ሌላ መንደር ውስጥ ገባሁ። ቀስ በቀስ ከዚህ መንደር ያሉትን የሻይ ቤቶችና አካባቢያቸውን አጠናሁ። በዚህ መንደር ውስጥ ብዙ ሴትኛ አዳሪዎች አሉ። ለመሆኑ ሴትኛ አዳሪ ማለት ምን ማለት ነው?

እህ! የኢትዮጵያችን ታሪክ የሁሉም ዜጎቿ ታሪክ ተደምሮ በጥቅሉ ሲነገር ነው እንጂ፥ የአንድ ንጉሥ ወይም የግለሰብ ታሪክ ብቻውን አይደለም፤ ታዲያ፥ ሁሉም ፖለቲከኛ በሆነበት ምድር፥ ማን ያውራ ስለነርሱ - ስለ ሴትኛ አዳሪዎቹ።

ሴትኛ አዳሪ ማለት ሴቶች በምድር ላይ ራሳቸውን ችለው መኖር ሲያቅታቸው፥ በኑሮ የሚያግዛቸው ባል ሲያጡ፥ በምድር ለመቆየት ሲሉ ወንዶችን የሚለምኑበት ዘዴ ነው። ወንዶችም የሚሠሩትን ሠርተው፥ የእንስሳነታቸውን ደግነት ለመግለጽ ሲሉ፥ ገንዘብ ጣል አድርገው ይሄዳሉ።

በዛ በረሃቡ ዘመን - ድርቅ በሆነበት ሥፍራ (በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ) ባሎች ሚስቶቻቸውን ማስተዳደር አቃታቸው። ሚስቶችም የሚያበስሉት ምግብ አጡ። በትዳር ውስጥ የረሃብ ሞት ገባ። ከዚህ ለማምለጥ ብለው፥ ባልና ሚስት ሳይፋቱ፥ የተለያየ ሥራ ጀመሩ። ባል ባቅራቢያው ከሚገኘው የባላገር ከተማ በቀን ሥራ ሲሸቅል፥ ሚስት ደግሞ፥ ሽቃዮች ከሚያስገኙት ገንዘብ ለመካፈል ስትል፥ ጠላ ሻጭ ሆነች።

ይህችና ሌሎችም ሴትኛ አዳሪዎች ዘመዶቻቸው በምግብ እጦት ሥጋና ነፍሳቸው ሲለያይ የተመለከቱ ናቸው። የባላገር ኑሮ ሲያል እየሆነ መኖር ሲያቅታቸውና ከሞት በስተቀር ሌላ አማራጭ ሲጠፋባቸው፥ በሥጋቸው ተደስተው

ለመኖር ሳይሆን፥ ለዛ ነፍስን ለተሸከመ ሥጋ እንዳያንቀላፋ መደለያ ይሆናል ብለው ነው ሴትኛ አዳሪ የሆኑት። በነርሱ ምርጫ ሳይሆን ተገደው ነው። ታዲያ ገጠር በነበሩ ጊዜ ከተፈጥሮ ጋር ታግለው የሰውን ልጅ ከሞት ለማዳን ይጣደፉ ነበር። አልሆን ሲላቸው የራሳቸውን ነፍስ ለማዳን ብለው አዲስ አበባ ገቡ።

እንዲሁም በአዲስ አበባ ሠራተኛ ባል ከእስር ቤት ገብቶ የመፈታት ተስፋው ጥፍት ሲል፤ ሚስት ለባሏ የምታቀብለው፥ እሷም ልጇም የሚበሉት ምግብ ሲያጡ፥ እየከሳች እየመመነች ስትሄድ፥ ልጁም ሲቀጭጭ፥...

ባል ከእስር ቤት ለሚስቱና ለልጁ ሲጨነቅ፥ የነፍስ ማዳን አማራጭ ዘዴዎችን ሁሉ አስቦ አስቦ መልስ ሲያጣ፥ ልቡም በርህራሄ ሲነካ፥ የሚዘገንን ነገር በብጣሽ ወረቀት ጽፎ አቀበላት "ስፈታ እንጋባለን?"... ምን ማለት ነው?... ወይ ጉድ!!

በሰው ሰራሽ ችግር የሰው ምርጫው ሲሆን ኃጢአት፥
ጾታ በጾታ ላይ እንዲነግሥበት፥
ሥጋ በሥጋ ላይ በገንዘቡ እንዲያዝበት።
ሴቶች ነፍስ ዘሪዎች፥ ጡት አጥቢዎች፥
ነፍስ ዘርታችሁ ዝም የማትሉ፥ አሳዳጊዎች፥
በሕይወታችሁ ሁሉ፥ ለሰው ልጅ ተቆርቋሪዎች፥
በእውን የናንተ የቢሮ ሥራ ይህ ይሁን?..ይህ ይሁን?...
የደላው ብቻ - ቁጭ ብሎ - ተዝናንቶ ሲወንጅል ሌላውን፥
በሴቶቹ ላይ ያላክካል፥ ጥፋቱን፥ ኃጢአቱን።
የሰው አይምሮ ሁሉን ተገንዝቦ ሲያዝን፥
ግን ከሃዘን በቀር፥
ትግል ሲቀር፥
ኢሕአፓ ሲበተን፥
ተስፋ ሲመነምን፥
አይ አንቺ ምድር! ስንቱን አሳየሺን - ስንቱን።

ይህም ትንሽ ልጅ ገና ከልጅነቱ ከአባቱ ተለይቶ፥ ከሞት እንዲተርፍና እንዲያድግ እናቱ የምታደርገውን ትግል ሁሉ ለማስተዋል ይበቃና "....ይህች እናቴ ሴትኛ አዳሪ ሁና ያሳደገችኝ፤ ፍቅርን ስለመገበችኝ፥ ውለታ አለብኝ፤ ተምሬ፥ ሥራ ይገኔ፥ እናቴን ነጻ አወጣታለሁኝ ይላል።" አዎ! ይህንን ይላል፥ ያ ገና ነፍስ ያላወቀ

የሴትኛ አዳሪ ልጅ። ግን በጉርምስና እና በእውቀት፥ እርሱም የሚወድቅበት ጎዳና ከእናቱ የከፋ ይሆናል።

ከባላገር መጥተው ሴትኛ አዳሪ ለመሆን የተገደዱትን፥ በአዲስ አበባ ከተማ ተወልደውና አድገው ሴትኛ አዳሪ ለመሆን የተገደዱትን፥ ለምን እና እንዴት ወደዚህ ሥራ እንደተሰማሩ የሚያውቅ ማነው? ግን ምንም እንኳን ድህነት ሴትኛ አዳሪዎች እንዲሆኑ ቢያስገድዳቸውም፥ በልተውና ጠግበው የሚኖሩ ወጣቶች በጥይት እየተገደሉ ከደጃፋቸው ሲጣሉ ተመለከቱ። ከሴትኛ አዳሪነት ጋር ሌላ ተጨማሪ ሥራ በምርጫቸው ወስደው ነው የሰብአዊነት ተቆርቋሪዎች በመሆን ከኢሕአፓ ታጋዮች ጋር የተቆራኙት።

ቀደም ሲል፥ በኢሕአፓ በኩል የተደረገው ቅስቀሳ የመርካቶ ሴትኛ አዳሪዎችን የዲሞክራሲያዊ ግንባር ውስጥ እንዲሳተፉ አድርጓቸው ነበርና፤ ብዙ ሴቶች በሉሉታ ኮሚቴዎች በመሳተፍ "ሉ!ሉ!ሉ!ሉ!ሉ!ሉ!ሉ!ሉ!ሉ!.........." እያሉ በመጮህ፥ የደርግ ወታደር መርካቶ እንዳይገባ ባቅማቸው ተከላክለዋል። ለዚህ ነው እኔም በሴትኛ አዳሪ ወታደሮች ከሚጠበቅ መንደር - ከመርካቶ የገባሁት።

በዛ በቀውጢ ቀን፥ መጠጊያና መሄጃ አጥተው ባለቤት እንደሌለው ውሻ ከርታታ በመሆን፥ ለማኝ በሽተኛ መስለው የሚታዩትን የኢሕአፓ ታጋዮች፥ የመርካቶ ሴትኛ አዳሪዎች በማስጠጋት ረድተዋል።

ከደጋግ ሰዎች ዘንድ ያለ (የተፈጠረ) ርህራሄ በሴትኛ አዳሪዎችም አለ። ስለሆነም፥ ከሰዓት እላፊ በኋላም ቢሆን፥ ለአልቤርጎ የሚከፈለውን ያህል ብቻ እያስከፈሉ፥ ወይንም በነፃ በማሳደር፥ የብዙዎችን ነፍስ አድነዋል።

በተቃራኒ ደግሞ፥ አንዳንድ ሴትኛ አዳሪዎች፥ ሰዓት እላፊ ሲቃረብ፥ እንደኔ አይነቱን ጠውላጋ ከርታታ ገና ከሩቅ ሲያዩ፥ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው "እኛ አልቤርጎ አይደለንም፤ እንዴ! አሁንስ በዛ፤ እንዴ!..........." ይላሉ። ታዲያ፥ በዚህን ጊዜ ነው መፈጠር የሚያስጠላው። ግን ጥቂቶች ናቸው እንዲህ የሚሉ። እንደነዚህ ያሉቱ፥ ከኢሕአፓ ወገን ለመሆን የፈሩ፥ ሥጋዊ እውነት ያላቸው፥ መንፈሳዊነት የራቃቸው፥ የተለዩ፥ የተለዩ፥ የተለዩ፥ የተለዩ፥.......ናቸው።

## <u>የአንድ ቄስ ምክር</u>

ከዕለታት አንድ ቀን፥ ጠላ ቤት ገብቼ ለመጎለት ወደ በሩ ጠጋ ስል፥ አንድ ቀዥቃዣ ሰው ከቄስ ጋር ሲጣላ ደረስኩ። ይህም ሰው እንዴት አንድ ቄስ ከሴትኛ አዳሪ ሴት ቤት ይገባል ብሎ የራሱን የከፋት አስተሳሰብ አንጸባረቀ፤ ሊጣላ፥ ሊማታም ከጀለ።

ሴቲቱም ቄሱ እንዳይመታባት በመፍራት ከሁለቱ መሃል ቆመችና እንባዋን ኮለል ኮለል በማድረግ ሰውዬውን እንዲህ አለችው፡-

"ስማህ የኔ ወንድም! ለመሆኑ ምንም እንኳ እድሌ ሆኖ በዚህ ሥራ ብሰማራ፥ እኔስ እንዳንተው ከሰው አይደለም እንዴ የተፈጠርኩት? ሥጋዬ ቢበድልና እግዚአብሔርን ባስቀይመው፥ ነፍሴን እንዲያድንልኝ ብለምነው፥ ማነው የሚከለክለኝ? እርሳቸውስ አባቴ ከቤቴ ገብተው ቢጸልዩልኝና ቢያማልዱኝ አንተ ምን ገደደህ። ከቤቴ እርኩስ መንፈስ እንዳይመጣብኝ፥ ከመጥፎ ሰዎች እንዲያርቀኝ፥ ደጋጎቹን እንዲያቀርብልኝ፥ ወይንም ከዚህ አሁን ካለሁበት የከፋ ኑሮ ውስጥ እንዳልገባ፥ ወይንም ሻል ያለ ኑሮ እንዳገኝ አባቴ እግዚአብሔርን ቢለምኑልኝ፥ ከቤቴስ ጸበል ቢረጩልኝ ያስነውራል? ወይንስ ተከልክሏል? አዬ! ተው - ተው የኔ ወንድም! ፍርድ የእግዚአብሔር ስለሆነ ሰውን ለመኮነን አትቻኮል....።"

ቄሱም ቀስ ብለው በትእግስት እንዲህ አሉ: "ስማህ የኔ ወንድም! አሁን እርሷ ያለችህን ሰማህ። ቄስ የሴትኛ አዳሪ ዘመድ ሊኖረው አይችልም? ሴትኛ አዳሪዎችስ የቄስ ዘመድ እንዳይኖራቸው ምን ይከለክላቸዋል? ይህች ሴት ዘመዴ ስለሆነችና ስለምወዳት፥ በሥጋዋ ረከሳለች ብዬ፥ ተጠይፊ አልራቅኋትም፤ ልጸልይላት አስቤ ከቤቷ መጣሁ እንጂ። ይህን ማድረጌን እንደ ኃጢአት ቆጠርከው? የኔ ወንድም።

አውቃለሁ፤ ከዚህ ስለገባሁ በሌላ ነገር ጠርጥረኸኝ እንደሆነ። የሁላችንንም ሥራ የሚያውቅ እግዚአብሔር ነው። ለመሆኑ፥ ከኔ፥ ካንተና ከሷ የሚጸድቀውን የሚያውቅ ማነው? እኔ ቄስ ስለሆንኩ ብቻ የምጸድቅ፥ እርሷ በዚህ ሥራ ስለተሰማራች ብቻ የምትኮነን ለመሆኑ ማን አወቀ?

እኔ ግን በዚህ ሥራ ተሰማርታለች ብዬ ዝምድናዋን አልፍቀውም። ማንም ሰው የፈለገውን ይበለኝ እንጂ፥ እኔስ ድሮ እንደምጠይቃት አሁንም እጠይቃታለሁ። ይህች አለም አታላይ ናት። "ለኑሮአችሁ የሚሆን ከዚህ ሥፍራ ተዘጋጅቶላችኋልና፤ ኑ እዚህ.." ብላ ሰውን ካልሆነ ሥፍራ የምትጥል አሳሳች ናት።

ሴቶች ልጆቻችን እና እህቶቻችን አይናቸው እያየ ምድራዊ ሲኦል ውስጥ እየዘለሉ የገቡት በምርጫቸው ሳይሆን ተገደው ነው። ይህችም ሴት ሳትወድ የገባችበት ሥራ ሁል ጊዜ እየጸጸታት ነው፤ እድሉ ሲያጋጥማት ከዚህ ሥራ ትወጣለች። እኔም የመጣሁት አንዱም ሌላ አማራጭ እንድትፈልግ ልመክራት ብዬ ነው። እስከዛው ግን በሥጋዋ ብትረክስ ነፍሷ እንዳይረክስ በምታደርገው ጸሎት ልራዳት ብዬ ነውና፤ ወንድሜ አትቆጣ። ይህ ጥለን የምንሄደው አለም ሁላችንም የተለያየ ችግር ውስጥ ይከተናል፤ ማነው ወዶ የሚፈልገውን ብቻ እያደረገ የሚኖር?..ማነው ወዶ የሚፈልገውን ብቻ እያደረገ የሚኖር?.." አሉ በትካዜ።

በዛን ወቅትና በዛ ሥፍራ ብዙ ጭቅጭቅና ብዙ ወሬ ነበር። ሴቶቻችን መሄጃ አጥተው ሲንከራተቱ፥ መንግሥትም እያየ ዝም ሲል፥ እኔ በሰማሁት ብቻ ሳይሆን፥ በሃሳብ በተወጠረው አንጎሌ፥ ይህን እና የመሳሰለውን ሳይሆን አይቀርም የተናገሩት በማለት፥ የሰው ልጅ በዕድሜው ውስጥ የሚደርስበትን ፍዳ ከሁኔታው ጋር በማገናዘብ ለመግለጽ ስል ነው ከራሴው ሃሳብ ጨማምሬ የተናገርኩ።

“ይህ ጥለን የምንሄደው አለም ሁላችንንም የተለያየ ችግር ውስጥ ይከተናል፤ ማነው ወዶ የሚፈልገውን ብቻ እያደረገ የሚኖር?..ማነው ወዶ የሚፈልገውን ብቻ እያደረገ የሚኖር?..” የተሰኘው ግን እኔንም ይመለከታል። አዎ! ጊዜ ያልፋል፥ እስኪያልፍ ያለፋል።

የሰው ልጅ ሕይወቱ አካል ሰውነቱ፥

ቢረክስ ቢዋረድ፥ ክብር አልባ ከንቱ፥

ሌላ ሕይወት አለው፥ የመንፈስ ሰውነት፥

ከጥፋት አውጥቶ ጨዋ ሥፍራ ‘ሚከት።

አለም ሁለት ናት፥ በሁለት ዓይን ስናያት፥

መጥፎውን በጥሩ ይቻላል መተካት።

ከፉውን ብቻ እያየን፥ ተስፋ ከመቁረጥ ያድነን። ባቅማቸው የተራበን ያበሉ፥ የተጠማን ያጠጡ፥ የታረዘን ያለበሱ ሴትኛ አዳሪዎች በሰማይ የሚያገኙትን ሥፍራ፥ ከአልጋቸው ሳይነሱ፥  የቤት ሠራተኞቻቸውን “ውሃ ቀጠነ” ብለው የሚጨቃጨቁ፥ የሚያመናጨቁና የሚቆጡ የቤት እመቤቶች አያገኙትም (ይሆናል)።

ረዓብ የምትባል ጋለሞታ ሁለት የእስራኤል ሰላዮችን ከቤቷ ደብቃ የኢያሪኮ ንጉሥ እንዳይገድላቸው ስላደረገች፥ ስሟ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎላት  እስካሁን ትታወሳለች፤ ምሕረት የሚገባት (ሩሐማ) እየተባለች (ኢያሱ 2፡ 1- መጨረሻ)። ለኢትዮጵያም ሴትኛ አዳሪዎች ምሕረት ይመጣል። ደጋግ የኢትዮጵያ ሴቶች የድህነትና የረሃብ ጦር ከባላገር አባሮ አዲስ አበባ አመጣቸው፤ ከዚያም የሚወዱትን ሳይሆን፥ የሚጠሉትን ሥራ እየሠሩ ይኖራሉ። እነርሱ ጋለሞታዎች አይደሉም። ቸሩ እግዚአብሔር ሁኔታቸውን ተመልክቶ ከጥሩ ሥፍራ ያስቀምጣቸዋል።

ከወጣቶችና ከሽማግሌዎች፥ ከቄሶችና ከዲያቆናት፥ ከመንግሥታዊ ድርጅቶችና ከሃይማኖታዊ ተቋሞች በመዋቀር የኢትዮጵያን ሴትኛ አዳሪዎችን ሁሉ ወደ ተሻለ ሥፍራ እየመራ የሚወስዳቸው መንፈስ በቅርብ ጊዜ በሥፍራዎች ሁሉ ሥራውን እንደሚጀምር ይህ መጽሐፍ ያውቀዋል።

**ሃሳቦች እና ጭንቀቶች**

ከእለታት አንድ ቀን፥ ከጧቱ ሁለት ሰዓት ላይ፥ አንድ የንኡስ ከበርቴ ቡና ቤት ገባሁና፥ ቡና አዝዤ፥ ከአንድ የግርግዳ ማእዘን ተጠግቶ የተቀመጠ ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ። ከኔ በስተቀር ሌላ ሰው አልነበረም። የቡና ቤቱ ሰራተኛ (ቦይ) ሲጠራርግና ሲወለውል አየዋለሁ። እርሱ ጭቁን ነውና ገቢውም ሴቶቹ ከሚያገኙት ያንሳል። ስለዚህም ይመስለኛል፥ ለሴቶቹ ሁሉ እርሱ ታዛዥ ነው። እርሱ የነርሱን ፍላጎትና ስሜት በተቻለው መጠን ይጠብቃል።

እንደገባሁ፥ ያዘዝኩትን ቡና ግማሹን ጠጥቼ፥ እንዳስቀመጡት እቃ ሳልንቀሳቀስ ብዙ ቆየሁ። መቼስ የት እሄዳለሁ ብዬ እስከ ቀኑ አምስት ሰዓት ድረስ ቁጭ አልኩ። ለተመለከተኝ፥ በሃሳብ ሰጥሜ ያለሁበትን የማውቅ አልመስልም። ቦዩም ሥራውን ጨርሶ ሥፍራውን ለተረኞች ሴቶች ለማስተላለፍ ሲሰናዳ፥ የኔ ከቡና ቤት አለመውጣት አሳሰበው። ሳልንቀሳቀስ - ከወንበሩ ተጣብቄ ብዙ ስለቆየሁ ቦዩ ተጨነቀ፤ ተቅበጠበጠ፤ ሴቶቹ ሊመጡ ሆነ።

ሴቶቹ ከእንቅልፋቸው ተነስተው፥ ተፀዳድተው፥ ቁርሳቸውን በልተው፥ ተኳኩለውና አበባ መስለው ብቅ ብቅ ሊሉ ሆነ። ሂሳቡን ከፍሎ እንዳይሄድ፥ የማይፈለግ ሰው ከዛ ወንበር ተጣብቋል። ከዛ ሰዓት በኋላ፥ ከዚያ ሥፍራ መቆየት እንኳን ለኔ ለርሱም አልተፈቀደ።

ቦዩ ልክ እንደሌለሁ ቆጥሮ፥ የዝንብ መግደያ (ፍሊት) ሲነፋ ለኔም ጭምር መሆኑ በደንብ ገባኝ። እኔም ልክ ከእንቅልፉ እንደተቀሰቀሰ ሰው ብንን አልኩ። ቦዩን ምንም ሳልቀየመው አይኔን እያሻሸሁ ቶሎ ብዬ የቡናውን ሂሳብ ከፈልኩና ወጣሁ።

አዎ! ወንዶች ደጎች ናቸው፤ ግን ደግነታቸው እንደ ሴቶች ደግነት አይለሰልስም። ይህስ ቁንጽል፥ ኢሳይንሳዊ አባባል ላይሆን ይችላል። ደግነትን ከርህራሄ ጋር ለማዋሃድስ እንደ ሴቶች ለወንዶች ቀላል አይመስለኝም።

ወይ ጉድ! .. በኦሮምኛ እንዲህ የሚል ተረት አለ "ኢዬይሳ በካ ቡሉ ወጋ ደቤ ዱፉ ኢቲ ባይሳ" ይህም ማለት፡- ደሃ ሰው ማደሪያ ሲያጣ ፈሱን ያበዛበታል ማለት ነው። ከዛን በኋላ "ጥንትም የንኡስ ከበርቴ ቡና ቤት ለኔ አይሆነኝም" አልኩና፥ ቡና ቤት መግባት አቆምኩ።

በጠላ ቤት አካባቢ ያለውን ሕይወት ሲመለከቱት እንጂ ሲኖሩበት ከባድ ስለሆነ፥ ጠላውን ትቼ ሻይ ብቻ በመጠጣት ጤንነቴን ለመቆጣጠር ከጀልኩ። ይህን የቀድሞውን አይነት ኳኳታ የሚያባብስ፥ ሽብርና ትርምስን የሚፈጥር፥ አይምሮን የሚያውክ እንደገና ደፍሬ ገባሁበት። ግን የሻይ ቤቱን ጩኸት ችዬ ልቆይ የምችልበትን

ጊዜ ስቆጥረው ጊዜ፥ አንዷ ደቂቃ እንደ አንድ ሰዓት ሆነችብኝ። ይህንስ አልችለውም አልኩና ወጣሁ።

ከጠላው ቤት ደግሞ ምንጊዜም እኔ በገባሁበት የሚከታተለኝ አንድ ሰው አለ። ይህ ሰው ምድቡ ከደጋግ ሰዎች ይመስላል፤ ገር ከሚመስለው ፊቱ የሚፈነጠቅ የብርሃን ኃይል ከደግነት በስተቀር ክፋት እንደሌለበት ይመሰክርበታል። እኔን አናግሮኝ አያውቅም፤ ግን ሁል ጊዜ ለኔ የሚያዝንልኝ ይመስለኛል። እኔን በጠላትነት ክፋት የሚከታተል ቢሆን ኖሮ፥ እንዴት ሁልጊዜ ከኔ አስቀድሞ ከምገባበት ጠላ ቤት ይገባል? የዚህ ሰውዬ ነገር አሁንም ቢሆን ይገርመኛል። መርካቶ ደጋግ ሰዎች የሚበዙበት አካባቢ ከመሆኑም በላይ፥ አላፊ አግዳሚው ሁሉ ኢሕአፓን በተለያየ መንገድ ይደግፋል። የነኚሁ የደጋግ ሰዎች መንፈስ ነው የደርግን ታንክና መትረየስ በመመከት መርካቶ እንዳትቃጠል የተከላከለ።

ከእለታት አንድ ቀን ያን አሻግሬ የሚገኝበትን ሻይ ቤት ስፈልግ ውዬና አምሽቼ፥ ድክም ብሎኝ ማደሪያ ስፈልግ፥ ሰዓት እላፊ ደረሰብኝና እራሴን ከቀበሌ ዘበኞች ለማስመለጥ ስደናበር፥ አንድ ግቢ ውስጥ ገባሁ። እንዳጋጣሚ ሆኖ በዝቅተኛ ዋጋ የሚከራይ ትርፍ አልጋ ነበር። ወዲያው ተኛሁና ልዩ የህልም አለም ውስጥ ገባሁ። ጧት ብንን ስል ከጧቱ ሁለት ሰዓት ሆኖ ነበር። እንደ ዛሬም ታላቅ እረፍት ተሰምቶኝ አያውቅም አልኩና፥ በልቤ ተመስገን፥ ተመስገን፥ ተመስገን እያልኩ ወጣሁ።

አሁንም ያ ከአሻግሬ ጋር የምንገናኝበትን ሻይ ቤት ላገኘው አልቻልኩም። ምን እንደሰወረብኝ ሊገባኝ አልቻለም። ያ ከሩቅ ይታየኝ የነበረ ገላጣ ሜዳ፥ ከመሃሉ ስሙን አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሚሉት ቤተ ክርስቲያን፤ በሁለት አገር መካከል ወሰን - ድንበር ሆኖ እንደተተከለ፥ ጥሩ ምልክት ሆኖልኝ ነበር። ቁም፤ ካገር ድንበር ደርሰሃልና ወደዛ አትሂድ ብሎ የሚከለክለኝ ይህ ቤተ ክርስቲያን ነበር። አሁን ግን፥ ወዲያ ብሄድ ወዲህ ብመጣ፥ ይህ ቤተ ክርስቲያን አልታይ አለኝ ("ተሰወረብኝ")፤ ምልክት የሚሆነኝንም አጣሁ።

አሻግሬን አግኝቼው፥ የተቋረጠውን የኢሕአፓ ግንኙነት መሥርቼ ከታጋይ ጓዶቼ ጋር የምገናኝበትን መንገድ ሁሉ በተስፋ እያሰላሰልኩ ብዙ ቀናት አለፉ። ይህ የማይጨበጥ ተስፋ ከቀን ወደ ቀን አስጨናቂ እየሆነ መጣ።

በችግር ጊዜ ስለ እግዚአብሔር መኖር ወይም አለመኖር ማሰብ አይቀርም። ግን፥ በጭንቅላቴ ከማይጠፋው የአንጃዎች ርዕዮት፥ የኢሕአፓ ግትረኛነት፥ እና ሌሎችም የሚታሰቡ ሃሳቦች ሁሉ ጋር ተደባልቆ፥ ከቀበሌ ዘበኞች ማሳደድ ጋር፥ ከመርካቶ ትርምስና የድብብቆሽ ኑሮ ጋር፥ ከእውነታና ከቅዠት ጋር፥ ጤንነትን ማጣት ተጨምሮ፥ አጠቃላይ ሁኔታውና ትርምሱ ጭንቅላቴን አደነዘዘው።

መሄጃ አጥቼ ተደነባበርኩ፤ ያለሁበትንም አላወቅሁት። በጭንቀት ተወጥሬ ሳለሁ፥ ተስፋ የተሞላበትና ደስ የሚል ስሜት በሰውነቴ ይሰራጫል፤ ምክንያቱ ምን እንደሆን ሊገባኝ አይችልም። የሰው ልጅ ሰውነቱ ሲጎዳ ደስ ይለዋል እንዴ? እኔ ሁለት ነኝ። አንደኛው እኔ ሲከፋኝ፥ ሌላኛው የእኔነቴ "ተቀናቃኝ" ደስ ይለዋል።

ወይ ጉድ! ጀግንነትና ፍርኃት በውስጤ ይደበላለቁብኛል፤ ክፋትና ደግነትም በአንድነት ይወሩኛል። በፍልስፍና ውስጥ ስምጥ ያልኩ እንደሆነ፥ ቶሎ ብዬ ሌላ አለም ውስጥ እገባለሁ። ያለሁበትንም ነገረኛና ነትራካ አለም በውስጣዊ የአዎንታዊነት ተስፋ እለውጠዋለሁ።

ይህ ሥፍራ (መርካቶ) የድሃ ልብስ የለበሱ ሰዎች ብዙ ብሮች ከኪሶቻቸው እየመዘዙ ለሚጠቀሙባቸው ሰዎች ሲያከፋፍሉ የሚታይበት ሥፍራ ነው። ሃብታሞቹ እንደ ተንቀሳቃሽ ባንክ ቤት ሆነዋል። ባለ ገንዘብ ሳይሆን፥ ሥራ የሚከበርበት፤ ገንዘብ መነገጃ፥ መጠቃቀሚያ፥ ኑሮን በጋራ ማሻሻያ እንጂ፥ በሰዎች መካከል ከፍና ዝቅን ፈጥሮ፥ የሌለው ካለው የሚሰግድበት ሥፍራ አይመስልም።

ግን በሌላ በኩል ደግሞ፥ ፍቅር ከድሃው እስከ ሃብታሙ ድረስ ካለ ምንም ይሉኝታና እፍረት፥ በነፃነት ሲንሸራሸር አላይም። ታዲያ ይህ ተለዋዋጭ ሁለት መልክ ከየት መጣ?

አብዮታዊው ትግላችን ጠቅላላ ኢትዮጵያን ነጻ ለማውጣት መሆኑን እየዘነጋሁ፥ ባካባቢዬ ላይ ብቻ በማተኮሬ፥ የሃሳብ ውዥንብር ውስጥ ገብቼ በሆዴ ብዙ - ብዙ የምለፈልፍ ወሬኛ ሆኛለሁ።

ምንም ይሁን ምን፥ በውስጤ ያለውን እውነት የሚያንጸባርቅ ኃይል፥ እኔንም ጥሎ እንደማይጥለኝ አውቀዋለሁና፤ በአይምሮዬ ብቻ ስኖር የሥጋዬንም መጎዳት እንድረሳው ያደርገኛል። በልቤ የቀረጽኳቸውን ጥሩ ጥሩ መጽናኛ ሃሳቦችን እደጋግማለሁ። ብዙውን ጊዜ በሰዎች የማይታሰቡ ስለሆነ፥ የተለዩ "ሰማያዊ" ሃሳቦች ናቸው ልበል? "ባካባቢዬ ሰው ባይኖር ኖሮ፥ የኔው አለም ለራሴ እንዴት ባማረልኝ ነበር!" እያልኩ፥ እራሴን በራሴ የማታልልበት ሃሳብ እየፈጠርኩና እያባዛሁ ብዙ መቆየት ቻልኩ።

በበኩሌ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ለማድረግ ባላቃተኝ ነበር። ግን ምንም አይደል፤ በእውነት መቆየት የምችለውን ያህል እቆያለሁ እንጂ፥ ላገሬ ሕዝብ የገባሁትን ቃል ኪዳን ለሥጋዬ ብዬ በውሸት አልለውጠውም። አስተሳሰቤ ከራስ ወዳድነት ጋራ የሚጣላ ነውና፤ ሞት ጠሪ መሆኔንም እያወቅሁት፥ ወደ ጤነኛ ሰው ተጠግቼ ሞት አልጋብዝም። ካለ አጃቢ ብቻዬን እሞታለሁ እንጂ፥ ሌሎችን አላስቸግርም። እንደገና ወደ ቀበሌዬ ተመልሼ ነፍሴን ያብዮት ጠባቂ መጫወቻ አላደርጋትም። እነርሱም "እኛ

አጋልጧል ብለን ስንፈታው፥ ለካስ ቀንደኛ የኢሕአፓ አባል ሆኖ ተገኘ! ወይ ጉድ! በሬ ካራጁ የሚባለው ተረት በኛ ላይ ደረሰ እኮ!" ብለው፥ ቀጥቅጠው ይገድሉኛል። ስለዚህ፥ ቢከፋም ቢለማም ከመርካቶ የተሻለ ሥፍራ ስለሌለ፥ ከዚሁ ከርሜና ሰንብቼ እድሌን መሞከር ነው ያለኝ ምርጫ።

**<u>የብቸኛ ወሬ</u>**

አይምሮዬ ባንድ በኩል የራሱን ጤንነት ለመጠበቅ ሲል ይታገላል፤ ግን ለሰውነቴ የሚጠቅመውን መምከር አቃተው። አንተ እንቅልፍ የማይወስድህ አይምሮዬ፥ በጭንቅላት ሕዋሳት ስትንቀሳቀስ እንዳሻህ ስሜቶችን የምትሰርጽ፥ አንተ በጉልበትህ አብራኮችን የምትገዛ፥ እስቲ ምን አለህ የምትነግረኝ?...ምን አለህ የምትነግረኝ ብዬ ጥያቄ አበዛሁ።

የሰው ህመሙ ምንድነው? የገዛ ፍጥረቱ አተኩሶ በሽታ ሲሆነው፤ ተስፋ የቆረጠውም መኖሩን ሲያስጠላው። አይ! ሰው መሆን ማለት ግን፥ ተሸካሚ ሥጋን ማሰማመር፥ ካለ ምንም ፍርኃት ወደ ጎዳና ወጥቶ፥ ደረትን ሰፋ አድርጎ፥ ከአፍ የሚወጣውንም ወደ ጆሮ ከሚገባው ጋር አስተካክሎ መናገር፤ መጫወት፤ ምንጊዜም እያስመሰሉ መኖር፤ ፊትን ኮስተር፥ ፈገግ፥ ሳቅ፥ ቆጣ ማድረግ፤ ተንቀሳቅሶ ወደሞት የሚያደርስ ጉስቁልና ውስጥ መግባት፤ ቆሞ ሰለማያውቁት ነገር ጸንቶ መጠበቅና መሰልቸት፤ ቁጭ በማለት ሰውነትን ማቁሰል፤ በመተኛትም በሌላኛው አለም (ቅዠቶች) ከተንኮለኞች ለማምለጥ መሮጥ ሲሆን፥ ይህን ሁሉ ዕዳ የተሸከመውን ሰው ምድራችን የምትታቀፈውን ሰው እርሷ ራሷ እያንገዋለለች ርጋፊውን ትጥላለች።

አልሞትኩም እንጂ፥ ምድር እኔን አንገዋላ ጥላኛለች። ዘመዶች፥ ጓደኞችና የሚያውቁኝ ሁሉ ይህ ጨካኝ፥ እራሱን ደበቀብን እያሉ ይንጫጫሉ። እኔም "ሰው በምክንያት ይለወጣልና፤ ከእንግዲህ ምድቤ ያልታወቀ፤ እኔ ዛሬና ነገ፥ ምንጊዜም የምደበቅ ሰው ነኝ። የምደበቀውም በአይምሮዬ ውስጥ ካሉ ደጋግ ሰዎች መካከል ነው። ደግነታችሁ ለሰማይ ቤት ይቆየኛል እያልኩ፥ ከቀን ወደ ቀን ሞቴን የምጠባበቅ እኔ፤ ከእንግዲህ ልክ እናንተ እንደምታውቁኝ እሆንላችሁ ዘንድ የማይቻለኝ ሆኛለሁ፤ እባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ....." በማለት በሃሳቤ ተማጸንኩ።

ሰው ሲጨነቅ ሃሳብ ያበዛል፤ አንጎልም ሊሸከም የሚችለው የሃሳብ መጠን የተወሰነ ነው። ሰው የጉልበት ሥራ ሲሠራ እንደሚደክመው ድክም ይለውና፤ የመሰልቸት ሥራን ሲሠራ የማይታሰበውን ሁሉ ያስባል።

ሙታን የሚባሉ ሰማያዊ ሕያዋን ካጠገብህ አሉልህ የሚል "ድብቅ እውነታ" ውስጥ ገባሁ። ርህሩህ የሴት አያቴ ሥጋቸው ቢሞት፥ መንፈሳቸው አልሞተም

አልኩና፤ ባንድ በኩል፥ ወደርሳቸው መጠጋትና ከርሳቸው ጋር መሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ፥ እስከዛውም ጊዜ ድረስም ቢሆን እርዳታ እንዳገኝና ከዚህ ማጥ ውስጥ እንዲያወጡኝ ፈለግሁና ተጣራሁ። የልቤ መጣራት በአፌም ጩኸትን ቢያወጣ፥ በመርካቶ ካለ ጩኸት ሁሉ የኔ ጩኸት ከመሬት አልፎ ሰማይ ላይ ይወጣ ነበር ብዬ እገምታለሁ።

ባንድ በኩል “ሕይወት ያለው ከዚህ ነው፤ ያ ያለህበት የውሸት አለም ስለሆነ፥ ተወውና ና! እዚህ አብረን እንኖራለን።” በሌላ በኩል ደግሞ፥ “አይዞህ ካጠገብህ ሆኜ እረዳሃለሁ” የሚሉኝ እየመሰለኝ፤ በምድር ላይ ተንከባክበው እንዳሳደጉኝ አሁንም በጭንቀቴ እንዲደርሱልኝ አጥብቄ ለመንኳቸው። ለጩኸቴ ምንም መልስ ባለማግኘቴ፥ ጩኸቴን አቁሜ ራሴን ማዳመጡ ነው የሚሻለው በማለት እራሴን አጽናናሁ። አይምሮዬ የራሱን ጤንነት ለመጠበቅ ሲል ከስሜታዊነቴ ጋር ይታገላል።

እስቲ ልቦናዬን መለስ ላድርገውና እራሴን ልመልከት በሚል ሃሳብ ውስጥ ተጠምጄ ሳለሁ፥ የልጅነቴ ትዝ አለኝ።

ከእለታት አንድ ቀን፥ ሁለት ሴቶች ተጣልተው ሲሰዳደቡ ቆሜ እመለከት ነበር። መሰዳደቡ እየተባባሰ ሲሄድ፥ የሁለቱ መጯጯህ እኔን በድንጋጤ ተገትሬ እንድቆም አደረገኝ። በድንጋጤ ላይ እንዳለሁ፥ አንደኛዋ ሌላዋን አይኗ ላይ ቢላዋ ስትተክልባት ተመለከትሁ። የተጠቂዋ ደም ከአይኗ ጀምሮ ወደ ሰውነቷ ሲወርድ ተመለከትሁ። እንዲህ አይነት ጭካኔ በልጅነቴ አይቻለሁ። ከዚያን ቀን ጀምሮ የሰው ልጅ በውስጡ የአውሬነትም ጠባይ እንዳለው ተገንዝቤአለሁ።

በዚህ አለም ላይ መኖሬ፥ ይህን በልጅነት አይምሮ የተቀረጸ አሳዛኝ ትእይንት አብራራልኝ፤ በጉልህ በተደጋጋሚ እንድመለከተውም አደረገኝ። ይህንኑ አይነት ትርእይት ሳይ ነው የቆየሁት። አዎ! ዘመን አለፈና፥ አይምሮዬ ጎለመሰና፥ ሰውነቴ አደገና፥ አይኖቼም ቦግ ቦግ አሉና፤ በወጣትነቴ የሚከተለውን ለማየት በቃሁ።

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሴት ወንድሞቿ ሁሉ በደርግ ተገድለው አንዱ ሲቀር፥ የዚህን የመጨረሺያውን ታናሽ ወንድሟን ከመንገድ አስፋልቱ ላይ ተጥሎ ተመለከተች። ወዲያውም ሮጣ ከሬሳው ዘንድ ስትደርስ፥ የወንደሟ ደም ኮለል ብሎ ባስፋልቱ ላይ ሲፈስ ተመለከተች፤ ውሾችም ወደ ደሙ ተጠጉ። የወንድሜን ደም ውሻ ከሚልሰው ብላ ነው መሰለኝ፥ ከደሙ ላይ እንዘፍ ብላ ወደቀች። ሁለት እጆቿን ዘርግታ ከዚያው በደረቷ ተኛች።

ቆይቶ የቀበሌ ዘበኞች መጡና፥ “ቀንደኛ ጸረ አብዮተኛ” እያሉ፥ እያዳፉ ከነ ደሟ ከእስር ቤት አስገቧት። ይህቺም ሴት ልጅ አልፎ አልፎ ጭንቅላቷን ወዝወዝ

ወዝወዝ ያደርጋታል። ድንጋጤ ለዚህ አበቃት። አንዳንድ ሰዎች “የወንድሟን ደም ውሻ ከሚልሰው ብላ፥ እሷው ራሷ ልሳ ነው እንዲህ የሆነችው” ይላሉ።

ታዲያ፥ እህ! ደስ ደስ የሚለው ብቻ አይደለም እኮ የኢትዮጵያችን ታሪክ፤ እንዲህ የሰውን የአውሬነት ጠባይ የሚገልጸውም ጭምር ነው እንጂ። በሁላችን ላይ የመጣ መዓት ከጠባዮቻችን ጋር ተደምሮ እኛን ጎዳን።

ትንፋሽ ሲቋረጥ፥ ከአንድ ሕይወት ወደሌላ ሕይወት፥

ልጆቿን ሁሉ ከደጃፏ ገድለው ሲጨርሱባት፥

አብዳ፥ ጨርቋን ጥላ በአውራ ጎዳና ስትንከራተት፥

ያቻትና እኮ! በሥጋዋ የሞተችዋ ሴት፥

እስከ ዘለአለም የምትኖር የፍቅር ባለቤት፥

እህት፥ እናት፥ በኢትዮጵያችን ውስጥ፥

ወንድም፥ አባት፥ በጉልበተኛው ሲረገጥ፥

ቀን አልፎ ቀን ሲተካ፥

ማነው ባለ ታሪክ፥ ስሙ የገነነ፥

ከሞት ብቻ ሳይሆን ከእብደትም የዳነ።

በየቀበሌው ያየሁት ድብደባ በአይምሮዬ ውስጥ ተቀርጾ፥ እየቆጠቆጠኝ ለዘለአለም እንዳይቀመጥ፥ በውስጤ የሚገፋፋኝ መንፈስ ይህንን እንድጽፍ አደረገኝ።

በሥጋ ሰውነቱ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ አለው የሚባል ይህ ሰው የተባለ ፍጡር እንደ አህያ መደብደብ የለበትም ነበር። ሰውን ሰው ሲመታው እግዚአብሔርንም አብሮ እንደመታው ይቆጠራል። ሰው በሰው ላይ እጁን ካሳረፈ ጨካኝ አውሬ መሆኑ ነው። ህያው ፍጡርን፥ ሰውንም ሆነ እንስሳን ማሰቃየት በተፈጥሮ ላይ ጥላቻን መግለጽ፥ የእግዚአብሔርንም ድንቅ ሥራ መንቀፍ ነው።

ሰው በሥጋው ሲያዩት ሁሉም ተመጣጣኝ ሰውነት ነው ያለው። የሁለት ግለሰቦች ነፍስ ሚዛኑ ሲታይ፥ ያንዱ እንደ አንበሳ ነፍስ አይነት ይሆንና፥ የሌላው ደግሞ የዶሮ ነፍስ አይነት ይመስላል (በአይን የማይታይ የነፍስ ክብደት)። ሰውን በቁመናውና በመልኩ ሲመለከቱት፥ ሁሉም አንድ አይነት ይመስላል። ግን አንዱን ሰው እንደ አለት ከባድ፥ ሌላውን ደግሞ እንደ ዶሮ ላባ ቀላል የሚያደርግ፤ ማነው ይህንን ለሰው የማይታይ (የተደበቀ) ነገር - ከሰው ሚዛናዊ አስተሳሰብ ጋር የተዛመደ የሰው ጠባይ ከበላይ ሆኖ የሚመለከት?

ሰው ለራሱ እውነት የሚለውን ሁሉ (ጠቅላላ ህልውናውን) ይህች ቀውስ ምድር ሳያስበው ግልብጥ ልታደርግበት ትችላለች። የራሱን እውነት በዚች የእውነትና ውሸት ዲቃላ በሆነች ምድር የፈተነ ሰው እራሱን ለአደጋ ያጋልጣል።

እውነት እውነት ስለሆነ ዘለአለማዊ ነው፤ ውሸትም ውሸት ስለሆነ ጊዜያዊ ነው። ታዲያ፥ ሰው ለዘለአለም የማይኖረው በተፈጥሮው ውሸት ስላለበት አይደለም እንዴ?

አዎ! ልክ ነው። ለዚህ ማስረጃው፥ የሰው ልጅ ከተፈጠረ (ከተወለደ) ጀምሮ ትንሽ ትንሽ እየሞተ፥ ትንሽ ትንሽ ይኖራል። ነገር ግን ከእውነትና ውሸት አንዱ ማሸነፍ ስላለበት ከብዙ ትንንቅ በኋላ፥ በሥጋ ሞት ዘለአለማዊ ሕይወት ያቸንፋል፤ ሥፍራውን ለፍጹማዊና ዘለአለማዊ እውነት ለቀቀ ማለት ነው። ስለዚህ በምድር መኖር ማለት፥ በጊዜያዊ ውሸት እየተወጠሩ፥ በዘለአለማዊ እውነት መሰንበት መሆን አለበት።

ሰው ሲሞት፥ እውነት ከሙታን ተለይቶ ሲወጣ፥ ሥጋና ውሸት አብረው ሲቀበሩ፥ የሚያዝኑና የሚያለቅሱ ሰዎች በሞተው ውስጥ የነበረ እውነት እየታያቸው "የታለ እውነት? የታለ እውነት? ወዴት ሄደ?" እያሉ ያለቅሳሉ። በጣም የሚያዝኑትን "እገሌ አልቃሻ ነው" ማለት ትክክል አይሆንም። ምክንያቱም ያ አልቃሻ የተባለው ሰው የቅርብ ወዳጁ ሲለየው፥ ለርሱ የሚታየው የሟቹ እውነት ለሌላው ላይታይ ይችላል።

ከሥጋ ቁስል በስተጀርባ፥ የሰው ሃዘኑ "መንፈሳዊ መልክ" ሲያወጣ፥ ከሰው እድሜ በላይ ለሚኖረው መንፈሳዊ ሰብአዊነትም መልክ መስጠቱ ይቀራል? ጥንትም ሆነ አሁን፥ በአለም ዙሪያ ከሚኖሩ ሰዎች መካከል፥ እንዲህ አድርጌ ገደልኩት እያሉ የሚያወጉ "ጀግኖች" ብዙዎች ናቸው። እንደዚህ አድርጎ ገደለኝ ብሎ የሚያወራ ግን አንድ አይገኝም። ለምን? - ሞቷላ! - ሞቷል እንዴ!

ከሞት ቢተርፉም፥ በአለንጋ ተሰንጥቆ - ተቆርጦ ቆዳቸው፥
እንደ ታረሰ መሬት መልክ (ከታራ) አውጥቷል ጀርባቸው።
ይህን እና የመሳሰለውን ሁሉ ታሪክ ባይመዘግበው፥
ምድሪቱ በውስጧ የተፈጸመውን አይታና ሰምታ ዝም አትል፤
ሰንበር - ጠባሳው - ምልክቱ ይናገራል፤
የፈሰሰው ደም ይመሰክራል፤
ከታሪክም በላይ ታሪክ፥ ከትዝታም በላይ ትዝታ፥
እስቲ ስለ አንዲት ወጣት ልጃገረድ ጥቂት እናውራ ላንድአፍታ።

ቀይ ቀለም ከብሩሽ ጋር በጉያዋ ሸጉጣ፥
ነጠላ ተከናንባ ከቤቷ ስትወጣ፥
የቀበሌው ዘበኛ ጠብ መንጃውን አንግቶ፥
የአውሬ አደን እንዳይመስልበትም ሰግቶ፥
ቀስ እያለ፥ ተከትሎ፥ መሄጃዋን አጣርቶ፥
ጓደኛዋም ብቅ ስትል አይቶ፥
ሥራ እንዳይበዛበትም ፈርቶ፥
ሁለት ሆነው ተገናኝተው ሲቀርቡ ከግርግዳው፥
ቀለሞቻቸውን ከጉያቸው አውጥተው፥
የኢሕአፓን መፈክሮች ሲጽፉ ባንድነት ተባብረው፥
ክንዱን አነሳ፥ አስተካከለ አፈሙዙን፥
ቃታውን ሊስብ አሾልኮ ጣቱን፤
በል  በል ሲለው እርኩስ መንፈስ በፍጥነት፥
ሳያስበው ሹልክ አለ ጥይት፤
አንዷን ከሩቁ አደባያት - ገደላት - አሳ..ረ..ፋት።
ያቺ ትንሽ ወጣት ወዲያው ስትል ድፍት፥
ሰውዬውም ከሁለት ተከፍሎ በድንጋጤ ጭንቀት፥
ሲታየው የወደፊቱ ጸጸት፥
የገዛ መንፈሱ ሲነግረው፥ በማያውቀው ገብቶ የሠራውን ስህተት፥
ቶሎ ቶሎ አሰበ፥ አሁንም ለርሱ ሥራ እንዳይበዛበት።
በሩጫ ወደ ጓደኛዋ ተጠግቶ፥
እንዲህ ሲል መከረ፥ በድንጋጤ ተርበትብቶ፥
“ጓደኛሽ ስትገደል፥
አንቺ ሸሽተሽ አታመልጪም?
ደግሞስ ይህን የምትጽፊውን አታቆሚም?
አቁሚ ብዬሻለሁ፥ አንቺንም ሳላቃጥልሽ!
ተነስተሽ ሂጂ ሳልገድልሽ።”
ምንም ቢላት፥ በቁጣም መልክ ቢመክራት፥

በፍርኃት ተንቀጥቅጣ መሮጥ አቅቷት፥
ከዛው ቁጭ ብላ መጻፏን ቀጠለች፥
"ኢ.ኢ.ኢ.ጎ.ቴ!.....ጽ.ሑ.ፌ.ን ስ.ጨ.ር.ስ ት.ገ.ድ.ለ.ኛ.ለ.ህ!" እያለች።

አይደለምንዴ?
ይህ ባይናችን ያየነው፥
ካድሬዎች ካድር ባዮች ጋር ተወዳጅተው፥
ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቷቸው፥
ደም ከጠማው ንጉሣቸው፥
የሰው ደም አርከፍክፈው በየቀዬው፥
ሲፈነጥዙ በከተማው፤
አባት ከሞት የተረፉትን ሲቆጥር፥
እናት ከቤቷ ደጃፍ ተገድሎ የተጣለ ልጇን ታቅፋው ስትዞር፥
በድን ሲሆንባት የማይናገር፥
እርሷም በድን ሆና ስትቀር..።

አዬዬዬ... አዬ..ዬ...ዬ ..ሆይ! ..
አለ ወይ! አለ ወይ፥ አለ ወይ!
ተመልካች ከላይ! ...ተመልካች ከሰማይ!
በምድር የሚሠራውን ግፍ ሁሉ የሚያይ።
አለ ወይ! ተመልካች ከላይ! ተ..መልካች ከ..ላ....ይ!
ተ..መልካች ከ..ሰ..ማይ።

አይኖቼ የተመለከተልኝ ክፉ ክፉውን ብቻ ከሆነ፥ እዚህ ላይ ልግታው በማለት፥ ጭንቅላቴን ወደተለየ አቅጣጫ አዘነበልኩትና የብቸኛ ወሬዬን ትንሽ ቀጠልኩ፤ እንዲህም አልኩ። ከልጅነቴ ጀምሮ ያየሁት የሰውን ልጅ ክፋት ብቻ ነው ብዬ አልዋሽም።

ከእለታት አንድ ቀን በልጅነቴ፥ እጅግ ርቦኝ ሳለ፥ በጎርጓዳ ሳህን ብዙ የስኳር ድንች (ሚጣጢስ) ቀረበልኝ። እኔም ሆዴ ጥግብ እስኪል ድረስ በላሁና የሚቀጥለውን አሰብኩ፡- "ወይ ጉድ! እንዲህ የሚጣፍጥ ነገር እስከዛሬም በልቼ አካውቅ። ከመጣፈጡም በላይ ሆድን ጥግብ ማድረጉ። ለመሆኑ ከዚህ የተሻለ ምግብ በአለም ላይ ይገኛል? ለንጉሡ በየቀኑ የሚያቀርቡላቸው ምግብ ይህን ሳይሆን አይቀርም።"

ይህ በልጅነቴ ያሰብኩት ነው። ይህን በማሰብ፥ በዚች ትንሽ ነገር ሕይወቴን ያስደሰትኩበት ጊዜ ነበር ለማለት ስል ተናገርኩ። አዎ! በዚህ አለም ላይ መኖሬ ይህን በልጅነት አይምሮ የተቀረጸ ደስ የሚል ትእይንት አብራራልኝ፤ በጉልህ በተደጋጋሚ እንድመለከትም አደረገኝ፤ ሰዎችም በምግብ ሲደሰቱ አየሁ። አዎ! ዘመን አለፈና፥ አይምሮዬ ጎለመሰና፥ ሰውነቴ አደገና፥ አይኖቼም ቦግ - ቦግ አሉና፤ በወጣትነቴ የሚከተለውን ለማየት በቃሁ።

የዚህ አለም ሕዝቦች መደሰቻ ብዙ - ብዙ ነገር እያለ፥ የኢትዮጵያ ሠፊው ሕዝብ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ለስኳር ድንች (ለሆድ) ብቻ ሆኗል።

ከፈላስፋው ከኤንጀልስ ዳስ ካፒታል ከተባለው የኢኮኖሚ መጽሐፉ፥ የሚከተለውን የኤንጀልስ ሕግ አስታውሳለሁ። “ድሃ ሰው በደኸየ ቁጥር፥ አብዛኛውን ገንዘቡን (ጊዜውንም) የሚያጠፋው ለሆዱ ብቻ ይሆናል።”

ኑሮአችን ለሆዳችን ብቻ ከሆነ (ሥጋን ለማደለብ) ምንድነው የመኖር ትርጉሙ? ምንድነው ምድራዊ ሕይወት ማለት? መኖር ላለመሞት የሚደረግ ትግል ብቻ ሆኖ ከቀረ። እህ! ሥጋን ለማደለብ ሳይሆን፥ ነፍስና ሥጋ እንዳይላቀቁ የደከሙት ወገኖቼ ትዝ አሉኝ።

በደረቅ አይኔ የተመለከትኳቸውና ፎተግራፍ ያነሳኋቸው፥ በአፋር በረሃዎችና በወሎ ሸለቆዎች የሞቱትንና ለሞት የተዘጋጁትን ሁሉ አሰብኳቸው። ግን ይህንን ሳስብ፥ አይምሮዬ የትላንትናውን ከዛሬው፥ የዛሬውንም ከወደፊቱ ጋር እያመሳጠረ ቢሆን፥ እኔ ልከላከለው አልችልም። ስለዚህ፥ በጊዜ ውስጥ እንደ ጥላ የሚያልፍ ትእይንት ሁሉ በውስጡ ተስፋ እንደሌለው፥ እንደ ጨለማ ብቻ እንዳይሆን ይህንን ከዚህ ልግታው።

አዎ! ሲነገር በጥቅሉ፥ እንዲህ ይመስላል - ነበረ ማለታችን፥

ያለፈው እንዲሁም የወደፊቱን ሲያሳስበን፥

በየቀኑ በረሃብ ፍንግል እያሉ ሲሞቱ የሚታዩንን፥

ስናስተውል - አሮጊት፥ ሽማግሌ፥ ሕጻናት ሁሉ ማለቃቸውን፤

እኛ ተስፋ የሚኖረን፥

ከላይ ሆኖ በሚጠብቀን በአምላካችን።

አይምሮም የራሱ አለም አለው። በውስጡ የሚከፈትና የሚዘጋ በር የለም፤ መጥፎ ለሚያስብ የአይምሮው ክፍል ክዳን አልተበጀለትም። ግን ሰው በተፈጥሮው ጭ<u>ንቅ</u> ሲለው፥ ይህ ጭንቀት ምክንያታዊ መሆኑን ለመግለጽ ሲል፥ አይምሮ በሃሳብ ይቀሰቀስና፥ ከፉ ክፉውን ከተደበቀበት ጓዳ እያወጣ፥ ፊት ለፊት ይደረድረዋል።

"እንግዲህስ ይኸውልህ፤ ከጭንቀት ለመግባትህ በቂ ምክንያት አለህ...." ሲል አይምሮ ለራሱ ያስረዳዋል። ነገር ግን፥ ተስፋ የማይቆርጥ ሰው፥ መጥፎ መጥፎውን ያሳየኝ አይምሮዬ ጥሩ ጥሩውን ያሳየኛል በማለት በተስፋ ይጠባበቃል። እድለኛው "ጥሩ አይምሮ" ያለው፥ በተስፋ ሲኖር፥ አዎንታዊ ይሆንና፥ ጥሩ ጥሩውን ብቻ እያየ ይኖራል። እድለ ቢሱ "መጥፎ አይምሮ" ያለው፥ በተስፋ መቁረጥ ሲኖር፥ አሉታዊ ይሆንና፥ መጥፎ መጥፎውን ብቻ እያየ ይኖራል (እብደት የሚሉት አይነት)።

የሃይማኖት መሪዎች እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ እያሉ ይሰብካሉ። በገንዘብ በኩል የሚመጣ መበላለጥ ሳይቀር፥ የሆዳምነት ፍልስፍና ሳይጠፋ፤ የግለኝነት አስተሳሰብ ሳይደመሰስ፥ እውነተኛ ፍቅር ከየት ይመጣል? በመጀመሪያ የሆዳምነትን ፍልስፍና ማጥፋት ሞራላዊ ግዴታ እንደሆነ፥ እንዴት ይህንን የሃይማኖት ሰባኪዎች አይረዱትም?

ገንዘብ የሚፈጥረውን መበላለጥ ተፈጥሮአዊ የሚያስመስሉትም አሉ። ሰው ሁሉ መቶ በመቶ እኩል አለመሆኑን የማይገነዘብ የለም። እርግጥ ለመጠነኛ መበላለጥ ቅናት የሚያድርበት ሰው አይኖርም፤ ግን ፍቅርም የሚያካትተው መበላለጥ አለ፤ ፍቅርም የማያካትተው መበላለጥ ይኖራል። ታዲያ፥ ከልዩነቶቻችን ሁሉ ባሻገር፥ አንዱ በገንዘቡ እንደ መልአክ ሲከበር፥ ሌላውም በእጦቱ እንደ ውዳቂ ዕቃ ሲጣል፥ እንዴት በሰዎች መካከል ፍቅር ሊመሠረት ይቻላል? ይህስ መበላለጥ በሕብረተሰብና በአገር አቀፍ ደረጃ ተባብሶ ስለቆየ አይደለም እንዴ ጦርነትን ያስከተለው?

ከመጠን በላይ የሆነ መበላለጥን ለማጥፋትና በሰዎች መካከል ጤነኛ ሰብአዊ ግንኙነቶች ተመሥርቶ፥ ሰዎች እርስ በርስ እንዲፈቃቀሩና በሰላም እንዲኖሩ ለማድረግ ሲሉ ሕይወታቸውን ያጡ የኢሕአፓ ሰማዕታት፥ ከምድር ምንም ክብር አልጠበቁም፤ ከሰማይም የድካም ዋጋ ይከፈለናል ብለው አልተመኙም (ይህንንስ ጭራሽ አላሰቡትም)፤ በሙታን ትንሳኤ፥ በመንግስተ ሰማያትም መኖር የማያምኑ ናቸውና። ግን በመልካም መንፈሳቸው (በቀና አስተሳሰባቸው) ሰማያዊው እድል ፈንታቸው ከጻድቃኖቹ ጋር ይደምራቸው ይሆናል።

ሰውም በፍጥረቱ፥ አንዲት ለልጆቿ ሁሉ የምታስብ ደግ ምድር እናቱ፤ በዙሪያዋ የሚነፍስ ነፋስ አፍ አውጥቶ ቢያወራ፥ "ከጸብ ፍቅር ይበልጣል፤ ከስግብግብነት እርስ በርስ መተሳሰብ ይሻላል፤ ሰው እርስ በርሱ እንዳይተላለቅ፥ እናት ምድርም እንዳትጠፋ፥ ሰብአዊነት አይምሮ ገዝቶ፥ የሰዎችን ሁሉ ሰብአዊ መብት የሚያስከብርና የማያዳላ ስርዓት ቢመጣ ይሻላል" ትል ይሆናል።

በየመንገዱ የተረፈረፈው የሰው ሥጋ በመኪና እንደተጨፈለቀ ቲማቲም ሲቆጠር በማየቴ፥ የሞቱ ሰዎች መንፈሶቻቸው ከመጮህ የማያርፍ በመሆኑም ነው የምለፈልፈው (ይመስለኛል)።

እስትንፋሴ የነርሱን ጩኸት ያስተጋባል (ይመስለኛል)፤ የኢትዮጵያ ተራሮች ግን ይህን የሰው ጩኸት አያስተጋቡም። ጋዜጠኞች ባገር የሉም፤ በኢትዮጵያ ዙሪያ ምድር ሰው እንደሌለባት ባድማ ሆናለች። ሌላው አለም ስለ ኢትዮጵያ ወሬ አይደርሰውም። ቋሚዎች እውነቶቻቸውን በሚያንቀላፉ አይምሮአቸው ዘግተው ዝም ብለዋል (ረቂቅ የመኖር ፍልስፍና)።

አዎ! ሁለት ተቃራኒ የሆነ አስተሳሰብ ያላቸው “ኃያላን” ሰዎች አስተሳሰባቸውን ለሕብረተሰቡ ያስተጋቡ እንደሆነ፥ የአስተሳሰብ ወገናዊነትን ይመሠርታሉ። ከሁለቱ አስተሳሰብ ውጪ በገለልተኛነት የተቀመጡ፥ አይምሮአቸውን ከጭንቀት በማውጣት፥ ከዚች አለም ጋር ካለ ቅራኔ ለመኖር ሲሉ፥ ተፈጥሮን እየደለሉና እየተለማመጡ እድሜአቸውን ያራዝማሉ።

አንድ እውነተኛ ሰው ከምርምር እና ከሃሳብ ብዛት፥ ከሚያስበው እውነት እና ከራሱ እውነት በስተቀር የተቀረው አለም ትርጉም አልባ ይሆንበታል። እውነትን ፍለጋ ሰውነቱ (ሥጋው) የደከመ ግለሰብ፥ ወቀሳና ችግር ይደርስበታል፤ ደካሞች ሲዘባበቱበትና ሲያላግጡበት አካባቢውን መምሰል ያቅተዋል። የሰው ልጅ ሕሊና አርፎ የማይተኛ በመሆኑ፥ እውነት እየተዛባ ፍርድና ፍትህ ተጓድሎ ሰዎች ሲቸገሩ እየተመለከተ፥ በገለልተኝነት መኖር የሚያቅተው ሰው ለማንኛውም አደጋ እየተጋለጠ የእሳት እራት ይሆናል። አዎ! እውነት ያስፈራል፤ ህልውናም ያሳጣል።

ገለልተኛ የሆኑ ሰዎች “በማንኛውም የአስተሳሰብ አውታሮች (በፖለቲካ፥ በሃይማኖት፥ ወ.ዘ.ተ...) በሰዎች መካከል የተካረረ አስተሳሰብ እየተከሰተ፥ ሰዎችን እርስ በርስ ሲያጣላ እና ሲያጋድል፥ “ይህ የሕብረተሰብ በሽታ ነው፤ እኛ ከደሙ ንጹህ ነን” ይላሉ። ለነርሱ ደስ የሚሰኛቸውን አዱኛ (ምድራዊ ሃብት) ሁሉ እየሰበሰቡ፥ በደስተኛነት ይኖራሉ፤ አለም የነርሱ ናትና።

የሰው ልጅ ተፈጥሮው የእውነትና የውሸት ዲቃላ፥

ሥራው ብዙ፥ የማይወደድ፥ የማይጠላ።

ባለ ሥልጡን ሃቅ፥

እውነትን ከውሸት ደብለቅ፥

ትንሽ ትንሽ ማታለል፥ ትንሽ ትንሽ መስረቅ።

ከፊት ለፊት እውነት፥ ሃሰትም ከጉያ፥

ይህ ነው እውቀትና ፍልስፍና፥ ኑሮና ብልሃቱን ማስማሚያ፤
ሁሉን እንደያመጣጡ መቀበያ፥
የውሸት ሳቅ መደለያ።
ይህች ምድር የተጣመመ እውነት - የተቃና ውሸት የበዛባት፥
ያልጠራ ሕይወት፥ ግማሽ ጤንነት፥ ግማሽ እብደት።

**<u>ለወሬ ነጋሪ የተረፈ</u>**

መሠራት ያለበት ኃጢአት እንደሚሠራ ሁሉ፥ መወራት ያለበትም ወሬ መወራቱ፥ መጻፍም ያለበት መጻፉ አይቀርም። ግን ለምን? ኃጢአት ከተሠራ በኋላ ምን ይመጣል? ከተወራ፥ ከተጻፈስ በኋላ ምን ሊፈጠር? የሚሆነው ይሆናል ማለት ነው እንጂ፥ ስርየትን ለማግኘት ኃጢአት ሥሩ ባይባልም፥ ኃጢአት ተሠርቶ ሲያልቅ ግን ጥሩ ነገር መምጣቱ አይቀርም[7]። ማውራትና መጻፍ ግን ከራስ አልፎ ሌላውን የማያሳንስ ከሆነ፥ ምንም አይደል።

አዬዬ! ተጨናቂው አይምሮዬ በሰውነቴ አካሎች ሁሉ ከፍተኛ ቁጥጥር ለማድረግ አልቻለም። ከእለታት አንድ ቀን፥ በመሄድና በመንከራተት መካከል እንዳለሁ ቀኑ ጨለመና፤ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆነ። ከአንድ የግንብ አጥር አጠገብ ስደርስ፥ በመጥፎ ሽታ አካባቢን መበከላቸውን ከምንም እንደማይቆጥሩ ሰዎች ለመሆን ወሰንኩ። ግን በቅድሚያ ይህ የኔ ውሳኔ ትክክል መሆኑን እና አለመሆኑን ሳሰላስል ብዙ ቆየሁ። ጨለምለም ካለ ሥፍራ ቆሜአለሁ፤ ሰውም ባጠገቤ አያልፍ። ሽንቴን ላለመሽናት ምን እንደሚከለክለኝ አላወቅሁትም። አንድ ግለሰብ በሁለት ሃሳብ ሲወጠርና መወሰን ሲያቅተው፥ መረጃዎችን ወደአይምሮ የሚያስተላልፉ ነርቮች መረጃዎቹን በቶሎ እንዳያደርሱ በየመንገዱ እክል ሲያጋጥማቸው፥ አንጎል አስቦ ወቅታዊ ውሳኔ መስጠት ሲያቅተው፥ ይህ ሁኔታ የግለሰቡን ታማሚነት እንጂ፥ ጠባዩን ወይንም ማንነቱን አይደለም የሚያንጸባርቀው (ጊዜው ነው የታመመው ማለት ይቀላል)።

የቀበሌ ዘበኞች ከሩቅ አይተው ወደኔ ሲጠጉ ሃሳቤን ለውጬ ሳልሸና ሄድኩ። ቶሎ ብዬ በአንድ ታጣፊ መንገድ ዞር ብዬ ካቅራቢያዬ ከሚገኝ ሽይ ቤት ገባሁ። ከሰዎች መካከል ለብቻዬ ጨለም - ደበቅ ያለ ሥፍራ፥ ጠረቤዛ ይዤ ቁጭ አልኩ። ዘበኞቹም በር ላይ ቆመው፥ በአይኖቻቸው ቃኘት ቃኘት እያደረጉ ሲፈልጉኝ፥ እኔም በሃሳቤ "የናንተ የሥስታችሁም ደምወዝ ተደምሮ በአምስት ሲባዛ የሚከፈለኝ

[7] ይህ ሃሳብ ወደ አራተኛው መጽሐፍ ዞሯል።

የመንግሥት ሠራተኛ ነበርኩኝ፤ ሥራዬን ጥዬ ለናንተ በመታገሌ አታሳዱኝ፤ ሂዱ!...” ብዬ በሃሳቤ አባረርኳቸው፤ እነርሱም ሄዱ።

በቆራጥ ውሳኔ ይህን ጥብቅ ትእዛዝ ለማስተላለፍ የቻለው አንጎሌ ደስ አሰኘኝ፤ ግን ወዲያው ሊያስከፋኝ ነው። ዘበኞችን በሃሳብ የሚያባርር አይምሮዬ የፊኛዬን ንጭንጭ ሊቋቋመው አልቻለም። አይምሮዬም “ቆይ ትንሽ ረጋ በል፤ ቆይ ትንሽ ረጋ በል” እያለ የተለመደውን ትእዛዝ ከማስተላለፍ አላቋረጠም። ለይስሙላ አንድ ሻይ አዘዝኩ። ሻዩን ሲያይ በላዬ ላይ ሊጨምርብኝ ነው ብሎ ነው መሰለኝ፥ ፊኛዬ ተነፋ፤ ተወጥሮ ከፉኛ አሳመመኝ። ወዲያው በጭኖቼ መሃል ሙቀት ተሰማኝ።

ከሻዩ የተለየ እንፋሎት ከወደ ታች ወደ ላይ እየተነነ ወደ አፍንጫዬ ሲገባ፥ ምን መሆኑ ገባኝ። ተነፈስኩ፤ ግን ሌሎችን እንዳይሸታቸው፤ እንዲህ ያለውም ነውር ይፈጸማል ብለውም እንዳይጠራጠሩ፥ ሻዩን በጠረቤዛው ላይ አፈሰስኩት፤ ወደ ሱሬዬም እንዲዳረስ አድርጌ። ይህ ሁሉ ሲሆን፥ ለካስ የሻይ ቤቱ ሠራተኝ ይመለከተኝ ነበር። ቀስ ብሎ ወደኔ መጣ፤ ጠረቤዛውን ጠራረገልኝና እንደ እናት በመንከባከብ፥ “አይዞህ! አይዞህ..” እያለ አበረታታኝ። ሌላ ሻይ ሊያመጣልኝ ሲል “አይ በቃኝ” አልኩት።

መታመም አለመታመሙን ለይቶ የማያውቅ አይምሮዬ መረታቱን አውቋልና፤ እስካሁን የተፈጸመው ሳይሆን የወደፊቱ ምን ይሆናል ብሎ ማሰላሰል ጀመረ። በማሰብ ብዛት ከባድ ድካም ላይ ስለሆነ፥ ዝም እንደማለት ብሎ፥ በቀሰስተኛ ድምጽ “መንገዱ ሁሉ ታጥሯልና፤ ያለው አማራጭ እራስን እንደማይፈለግ፥ እንደ አሮጌ እቃ ቆጥሮ መንገድ ላይ መጣል ነው” ይለኝ ጀመር።

ይህን እና የመሳሰለውን ሳስብ ከፍርኃትና ከድንጋጤ ጋር ላብ አጠመቀኝ፤ እራሴ ዞረብኝ (አዞረኝ)። የባሰ ሳይመጣ ከዚህ ልውጣ አልኩ። የሻዩን ዋጋ ከፍዬ ልወጣ ስል፥ የሻይ ቤቱ ሠራተኝ “ለፈሰሰ ሻይማ አትከፍልም” አለኝ። የጥንካሬ ምልክት በማሳየት እጁን ጭብጥ አደረገና፥ “አይዞህ በርታ” ብሎ፥ በድጋሚ በማበረታታት አሰናበተኝ።

ከሻይ ቤቱ በር ወጣ እንዳልኩ፥ ቆሞ መራመድ ተሳነኝ፣ እንደሰከረ ሰው መንገዳገድ ጀመርኩ። ራሴን እያመመ ያዞረኛል፤ አይኔም አላይ ብሎ እንደ እውር እደናበራለሁ። በዛ ላይ ጨልሟል። ያ “እራስን እንደማይፈለግ፥ እንደ አሮጌ እቃ ቆጥሮ መንገድ ላይ መጣል ነው ያለኝ አይምሮ ልክ ነው እንዴ?” አልኩ። ቢሆንም እንኳ፥ አካባቢው “በእኔ ብጤዎች” እጅግ የተጨናነቀ ስለሆነ፥ የሰው እንቅፋት ከመሆን በስተቀር፥ ራስን መጣያ ሥፍራ የለም። መራመድ ሲያቅት፥ መቀመጫያና ማረፊያም ሲጠፉ፥...ግርግዳ በመደገፍ እየቆምኩም፥ እያረፍኩም፥ እንደምንም ብዬ ብዙ

ተጓዝኩና ከአንድ በር ደጃፍ እንዘፍ አልኩ። አይኔ ባይለየውም፥ አይምሮዬም ባይገነዘበው፥ እድል ፈንታዬ ነው ከዛች ከደጓ ሴት በር ላይ የጣለኝ። ግባ ብላ አስገባችኝ።

አመጣጤ በጤናዬ አለመሆኑን በመረዳት፥ በተለየ የሃዘኔታ አቀባበል ተቀበለችኝ። ሁኔታዬ ሁሉ ቶሎ ስለገባት፥ "ሱሪህን አውልቅና ስጠኝ ልጠብልህ" ብላ አጠበችልኝና እንዲደርቅ ከወንበር ላይ ሰተረችው (አሰጣችው)፤ እጣቢውንም እንዳይሸት ከውጪ ራቅ አድርጋ ደፋች።

አዎ! በዚህ ምድር ላይም እንዲህ አይነት ደግነት ይሠራል። በሁለት ቦታ የተጠቀለሉ ብሮች ነበሩኝ። አንደኛው ነገ ጧት አውቶቡስ ጣቢያ ሄጄ ለኔና ለአሻግሬ የአውቶቡስ ቲኬት እንድገዛበት የታሰበ ይመስለኛል። ያለኝን ገንዘብ በጠቅላላ ባንድ ላይ አድርጌ፥ ሰዓቴንም ጭምር በካልሲ ውስጥ አስገብቼ፥ ካልሲውን ቋጠርኩና ከትራሱ ሥር አስቀመጥኩት፤ ጊዜው ሲመጣ ትወስደዋለች ብዬ።

የሰሞኑ እንቅልፍ እጦት አይኔ እንዳይከደን ማድረጉ ብቻ ሳይሆን፥ ሰውነቴንም አደንዝዞ ለመግደል የከጀለ ይመስላል። አይምሮዬ ግን "አንተ ከዳተኛ፥ አሻግሬ ቲኬቱን ለነገ ጧት እንድታደርስለት እየተጠባበቀህ አይደለም ያለው?" ይለኛል። በሌላ በኩል ደግሞ የቲኬቱ መገዛት ለምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም። የአውቶቡስ ጣቢያ መንገዱን ለማስታወስ ብሞክር፥ ምንም ምንም ትዝ ሊለኝ አልቻለም። ታዲያ አሁን ትንሽ እንቅልፍ ቢወስደኝ ይሻላል እላለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ እዛው አውቶቡስ ጣቢያ ካላደሩ ቲኬቱን መቁረጥ እንደማይቻል ይገባኛል። አውቶቡስ ጣቢያው የት ነው? ኮዱ መቼ ተሠራና???? ጺጋዬ ስለዚህ ጉዳይ ምን የነገረኝ አለ? ለመሆኑ እስከዛሬ የት ነበርኩ? ለምን ቀደም ብዬ ቲኬቱን አልቆረጥኩም? ለማንኛውም ትንሽ ጋደም ብዬ ስነቃ፥ ሴቲተን አቅጣጫ እጠይቃትና እሄዳለሁ" እያልኩ በሃሳብ ስንገላታ፥ መግለጽ በሚያስቸግር ስሜት ውስጥ ገባሁ።

የጭንቅላቴ መደንዘዝ ሁሉን ሃሳብ ሲዘጋብኝ፥ ቲኬት፥ ቲኬት፥ ቲኬት የምትለዋን ቃል ብቻ እንድትቆረቁረኝ ትቶልኛልና፤ ይህን ብቻ ሳሰላስል እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም። ሰውነቴ የመደንዘዝ በሽታ ይዞታል፤ ተኝቼ ሳለ፥ እግሮቼና እጆቼ ለብቻቸው ነፍስ ያወጡ ይመስል ብርግግ ብርግግ ይላሉ። አዛጋለሁ፤ አይኖቼም ክፍት ዝግት ይላሉ (ይመሰለኛል)። ከእንግዲህ ምንም ተስፋ እንደሌለኝ የተገነዘበው ልቦናዬ ሰውነቴን በቁጥጥሩ ለማዋል ባለመቻሉ፥ ለአንድ ላልታወቀ ኃይል አሳልፎ ሳይሰጠኝ አልቀረም። ራሴን ሳትኩ።

ባጠቃላይ የነበረኝ የበሽተኛ ምልክት ሴትዬዋን ሊያስተኛት አልቻለም፤ ፍርኃት ውስጥ ከተታት። ሰዓት እላፊ ደርሶ፥ ሰው ሁሉ በሩን ዘግቷል። ሴቲቱ "ምን

ሆንክ? ምን ሆንክ?” እያለች ትወተውተኛለች። ከኔ ምንም መልስ በማጣቷና ስለተጨነቀች፥ ጎረቤቶቿን ልትጠራ በሩን ከፍታ ወጣች።

ወዲያው ሴቶች ተሰባስበው እንደ ጉድ ይመለከቱኝ ጀመር። በዚህን ጊዜ አንዷ ሴት “ይህ ሰውዬ በእጃችን ላይ ቢሞት፥ ተጠያቂ የምንሆነው እኛ ሁላችንም ነን። ይልቅስ የቀበሌ ዘበኞች ጠርተን ቢወስዱልን ይሻላል” ስትል ሰማኋት።

ወዲያው ብድግ አልኩና፥ ኮቴንና በካልሲ የተጠቀለሉ ብሮቼን ትቼ፥ ጫማዬን በደረቁ አጠለቅሁና፥ ከፊቴ የተደረደሩትን ሴቶች በመጣስ ገፈታተርኳቸውና ሩጫ ጀመርኩ።

እንደ ፈራሁት የቀበሌ ዘበኞች ተከተሉኝ። ያቺ ደግ ሴትዮም ከሩቅ ሆና “በእንቅልፍ ልቡ ሊሆን ስለሚችል አታስደንግጡት” የምትል ይመስለኛል። የኔም ፍላጎት በአንድ በኩል ለማምለጥ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ተኩሰው እንዲገድሉኝ እንጂ፥ ይዘው እንዳያንገላቱኝ ስለሆነ፥ ጠጋ ሲሉ ስሮጥ፥ ራቅ ሲሉ ስቆም፥ በመርካቶ ጠባብ መንገዶች ስሽሎኮለክ፥ ባንድ በኩል እንደ ሌሊት ጅብ፥ በሌላ በኩል ደግሞ እውነተኛ ሰው የሆንኩትን እኔን ሳልሆን፥ ሌሊቱን በሙሉ ሳልቆም፥ ሳልቀመጥ፥ እንዲሁ በእንቅልፍ ትእይንት ስንቀሳቀስ ሌሊቱ ተገባደደ።

ከዛም፥ ሊነጋጋ ሲል፥ እንደመንቃትም ያልኩ ይመስለኛል፤ አንድ ሰው ግቢ ውስጥ ገባሁ። ለመደበቅ የምሞክር ይመስለኛል። የመርካቶ ድሆች መኖሪያ አካባቢ በመሆኑ፥ ለመጸዳጃ በእጅ የተቆፈረ ሰገራ ውስጥ አንድ እግሬ ድንገት ጥልቅ አለ። ሁለት እግሮቼን የሚከት ቢሆን ኖሮ፥ እዛው ጥልቅ ብዬ በቀረሁ ነበር። እግሬን ከሰገራው አወጣሁና ከጨለማው ሥፍራ ተደብቄ ቆየሁ።

የጸሐይ ጮራ ሲፈነጥቅና በግቢ ውስጥ ያለውን ቁሳቁስ ሁሉ ሲያሳይ፥ አንዲት ሴት ብቅ አለች። እስካሁን ድረስ ሴቶች አዳኞቼ ናቸው፤ ከሞትና አደጋ ይጠብቁኛል። ስለ ሁኔታዬ እንድትረዳና እንድታዝንልኝ ምንም ያደረግሁት ነገር አልነበረም። እርሷ ግን ስለ ሁኔታዬ ለመረዳት ደቂቃም አልፈጀባት። ወዲያው በባልዲ ውሃ አምጥታ በእግሬ ላይ አፈሰሰችልኝ፤ ማድረቂያ ጨርቅም አምጥታ ሰጠችኝ። ምናልባት ታወራኝም እንደሆነ ትዝ አይለኝም። በል እንዳይመጡብህ ከዚህ ተደበቅ የምትለኝ ይመስለኛል።

ይህች ሴት ደግነትን እንደምታሳየኝ ገብቶኛል። በጣቶቿ አፍንጫዋን ይዛ አልሸሸችኝም፤ ለኔ ውሃ ለማምጣት ስትል ተጣደፈች እንጂ። አፏን በጇ ይዛ አልታዘበችኝም፤ ለኔ ምክር ለመስጠት ስትል ለፈለፈች እንጂ።

የሴቶችን ደግነት ከልቤ እረዳዋለሁ፤ ሆኖም የሞተ ሰው ለማዳን በምታደርገው ጥረት አልተባበርኳትም። ፍርኃት ተደምሮ ተደማምሮ ድፍረትን

እንደሚያመጣ ሁሉ “ግድ የለም! ግድ የለም! እንደ ሌሎቹ ጓዶቼ ቀጥቅጠው ይግደሉኝ” ብዬ ቆረጥኩ።

በራሴው ቆራጥ ውሳኔ፥ ራሴን ለውጬ፥ ሌላ ሰው ሆንኩ፤ በሽታዬ ሁሉ ጠፋ፤ የኔ ፍርኃት ከዚህ ላይ አከተመ። በዚህ አለም ላይ የመኖርና የመታገል ተስፋዬንም ባጭሩና በጉልህ ለአለም ሕዝብ ለማሳየት ቆረጥሁ።

እስኪገድሉኝ ድረስ ልታገል፤ ለአብዮታዊው ድርጅቴ፥ ለኢሕአፓ ያለኝን ታማኝነት ዛሬ ላስመስክር። በዚች በቀረችኝ ሕይወቴ ኢሕአፓ ያቸንፋል እያልኩ ልጮህ። ይህ የመጨረሺያ ትግሌ ይሆናል። ይህ የአብዮታዊ ቅስቀሳ፥ ሰሚ ጆሮ ውስጥ ቢገባ፥ የሚያስብ የሕዝቦችንም የአይምሮ ህዋሳት ቢቀሰቀሰና በኔ ምትክ አንድ ሰው እንኳን ለኢሕአፓ ቢገባለት፥ ይህ ብቻ ከእኔ የሚተርፍ እውነት መኖሩን ያረጋግጣል (ቼ ጉቬራም ይህንኑ ነበር ያለው፡- “Whereever death might surprise us, it shall be welcomed, provided that this new battle crisis reach some receiptive ears, and that those other men come forward to intone our funeral dirge with staccato of machine gunes.”)። ይበቃኛል፤ ቅስቀሳዬን በዚሁ ልቀጥልና ዘበኞች ተኩሰው ይግድሉኝ።

በየመንገዱ የሚያጋጥመኝን ሰው ሁሉ ኢሕአፓ ያቸንፋል በሉ እያልኩ መጮህ ጀመርኩ። ትናንሽ ልጆችን እያስፈራራሁ በግድ ኢሕአፓ ያቸንፋል ማስባል ጀመርኩ። ይህ የመጨረሺያ የጣረ ሞት ትግል አስደሰተኝ። ብዙዎችን ኢሕአፓ ያቸንፋል አሰኘሁ።

የቀበሌ ዘበኞች ሲከተሉኝ እንዲገድሉኝ ብዬ ሮጥ ሮጥ እልባቸዋለሁ። ግን ተኩሰው አይገድሉኝም፥ ወይም አይይዙኝም። ከሩቅ ሆኜ ሳያቸው ከትናንሾቹ ልጆች ጋር ያወራሉ። “ያ ሰውዬ ምን አላችሁ?” ብለው ነው የሚጠይቋቸው። ልጆቹም፥ ዘበኞቹ ተኩሰው እንዳይገድሉኝ በማሰብ፥ “አብዮታችን ግቡን ይመታል ነው የሚለው፥” እያሉ የሚነግሯቸው ይመስለኛል።

ሮጬ ሮጬ ሲደክመኝ ከአንድ ሥፍራ ተገትሬ ቆምኩ፤ የቀበሌ ዘበኞቹ ባጠገቤ ሲያልፉ አየኋቸው፤ በዚህን ጊዜ የራሴ መኖርና አለመኖር አጠራጠረኝ። አንገቷን እንደተቀነጠሰች ዶሮ፥ መንፈሱ ከውስጡ አፈትልኮ እንደሄደበት፥ እንደ “አንድ ሰው ብቻ” ሆኜ በሥጋዬ ብቻ ቆምኩ፤ ማንም አላየኝ። ግራ ገባኝና እንዲህ አልኩ “እኔ ማነኝ? እኔ ማነኝ? በእግዚአብሔር ለማላምን አንድ አቴይስት፥ ከየት መጡ ልሙት ስል እንዳልሞት የሚከላከሉ መካእክት?

የቀበሌ ዘበኞች ለይተው አውቀውኛል፤ ግን የቀይ ሽብሩ በረድ ያለበት ጊዜ ስለነበር፥ እንደበፊቱ ሥራ አልበዛባቸውም። "የት ይሄዳል፥ የትስ ያመልጠናል" ብለው ይሆናል የተውኝ።

"በሌላ ቀን" ካለወትሯቸው ከፉኛ ተከታተሉኝ፤ አሁንስ የሚለቁኝም አልመሰለኝ። በተለያዩ እቅጣጫዎች ሲያጠምዱብኝ፥ መሄጃ አጥቼ፥ ከአንድ የቤት ጣሪያ ላይ ወጣሁ፤ እንዴትም ጣሪያ ላይ እንደወጣሁ አላስታውስም። የመርካቶ ቤቶች ትፍግፍግ ያሉ፥ ካንዱ ጣሪያ ወደ ሌላው በቀላሉ የሚዘለልበት ስልሆነ፥ ካንዱ ቤት ጣራ ወደሌላው ተሸጋግሬ መንገድ ዳር ካለው ጣሪያ ስደርስ ቆምኩ። አንድ ትንሽ ልጅ ከታች ቆሞ ቀለደብኝ። "በላ ዝለል! ዝለላ! አንተ የዘለልከውን እኔ የሚያቅተኝ ይመስልሃል? ዝለል እስቲ ጉብዝናህን እንይልህ!" አለ። ከጣሪያው ብዘል የማልሞት መሆኑ ገባኝ፤ እዛው ቁጭ ከማለት የተሻለ አማራጭ አልነበረኝም።

ወዲያው የቀበሌ ዘበኞች ከጣሪያው ላይ ወጥተው ዙሪያዬን ከበቡኝ። ከየት እንደመጣ አላውቅም፤ ከዛው ከጣራው ላይ የምጽፍበትን ደብተርና እስክሪፕቶ አገኘሁ። ይህ ቀድሞኝ የመጣ ነገር - "የተገለበጠ አጋጣሚ....።"

ዘበኞቹን ችላ ብዬ መጻፍ ጀመርኩ። እራሴን የማጋለጫ ጽሑፍ የምጽፍ መስሏቸው ነው መሰለኝ፥ ቆመው ይጠበቁኛል። እኔ ግን ምን ነበር የምጽፈው? የጻፍኩትን የማላውቅ ነኝ እንጂ፥ ይህን ነበር የጻፍኩት ብዬ አልዋሽም፤ ይህንንስ ማስታወስ አልችልምና። ግን በዚህ አጋጣሚ የነበርኩበትን ሁኔታ ሳስበው ምናልባት የጽሑፌ ስሜቱ ይህንን ይመስል ይሆናል፡-

"ይድረስ ለጓዴ ለአሻግሬ፤ እንደምን ከርመሃል? እኔስ እንዲሁ በመንከራተት ላይ ነኝ። ግን እስካሁን አለሁ፤ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የማልኖር ስለሆንኩ ይህንኑ ልነግርህ ብዬ ነው የምጽፈው። ሳላገኝህ በመቅረቴ እጅግ ያሳዝነኛል። ከቁጥጥሬ ውጪ ስለሆነብኝ ነውና አትፍረድብኝ። ሞተህም ከሆነ ከሰማይ ቤት፥ በሕይወት ካለህም በምድር፤ በእውነት እኔ ከልቤ ያላጠፋሁህ መሆኑ በደንብ ይገባህ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ይህንን ጻፍኩ።

ውድ አሻግሬ! ደህና ሰንብት ብዬ ስሰናበትህ፥ ሁላችንንም የሚያገናኝ የታጋዮች መንፈስ እንደማይሞት፤ ያሰብነውም ሁሉ በተለያዩ መንገዶች እንደሚስተካከል ተስፋ በማድረግ ነው። ካንተ ጋራ ሳወራ ስሜቶቼን ሁሉ በዝርዝር ታውቃለህ። በኔ በኩል ያለውን የትግል መንፈስ (የከሸፈ መንፈስ ቢመስልም) ከዚህ ደብዳቤ አውጥተው የሚጠቀሙበት የወደፊቱ ትውልዶች፥ "የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መብት በእውነተኛ ታጋይ ሕዝቦቿ መስዋእትነት ይመሠረታል።

አገራችን ኢትዮጵያ ነፃነት፥ ሰላም፥ እኩልነትና አንድነት የሰፈነባት አገር ትሆናለች!" እያሉ ሲጮሁ ይሰማኛል።

ላንተም ሕይወትህ ከወገኖችህ ጋር ሆኖ እንደምትፈልገውና እንደምታስበው እንዲሆን የሚያደርግ ታላቁ አብዮታዊ ተስፋህ ምን ጊዜም ከልብህ እንደማይጠፋብህ አምናለሁ። ከጓዶቻችን ኢሕአፓዎች ጋር ትደባለቅ ዘንድ ልባዊ ምኞቴን አስተላልፋለሁ። በሄድክበት የሕዝቦች ፍቅር ይጠብቅህ።

ግን፥... አሻግሬ፤ አንተ ከኔ ስለምትሻል፥ ምናልባት በቀይ ሽብር ተገድለህ በመንገድ ላይ ተጥለህ ይሆናል። ብትሞትም፥ ከእንግዲህ በኔ በኩል ጨርሻለሁና፤ ትግሌና ሕይወቴ በዚህ ላይ አክትሟል በማለት፥ ለማይበገረው አብዮታዊ መንፈስህ ነው የማወራው። እኔስ ትግል ከብዶኝ ሳይሆን፥ ለትግል የከበድኩ በመሆኔ ምክንያት ከምድር ገጽ መጥፋቴ ነው። ምናልባት፥ እንዳጋጣሚ ሳልሞት ብቀር ግን፥ ለወሬ ነጋሪነት እንደሚተርፉ ሰዎች መሆኔ ነውና፤ አይዞህ! በአብዮታዊ ትግል ተሳታፊ ለመሆንና ታሪክ ለመሥራት ሳይበቁ፥... ያበዱትም ቢሆኑ፥ መንፈሳቸው ለኢትዮጵያችን የሚሠራ መሆኑን እናገራለሁ (ይህ መጽሐፍ ይመስክር)።

አሻግሬ! አንተ ካልሞትክና እንዳጋጣሚ መድህን እና ጸጋዬን ካገኘሃቸው፥ አብዮታዊ ሰላምታዬን አስተላልፍልኝ። ምንም ባይሳካም፥ ስለደህንነቴ ስላሰባችሁልኝ አመሰግናለሁ በልልኝ። ደህና ሰንብት!.."

ወይ ጉድ! ካጠገቤ የቀበሌ ዘበኞች ጠመንጃቸውን እንዳነገቱ ቆመው አይቻቸው አልነበረም? ወዴት ሄዱ? እኔ ይህንን ደብዳቤ (ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ደብዳቤው አሁን የተጻፈ ነው) ከጣሪያ ላይ ቁጭ ብዬ የምጽፈውን እጽፍ ነበር። ስጽፍ ቆይቼ፥ "ከብዙ ሰዓታት፥ ወይንም ከጥቂት ደቂቃዎች?" በኋላ፥ በድንገትም ዞር ስል ዘበኞቹ የሉም። ይህም ህልም እንጂ እውነት ባይሆን ይሻል ነበር። ግን ዘበኞቹ ጽሑፉ የማያቋርጥ ሲሆንባቸው ጊዜ፥ እንተወው፥ ጽሑፉን ከጨረሰ በኋላ እንይዘዋለን ብለው ይሆናል ጥለውኝ የወረዱት። እንጃ! ይህ ደግሞ ምን አይነት አጋጣሚ እንደሆነ ሊገባኝ አይችልም። ዞሮ ዞሮ ሁኔታዎች ሁሉ የሚስተካከሉት እኔን ለማሳበድ እንጂ እኔን ለመግደል አልሆነም። ግን በእውነት አይምሮዬን ሳልስት (ሳላብድ) የአንዳንድ ሁኔታዎች ክስተት (ያጋጣሚዎቹ ትርምስ) እስካሁን ይገርመኛል። እስካሁን በኔ ላይ የደረሰ ሁሉ ማንንም ጤነኛ ሰው ያሳብደዋል ብዬ እገምታለሁ። በእውነት ታሪኩ ብዙ ነው፤ ግን ያንባብያንን ጊዜ ላለመፍጀት አሳጥሬዋለሁ።

ከጣሪያው ላይ በወጣሁበት አቅጣጫ ወረድኩ። ለጥቂት ደቂቃዎች እንደጤነኛ ሰው በሰዎች መካከል ተመላለስኩ። ግን አይምሮዬ በዚች አለም ካለ

ጭንቀት ለመኖርም ተስፋ መቁረጥና መሰናበት ለችግሮች ሁሉ አንዱ "መፍትሔ" መሆኑን በደንብ ስላስረዳኝ፡- "የመርካቶ እብድ ተብዬ ብቀር፥ ሌላውን እያስቸገርኩ በመኖር፥ በሕብረተሰቡ ላይ ሸክም ከመሆን በስተቀር፥ ሥጋዬ እየተወዛወዘ ለማንም ጥቅም አይሰጥምና፤ ተፈጥሮ ቸርነቷን በኔ ላይ ለመግለጽ ከፈለገች፥ ይህን በእውር አይኔ ያየሁትን፥ በደንቆሮ ጆሮዬ የሰማሁትን፥ ባልበሰለ አይምሮ ያሰብኩትን ሁሉ ጥፍት አድርጋ፥ ሌላ አለም ውስጥ ትክተተኝ። አለበለዚያ ይህን እንስሳ የሆነ ሥጋ እኔው ራሴ ገድዬ ባሳርፈው ነው የሚሻለው" በማለት ቁርጥ ውሳኔ ለማድረግ ስነሳ፥ "ግን ቆይ፤ በቅዱሳን ሬሳዎች ላይ የእውነት አበባ አለምልማ፥ የሌሎችን አስተሳሰብ በጥሩ ሽታ ታውዳለች፤ በኔ በኃጢአተኛው ሬሳ ላይ የምታድግ አበባ የምትገማ ከሆነስ፥ ሞቴም ለጥሩ ሳይሆን ለመጥፎ ሆነ ማለት ነውኮ፤ አደለም እንዴ? የሚል ሃሳብ አንገዳገደኝ።

ስለ ሞት ሳስብ፥ ከመጠን በላይ መንፈሴን ደስ ይላትና፥ ወዲያው ደግሞ ክፍት ይላታል። በሰውነቴ ላይ የሚደርስ ጉዳት፡- ረሃቡም ህመሙም፥ ሁሉም ወደ ሞት የሚያመራኝ እየመሰለኝ፥ የተደበቀ ደስታ ይሰጠኝና እንደገና ልውጥ ይላል። ግን ባጠቃላይ፥ የሥጋዬ መጎዳት አስቤው ከነበረው ጋር በመስማማት ወደ ሞት ከሚያመራው ጎዳና የሚከተኝ እየመሰለኝ፥ ከምን ጊዜውም የበለጠ ውስጣዊ ደስታ ይሰማኛል።

የመኪና መንገድ የማቋርጥ እየመሰልኩ መሃል መንገድ ላይ መቆም ጀመርኩ፤ ሹፌሮችን ከማናደድ በስተቀር የጠቀመኝ ነገር አልተገኘም። አስተሳሰቤ ሁሉ ሞት ላይ ቢያተኩርም፥ በተጻራሪ ሃሳቦቼ ምክንያት፥ ሞት በረከሰበት አለም ለሞት እንኳን የማልበቃ ሆኛለሁ።

ይህን የመሳሰሉ ድርጊቶች በላዩ ላይ የተፈጸመበት ሰው፥ እሱ ራሱ ደራሲ ከሆነ፥ እንደ ልብ ወለድ አድርጎ ውሸትን እየደባለቀ ካልጻፈ በስተቀር፥ በእውነት ድርጊቶችን ሁሉ አስታውሶ መጻፍ ያቅተዋል። ግን እውነት ልብ ወለድ ከሚመስል ቢቀር ባይነገር ይሻላል። እህ! ታዲያ ምን ልበል? ረሳሁት። ስለረሳሁት አሁን ዝም ልበል እንጂ፤ እኔስ የለመድኩትን በንዑስ ከበርቴነት ሁለት አይነት ኑሮ - ነፃ የቢሮ ሥራ እና ድብቅ አብዮታዊ ትግል አጥቼ፥ አሲምባ ገብቼ ልታገል ብዬ ስማጸን፥ አንድም የራሴን ሕይወት ለማትረፍ ነበር። ግን ያ ተስፋ መቅረቱ፥ እንዳው በደፈናው፥ እኔን ከእልኸኛነት ወደ እብደት አሸጋግሮኛል ብል ነው የሚቀለኝ።

እና፥ የቀን ጸሐይ ሙቀት ከጧቱ ብርድ አላቆ ተሲአት (እኩለ ቀን) ላይ ሲያቃጥለኝ እንደነበረ፥ ንኡስ ከበርቴዎች ከማይደርሱበት "ከቆሻሻው አጠገብ" መቆሜ፥ መቀመጤ፥ ጋደም ማለቴ.. የቀኑም መርዘም ትዝ ይለኛል። በቃ ይኸው ነው፤

ግን አካላዊ ሥጋ ጥፍት ብሎ ወደ "ምንምነት" ቢለወጥም፥ ያ "ምንምነት" የተሰኘ ቃል በቁስ አካላት ከተገነቡ፥ በእግዚአብሔር ከማያምኑ ሰዎች የፈለቀ ቋንቋ ሆኖ ነው እንጂ፥ ምንምነት የለም። በሳይንስ ወደ ምንምነት የሚጠጋ ወይም ምንም የሆነ "ነገር" የሚባለው ብርቅነት (singularity) ነው። ይህም ታላቅ ኮከብ ሲከስም የሚከሰት ታላቅ ኃይል መሆኑ በሳይንስ ይታወቃል፤ እኛም ከዋክብት ነን (ሦስተኛውን መጽሐፍ ይመለከቷል)።

**እስር በመርካቶ የከፍተኛ አምስት ጽሕፈት ቤት**

የሰው ልጅ ራሱን ነፃ ለማውጣት ሲል ተክለ ሰውነቱን ከራሱ ላይ አያራግፍም፤ ግን ሁኔታዎች ከሁለት አለም እየከተቱ ማንነቱን እስኪስት ድረስ ያንገላቱታል፤ ወደ አልታሰበ ሥፍራም ይከቱታል። እነሆ! ከጥቂት ቀናት በኋላ የደረስኩበትን፥ በግልጽ ትዝ ትዝ የሚለኝን ብቻ እየመረጥሁ እናግራለሁ።

ከሰዓት በኋላ ይመስለኛል። መንገዴን ወደ ሰሜን አመራሁ። ከሩቅ ለሩቅ አንድ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ታይቶኛል። ይህም አውቶብስ ወደ ደብረ ሊባኖስ የሚወስድ ነበር። ለኔ ግን፥ አውቶብስ ሁሉ ወደ ኮረም የሚወስድ መስሎኛል።

ታጋይ ጓዶቼ ከሚገኙበት የሚያደርሰኝ መስሎኝ፥ እንዳያመልጠኝ ብዬ ወደ አውቶብሱ ሮጥኩ። አውቶብሱ ዘንድ እንደ ደረስኩ ተሳፋሪዎቹ ሁሉ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ቁጭ ቁጭ ብለዋል። ሹፌሩም ሞተር አስነስቶ ከውጪ ቆሞ ከሰዎች ጋር ያወራል።

አንዱ አልሆን ሲለው ሌላ ከመሞከር የማይሰለች አይምሮ አሁንም "ሊመክረኝ ወይንም ሊያታልለኝ" ነው። ጭንቅላቴ መሥራት አለመሥራቱን በጥቂት ሰኮንዶች ውስጥ ፈተንኩት። ሰዎች አውሮፕላን እንደሚጠልፉት አይነት አሳሰበኝ። ተንደርድሬ ካውቶብሱ ገባሁና የሹፌሩ መቀመጫ ላይ ቁጭ ብዬ ለመንዳት ተዘጋጀሁ። ወዲያው ማርሹን ወደ አንደኛ ማርሽ ለማድረግ ስታገልና ቤንዚን መርገጫውን በእግሬ ስፈልግ፥ ሹፌሩ ዘሎ ገባና እጄን ያዘኝ። ከዛም ከሹፌሩ ጋር ትንንቅ ሆነ።

የቀበሌ ዘበኞች ከአውቶቡሱ ገቡ፤ ሁኔታውንም አይተው ትንንቁ ወደ መጥፎ እንዳያመራ ቶሎ ብለው እጆቼን ከሹፌሩ እጅ አላቀቁ። ወዲያውም ተሳፋሪዎች "ይህ እብድ ገደል ሊከተን ነበር እኮ! ወይ ጉድ! ሊጨርሰን?.." እያሉ ተንጫጩ። የቀበሌ ዘበኞች በጠመንጃ እየጎሻሸሙ ከፊትለፊታቸው እንድሄድ አስገደዱኝ፤ እያዳፉ ከቀበሌ እስር ቤት ከተቱኝ። ከዛ እንደደረስኩ፥ መሬት ላይ

አጋድመው ረጋገጡኝና በጠብመንጃው መዳፍ ደበደቡኝ። ሰውነቴ ደንዝዞ ነበር መሰለኝ ብዙም ህመም አልተሰማኝም።

መሬት በደረቴ ተኝቻለሁ። በጆሮዬ የጠመንጃውን አፈሙዝ ከተቱና ማንነቴን ለማወቅ ይጠይቁኝ ጀመር። በጥያቄ አጣደፉኝ፤ ቶሎ ቶሎ መለስኩላቸው፤ ግን አፌ መሬት ጋር ስለተጣበቀ ድምጼ በደንብ አይወጣም። “ሥራህ ምንድነው?” ሲሉኝና ስመልስላቸው፥ የንግድ ሚኒስቴር ወታደር ነኝ,,,” ያልኩ ቢመስላቸው፥ “ዘበኛ ነኝ፤ ነጋዴ ነኝ፤ ሥራ ፈት ነኝ” ብላቸውም፥ ቀብጠርጠር በማድረግ፥ ከነርሱ ጥያቄ የኔው መልስ እንዲበረከት።

ከመካከላቸው አንዱ “መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ታውቀዋለህ?” ብሎ ጠየቀኝ፥ “አዎን አውቀዋለሁ፤ እርሱ ወታደር ነው፤” አልኩ፤ ቀስ ብዬም እገድለዋለሁ ያልኩ ይመስለኛል (እኔው ራሴ በውስጤ ሁለት ሰው እንደሚያወራ ሆኛለሁ)። ቀስ በሚል ድምጽ ብዙ አወራሁ። “ምንድነው የሚቀባጥረው ይህ ሰው? መንግሥቱን ታውቀዋለህ ወይ?” ነው የምንልህ” ሲሉኝ፥ እኔም ቀስ ብዬ “አዎ አውቀዋለሁ” ስል፥ ጓደኛዬ ነው ያልኳቸው ይመስላቸዋል።

በጆሮው ላይ የጠመንጃ አፈሙዝ የተተከለበት ሰው ጮክ ብሎ ካወራ፥ ከጠመንጃው ቃታ ውስጥ ያሉ ጥይቶች በድንጋጤ ተፈትልከው ይወጡና ሰው ይገድላሉ (ይህን ሊያውቅ የሚችል የደረሰበት ብቻ ነው)። በጠመንጃቸው አፈሙዝ ጆሬዬን ሲኮረኩሩትና ሲጎሻሽሙት ይገድሉኝና ያሳርፉኛል የሚል እምነት ቢያድርብኝም፥ ለመትረፍም እየጓጓሁ፤ ቀብጠርጠር እያደረግሁ እብድ መስዬ ስለፈልፍ፥ በቋንቋም ግራ አጋባኋቸው።

ይህን ከመሬት የተደፋ ሰው መግደል ለምን እንዳስፈለገ የባለጠብመንጃው ሕሊና እየተመራመረ እንዲቆይ እንጂ፥ ቶሎ ብሎ ቃታውን ስቦ እንዳይገድለው ለማድረግ፥ እንደ ህጻን መንተባተብ እና እንደፈላስፋም አጣርቶ መናገር አስፈለገ። የመርማሪው ሰውዬ አይምሮ ከጥሩው መንፈሱ ጋር ተወያይቶ እንዲምረኝ ጊዜ ለመስጠትም ነው - ይህ ‘ማይደል በሕይወት ለመቆየት የሚያስችል ተፈጥሮአዊ ብልሃት።

ሰው እንዳይሞት እንዲሞትም የሚያደርጉትን ምሥጢሮች፥ አውቀንም፥ ሳናውቅም እንጠቀምባቸዋለን። የሰው ልጅ ሁሉ የሁለትነት ጠባይ በከባድ ሁኔታዎች ሲፈተን፥ አንዱ ሰው ከውስጡ ራሱን ለመግደል ሲታገል፥ ሌላው ሰው ደግሞ ከውስጡ ራሱን ለማዳን ሲታገል፤ ከሁለት የአንዱ የመሰናበቿያ፤ የሌላውም የመቆያ ምሥጢር።

የጠመንጃውን አፈሙዝ ከጆሮዬ ዞር አድርገው በእርጋታ፥ “ሊቀ መንበሩን የት ነው የምታውቀው? አጋዴን ነው ሐረር?” ብለው ሲጠይቁኝ፤ እኔም ሊቀ መንበር የተባለው ቃል ግራ እንዳጋባኝ ሆኜ፥ ቶሎ ቶሎ እየደጋገምኩ፥ “የት ነው ያለሁት? የት ነው ያለሁት? የት ነው ያለሁት?” ማለቴ በጣም ትዝ ይለኛል። በዚህን ጊዜ አንዱ ዘበኛ በአጋዴን ያለሁ መስሎኝ የምለፈልፍ መስሎት እንደሆን እንጃ፥ “ይህ ሰው በአጋዴን በረሃ ችግር ደርሶበት ያበደ ወታደር ነው” ብሎ ደመደመና ሌሎቹንም አሳመናቸው።

ሌላው ዘበኛ “እባክህ ይህንንስ እብድ እዛ ወስዶ መጣል ነው” ይልና፥ ከአንድ የእቃ ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ ዘግተው ይተውኛል። ረስተውም ሆነ አውቀው፥ ለሦስት ቀን በሩን ከፍቶ የተመለከተኝ አልነበረም። እኔም ሌትና ቀን ጨለማ በሆነበት ሥፍራ ሰነበትኩ። ደግነቱ በጭላንጭል አንድ ትንሽ ከረጢት አይቼ ነበርና፥ ከፈት ሳደርገው በውስጡ ስኳር አገኘሁ። ቀስ ቀስ እያልኩ ሁሉንም ስኳር ቅሜ ጨረስኩ፤ ይህም ለሦስት ቀን ምግብ ሆነኝ።

በዚህ እስር ቤት ብዙ ብዙ ለሰው መግለጽ የሚያዳግት አስገራሚ ትእይንቶች ታዩኝ። ግን ይህ ነው ብሎ መናገር የማይቻል በመሆኑ፥ እስከ ዛሬ ድረስ ምን ነበር ያየሁት የሚለውን ለኔም ለራሴ ማወቅና መረዳት ያቅተኛል። ግን ከሁሉም በላይ ብዙ ወጣቶች (ወንዶችም ሴቶችም) ይታዩኛል፤ የማድናቸውም ይመስለኛል።

የመርካቶ ቀበሌ ሠራተኞች፥ እንደ ስምጥ ሸለቆ ከብት አርቢዎች ወሬ ቶሎ ቶሎ ይለዋወጣሉ መሰለኝ፤ በሦስተኛው ቀን ከየት ተነስቼ እዚህ እንደደረስኩ ተመርምሮ ስለተደረሰበት፥ ወደ ሌላ ቀበሌ እንድሄድ ተደረገ።

ለመሸተ ወደገበያ እንደሚነዳ በግ፥ በከተማ መሃል ጠመንጃ ባነገቱ ሰዎች እየተነዳሁ፤ ሁለተኛውን ቀበሌ አልፌ ሦስተኛው ላይ ደረስኩ። ይህ ቀበሌ ያች እናት የሆነች ደግ ሴት ያለችበት ቀበሌ ነው። ከቀበሌው እንደደረስኩ፥ ያቺን ደግ ሴት ከቀበሌው ጽሕፈት ቤት ቆማ አየኋት። “ይህ ነው ወይ?” ብለው ሲጠይቋት ሰማሁ። እርሷም እኔን ስታየኝ እንባዋ ቅርር አለና፥ በቀጭን ድምጽ “አዎን” አለች። ከዛም በጇ የያዘችውን ኮቴን እንድትሰጠኝ አደረጉ።

“ሌላስ ከርሷ የቀረህ እቃ አለህ?” ብለው ጠየቁኝ። በዚህን ጊዜ ትኩር ብላ አየችኝ። “አንተ ተናዘህልኝ የሄድከውን ገንዘቡንና ሰዓቱን፥ አሁን አልሞትኩምና መልሺልኝ..” የምላት መሰሏት ይሆን? አልኩ በልቤ። አይ ይህ የኔ እስተሳሰብ ነው። እርሷ ግን በድምጽ አልባ ንግግር፥ በሕይወት በመትረፌ ፈጣሪዋን ማመስገኗ መሆኑ ገባኝ። ወዲያው ብንን እንደማለት ብዬ፥ “የለም፤ የለም፤ ምንም የቀረ የለም”

አልኳቸው። እንደገናም ጠየቁኝ፤ እኔም ምንም የቀረኝ አለመኖሩን በማረጋገጥ መለስኩላቸው።

እርሷንም “በይ ሂጂ!” ተብላ ልትሄድ ስትል፥ ሌሎች እንዳይገባቸው አድርጋ፤ ምስጋናዋን ከምርቃት ጋር በገጽታ ንግግሯ ለኔ ብቻ ለመግለጽ በቅታለች (የሴቶች ችሎታ)። ምስኪን ሴት፥ በቀስታ “እግዚአብሔር ይጠብቅህ” ብላኝ ነው የሄደች።

እኔም፥ “አንቺ ሴት ገብቶኛል ደግነትሽ፥ በሄድኩበት ታቅፎኛል መንፈስሽ፤ አዞሮ አዞሮ አቁሞኛል ከፊትሽ። በይ ሂጂ ግቢ ከቤትሽ” ብዬ አንገቴን ወደ መሬት ደፋሁ። ሴቲቱም ካጠገቤ ርቃ ሄደች።

“በል ልበስ!” ተባልኩ፤ በቁጣ። ኮቴንም ለበስኩና እጆቼን ቶሎ ቶሎ ወደ ኪሶቼ መከተትና መፈታተሽ ጀመርኩ፤ እቃ ጠፍቶት እንደሚፈልግ ሰው ሆንኩና። የጻፍኩበት ደብተሬ የለም። “ጽሑፌን ከዚች ደግ ሴት መላእክት (ወይም ኢሕአፓዎች) ወስደው ያነቡታል፤ ሁሉም ደግ ነው…፤” አልኩ በልቤ።

ከኮቴ የጉያ ኪሴ እጄን ሳስገባ የሆነ ወረቀት አገኘሁ። ስመለከተው የቀበሌ የፈቃድ ወረቀት መሆኑ ትዝ አለኝና ቶሎ ከአፌ አስገባሁና ማኘክ ጀመርኩ (ይህ ነው የሰው ልጅ የአርባ ቀን እድሉ ሴኮንድ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የሚወሰን)።

ዘበኞች አንዴ ዘለው አፈኑኝ። አፌን ጥርቅም አድርገው ይዘው ወረቀቱን አወጡት። የቀበሌ ፈቃድ ወረቀት መሆኑን ሲረዱ፥ እውነትም እንደተጠራጠሩት ተራ እብድ ሳልሆን፥ እውነተኛ የኢሕአፓ አባል መሆኔ ገባቸው። ሁሉም እንደ የማርያም ጠላት በየተራ ደበደቡኝ፤ ቀጠቀጡኝ፤ ወገሩኝ። እውነተኛ ዱላ የቀመስኩት የዛን ጊዜ ነው። እጆቼን የኋሊት ጥፍር አድርገው በገመድ አስረው፥ እያዳፉ ወደ ከፍተኛው ጽሕፈት ቤት (እስር ቤት) ወሰዱኝ።

የመርካቶ ከፍተኛ እስር ቤት እንደደረስኩ፥ የታሰሩ ወጣቶች ውጪ ተፈቅዶላቸው፥ ተደርድረው አየኋቸው። በዚህን ጊዜ ሦስት ቀን በቀበሌ ታስሬ ሳድር ካየሁት ትእይንት ጥቂቱ ግልጥልጥ ብሎ ታየኝ። በእውነትም የራሴን ሕይወት አሳልፌ በመስጠት እነኚህን ወጣቶች ለማዳን የምችል መሰለኝና የሚከተለውን አሰብኩ፦

“ከጥቂት ወራት በፊት፥ ቀበሌዎች ድንገት ቤቴ ቢመጡብኝስ እያልኩ የኢሕአፓ ጽሑፎችን እደብቅ ነበር። ትዝ የሚለኝ፥ እኔን በዚህ ምክንያት እንዳይገድሉኝ ብዬ ከኢሕአፓና ከአንጃዎች የሚደርሱኝን ጽሑፎች ከቤቴ ውስጥ ሊገኝ ከሚችል የመደበቂያ ሥፍራ ሁሉ ደበቅሁ፤ በመጨረሺያም በጓሮ በኩል መሬት ቆፍሬ ቀበርኩ። የእነኚህ ወጣቶች እናቶች ደግሞ፥ ልጆቻቸውን ለመደበቅ ወደ ማህጸናቸው መልሰው መክተት ብቻ ሲቀራቸው ሁሉን አደረጉ። እነኚህ ከፊት ለፊቴ የሚታዩት ወጣቶች ከዛ ሁሉ ድበቃ በኋላ፥ ከተገደሉት የተረፉት ናቸው እኮ! ዛሬ

ለነኚህ ወጣቶች ስል እሞታለሁ፤ ዛሬ ለነኚህ ወጣቶች ስል እሞታለሁ፤ ለመሞቻዬ የሚሆነኝ በቂ ምክንያት አሁን ገና አገኘሁ!" አልኩና ከሥጋ ቁጥጥር ውጪ የሆነ ጩኸት ጮህኩ፡-

"ወጣቶችን በማሰር ምን ትጠቀማላችሁ? ያው ግደሉኝ፤ እኔ አለሁላችሁ! ወጣቶች ምን ባጠፉ ይቀጣሉ። ያው አለሁላችሁ ግደ..ሉኝ! ግደ.....ሉኝ" አልኩ።

የከፍተኛው ሊቀመንበር ወጣቶቹን በቁጣ ቃል "በሉ ቶሎ ግቡ! ግቡ! ግቡ!.." ብሎ እየጮኸ ቶሎ ወደየክፍላቸው እንዲገቡ አደረገ። ወደ እኔም ዞር በማለት ከተመለከተኝ በኋላ፥ በዙሪያዬ የከበቡኝን የቀበሌ ዘበኞች፥ "ይህ አናርኪስት ባይናችን ላይ ቅስቀሳ ሲያካሄድ ዝም ብላችሁ ታያላችሁ?" ብሎ በመጮህ፥ አንድ ጡጫ በፊቴ ላይ አሳረፈብኝ። እኔም እጆቼን የኋሊት ታስሬ፥ ሰውነቴም በጾም ብዛት የደከመ ስለነበረ፥ ወዲያው መሬት ላይ ባፌ ተተከልኩ። እዛው እንዳለሁ እያንዳንዱ የአብዮት ጠባቂ (ዘበኛ) አብዮታዊ ግዴታውን እኔን በመደብደብ አስመሰከረ።

ከዛም ሊቀመንበሩ "በቃችሁ! በቃችሁ!" አለ፤ የኔ ነፍስ ያደረችበትን ሥጋ በቀላሉ ለቃ የማትወጣ መሆኑን ባለማወቁና የምሞት ስለመሰለው፥ ከኔም መረጃ ስለሚፈልግ፥ ሳልሞት በፊት ሊመረምረኝ፥ ኑዛዜዬንም ለመስማት አሰቦ።

ወዲያው ከቢሮው እንዲወስዱኝ ትእዛዝ አስተላለፈ። ከቢሮው እንደገባሁ፥ "ሃሽሽ ትወስዳለህ እንዴ?" ብሎ ጠየቀኝ ሊቀመንበሩ። እኔም "አይ አልወስድም" አልኩት። "ጭራሽ ወስደህ አታውቅም?" ብሎ በመደጋገም ጠየቀኝ። እኔም እንደማልወስድ አረጋገጥኩለት። "በትምህርትህ ስንተኛ ክፍል ደርሰሃል?" አለኝ። እኔም አስራ ስድስተኛ ክፍል መጨረሴን ነገርኩት።

የሊቀመንበሩ ፊት በድንገት ትንሽ ፈገግ አለ፤ ያዘነልኝም በመምሰል "ኮድ ተቀብለህ አሲምባ ከጓዶችህ ጋር ለመቀላቀል ስትዘጋጅ እንደተያዝክ ተነግሮኛል። ይህ እውነት ነው ወይ?" አለ። እኔም "አዎን እውነት ነው፤" አልኩት።

አሁንም የበለጠ ፈገግ አለ፤ ከወንበሩ ላይ በመደላል ዘና ብሎ፥ ወረቀትና እስክሪፕቶ ያዘና፥ "ታዲያ ኮዱን ለኔ ልትነግረኝ ፈቃደኛ ነህ?" አለ ለስለስ ብሎ።

እኔም በማረጋገጥ "አዎን ፈቃደኛ ነኝ" አልኩት። በዚህን ጊዜ እጅግ ደስ አለው። ረጋ ብሎ ኮዱን ለመጻፍ ይችል ዘንድ፥ እራሱን በወንበሩ ላይ አስተካከለ።

"ለአብዮታዊ ትብብርህ ሳናመሰግንህ አናልፍም" በማለት ሳቅ አለና፥ "ጓድ በል ኮዱን ንገረኝ" አለ፤ ከፊትለፊቱ ያለውን ወረቀት በእስክሪፕቶው እየወጋ። እኔም በልቤ "ያንጎድጉድህ" አልኩና" "ኮዱማ ከልቤ ውስጥ ነው ያለው፤ ስትፈልግ ደረቴን ሰንጥቀህ ከልቤ ውስጥ አውጥተህ መውሰድ ትችላለህ" አልኩት።

ሊያምን አልቻለም፤ እንደገና ድምጹን ከፍ በማድረግና በመጮህ "ኮዱን አውጣ ነው የምልህ! ቀጥቅጬ ሳልገድልህ!..." አለ በታላቅ ቁጣ።

እኔም በልቤ ከርሱ ጩኸት አስራ ሁለት ጊዜ አስበልጬ የጮኽኩ ይመስለኛል፤ ካፌ ሲወጣ ግን ስልል ያለ ድምጽ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። "ኮዱ ልቤ ውስጥ ነው ያለው፤ ከቻልክ ልቤን ቀደህ አውጥተህ መውሰድ ትችላለህ ብዬሃለሁ!.." አልኩት። እንዳልሰማ ሆኖ፥ "ምን? ምን?" አለ። እኔም ያልኩትን ደግሜዋለሁ፤ መልሶም ቢጠይቀኝ ይህንኑ ነው ደጋግሜ የነገርኩት።

## ተረካቢ ያጣች ነፍስ

ይህን መከራ ላይ የጣለኝን ሥጋዬን ለመጨረሺያ ጊዜ የሚያሳርፍልኝን ነገር አሁን ገና አገኘሁት። በአማርኛ እንኳን ተቀራራቢ ፍቺ የማይገኝለት "ቶርች" የተባለውን፥ የሚገድል ወይንም ከሞት አፋፍ የሚያደርስ ድብደባ ሰጥተውኝ ይሆናል። ታዲያ፥ ልክ እንደ ጠጅ እየጣፈጠ ገብቶ ያሰከረኝ፤ ሰመመን ውስጥ አስገብቶ ራሴን ያስረሳኝ ምንድነው? ቅዠት ወይንስ ስካር።

አይምሮዬ ከሥጋዬ በመገንጠል ለብቻው ማሰብ ጀምሯል ወይም ሄዷል (ሞቻለሁ)። የኔ ጩኸት ሊቀ መንበሩን በሰውነት ኩምሽሽ አድርጎ ያሳነሰው፤ በዙሪያዬ የነበሩ ሌሎቹም በኔ ጩኸት ተደናግጠው ሮጠው ያመለጡ፤ እኔም ለብቻዬ የቀረሁ እንዲመስለኝ ያደረገ ኃይል ምንድነው?

ከእንግዲህ ለኃጢአቴ ሁሉ የቶርችን ፍሬ ከበላሁ፤ አዳምና ሔዋን ከነበሩበት ከገነት እገባለሁ፥ የሚል ተአምራታዊ ሃሳበ ቅሬት በጭንቅላቴ የተቀረጸ ይመስል፤ የሚፈልገኝና የሚያሳድደኝ አለመኖሩን በማስታወስም ይሆናል...፤ ይህ ነው የማይባል እረፍት ተሰምቶኛል። እንጃ! እንጃ! ስለማላውቀውና ስለማይገባኝ ነገር ብዙ ማውራት አልፈልግም። ግን፥ ከአይምሮ በስተጀርባ የተቀበረ፥ ይህ የማይረሳ ትዝታ፥ ዝም ቢሉ የማያስችል፥ ቢናገሩት ለማሳመን የሚያስቸግር፥ ...

ብቻ በቀበሌው ዙሪያ የሚያበሩ የኢሌክትሪክ አምፖሎች እንዳየሁ ትዝ ይለኛል። ወደ ላይ በመውጣት ወደ አምፖሎቹ የሄድኩ ይመስለኛል። አምፖሎቹ ጋ ደረስኩ፤ ከዚያም አልፌ ሄድኩ። ከሰማያዊ ብርሃን ውስጥ ገብቼ ሰመጥኩ። በሄድኩበት ሥፍራ ውስጥ ያለውን እጅግ በጣም የሚያስደስት፥ በምድራዊ ቋንቋ የማይገለጽ፥ ፍጹም የሆነ መጀመሪያና መጨረሺያ የሌለው ዘለአለማዊ ሥፍራ ተመለከትኩ።

እኔ የደረስኩበት ሥፍራ፥ ኢትዮጵያ ሕዝቦቿን አቅፋ በሰላም የምትኖርበት፥ ለጠላት የማይታይ እውነተኛ ሥፍራ ነው። ግን፥ ቤት ይሁን አገር ይሁን አልለየሁትም። ያ ሥፍራ ብርሃን የሚያገኘው ከጸሐይ አይመስልም፤ ግን ልዩ አይነት፤ በምድር ላይ ሊነጋጋ ሲል ያለውን የሚመስል፤ እንደሚተነፈስ አየር የሆነ፥ ልዩ ብርሃን አለ። ራቅ ብዬ ብሄድ፥ የሰው ዘር ሁሉ የሚኖርበት ሥፍራም ከዚሁ መሆኑን ሳልገነዘብ አይቀርም...። እኔ ግን ባንድ ሥፍራ ተወስኜ ተመልካች ብቻ ነበርኩ እንጂ፥ ለመሳተፍ ገና አልተፈቀደልኝም።

ከዚህ ሥፍራ እጅግ የሚያማምሩ፥ አዳዲስ "ልብስ" የለበሱ፥ ቆንጆ ቆንጆ ወንዶችና ሴቶች በልተውና ጠጥተው፥ ጠግበው፥ ደስ ብሏቸው፥ አምረውና አጊጠው፥ አሸብርቀው፥ በመዝናናት ሽር ጉድ ይላሉ። ከስበት ጋር የተጣበቁ ሳይሆን፥ እንደ ልባቸው፥ ሲፈልጉ ወደ ላይ፥ ሲፈልጉ ወደታች፤ እንዳሻቸው አቅጣጫ በመቀያየር፥ ከመሬት የተለየ አይነት እንቅስቃሴ ያሳያሉ። ተቀምጠው የሚያወሩም አሉ።

የአድማሱ ክልል አይታይም፤ መጨረሻያም የሌለው ይሆናል..። ሥፍራውም አካላዊ (ሥጋዊ) ይመስላል፤ ግን ከዚህ ሥፍራ አፈር፥ ድንጋይና ውሃ አይታይም..። ሁሉም ነገር ከእሳትና ከአየር የተገነባ ይመስላል። በመሬት ካሉት ነገሮች መካከል እንደ ትምህርት ቤት (ዩኒቨርሲቲ) የበዛበት ይመስላል። የሚማሩትም ትምህርት በአጠቃላይ እኛ ሰዎች የምናውቀውን ጊዜን እየደመሰሰ፥ ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየሄደ፥ እንደ ታሪክ፥ እንደ ሃይማኖት አይነት ሰማያዊ ፍልስፍና - ስለ ሰው ልጅ፥ ስለ ተፈጥሮ፥ ስለ እግዚአብሔርም ይመስላል።

የአዲስ አለም መኖር እንዲህ ጥሩና ቆንጆ የሆነው ሰውን ለማስኖር ከሆነ፤ በምድር ላይ መኖርና መሞትም የመጨረሻያው አላማው በዚሁ አዲስ አለም ውስጥ ፍጹማዊ ሆኖ ዘለአለማዊ ለመሆን ከሆነ፥ በምድር ላይ እንኳን ሰይጣን ኖረ፥ እርኩሳን መናፍስትም እንኳን ሰውን አስቀያሚ አስመሰሉት ያሰኛል። ይህም፥ ሴት ልጅ አርግዛ በስቃይ አምጣ የምትወልደውን ህጻን እቅፍ አድርጋ ስትስመው ከምታገኘው ደስታ ጋር ይመሳሰላል (እርግዝና - አምጦ ልጅ መውለድ ጥሩ ከሆነ፥ በምድር መኖርም ጥሩ ነው እንደማለት ይቆጠራል)።

ሰማዩን ደፍሬ ቀና ብዬ አልተመለከትኩትም። አንድ ነገር ብቻ እንደ ፈራ ሰው ቀና ማለት አቅቶኛል። እግዚአብሔር የሚያየኝ መስሎኝ ይሆን? ተደብቄ ከገባሁበት ሥፍራ "ውጣ!" እንዳልባል ብቻ ፈርቻለሁ። በዚህ ቆንጆ ሥፍራ ማንም ሳያየኝ ብዙ ብዙ ቆየሁ። ለደስታዬም ወሰን አልነበረውም። በተመልካችነት ሳስተውል፥ የዛ አገር ሰዎች ሁሉ፥ በሰማያዊ አካላቸው ረዘም- ረዘም፥ ጎላ ጎላ ያሉ፤

በሁኔታቸውና በጠባያቸው፥ ለመግለጽ በማይቻል አይነት፥ ፍጹም ጥሩዎች በመሆን፥ በፍጹም ደስታ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው።

ይህ በጣም ግልጽ ሆኖ ታይቶኛል፤ ግልጥ ከመሆኑ የተነሳ እስካሁንም አልፎ አልፎ በሃሳቤ ይመጣብኛል። ይህ ነገር እውነት ስለመሆኑ እንዳልጠራጠር፥ በደንብ የማውቃቸውን ሁለት ሰዎች (ወንድና ሴት) ከዚያ ሥፍራ በግልጽ አይቻቸዋለሁ። እነኚህ ሰዎች አሁንም በዚህ አለም ላይ በሕይወት አሉ። ሲያወሩ ይሰማኛል፤ ድምጻቸውም እጅግ ጥርት ያለ ሆኖ የሙዚቃ ቃና ያለው ይመስላል። የወንዱ ድምጽ ወፈር ያለ ሆኖ፥ የድምጹ ጥራትና የሚናገረውም የፍልስፍና ንግግር፥ ለመግለጽ የማይቻል እውነተኛነትና ፍጹምነት ያለው ነው። የሴቲቱም ድምጽ ቅጥን ብሎ፥ የሙዚቃ ቃና ያለው ነው። ስትነጋገር ሴትነቷንና ደግነቷን በተለየ መልክ ግልጽ ያደርገዋል።

እንግዲህ ያ ሁሉ የገዛ አይምሮዬ እኔን ለማታለል የሚጫወተው ሊሆን ይችላል። ግን አሁንም የሚከተለውን ያሳስብበኛል፡-

የሰው ልጅ በዚች ምድር ላይ ሲኖር፥ ያ “መኖር” የምንለው ቃል የመኖርና የመሞት ክስተቶችን ያጠቃልላል። ሰው በየሰከንዱ ሲኖር በየሰከንዱም እየሞተ ነው። በምድር ላይ ሁለቱም (መኖርና መሞት) ሕያዋን ናቸው፤ ከምድር የመሰናበቿያ (ሞት) እስኪመጣ ድረስ ሁለቱም ክስተቶች ሳይነጣጠሉ አብረው መጓዝ አለባቸውና። ሰው ሲሞት ግን (ምድራዊነቱ ሲለቀው)፥ ይህም ማለት፥ የሰው መጥፎነቱ ከላዩ ላይ ሲነሳለት፥ በውስጡ ያለው ጥሩነቱ ይዘልቃል... ይሄዳል ... ለርሱ (ለጥሩው ሰው) ተስማሚ ወደሚሆንለት ሥፍራም ይደርሳል። ጥሩነት ዘለአለማዊ ስለሆነም፥ ያንን አዲስና ጥሩ ሰው ዘላለማዊና ፍጹም ያደርገዋል.. (ይሆን?)።

እነኚህ የማውቃቸው ሰዎች ጥሩነታቸው ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ አሁን ገና ገባኝ። ክፉት የተባለ ሁሉ ከሰው ልጅ ከውስጡ ሲወጣ፥ ሰውም ከአውሬ ባህርዩ ሲላቀቅ ምን ያህል ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ተገነዘብኩ። ይህች ምድር (አለም) ናት እንጂ መጥፎ የሆነችው፥ ለካስ የሰው ልጅ ሲባል ሁሉም ጥሩ ነው (መጥፎነቱ ከሬሳው ጋር ከቀረ)። በአሮጌው አለም ከሌላው ሰው ተለይቶ የማይታየው የእነኚህ ግለሰቦች ጠባይ፥ በአዲሱ አለም ውስጥ እጅግ ጥሩ ሆኖ አገኘሁት። እነኚህ በሁለንተናቸው ፍጹምነት ደረጃ የደረሱ ሰዎች፥ እኔን ሊያዩኝ የሚችሉ አይመስሉም። ቢያዩኝማ ኖሮ.. በእንዴት አይነት ደስታ ተቀብለው ባስተናገዱኝ ነበር።

ታሪኩ በዚህ ላይ ተፈጸመ። አዬ ጉዴ! ከተመልካችነት አልፌ ተሳታፊ ሳልሆን መቅረቴ ነው። ነፍሴ ከሸረሪት ድር በቀጠነች ሐረግ ላይ ተንጠልጥላ፥ እዚህና እዛ ስትወዛወዝ ነበር አዲሱን አለም ያየችው። አንድ ወጥ የሆነውን ንጹህ አለም በቀጭን

ሐረግ ላይ ተንጠልጥዬ ነበር ያየሁት። ያ ቀጭን ሐረግ አጉል ሥፍራ ስደርስ ተበጠሰ። አይ ጉድ! ምነው አዲስ አለም ስገባ - ከዚያ በተበጠሰ ኖሮ። እየጎመጀሁና እየጓጓሁለት፥ ያ ደስ የሚል አለም በመጋረጃ ተዘጋ። እድሌ ሆነና፥ እዚሁ ተመልሼ ወደቅሁ። ተረካቢ ያጣች ነፍስ ተመልሳ መጣች ወደኔ። እኔና ነፍሴ፥ ቤታችን ካፈር ላይ ነው - ከመሬት።

ምነው ቀና ብዬ ወደ ሰማይ አንጋጥጬ በተመለከትኩ ኖሮ? ኮሙኒስትነቴ ቀርቶብኝ፤ "አምላኬ ላንተ እሰግዳለሁና፤ እባክህ አትጨክንብኝ.." ባልኩት ኖሮ። ለሚጠይቀኝ ጥያቄ ሁሉ፥ "ታዲያ ምን ላድርግ፤ ታዲያ ምን ላድርግ፤.." እለው ነበር። እርሱም የልቤን ቅንነት አይቶ ስለማይጨክንብኝ፥ "በል ለጊዜው እዚህ አረፍ በል.." ብሎ፥ ለየት ያለ ሥፍራ ይሰጠኝ ነበር እንጂ መልሶ ወደ መሬት አይጥለኝም ነበር። አለቀ፤ የኔ ነገር በዚህ ላይ አበቃ። ከሰማይም ከእግዚአብሔርም ሳልሆን ቀረሁ።

አለመሞቴ (በአዲስ አለም ውስጥ አለመወለዴ) በደንብ እንዲገባኝ ሆነና፥ የሥጋ ህመም ቀሰቀሰኝ። ድንግጥ አልኩ። "ውሸት! ሁሉም "ውሸት! ውሸት!.. መሬት ውሸት! እኔም ውሸት! ሁሉም ውሸት...." እጆቼ የኋሊት እንደታሰሩ ከቢሮው ደጃፍ እውጪ ተጥዬ በጣረ ሞት ላይ የምገኝ ሥጋ ነኝ። ሁሉ ነገር ውሸት መሆኑ በጣም ገባኝ፤ ውሸት በጣም አሳመመኝ።

ቀኑ መሽቶ፥ ሌሊቱም ወደመገባደድ ተዳርሷል። ሰው ሁሉ ተኝቷል። እዛው እንደተደፋሁ ሰውነቴ በውሃ ጥም አረረ። እውነተኛውን ሞት አሁን ላገኛት ነው ብዬ አሰብኩ። የጠጣሁት ቶርች በብርሌ የተቀዳ አሬት እንጂ፥ የሚያሰክር ጠጅ አልነበረም። አሬቱን ብዙ ባጠጡኝና በሞትኩ ምናለበት ነበረ? አፌ ደርቆ ምላሴም ከላንቃዬ ተጣብቋል።

"ወይ ሞት! ለካስ የሰው ልጅ የሞትን ጥሩነት ባለማወቅ ከፉኛ ይጎዳል.." አልኩ። ቀጥዬም፥ "የፈጠርከኝ አምላኬ ሆይ! እኔ ዛሬ ባንተ አምኛለሁና፤ እባክህ! እባክህ ውሰደኝ። ጨርሰህ ያልወሰድከኝ ስላላመንኩብህ አይደለም? በል አሁን አምኜብሃለሁና ውሰደኝ፤ እባክህ ውሰደኝ፤ እባክህ ውሰደኝ። ከዛሬ ጀምሮ ፈጣሪ አምካኬ አንተ መሆንክን ተቀብያለሁና እባክህ ውሰደኝ" እያልኩ ተማጸንኩ።

በዚህ የሞት ሽረት ሲቃ ስንፈራፈር ወደ መንጋቱ ተቃረበ። አንዲት ትንሽ ሴት ልጅ በሳህን እንጀራ፥ በኩባያ ውሃ በነጠላዋ ሸፍና አመጣችና፥ ማንም ሳያያት ተደበቃ ውሃውን አጠጣችኝ። ትንሽ ደቂቃዎች ብቆይ ይለይልኝ ነበር (የመጨረሺያውንና እርግጠኛውን ሞት አገኝ ነበር)። እኔም ለመሞት የከጀልኩት ሰውዬ፥ ውሃ ባፌ ሲፈስብኝ ጊዜ ሞትን ረሳሁት። ምግብ ልታጎርሰኝ ሞከረች፤ አልሆነላትምና ፈጥና ተመለሰች።

የጠጣሁት ውሃ ነፍስ ዘራልኝ። ቀስ በቀስ ያለሁበትንም ቦታ በደንብ መረዳት ጀመርኩ። "ይህ ነወይ የጸሎቴ መልስ?...ታዲያ የትኛው ነው ውሸት? የትኛው ነው እውነት?..ብኖርም - የመኖሬ ህልውና ቢረጋገጥም፥ ውሸት! ሁሉም ውሸት!.. መሬት ውሸት! እኔም ውሸት! ሁሉም ውሸት...."

ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሴቶች ተራ በተራ እየመጡ በድብቅ ውሃ ያጠጡኝ፥ ይመግቡኝም ጀመር። በዚህ አይነት አንድ ሳምንት አለፈ። አሁንም ከቢሮ ደጃፍ (እጆቼ የኋሊት እንደታሰሩ) እንደተጣልኩ ነው። ካድሬው ቢሮ በገባና በወጣ ቁጥር፥ "ይህ አመጸኛ አሁንም አልሞተም?.." እያለ፥ ልክ እንደ ተከላላይ የግር ኳስ ተጫዋች (ተርሲኒ) ሆኖ ይጠልዘኛል። የዛን ቀን ሊቀ መንበሩ ባሰቃቂ ሁኔታ ሲመረምረኝ፥ ካድሬው ቢኖር ኖሮ ቶሎ ይገላግለኝ ነበር።

ሌሎቹ እየዘለሉኝ ያልፋሉ እንጂ አይረግጡኝም። ሁሉም እየረገጡኝ ማለፍ ሲችሉ፥ አይነኩኝም። አንዳንዴ የማሰናክላቸው የአብዮት ጠባቂዎች፥ ብቻቸውን ሲሆኑ፥ "አይ!.." በማለት በስጨትጨት ይሉና፥ ሳያስቡት ሰብአዊ ርህራሄን የሚያንጸባርቅ የሃዘኔታ ቃል ካፋቸው ይወጣል። ሌላ ጊዜ ደግሞ፥ ያው ያዘነልኝ ሰው፥ ካጠገቡ ሌላ ሰው ያየ እንደሆነ፥ "ምን ይህ! ደንቃራ!.." ብሎ፥ መሬቱንና እኔን አንድ ላይ አድርጎ፥ ከፉኛ የጎዳኝ በማስመሰል፥ ይረግጠኛል። ይህ በተደጋጋሚ የተገነዘብኩት ሁለት አይነት የሰው ጠባይ ይገርመኛል።

ሞቼ በነበረ ጊዜ የተገለጠልኝ ምሥጢር ይህ ነው፡- ሰዎች በተፈጥሮ ደጎች ነን፤ ግን የተጣልንበት አለም ክፉ እንድንሆን ያደርገናል። አዎ! የሰዎችን ውስጣዊ ደግነት የሚሸፍን አለም ውስጥ ነው ያለነው። ታዲያ፥ ጥፋተኛው ማነው? ሰው ወይንስ ምድር (አለም)[8]?

## **የምሽት ትርኢቶች**

መሸትሸት ማለት ሲጀምር፥ በምድር ላይ የነገሡ የቀበሌ ባለ ሥልጣኖች የከፍተኛ ክልል ውስጥ የሚገቡትን ግለሰቦች እንዴት እንደሚያሰቃዩአቸው ከዛ ከተጣልኩበት ሥፍራ ሆኜ፥ በፍርሃት፥ አይኔን ገለጥ እያደረግሁ እመለከት ነበር። ማታ ማታ ሲሆን፥ አልፎ አልፎ የማየው ምድራዊ ትእይንት፥ ይህች ምድር በእውነት፥ በእውነት ገሃነመ እሳት መሆኗን አረጋገጠልኝ።

---

[8] ይህንን አስመልክቶ - "የእንፋረዳለን ቅዠት" በሚል ርዕስ አንድ ግጥም ከሁለተኛው መጽሐፍ ይገኛል።

ከከፍተኛው አጥር ግቢ ውስጥ አንድ ትንሽ የጨለማ ቤት አለች። በዚህ ውስጥ አስራ አምስት የሚሆኑ ግለሰቦች ይኖራሉ። ቁጥራቸው ሁል ጊዜ አስራ አምስት ነው። አይጨምርም፤ አንዳንዴ ይቀንሳል፥ ግን ቶሎ ይተካል። በውስጡ ያሉት ጸሐይን (ወይንም ሌላ ብርሃን) ለማየት ያልተፈቀደላቸው ናቸው።

ጊዜ ባነገሣቸው "አብዮተኞች" አስተሳሰብ ከጨለማ ቤት የሚገቡት ኃጢአተኞች ስለሆኑ፥ ምድራዊ ገሃነም እሳት የተባለውን በደንብ ማወቅ አለባቸው፤ እነርሱ የመሞቻቸው ቀን እስኪደርስ ድረስ በጨለማ ውስጥ ነው መኖር ያለባቸው። እነኚህ ከጨለማ ቤት ውስጥ ያሉት፥ የቀይ ሽብር ሲፋፋም በነበረ ጊዜ፥ አብረዋቸው በዛችው ክፍል ውስጥ ታጭቀው ከነበሩት፥ ከእኩለ ሌሊት (ከምሽቱ ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ)፥ ወጣ አድርገው "ጸረ አብዮተኞች" ለሚሏቸው ማስፈራሪያ እንዲሆኑ ተገድለው በየመንገዱ ከተጣሉት የተረፉ ናቸው።

ተገድሎ የተጣለ በጨለማ ቤት ውስጥ ከሚኖር የተሻለ እድል ያጋጠመው ነው። የኢሕአፓ ዲፌንሶች (የጦር ክንፍ አባላት) ቤት እንጂ፥ የእንደኔ አይነቱ ለፈስፋሳ የማይገባበት በመሆኑ ነው ወደዛ ያልተጣልኩት።

ካድሬው "ለአብዮተኞች" ብቻ ከተመደቡ መጠጥ ቤቶች ቆይቶ ሲመጣ፥ ትንሽ ሞቅ ብሎት ከሆነ፥ ከፍተኛ የመሬት መናወጥ ይከተካል። ደስ ሲለው የሚገድል ስለሆነ ነው የሚፈራው (የርሱ ምድብ ሙቶና ከዛ በላይ ከገደሉት መካከል ነው)። "የከፍተኛው ገድል በዘመነ ቀይ ሽብር" በሚል አርእስት ቢጻፍ አንድ ትልቅ መጽሐፍ ይወጣዋል። ካድሬዎች ከሊቀመንበሮች ጋር የአሜሪካን አገር ቴክሳሶች የሆኑበት፤ ወይም ሰዎቹ ወደ ሰይጣኖች የተቀየሩበት ወቅት ነበር ብሎ ማለፍ ይሻላል።

ይገርማል! ሌላ ለየት ያለ ትእይንት አየሁ፤ ከከፍተኛ እስር ቤት ተይዘው ከሚመጡት መካከል፥ አንዳንዶቹ አውቀው ለመገደል ሲሉ የሰከሩ በመምሰል ሲለፋደዱና ሲሳደቡ ቶሎ በጥይት ይቀለባሉ። እነኚህም እንደ እኔ ተንከራተው ተንከራተው፥ አለም ጭልምልም ሲልባቸው፥ ሆነ ብለው ሞትን በመፈለግ የመጡ የኢሕአፓ አባላት ሳይሆኑ አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። እነርሱ ቶሎ የመገደልን ምስጢር በማወቃቸው እና እድላቸው ሲስተካከል (ሲሰምር) ቶሎ ሞትን ያገኟታል።

በግቢው ውስጥ በውድቅት ሌሊት የሚፈጸመውን ሰይጣናዊ ትእይንቶች የምመለከት እኔ፥ ከዛው ከተደፋሁበት ሰው በጥይት ሲገደል ስላየሁ፥ በካድሬው ወይም በሊቀመንበሩ እጅ የምወድቅበትን ወቅት ብቻ በጉጉት እየተጠባበቅሁ የምኖር ሆንኩ። ግን፥ ከዚህ በጣም ዝነኛ - ገዳይ - እስር ቤት የገባሁበት ጊዜ፥ ነገር ከበረደ በኋላ ሆነና፤ የመሞቻዬ ቀን ተራዘመብኝ።

ሰው ሁሉ በሃሳቡ ይኖራል፤ ያ ሃሳቡ የተለየ አለም ውስጥ ይከተዋል። ሰው ሁሉ ለራሱ ጥሩ ነገር ስለሚያስብ፥ በዚህ አለም የማይገኘውን እጅግ ጥሩውን ነገር ያስመለክተዋል። ያ ጥሩ ነገር ጥሩ ከመሆኑ የተነሳ ከምድር ላይ አይገኝም በማለት፥ ሃሳብ ወደ ላይ - ወደ ሰማይ (መንግሥተ ሰማይ) - ወደ መንፈስ ይመጥቃል። ታዲያ ሰው ይህን በማሰቡ ምን አጠፋ? በእውነት ያለ ነገር በመኖሩ ምክንያት አይደለም ወይ በሰው ሃሳብ ውስጥ የሚቀረጽ? በህልሜም ሆነ በቅዤቴ፥ ያየሁትን፥ ለኔ መንግሥተ ሰማይ የመሰለኝን እያሰብኩት፥ አሁን ካለፍርኃት፥ ማንም ሰው በማያውቀው፥ ለኔ የኔ የሆነውን ውስጣዊ ደስታዬን እየተመገብኩ ኖርኩ።

**የጓዶች ፍቅር**

በሁለት ሳምንታት ውስጥ ማንነቴ ተጣርቶ ተደረሰበት። ታስሬ የተፈታሁ መሆኔና ከኔ ጋር በፓርቲ ውስጥ ይሠሩ የነበሩ አሁንም በሌላ ከፍተኛ እስር ቤት እንደታሰሩ መሆናቸው ታወቀ። ኮድ የተባለውም፥ ለኔ ለጊዜው መስሎኝ ነው እንጂ፥ በየቀኑ ለኔ ሲል ኮድ እየሠራ የሚጠብቀኝ እንደማይኖር እነሱም ስለገባቸው፥ በእልህ ብቻ ቀጥቅጠው ሊገድሉኝ አልፈለጉም።

ስለኔ ጉዳይ የከፍተኛው ሊቀ መንበርና ካድሬው ይጨቃጨቁ ጀመር። ሊቀመንበሩ "ይህ ግለሰብ ከፍተኛ ተሳትፎ ኖሮት ሊሆን ይችላል፤ ግን እንደነጋበት ጅብ መሄጃ አጥቶ ሲንከራተት ነው የተያዘው። ባሁኑ ወቅት ኢሕአፓ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራችን ውስጥ ነው ያለው። ስለዚህ ካሁን በኋላ ያንድ ግለሰብ መገደል ለአብዮታችን ምንም የሚያመጣው ለውጥ ስለሌለ፥ እጆቹን ፈትተን ከሌሎቹ እስረኞች ጋር ቢደባለቅ ይሻላል" የሚል ሃሳብ አቀረበ።

ካድሬው ደግሞ፥ "ቆይ! ትንሽ ይቀጥቀጥ! ያንድ ግለሰብ መገደል ለአብዮታችን ምንም የሚያመጣው ለውጥ ባይኖርም፥ የአንድ ኢሕአፓ አባል እንቅስቃሴ ለአብዮታችን ጠንቅ መሆኑን አለመገንዘብህ ከአንድ የከፍተኛ ሊቀመንበር የሚጠበቅ አልነበረም!" ብሎ ተቆጣ። ሊቀመንበሩም ዝም አለና እንደተስማማ ሆነ።

አሁንም ሁለት እጆቼ የኋሊት በገመድ እንደታሰሩ ናቸው። ለአንድ በግ የሚታዘነውን ያህል ሃዘኔታ ከሰዎቹ አላገኘሁም። ምን ይደረግ! በግን ቢያስሩት እርሰው ሊበሉት፤ እኔን ምን ያድርጉኝ።

የካድሬው እርግጫ አጥንቶቼን አድቆታል። ደግነቱ እንዳልሞት ሕይወቴን የሚጠግኑልኝ ሴቶች የድብቅ እንክብካቤአቸውን አላቋረጡም።

ይህ በዚህ እንዳለ፥ ካድሬው ለከፍተኛ አብዮታዊ ግዳጅ ተፈልጎ ወደ ሌላ ሥፍራ ተቀየረ። ከዛ በኋላ የከፍተኛው ሁኔታ ተሻሻለ። ካድሬው በሄደ ማግስት ሊቀመንበሩ እጆቼን ፈትቶ ከሌሎች የኢሕአፓ እስረኞች (ጓዶች) ጋር ቀላቀለኝ። በዚህ እኔን ባስገቡኝ ክፍል ውስጥ ሃያ ስንሆን፥ በኢሕአፓ መዋቅር ውስጥ የነበረን ተሳትፎ የተለያየ ነበር።

በዛች ጠባብ ክፍል አይምሮን ለማዝናናትና ለመርሳት የማይወራ ወሬ የለም። የተረት፥ የታሪክ፥ የግጥም፥ የዘፈን፥ የመዝሙር፥ የኩምክና ችሎታ ያላቸው ሁሉ እራሳቸውንና ሌላውን ለማስደሰት በሞቃት ስሜትና በፍቅር ይሳተፋሉ። በመጀመሪያው አንድ ወር ያህል እንደ ታማሚ ሰው ሆኜ ብዙ አላወራም ነበር። ከእስር ቤት ውስጥ ሁሉም ስለራሱ ሲያወራ በያንዳንዱ አይምሮ ውስጥ የሚያስጨንቅ ሃሳብ ፈታ ይላል። እኔም እንደነሱ ስለራሴ እያወራሁ ከጭንቀቴ እንድላቀቅ ጓዶች ይሻሉ። ግን አልሆነላቸውም። እኔ ብዙ ዝም ስል ስለራሴ ማውራት የማልፈልግ በመሆኔ ብቻ ሳይሆን ብዙ ነገር ስለምረሳ፥ ባስታውስም የማይገቡኝ ነገሮች ስለሚበዙ እንደሆነ ጓዶቼ አልተረዱልኝም። ግን አልፎ አልፎ የምናገረው ሁሉ ያስገርማቸዋል፤ አንዳንዴም ያስቃቸዋል።

ብዙዎች ሲዝናኑ ደስ ይለኛል፤ ግን አንዳንዶቹ (በኢሕአፓ ተሳትፏቸው ከፍተኛነት ጭራሽ የማይፈቱ የሚመስላቸው) መሬት እየቆረቆሩ  ሲያንጎራጉሩ፡-

አልነገርኩሽም ወይ ባጥር ተንጠልጥዬ፥

ከእስር ቤት ከገቡ መውጣት የለም ብዬ፤

ለምን የኔ ሕይወት ካንቺ ተጣመረ፥

እንደማጣሽ ሳውቀው ልቤ ተሸበረ።

ጉድ እኮ አረገችኝ፤ ጉድ እኮ ሠራችኝ፤

እውነት  አሳውሮኝ፥ በአንቺ እውነት ታሰርኩኝ፥

ስላንቺ ማሰቡ ጭንቀት ሆነብኝ።

ጉድ እኮ ዘየቴ፤ ጉድ እኮ ቀናቴ ይሏታል ይህችን ልጃገረድ  አብዮትና በውስጧ የነበሩ እክሎችን ሁሉ በማጠቃለል። እንደምንም ይመሻል፤ እንደምንም ይነጋል።

በአንድ የተወሰነ ወቅት የከፍተኛው እስረኞች ሁሉ (በተለያዩ ክፍሎች የነበርነው ሁሉ) በአንድ አዳራሽ ውስጥ እንድንዛወር ተደረገ። ለምን ይህ እንደሆነ ሁኔታው ተረስቶኛል። ሁላችንም ብርድ ልብሶቻችንን እየያዝን ወደ አዳራሹ ገባን።

ከዚያም ሁላችንም እንደ ቀድሞው በየክፍላችን እንደ ነበርነው ተፈላልገን ተቀመጥን። ትንሽ ቆይቶም፥ መኝቶቻችንን አስተካከልን።

በአዳራሹ ውስጥ ለመጀምሪያው ቀን ብቻ ደህና ተኛን። ግን ከቀን ወደቀን ቁንጫዎች እየበረቱ እንቅልፍ ያሳጡን ጀመር። አንዱ ሲገላበጥ፥ ሌላውም ሲቀሰቀስ፥ እንዲሁ ከዳር እስከዳር መተረማመስ ሆነና፤ ለጤንነታችን በቂ የሆነውን እንቅልፍ ማግኘት አቃተን።

አንድ ቀን፥ ከጎኔ ለሚተኛ፥ በእድሜም ጠና ያለ ሰው፥ ቀስ ብዬ፥ “እያንዳንዳችን የራሳችን ቁንጫዎች ከለበስነው እንዳይወጡ ጥርቅም አድርገን ይዘን፥ ዝም ብለን ብናጠግባቸው እነርሱም ሲጠግቡ እንቅልፍ ወስዷቸው ይተኛሉ፥ እኛም እናርፋለን። አለዚያ፥ ሆዳቸውን ለመሙላት ሲሉ እነርሱ ሲራወጡ እኛም ስንገላበጥ እንቅልፍ ላናገኝ ነው። እስቲ ይህን ዘዴ እንሞክረው” አልኩት። እርሱም ይህንን የነገርኩትን በማጣፈጥ፥ ድምጹን ጎላ አድርጎ እንቅልፍ ለወሰደውም ላልወሰደውም እንዲሰማ አድርጎ ተናገረ። ረጋ ያለ መካሪ፥ በእስረኞችም መካከል የተከበረ ስለነበረ እርሱን ሰሙትና ሁሉም በዚህ ሃሳብ በመተባበር፥ ቁንጮቻቸውን ማጥገብ ጀመሩ። በማግስቱና ከዛ በኋላ የተሻለ እንቅልፍ ተኛን።

በአዳራሹ የቆየነው ለሁለት ሳምንታት ብቻ ነበር። ከዛ በኋላ ቁንጫ ወደሌለባቸው ክፍሎቻችን ተመለስን። ከዛም የተለመደውን ወሬ ቀልድና ጨዋታ ቀጠልን። ብዙዎቹን ትንሽ ነገር ያስቃቸዋል። ያም በእድሜው ጠና ያለ ሰው ቁንጮቹን ስለማጥገብ ሃሳብ የፈለቀው ከኔ መሆኑን ስለተናገረም እንደሆን እንጃ፥ እንዳው የኔ ነገር ያስገርማቸውና ያስቃቸው ጀመር፤ የነርሱም ሳቅ ለኔ መድኃኒት።

ሁሉም ለኔ ሲያስቡልኝ፥ ዝም ብዬ የነበርኩትን ቀስ በቀስ እንደምንም ሲያናግሩኝ፥ ሲንከባከቡኝና ሲያጽናኑኝ፥ ሰው ከሰው ጋር ከሆነ ምንም ቢደርስበት ሁሉን ችግር ሊወጣው እንደሚችል ሲያስተምሩኝ፥ እኔም ከእንቅልፉ ብንን ብሎ እንደተነሳ ሰው ጤናማ ሆንኩ። ያለሁበት የደጋግ ሰዎች እስር ቤት መሆኑ በደንብ ገባኝና ተዝናናሁ። እኔን እንዲህ ውድድ የሚያደረጉኝ ለምን እንደሆነ እየገረመኝ፥ በሚያስተሳስር ጓዳዊ ጓደኝነት ጣፋጭ ኑሬዬን ቀጠልኩ (በእውነት የነርሱን ውለታ በሰማይ እንጂ በምድር መክፈል ይከብዳል)።

**ስለ መፈታት ወሬ**

እስረኞች ሁሉ እንደየጥፋታቸው እየተመዘነ፥ የሚፈቱትን ለመፍታት፥ የማይፈቱትን ደግሞ ወደከርቸሌ እስር ቤት በመላክ፥ የከፍተኛውን ጽሕፈት ቤት የቀን ተቀን ጉዳዮች ሥራ ማስኬጃ ብቻ ለማድረግ እቅድ ከወጣ ሰንብቷል። ስለ መፈታት ወሬም ብዙ ይወራል፤ በዚህ በጭንቅ ሰዓት "አንቱ! አንቱ! አይፈቱኝም?" ያለችዋም የዋህ ይቀለድባታል።

የከርቸሌው ሃሳብ ከመጣ በኋላ መዝናናት ጀመርኩ። ሁላችንም የእስር ቤት ኑሮን የተለማመድን ስለሆንን፥ አንዳንዶቻችን፥ በተለይ ዘመዶቻችን የሚኖሩበት አካባቢ ለከርቸሌ የሚቀርብ ከሆነ፥ ከዛው ከርቸሌ ለመሸጋገር እና እዛ ለመኖር እንመኛለን። እኔም ያቺን ቀን ስጠባበቅ ቆየሁ። ሆኖም እፈታለሁ/አልፈታም እያልን ሁለቱንም በልባችን ማሰብ አይቀርምና፤ ወሬ የተባለ ሁሉ መደምደሚያው ስለመፈታት የስነ አይምሮአዊ ተስፋ የሚሰጥ አይነት መሆን አለበት።

እኔም፥ ያ እጄን የፈታኝ ሰው ምንም ቢሆን እኔን ከእስር ቤት መፍታት አያቅተውም የሚል ሃሳብ ይመጣብኝ ጀመር። እንደአጋጣሚ ሆኖ ነው መሰለኝ፥ "አንድ ሰው ሰይጣናዊ ቢሆንም መልአካዊ ጠባይም በውስጡ ይኖረዋል.." እያልኩ አስባለሁ።

ያ ሲጠበቅ የነበረ ቀን ደረሰ። ወደ ከርቸሌ የሚሄዱት እስረኞች ስም ተጠራ። በፓርቲው ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸውም ያልነበራቸውም ወጣቶች ስም ሲጠራ ሁላችንም ተደናገጥን። እርስ በርሳችን አይዞህ፥ አይዞን መባባል ሆነ። እኔም "አይዟችሁ፥ ከእንግዲህ ወደ ከርቸሌ ብንሄድም፥ ከዛ ደግሞ ሌላ ኑሮ እንመሠርታለን.." እያልኩ ማደፋፈር ጀመርኩ።

አንዱ ስለሌላው መፈታት ያስባል። እኔ እንድፈታ የሚያስቡልኝ ብዙዎች ነበሩ። በደጋግ ሰዎች መካከል የሚኖር መልካም ምኞት በምግባር ተለውጦ አየሁት። እጅግ ይገርማል፤ ተፈተሃል ተባልኩ። እኔስ ተፈታሁ ከማለት ይልቅ፥ አመለጥሁ ማለት ነው የሚቀለኝ።

ተፈታሁና ወደጠላሁት አለም ተተፋሁ - ተለቀቅሁ፥ ያውም መፈታቴን ከሚያስረዳ የመታወቂያ ምስክር ወረቀት ጋር።

እስካሁን ያወራሁት ሁሉ በእውነት፥ እውነት ስለሆነና በመርካቶ አብረን የታሰርን ጓዶቼ ስለሚያውቁት፤ እኔ ይህን ሁሉ ስጽፍ በስሜት እያለቀስኩ እንደሆነ ይገባቸዋል፤ እነርሱም ሲያነቡት በትዝታ እንባቸው ይፈሳል፤ አውቃለሁ።

እስከ ዛሬ ድረስ፥ ችዬ ባፌ ሳልናገረው የቀረሁትን (ያቃተኝን) ከዝምታ የማይሻል ወሬ የጻፍኩት፥ በዚህና በሚከተሉት መጻሕፍት የተካተቱ ፍሬ ሃሳቦች አመጣጥ ከየት እንደሆነ፥ መድረሻቸውም እስከየት ድረስ እንደሆነ ግልጽ ማድረግም ስላስፈለገ ነው። ከገዛ አገሬ ያተረፍኩት የስነአይምሮ ጠባሳ ሲያስለፈልፈኝ፥ ከመጥፎው ጎን ጥሩውን ለማየትም እየታገልኩ ሆነና፤ ሰው በሥጋውና ለሥጋው ብቻ እንደማይኖር፤ በመንፈሱ እና ለመንፈሱም እንደሚኖር የተማርኩትን ማካፈሌ መስሎኝ፥ ደብቄ ማቆየት ያቃተኝን (ጊዜ ከዝምታ ፈልቅቆ ያወጣውን ወሬ) ተናገርኩ። እኔም በምክንያት ሸክሜን አራገፍኩ። በምክንያት አልኩ፤....በጣም ለምትወደኝና ለተለየችኝ አውርቼ ያልጨረስኩትን ወሬ ነው አሁን አውርቼ የጨረስኩ።

ሲያወሩት ደስ የሚል፥ ምድራዊ ክብር የሚሰጥ የጀግኖች ታሪክ ሲወራ ደስ ይላል፤ በአንጻሩ፥ እንዲህ ከመደበኛ ወሬዎች ሁሉ "ለየት ያለ ወሬ" ቢወራም፥ አንዳንድ ግለሰቦች ጀግንነት ሳይጎድላቸው፥ ግን ሁኔታዎች በበላይነት ሲቆጣጠሯቸው ማየቱ አይከፋም፤ ይህም ትምህርት - ታሪክም ሊሆን ይችላልና።

አንዳንድ ሰዎች ሳይወዱ በግዴታ የተደፈቁበት ሁኔታ ትንሽ ቢያስመስላቸውም፥ እነርሱ የውስጣቸውን ጥሩነት ብቻ እየተመለከቱ ወደፊት እንዲጓዙ ለእነርሱም ምክር ሊሆናቸው ይችላል።

መቼም ታሪክን በግለሰብም ሆነ በአገር ደረጃ በመገምገም፥ መለስ እያሉ ያለፈውን ሕይወት መመርመር የተለመደ ነው። ታዲያ፥ የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም እንደሚባለው ሳይሆን፥ በአንድ የተወሰነ ወቅት የብዙ ሰዎች ስሜቶች የቆሰሉበትን ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልኩ አይቶ፥ ግን ከክፋቶችና ከክፉ ቀኖች ባሻገር ጥሩነትና መልካም ቀን መኖሩንም ማሰብ ይጠቅማል። ሁሉንም ረስቶ፤ ክፋቶችን ሁሉ አስወግዶ (በመንፈሳዊነት) ወደፊት መራመድ ይቻላል።

በአንድ አገር ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ ቢመጣ፥ ያ ለውጥ በቀላሉ አልመጣም፤ ለዛ ለውጥ ተሳታፊ የሆኑት፥ ከሴትኛ አዳሪዎችና ጠላ ሻጮች ጀምሮ፥ እኛም ሁላችንም ነን። የአንድን አገር ታሪክ የሚወስነው የጠቅላላ ሕዝቦቿ ሥጋዊና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በመሆኑ፥ እንዲህና የመሳሰለው የግለሰብ ወሬ በታሪክ ባይመዘገብም፥ የግለሰቦችን ተሳትፎ፥ መጠንና ይዘተን ያሳያል። በዚህ ጽሑፍ የቀረበውን የመሳሰለ በአፍ መናገር የሚያቅት ብዙ የተደበቀ ታሪክ እንደሚኖር አያጠራጥርም።

አንዱ ሲያለቅስ አይቶ ሌላውም እንደሚያለቅስ ሁሉ፥ ለመኖር ፈቃድ ተሰጥቶት የሚኖር ሰው ሁሉ የሌሎችንም መንፈሶች ተሸክሞ የሚኖር መስሎኝ፤

በግርፋት ብዛት ደምተው የሞቱ የምወዳቸው ጓደኞቼ.. ወገኖቼ ሁሉ ትዝ እያሉኝ ጻፍኩት።

በቆራጥነት ታግለው ካለፉት ጎን - በአሲምባ፥ በበጌምድር ገጠር የነበራችሁ፥ ይህ የኛ የኢሕአፓዎች ታሪካችን ባለ ብዙ ዘርፍ መሆኑን ተመልከቱት። መናገር ሲያቅተኝ የነበረውን ታሪኬን፥ ዛሬ ለናንተና ለሌሎችም ከዚህ ምድር ለተለዩኝ ጓደኞቼ (ጓዶቼ) ስል አወራሁ። የውሃ ነፋስ ተነፈስኩ፤ የዝምታ ዕዳዬንም ከፈልኩ።

ከእንግዲህስ በቃኝ ብዬ ተረጋግቼ መኖር ስጀምር፤ ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ ተፈላላጊ ችግሮች እርስ በርስ ተጠራርተው ደረሱብኝ (የስነ አይምሮ መረበሽ)። አንዳንድ ቅሪተ ሃሳቦች ከአይምሮ ቶሎ ስለማይጠፉ፥ ከትዝታም በላይ ይሆናሉ። ያሳለፍኩት ሁሉ፥ በአንድ ወቅት ተመልሶ መጣብኝና፥ ካይምሮዬ አልጠፋ ብሎ ነው፥ የራሴን ጭንቀት ለማቃለል ስል (ተረጋግቶ ለመኖር ስል) ይህንን ሁሉ የጻፍኩት።

## <u>ከፖለቲካ ውዝግቦች ባሻገር - መልካም መንፈስ</u>

እጅግ ብዙ መከራ የደረሰባቸው የብዙ ታጋዮች ወንድሞችና እህቶች፥ አባቶችና እናቶች ታሪክ ቢወራም ባይወራም፥ ቢጻፍም ባይጻፍም፤ የሁሉም ታሪካዊ አቅጣጫው አንድ ነው። የሚያመራውም ከግለሰብ ወደ ሕብረተሰብ፥ ከሥጋዊነት ወደ መንፈሳዊነት ነው። ይህም ሂደት የኋላ ኋላ በመንፈሳዊ ግንኙነት ተዋሕዶ እንደ አንድ አቢይ ክስተት (የአንድነት መንፈስ) በጉልህ የሚታይበት ወቅት ያስገኝ ይሆናል።

ወገኖቼ ሆይ! በመኢሶን፥ በኢጭአት፥ በኢኮፓ፥ በማሌሪድ ወይም በግል የታገላችሁ ብትሆኑም፥ የናንተን የትግል መንፈስ እንደቀላል ነገር አትዩት። በረቀቀ መንፈስ (እናንተ በሚመስላችሁ መንገድ) ትግላችሁን ቀጥሉ፤ ኢትዮጵያ የሁላችንንም ሞቃት ተሳትፎ ትፈልጋለችና። የታሪካችን ምድራዊ ጎኑ ቢረሳ፥ ሰማያዊ (መንፈሳዊ) ጎኑ እንዳይረሳ "ያንን" ብዙ ሰው ሊመለከተው ያልቻለውን የእውነተኛ የኢሕአፓዎች በጎ አሳቢነትና መልካም መንፈስ - ስሜት (ወኔ) በየቦታውና በያቅጣጫው "ልዩ በሆነ መንገድ" እንቀስቅሰው። ነፍሳማው የሙታን ድምጽ ከመቃብር ይጮሃል - ይጣራል፤ ተከቶን ታጋይ ያልፋል፤ ትግላችን ይቀጥላል።

ጊዜው ተለውጧልና፤ ሰውም እንዲሁ ይለወጥ ዘንድ ግዴታ ሆኗል። ግን፥ ቢመረመር ሁላችንም አንድ ነን። በፖለቲካ የ<u>መ</u>ለያ ስም ቢሰጡን፥ ኢትዮጵያ የሚለው ነው እስካሁን የቀረው ስማችን፤ በምድርም በሰማይም የዘለአለም መጠሪያችን።

ሰዎች ሁሉ የመንግሥት ሥልጣን ሲጨብጡ የሕዝቦችን ጆሮ እየኮረኮሩ ያሰቃያሉ፤ አንዳንዶቹ በጠብመንጃ፥ ሌሎቹም እንደ ሳር - እንደ ጭራሮ በመሳሰለ

ነገር። አገራችን ለወደፊት የምትራመደው በአንድ ፓርቲ አመለካከት ብቻ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ፥ ከልዩነቶች ጋር ሁሉ፥ እርስበርስ በመከባበርና ለአንድ አገር በማሰብ ካልሆነ በስተቀር፥ የሚያስከትለውን የእርስ በርስ መገዳደል (አላስፈላጊ እልቂት) ተመልክተናልና፤ እርስ በርስ በመቻቻልና ግላዊ ስሜቶችን ገታ እያደረጉ፥ ለጋራ ጥቅምና እድገት፥ ለማሕበራዊ ኑሮአችንም መሻሻል በማሰብ ነው አገራችን ኢትዮጵያ ከፍ ከፍ የምትል። የአንድ ግለሰብ ወይንም የአንድ ፓርቲ የትግል ውጤት በአንድ ትውልድ ውስጥ ላይታይ ይችላል። ለዚህ ነው በየአቅጣጫው የሚደረገውን የሰውን ሁሉ ተሳትፎ ማክበር የሚያስፈልግ።

ለገዛ አገሩ ጠላት የሚሆን አይኖርም። ከውዲቷ አገራችን የማይወጣው መንፈሳችን ብንርቅም እንድንቀርብ ያደርገናል። ከታሪክ እየተማርን የተሻለውን እናድርግ እንጂ፥ ያንኑ ስህተት መልሰን አንድገመው።

ኢትዮጵያችን የእውነተኞች መንደር ተብላ እንድትጠራ፥ ከተለያየ አቅጣጫ የእውነት ብርሃን የምትፈነጥቁ ሰዎች ሁሉ፥ በዚህች ምድር ላይ ስትኖሩ፥ ለጠቅላላ ሰብአዊነት እንጂ ለራሳችሁ (ለግላዊነታችሁ) ብቻ ሳታስቡ ከሆነ፥ **እናንተ** ለዘለአለም ኑሩ።

አንቺም የድል ኮከብ፥ ከመንደር ያለሽው፥
ወጣ በይ ከጓዳ፥ ወገንሽን እዪው፤
ብርሃን ሰጪ አካል፥ መሆንሺን አትርሺው፤
ተደብቆ ኑሮ፥ መሸነፍን ፍሪው፥
ድሉ የሕዝብ እስኪሆን፥ ተስፋሺን አታጥፊው።

# ምዕራፍ ሦስት

## ቅሪተ ሃሳብ

ከእስር የተፈታሁበትን ወረቀት (የነፃነት ፓስፖርት) በኪሴ ይዤ፥ እንደገና በአዲስ አበባ መንገዶች ውስጥ መዘዋወር ጀመርኩ። ከከፍተኛ ወደ ከርቸሌ ተሸጋግረው ከዚያ ብዙ የቆዩትን ለተወሰኑ ጊዜያት ብቻ ጠየቅኋቸው። ምድራዊ ሁናቴዎች፥ የኔም አሻግሮ አለማየትና ራስን ወዳድነት ጠባይ ተጨምሮ፥ እስኪፈቱ ድረስ በየሳምንቱ እየሄድኩ ባለመጠየቄ ይቆጨኛል።

መላ ኢትዮጵያ ደግ ነው። ያልታሰሩ ጓደኞቼ ምንጊዜም ጓደኞቼ ናቸው፤ ወገኖቼ ምንጊዜም ወገኖቼ ናቸው። "ወይ ጉድ! ለካስ አንተም እንዲህ ያለህ ነበርክ!..."ብሎ የራቀኝ ማንም ሰው አልነበረም። ታዲያ፥ አንዳንዶቹ አስተሳሰቤን ሲመለከቱት፥ ማንም ሰው እራሱን የሚያመሳስልበት ሲያጣ፥ የገዛ ሕይወቱ ከሁለቱ አለም ለአንዱም የማይጠቅም እንደሚሆንበት ይሰማቸውና፥ "እህ!.." ብለው ዝም ይላሉ። እኔ ግን ራሴን ለቀቅ እያደረግሁ አካባቢዬንም እየመሰልኩ እንድኖር የሚያስችል ጠባይ የለኝም።

በዚሁ ልለውጠው ከታገልኩለትና ተሸንፌ ከተውኩት አለም ውስጥ ብቻዬን ያለሁ መስሎኝ ተከፍቻለሁ። ለዚህ አለም ሕይወት ትርጉም ስላጣሁበት ለቀሪ ጓደኞቼም ግራ የማጋባ ሆንኩባቸው፤ ጥንትም በደንብ አያውቁኝ ነበር፤ አሁን ደግሞ የባሰ እንግዳ ሆንኩባቸው።

የኮሙኒስት ስርዓት መሠረታዊና መንፈሳዊ መሰል (ምኞታዊ) አስተሳሰብ ይማርከኛል። በሰዎች ልጆች ፍቅር፥ በማንኛውም ረገድ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ኑሮን እመኛለሁ። ለኔ ኮሙኒስት መሆን ማለት የራስን ድሎትና ደስታ ሁሉ ለጋራ ድሎትና ደስታ አሳልፎ በመስጠት ውስጥ፥ የራስን ደስታ ማግኘት ማለት ነው። የክርስቲያናዊነትም አላማ ይህንኑ የሚመስል ስለሆነ ይመስለኛል፥ ከኮሙኒስትነት ሲወጡ ወደ ክርስቲያናዊነት (ሃይማኖተኛነት - መንፈሳዊነት) ዘንበል ማለትን በገሃድ የተመለከትነው።

በኮሙኒስት ዶክትሪን፥ በሳይንስ እውቀት፥ በግትረኛነትና አመጸኛ ጠባይ፥ እኔ ከእኔነቴ በስተቀር ሌላ ምን አለብኝ ብዬ፥ የራሴን ሕይወት በራሴ ለመምራት ስሞክር፤ "ተው አንተ!..." ብሎ የሚገታኝ ኃይል ተቋቋመኝ። ሰዎች ኮሙኒስት ቢሆኑ፥

ሃይማኖተኛም ቢሆኑ፥ ምንጊዜም የደግነታቸው ውስጣዊ ጠባይ አይለቃቸውም። ግን በሰዎች መካከል እየገባ የሚያበጣብጥ አለ። ከአገሬ ከኢትዮጵያ ጋር እራሴን ማጣጣም አቃተኝ። ኢትዮጵያ የማላውቃት (ባይተዋር) ሆነችብኝ - በባእድ አገር የምኖር መሰለኝ።

ያ የኮሙኒስቶች ህዋስ፥ በልዩ መልኩ የጠራ መንፈሳዊነትን ለማዋቀር ነበር እንጂ፥ እኔስ የኑሮ አቅጣጫዬ የጠመንጃቸውን አፈሙዝ እየተመለከትኩ እየሆነብኝ፥ በየጊዜው እየተሳቀቅሁ መኖር ሰለቸኝ። ትጉህ ሠራተኛ ተብዬ፥ በሚከፈለኝ ገንዘብ በሥጋዬ የደላኝ ብመስልም፥ ውስጣዊ ስሜቴ እና ስነ አይምሮአዊ ግንዛቤዬ ለየብቻ ሆነው ብዙ ብዙ ያናግሩኛል።

በሥራ ችሎታዬ የተወደድሁ ብሆን፥ በልቤ ከዳተኛ የሆንኩ እየመሰለኝ፥ ተለውጬ፥ በከፋች ምድር ላይ ለረዥም ዓመታት እንድኖር ያደረገኝን የድሮውን እራሴን አጣሁት፤ የወደፊቱንም እኔን ማየት ተሳነኝ። ይህን ያህል ዓመታት በኖርኩባት አገሬ እራሴን ማግኘት አቃተኝ፤ ለሚኖሩ ሰዎች ጥላ ሆኜ የቀረሁ መሰለኝ። ቀኑ ይረዝምብኝ፥ የእስር ቤት ለዛ (የጓዳዊ መተሳሰብና ፍቅር) ይናፍቀኝ ጀመር። ለሕዝቦች ተሰጥቶ የተመለሰ ትራፊ የሥጋ ሕይወት፥ በሰዎች መካከል - በአዲስ አበባ መንገዶችም የሚመላለስ እኔ፤ ሁለት ሰው - እኔ እና እኔ ባንድነት ሆነን እንኳን አንድ ሰው ለመባል ያልበቃን መስሎኛል።

ከምድራዊነት ውጪ (ፖለቲካ የሌለበት) አለም ውስጥ ገብተን በመንፈሳዊነት ለኢትዮጵያ ጥሩ ጥሩውን እየተመኘንና እየጸለይን ብንኖርም፥ ከአይምሮአችን የማይጠፉ ቅሪተ ሃሳቦች ይኖራሉ።

## ***<u>መንግሥታዊ አስተዳደርና ስርዓቶች</u>***

ሰውን ሁሉ በእኩልነት የሚመራ መንግሥታዊ መስተዳደሪያ ደንቦች - ሕግጋትም ይረቃሉ፤ ፖለቲከኞች ይሯሯጣሉ፤ ቅን አሳቢዎችም በየአቅጣጫው ይደክማሉ። ግን ማነው ለጋራ ብልጽግና የቆመ? ማን? ምንድነው የሰብአዊነትን ሁለንተናዊ ህልውናን የሚያስጠብቅ ስርዓት የሚያስገኝ?

በኮሙኒስት አገሮች የተገኘ የሰዎች የሕሊና እድገት ሥጋዊ ስነ አይምሮን አጎለመሰ እንጂ፥ መንፈሳዊነቱን አቀጭጮታል ቢባል፥ ከዚያ የኮሙኒስቶች አገሮች ነዋሪ የሆኑ፥ የሚፈልጉትን ለማድረግ እንዳይችሉ የሚገቱ፥ በብዛት ውስጣዊ መንፈሳዊ ደስታቸውን የተነፈጋቸው እንደሆኑ ይነገራል።

ኮሙኒስት መሆን እግዚአብሔርን ከማመን ጋር ቢሆን ኖሮ፥ ከይትም ይምጣ ከየት፥ የደጋግ መንፈሶች ጣምራነት አቸናፊ ይሆን ነበር (ይሆን?)። ኮሙኒስቶች ሦስት ጥፋቶች ብቻ አጠፉ፡

1ኛ) በእግዚአብሔር አናምንም አሉ።

2ኛ) ምድር ወጣ ገብ መሆኗን አልተረዱም።

3ኛ) የሰው ፍጥረቱ ሁለት አይነት መሆኑ አልገባቸውም።

በፈጣሪ ባለማመናቸው፥ ከሰው በላይ ሁሉን ሊያስተካክል የሚችል እግዚአብሔር መኖሩን አላወቁም። የምድርን ወጣ ገብነት (ለሰው ሁሉ እኩል አለመሆን) በደንብ አልተረዱትም፤ ቢረዱትም በሶሻሊስት ርዕዮት ማስተካከል የሚችሉ መስሏቸዋል። የሰው ልጅ በተፈጥሮው ሁሉም እኩል ሆኖ የተፈጠረ ቢሆንም እንኳን፥ ይህን እኩልነት የምድር አድሎአዊነት ሊለያየው እንደሚችል አልገባቸውም።

የኢኮኖሚ እድገትን በሶሻሊስት ርዕዮተ አለም ሲቀይሱ፥ የሰዎችን አልጠግብ ባይነትና ስግብግብነት በቀላሉ ተመልክተውታል። ይህ የሰው ሁሉ ምድራዊ ጠባይ በኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን ወሳኝነት ወደጎን አደረጉት። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ስርዓት ብቻ ቶሎ ቶሎ ወደፊት መራመድ የሚያዳግት መሆኑን በወቅቱ አላወቁትም ነበረ።

ቀደም ሲል ሌኒኒስቶች ይህን ችግር ከሞላ ጎደል ተረድተውት ልዩ (መለስተኛ) የኢኮኖሚ ፕላን (New Economic Policy) ዘርግተው ነበር። በኋላም ትሮትስካይቶች ይህን የሰዎች ሁሉ ችግር በመረዳት የጊዜያዊ ካፒታሊዝምን አስፈላጊነት ሲሰብኩ ነበር።

እስታንሊኒስቶች ግን፥ የሰውን ውስጣዊ ጠባይ አልተረዱትም፤ ክፉውን ሰው ከደጉ በጉልበት ለይተው ለማላቀቅ የሚችሉ፤ ወይንም ክፉውን ሰው ገድለው ቢጨርሱት የሚቀረው ሁሉ ደግ ብቻ የሚሆን መሰላቸው። የኮሙኒስት ጽንሰ ሃሳብ ከሰው ተፈጥሮ ውስጥ መጥፎውን ማጥፋት የሚችል፤ ኮሙኒስትነትም የምድርን ወጣ ገብነት የሚያስተካከል - የሰውን ጠባይ የሚያርቅ (የሚያሻሽል) መሰላቸው። በአንድ ኃይለኛ ስርዓት ድንጋጌ ብቻ የሰው ሁሉ ተፈጥሮአዊ ጠባይ በጉልበት ወይንም በስብከት አንድ ወጥ ሊሆን እንደሚችል አድርገው ወሰዱት።

ኮሚኒስቶች የሰው ፍጥረቱ ሁለት አይነት መሆኑ አልገባቸውም። በአንድ ካፒታሊስት ልቦና ውስጥ ቅንነትና ክፋት ባንድነት እንደሚኖሩ ሁሉ፥ በአንድ ኮሙኒስታዊ የሆነ ሰው ልቦና ውስጥም ቅንነትና ክፋት ባንድነት ይኖራሉ። የሰው (ሰብአዊ) ልቡና ክፉቱን በቅንነት እስኪለውጠው ድረስ ያ የምናስበው መልካም ስርዓት በቶሎ አይመጣም።

ሰው በሚሠራውና በሚያደርገው ሥራ ሁሉ ዘለአለማዊ አስተሳሰቡ (ጥሩው)፥ እሩቅ ወደ ሆነውና ወደማይጨበጠው አለም ያስመለከተዋል። በዚህ አንጻር፥ የአንዳንድ ዘመን አመጣሽ ሃይማኖቶችን (cults) መሠረታዊ አላማ ብንመረምረው፥ ባሁኑ ጊዜ የማይቻለውን ምድራዊ ሕብረተሰብአዊ አንድነት ለመፍጠር እንደሆነ እንገነዘባለን። በቶሎ ከመፍረድና ስህተተኞች ናቸው ከማለት ይልቅ፥ አሁን ላለንበት ዘመን የማይሆን ነው ብሎ ማለፍ ይሻላል።

በተመሳሳይ፥ ማርክስና ኤንጀልስ እራሳቸውን ከፍ፥ ሌላውን ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ የፊውዳላዊ ርዕዮት (አስተሳሰብ - አመለካከት)፥ ብዙሓኑን ሲጎዳ ተመለከቱና፤ "ይህን በሰብአዊነት ውስጥ ተረጋግቶ የተቀመጠ በሽታ ለማጥፋት እንነሳ፤ የሰውም ልጅ እስከዘለአለሙ ጤነኛ ሆኖ ይኑር።" ብለው አሰቡ።

የማርክስ እና ኤንጀልስን መሠረታዊ ፍልስፍና ብንመረምረው፥ እነርሱም ቢሆኑ መሠረታዊ ፍልስፍናቸው የተጠነሰሰው፥ ለሰው ልጅ እኩልነት በማሰብ፥ ምድራዊ ሕብረተሰብአዊ አንድነት ለመፍጠር ነበር። በቶሎ ከመፍረድና ስህተተኞች ናቸው ከማለት ይልቅ፥ አሁን ላለንበት ዘመን የማይሆን ነው ብሎ ማለፍ ይሻላል።

ያም ሆነ ይህ፥ መልካም አስተሳሰቦች ከክፉው ጋር ሳይጋጩ ለዘለአለም ረግተው አይቀመጡም፤ አንድ ቀን የጠፈር ኃይላት ቀና አስተሳሰቦች ሁሉ በረድፍ በረድፍ ተስተካክለው ሳለ፤ ጊዜው ይርዘም እንጂ፥ አለም አቀፋዊ ወንድማማችነት (መንፈሳዊ - ኮሙኒስትታዊ አመለካከት) መምጣቱ አይቀርም።

የወደፊቱን ለሕዝቦች የሚጠቅም መንግሥት መመሥረት የሚቻለው፥ በከፍተኛ የመንፈሳዊነት እድገት መሆኑን በሃይማኖታዊ ስነስርዓታዊ አስተዳደር የሚመሩ አገሮችም (አንዳንድ የእስላም አገሮች) የሚገነዘቡት ይመስላል። በነኚህ አገሮች ውስጥ ሃይማኖት የበላይነት ስላለው፥ የሰዎችን ሞራላዊነት (መንፈሳዊ ጨዋነት) ከፍ አድርጎታል። ግን የእስላም ወንዶች ብዙ ሴቶች ያገባሉ፤ ሚስቶቻቸውን ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ሸፋፍነው ይደብቋቸዋል። ማታ ማታ ለነርሱ አይን ብቻ እንዲታዩ አድርገው ይገልጧቸዋል። ሴቶቹም ወንዶቻቸው ባወጡት ሕግጋት እየተመሩ በሰውነታቸው ዝቅተኛነታቸውን ባያምኑበትም በግድና በፍርኃት ተቀብለውት ይኖራሉ።

ሴቶች ከወንድ እኩል ወይንም ከወንድ በላይ መብት የነበራቸው ዘመን ነበር ይባላል። የሴቶች መብት ከጠፋ ቆይቷል። ባሁኑ ጊዜ በአለም ዙሪያ ወንዶች ለሴቶች በቂ ክብር አይሰጡም። ሴቶችም በወንዶች ስላልተከበሩ፥ ራሳቸውን ዝቅ አደረጉት፤ ከዝቅተኛነታቸውም የተነሳ አንዳንድ የሚሠሩት ሥራ የማያምር ሆነ።

ብዙውን ጊዜ በዚህ አለም ላይ ለጥሩ ነገር (ለሰላም፥ ለፍቅርና ለደስታ) ምክንያት የሚሆኑ ሴቶች ሆነው ሳለ፥ ወንዶች ሴቶችን ስለማያዳምጧቸው፥ አንድም ይህ ነው በምድር ላይ ጭካኔ የመብዛቱ ምክንያት። ሴትን የመታ ማርያምን የመታ መሆኑን ያላወቀ ወንድ መንፈሳዊ ጎኑ ተደብቆበታል ማለት ነው። በዚህ አኳያ ሲታሰብ፥ የዚች አለም ወንዶች ሴቶችን ባለማክበራቸው የሰብእነት ማንነት (ሰው መሆን ምን ማለት መሆኑ) ቁልጭ ብሎ አልታየም - መንፈሳዊ ጎኑ አልተገለጠም።

በበለጸጉት የካፒታሊስት አገሮች የግለሰቦች ሠርቶ የማደር ችሎታ ፊውዳላዊ መበላለጦችን የደመሰሰበት ሥፍራ ስለሆነ፥ ማንም ለማንም አያጎበድድም፤ በመጠኑም ቢሆን፥ የሰው ልጅ በተፈጥሮአዊ እኩልነቱ ይከበራል። በጦርነት ሳይሆን በድምጻቸው ብቻ የመንግሥት አስተዳደርን የመለወጥ ችሎታ አላቸው። ሰብአዊ መብት ስለሚከበር ሰው በሥጋውም በመንፈሱም ደመቅ ያለ ኑሮ ይኖራል።

ሆኖም፥ ግለሰብ ምድራዊ ፍላጎቶቹን ብቻ እየተከተለ ሲጓዝ ተቆጣጣሪ ስለሌለው፥ ከመጠን በላይ ስግብግብ፥ ከመጠን በላይም እራስን ወዳድ እየሆነ መጥቷል። ይህም ወደተለያዩ ጥፋቶች እያመራ፥ አጠቃላይ ሰብአዊነትን አራክሶታል - የሰዎች ሞራላዊነት (መንፈሳዊ ጨዋነት) ዝቅ ብሏል። ስግብግብነትና ግለኛነት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑም፥ የሰዎች ማሕበራዊ ኑሮ ጠፍቷል፤ ባለ ስነ ስርዓት የሆነውም የጋርዮሽ ጠባይ ተደምስሷል። በሕብረተሰቡ የማይገታ (የማይታረም) ግለኛነት ወደ ሰይጣናዊነት ሲያመራ፥ ይህንን እንደ ሰብአዊ መብት የሚቆጥሩ ይኖራሉ። በካፒታሊስት ስርአት ውስጥ የግለሰቦችን ስንኩል ሥራ የሚገታ መንግሥታዊ ተቋም የማይኖረውም ለዚህ ይሆናል።

በተቀረው አለም (ሦስተኛው አለም) ያሉ ሕዝቦች "ይህችን ምድር በስነስርዓት የሚያስተዳድር መንግሥት ከወዴት ይገኛል?" እያሉ ይጮሃሉ። ፖለቲካዊ ፍልስፍናን እንደነርሱ ያወቀበት የለም። አለም አቀፋዊ ርዕዮት በድሆች አገሮች እንደሚገኝ፥ ሌላ "ሰለጠነ" ተብሎ ከሚጠራው አለም አይገኝም። ግን ይህ ድሆች የበዙበት አለም፥ የፖለቲካ ችግርም የመላበት፥ መፍትሔውም እንቆቅልሽ የሆነበት ሥፍራ ነው። ሃብት በጥቂቶች እጅ ስለሆነ፥ ኃይለኞች የሆኑት በገንዘባቸው እንዳሻቸው ሲኖሩ፥ የተቀረው ሕዝብ በድህነት ይኖራል። ሰው በሰው ላይ ግፍ ሲሠራ በገላጭ ይታያል።

እንግዲህ ባጠቃላይ፥ አንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ከሌላው የማይሻል ከሆነ፥ ገዳም ገብተው የራሳቸውን አስተዳደር ከመሠረቱት በስተቀር፥ ለሰው ልጅ ምንም አይነት ሥጋዊ (ምድራዊ) አስተዳደር የሚበጀው አይመስልም።

የሰው ልጅ በአካላዊ (ሥጋዊ) አለም ውስጥ እየኖረ ከመጥፎ ነገሮች (እራስን ወዳድነት፥ ስግብግብነት፥ ክፋት፥ ወ.ዘ.ተ...) ሊላቀቅ ስለማይችል፥ ያ ፍጹም አስተዳደር ከመሬት ሊገኝ የሚችል አይመስልም። ምናልባት ሶሻሊዝም ሲወድቅ ያዩ፥ እንዲሁም ለወደፊት ካፒታሊዝም ሲወድቅ ተመልክተው የሚማሩ ቢኖሩ፥ ምናልባት የዛን ጊዜ ሁለንተናዊ የሶሻል፥ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መፍትሔ ይፈጠር ይሆናል።

የአንድ አገር ሕዝብ፥ መንፈሳዊ የበላይነቱን አስከብሮ፥ የማንኛውንም አይነት የመንግሥት ሥርዓት (ዲሞክራሲ፥ ሞናርክ፥ ወ.ዘ.ተ...) በንድፈ ሃሳብ (በቲዎሪ) በተግባርም ቢከተል ለክፉ አይሰጠውም ይሆናል፤ ዋናውና ወሳኙ የአጠቃላይ የሕዝቦች መንፈሳዊ ንቃት ስለሚሆን።

እስቲ ከተባለው ሁሉ ያቺን ኢትዮጵያችንን እናውጣትና ወደ ኋላ እንመልከት ላንዳፍታ። ለአለማዊ ኑሮ ተስገብግበን፥ የአንድነታችን ማጠናከሪያ፥ የጥቁር ሕዝቦች መመኪያ የሆኑት ንጉሣችን እና በዙሪያቸው የነበሩ ደጋፊዎቻቸውን ሁሉ እንዲወገዱ ምክንያት ሆንን። በምትካቸውም የተገነባው የስርዓት ለውጥ ብዙ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን አሳየን። በገንዘብ የሚመጣ መበላለጥ ጠፋ። ሰዎች እርስ በርስ ሲከባበሩ አየን፤ ግን በብዛት የመፈራራት መከባበር ነበር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ፥ በፊውዳላዊ ስርዓት አስተሳሰብ የሚመሩ ገዢዎቹን ሲያስተዳድር (ሲያበላና ሲያጠጣ)፤ ኑሮውን ሁሉ ለነርሱ አድርጎ፥ የራሱን ኑሮ ትቶ፥ እነርሱን ብቻ ሲያስኖር ኖረ በፍርኃት። አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍርኃት አልተላቀቀም። አሁንም ስነአይምሮው በነፃነት አያስብም፤ ውስጣዊ አስተሳሰቡን ካለፍርኃት መግለጽ አልቻለም። ጥንት የሚሸልሉትና የሚያቅራሩት ፊውዳሎች ነበሩ፤ አሁን በነርሱ ፋንታ እግዚአብሔር የለም እያሉ፥ አለ የሚለውን የመናገር መብት የሚነፍጉት ናቸው። መንግሥት ለብቻው ኃይለኛ ሆኖ ሕዝብን እንደ ራሱ ፍላጎት ያስተዳድረው ጀመር (ሰብአዊ መብት እንደተረገጠ)።

ከጥንት ጀምሮ በታሪኳ፥ በአገራችን ኢትዮጵያ ጥቂት ጀግናዎች ለራሳቸው ክብርና ለሆዳቸው ሲሉ፥ ጠብ መንጃ ይዘው ሕዝቦቿን እያስፈራሩ፥ ካለውዴታ በግዴታ እንዲገብሩላቸው አደረጓቸው። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ አየር በፍርኃት የተበከለ ሆኗል። ከነርሱ ከጀግኖቹ በስተቀር ሃሳቡን ካለፍርኃት ገልጦ የሚናገር ጠፍቷል። ጥንት በፊውዳሊዝም፥ ዛሬ ደግሞ በሶሻሊዝም፥ እንዲሁ እንዳቅራሩና እንደሸለሉ አሉ፤ (ጥንት ባባቶቻቸው፥ አሁንም በልጆቻቸው)።

በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ጭቅጭቅ የሚከረው ከጥንት ጀምሮ ሥር በሰደደው ፊውዳላዊ ጠባይ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። ፊውዳሎች ሰው የሚለውን አይሰሙም፤ ጆሮአቸው የሚሰማው እነርሱ እራሳቸው የሚናገሩትን ብቻ ነውና።

ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ መሪዎቹ እነርሱና የነርሱው ርዝራዦችና ልጆቻቸው የሰፊውን ሕዝብ የልብ ትርታ ቀስ ብሎ የሚነግራቸውን ሰው አይሰሙትም። የድሃው ተሰሚነት የጠፋበት፤ ታዋቂ ፖለቲከኛ ብቻ የገነነባት አገር።

ይህች ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ በሰዎች ላይ በደረሰ ፈተና የማይማር ሁሉ እየተቀጣ እዚህ ደረስን። ሰው እየተማረ ስህተቶችን ባይደጋግም - ጠባዩን ቢያሻሽል፥ በምድራዊነት ላይ ብቻ የሙጥኝ ከማለት ፋንታ እራሱን ትንሽ ረቀቅ ቢያደርግ፥ በሕይወቱም ውስጥ መንፈሳዊነቱን ቢያጎለምስ፥ ሰላሙን እና የጋራ ብልጽግናውን ማሻሻል እንዲህ ከባድ አይሆንም ነበር።

ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ትግል ያስገኘው የአስተዳደር የስርዓት ለውጥ ትንሽ ወደፊት አራመደን፤ ግን ያልገባን ነገር አብሮን ስለቆየ፥ ከማጡ ውስጥ ጨርሶ መውጣት አቅቶናል። እግዚአብሔርን ክዶ፥ ሃይማኖትን አውግዞ፥ የሰብአዊነት ምድራዊነቱን ብቻ ይዞ የሚጓዝ መንግሥታዊ አስተዳደር ብዙ እንደማይዘልቅ ያስታውቃል።

ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን በመካድ ላይ በተመሠረተ ፍልስፍና ወደፊት መራመድ አልቻለችም (አትችልም)። በዚች ምድር ሰው ከሃይማኖቱ ተለይቶ መኖር አይሆንለትም። ኢትዮጵያና ልጆቿ ከእግዚአብሔር ርቀው ብዙ መቆየት አይችሉም።

**<u>የለውጡ ትሩፋቶች</u>**

የመንግሥት ስርዓት ሲለወጥ፥ የተለያዩ የሕብረተሰብ አካሎችም ልዩ ጠባዮች ማውጣታቸው የማይቀር ነውና፤ እነሆ! ያለፈው እንዳይረሳ ማስታወሻ።

ወታደሮች ትእዛዝ አክባሪዎች ናቸውና፤ ግደሉ ሲባሉ የሚገድሉት ከበላይ አካል የሚሰጣቸው መመሪያ ለአገር - ለወገን የሚጠቅም መሆን አለበት በማለት ይሆናል። በየአቅጣጫው ኢትዮጵያን የሚጠብቃት የእውነት አምላክ እንጂ ሰው አለመሆኑን የተረዱ ወታደሮች ፈጣሪያቸውን በጸሎት እየተማጸኑ ሥራቸውን በማክበር ቢሠሩም፥ ጥሩ መንግሥት መምጣቱ የሚታወቀው ወታደሮች በሥራቸው በሕሊናቸውና በልባቸውም ሲደሰቱ ሲታይ ይሆናል። (ይሆን?)።

ድሆች በወታደራዊው የአስተዳደር ስርዓትም በርክተዋል። ባለ ለስላሳ ልቦች የሆኑ ሁሉ አዝነዋል፤ ተክዘዋል። ባለ ጠጣር ልቦች ደግሞ ለራሴ ብቻ በማለት በገዛ ወገኖቻቸው ላይ እንደጨከኑ ናቸው። የሚበሉት ያጡ ድሆች በምን አይነት መንገድ ምግብ አግኝቼ ሕይወቴ ቶሎ እንዳታልፍ ልከላከል እያሉ ይጨነቃሉ። የሚ<u>በላ</u> ባገኙም ጊዜ ያ ጭንቀታቸው ይወገድላቸውና በሰላም መኖር ይጀምራሉ፤

በመኖራቸው ብቻ ይደሰታሉ። አንድ በእግዚአብሔር የሚያምን ድሃ የሚበላው ካገኘ፥ ቀሪ ሥጋዊ ፍላጎት ስለማይኖረው፥ ልቡ በመንፈሳዊ ደስታ ብቻ ይሞላል። አለም የተሰጠችው ለተቀረው ሰው ቢሆን ደንታ አይሰጠውም፤ የዘለአለም እረፍተን የሚከለክለው የለምና።

ጭቁን ሠራተኞችም በደሞዛቸው ላይ ጥቂት ብሮች ተጨምሮላቸው ደስ ብሏቸዋል። የፖለቲካ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት እየሄዱ ርዕዮተ አለማቸውን ሶሻሊስት አድርገውታል (አስመስለውታል - መስሏቸው ነው)። ቋንቋቸውም የበሰሉ ፖለቲከኞችና ፈላስፎች እንደሚናገሩት አይነት ሆኗል። የፖለቲካውን ትምህርት ለጨረሱትና ለከደሩት (የፖለቲካ ካድሬ ለሆኑት) "ከጸረ አብዮተኞች" እራሳቸውን የሚከላከሉበት አንዳንድ ሽጉጥ ተሰጥቷቸዋል። በሄዱበት ሁሉ ደረታቸውን ነፍተው፥ ጎርደድ - ጎርደድ እያሉ እንደልባቸው "አብዮታዊ ስድብ" ይሳደባሉ። ከፈለጉም ያስራሉ፤ ያሳስራሉ።

ተንኮለኛ ሰው አውቆ ያጠፋል፤ የሥልጣን ጥም ያለበትም ለራሱ ክብርና ጥቅም ሲል የአገሩንና የወገኑን ጥቅም ይለውጣል። ንኡስ ከበርቴዎች ከጭቁን ሠራተኞች የተሻለ ገቢ አላቸው። ቤት የማይሠራ፥ መኪና የማይገዛ ገንዘብ፥ በመጠጥ ቤት ሲበተን ነው ብዛቱ በይፋ የሚታወቅ። ንኡስ ከበርቴ,ዎች በየቡና ቤቱ ይሰገሰጋሉ፤ ጣዕም ያለው ሙዚቃ ይሰማሉ። ሙዚቃውም ለትካዜ ያመቻል። ለአንድ ንኡስ ከበርቴ የሚታሰቡት ሁሉ በርከትከት ስለሚሉ፥ ለብቻ ቁጭ ብሎ ሙዚቃ በማዳመጥ በሃሳብ መመሰጥ የአንድ ግለሰብ የህልውና መጠበቂያ ሥራ ይመስላል።

ሙዚቃ በውስጣዊ ስሜት መንፈሳዊነት የሚታደስበት ስለሆነ፥ ሰዎች ሁሉ ዘና ዘና እንዲሉ፥ ከፉውን ጊዜ እየረሱ፥ ደግ ደጉን እያሰቡ እንዲኖሩ ይጠቅማልና፤ ዘፋኞቹን በደንብ ለማዳመጥ ውዝዋዜአቸውንም በቴሌቪዢን ለማየት ወደ ቡና ቤት ሰተት ማለት ተለምዷል። አንዳንድ ጊዜ አስደስቶ የሚያስፈነድቅ ዘፈን ተፈላጊነት ስለማይኖረው፥ ዝም ብለህ ሙዚቃውን አዳምጥ ተብሎ የተገደደ ይመስል፥ ንኡስ ከበርቴው የሞተ ዘመዶቹንና ጓዶቹን ሁሉ እያሰበ፥ ለሚያዳምጠው ሙዚቃ ከሚስማማ ሃሳባዊ ትእይንት ውስጥ ራሱ ትያትረኛ ሆኖ ይገባል። የኦሮምኛ ወይንም የምንጃር ዘፈን ሲሰማ፥ ድንገት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ሰውነትን ማፍታታት የመሰለ ውስጣዊ ዳንኪራ ያከናውናል። ግን ወዲያው፥ ለዳንኪራና ለደስታ አለመፈጠሩን ሲያስታውስ፥ ቢራውን (ወይንም አረቄውን) ያጫልጣል፤ ከዚያም፥ ትዝታዎችን ሁሉ በመደምሰስ ታዋቂ ወደ ሆነው ስካር ውስጥ ይገባል፤ ገንዘቡን ከፍሎ ይወጣና፥ ከምሽቱ ልክ ስድስት ሰዓት ሲሆን የቤቱን በር በጁ ይነካል።

አጽናኞችም መንፈሳዊ እድሳትን ያሰጣሉ። እንደ ንኡስ ከበርቴዎች ለመዝናኛ የሚሆን ገንዘብ የሌለው ተረፈ ኢሕአፓ (ወይንም ሌላው) በሳምንት አንድ ቀን ሰንበትን ጠብቆ ከቤተ ክርስቲያን ሲሄድ ብቻ ነው ደስታው። ወቅቱ ብዙ ወጣቶች ከቤተ ክርስቲያን መሄድ የጀመሩበት ወቅት ነበረ። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች የልቅሶ ቤት ይመስላሉ። ሰውም በርከት ብሎ የሚመጣው ከእንደዚህ ያለው መላቀሻ ሥፍራ ነው። ወቅቱ ከቤታቸው ለማዘንና ለማልቀስ የተከለከሉ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን እየመጡ የሚያለቅሱበት፤ ጴንጤቆስጤዎችም በመንፈሳዊ መዝሙር እና በስብከት የሰውን መንፈስ የማረኩበት ወቅት ነበር።

ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚሰሙት በልባቸው ያለውን ነው፤ እውነት ደግሞ ከእውነታዎች ጋር ተደርቦ በስሜት ሲነገር፥ አድማጮቹም በስሜት ሲሰሙት ሊያስለቅስ ይችላል። ሰባኪያንም ደግመውና ደጋግመው፥ “በቃ! እስከመቼ?... ከሚከብደው ወደሚቀለው አለም እንሻገር፥ ወደ እግዚአብሔር እንሂድና በእግዚአብሔር መንፈስ እንጽናና..” እያሉ ይሰብካሉ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ “እናንት ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደኔ ኑ፤..”፤.. ማቴ ፲፩፥30 የሚለውን እየጠቀሱ።

በጥቂት ጊዜያት ብዙዎች ወደ መንፈሳዊነት የተሳቡበት ዘመን ነበር። ይህ ዘመን ከማርክስና ኤንጅልስ ፍልስፍና ይልቅ ማንኛውም ሃይማኖታዊ ፍልስፍና በልጦ የታየበት ወቅት ነበር (እስካሁን እና ለወደፊትም)።

ተማሪዎች ብሩህ ተስፋ አይታያቸውም። ትምህርት ቤት በብዛት ተከፍቷል፤ ግን የተማሪዎቹ የወደፊት ተስፋ ተጭለምልሟል። አጥንቶ ፈተና ለማለፍ ብቻ ሳይሆን፥ ልጆች የተማሩትን እያወቁ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ ጉጉት የሚያድርባቸው ከአካባቢያቸው ከሚያገኙት ተስፋ ነው። ከድሮ ከኃይለ ሥላሴ ዘመን ወዲህ በኢትዮጵያ ተማሪዎችን የሚያበረታታ ነገር እየቀነሰ መጥቷል። ቤተሰብ ሂዱና ተማሩ ብሎ ትእዛዝ ከማስተላለፍ በሰተቀር፥ የሚማሩትን ሁሉ ለመከታተል አይችልም፤ መንግሥትም የወደፊት ተስፋቸውን እያዩ እንዲማሩ የሚያበቃ የሥራ መስክ አይከፍትላቸውም።

ይህ ዘመናዊ ትምህርት ለጠቅላላ የሰው ልጅ የተሰጠ ስለሆነ፥ ሁሉም ይማረው ዘንድ ግዴታ ነው። ግን፥ “በእንዴት አይነት መንገድ ነው ሰው ትምህርትን የራሱ እያደረገ መማር የሚችል?” ብለን ስንጠይቅ፥ የሚከተለውን እንገነዘባለን፡

- አለማወቅን (በልማድ ያደጉ ኋላ ቀር አስተሳሰቦችና ድንቁርናዎች ሁሉ) ከቤተሰብ፥ ከሕብረተሰብና ከአገር ውስጥ ማጥፋት፤
- አገር ገንቢ (ለኑሮ የሚጠቅሙ) ትምህርቶችን (ምድራዊና ሰማያዊውን በማጣመር) መማር፤

- *ዘመናዊ ትምህርትን ለራስ እንዲጠቅም ለማድረግ ከተጠቀሱት ሁለት ነጥቦች ጋር እያስማሙ መማር።*

*መንግሥታት* በደንብ ያልተረዱት ቢኖር፡- ከመኖር ጋር አለመኖር እንዳለ ሁሉ፥ ከማወቅ ጋር አለማወቅም አብሮ ሊያድግ ስለሚችል፥ በዚህ ምክንያት፥ በሕብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ አለመግባባት እየተፈጠረ አብሮ መሥራት እንዳያስቸግር፥ ሕብረተሰብን በጥሩ መንፈሳዊ ፍልስፍና ለማጎልመስ መሆን ነበረበት የትምህርት አላማውና ተግባሩ።

ምድራዊ ትምህርትን ብቻ ይዞ መጓዝ ምድራዊ - ሰማያዊ የሆነውን ሰው በግድ ምድራዊ ብቻ እንዲሆን ማድረግ ይሆናል፤ ሰውን ቀውስ ውስጥ ይከታል፤ ከእውነትም ያርቃል። ምድራዊ እና ሰማያዊ ሆነን በመፈጠራችን ምድራዊ ትምህርት ብቻ አያረካንም፤ አይበቃንም። ከጥንት ጀምሮ ተማሪ ሲባል በኑሮ ተቸግሮ፥ በትጋት አጥንቶ፥ ፈጣሪውን ዘወትር በጸሎት መማጸን እና፥ ሕዝብን - ቤተ ክርስቲያንን (ቤት መቅደስንም ሆነ መስጊድን) ማገልገል ነው። ይህ የተማሪዎች ባህል እስካልጠፋ ድረስ፥ በዚህም በዚያም ተፍጨርጭረው ኢትዮጵያን የሚያሳድጓት ተማሪዎቿ - ልጆቿ አሉላት። ለነርሱም ለሕይወታቸው የሚበጃቸው በተማሩት ሠርቶ፥ ገንዘብ አግኝቶ መኖር ብቻውን ስላልሆነ፥ በየጊዜው ከሚማሩት ውስጥም ሞራላዊነትን (መንፈሳዊነትንም) እየለዩ ቢያስተምሯቸው ለቀን ተቀን ሕይወታቸው የሚጠቅማቸውን ያገኙበታል፤ ለመልካም ሕብረተሰብም መሠረት የሚጥሉ ይሆናሉ።

በዚህ በአካላዊነት ከሚታየን የዘመኑ "ሥልጣኔ" ሌላ "መንፈሳዊ ሥልጣኔ" በግልጽ ከማይታይበት አለም ውስጥ ነው ያለነው። በመንፈሳዊነት ብናድግ ኖሮ፥ ይህ "ሥልጣኔ" የምንለው ቃል ምናልባት "ኋላ ቀርነት" ከሚል የተሻለ ስም ባላገኘ ነበር። ይህንን አባባል ትንሽ ዞር አድርገን ብንመለከተው፥ ሰው ከቁመናው ጋር ትልቅ ጭንቅላት ስላለው ለዚህ ለዘመኑ "ሥልጣኔ" በቃ። ግን ይህን "ሥልጣኔ" ያገኘው በእንስሳዊ ጠባዩ ነው፥ ወይንስ በመልአካዊ ጠባዩ?

ሰው እንደ እንስሳ ሆኖ በአካላዊነቱ ብቻ የኖረበት ዘመን ቢኖር፥ በሥጋዊ አካሉ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለተጨመረበት ዘመናዊ ሰው አላደረገውም፤ ሥጋዊ የሆነው አካሉ ለምድራዊነት ይስማማው ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ችሎታው ሁሉን ሲሞካክር ከዚህ ደረጃ ደረሰ እንጂ። ስለዚህ፥ ሰው ከቁመናው ጋር ትልቅ ጭንቅላት ስላለው ለዚህ ለዘመኑ "ሥልጣኔ" በቃ።

"የሰው ልጅ በሥጋዊ አካሉ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለተጨመረበት ዘመናዊ ሆነ (ወይም አልሆነም) ብሎ መከራከር ካቅም በላይ ሊሆን ይችላል። ደግሞም፥ የዘመኑ "ሥልጣኔ" ሰውን ከመንፈስም ከእግዚአብሔርም አርቆት

እንደሆነም ማወቅ ያስቸግራል። መልስ የሚገኝለት ጥያቄ ቢሆንም ባይሆንም፥ ይህንን ሰፊ አርእስት ለጊዜው በዚህ እንግታ[9]።

ገበሬዎችና የስምጥ ሸለቆ ከብት አርቢዎች በለውጡ መደሰታቸውን ማን ጠየቀ? ድርቅ ሲሆን በቅድሚያ የሚጠቁ የምንመገበውን ሁሉ የሚያመረቱ ገበሬዎችና የስምጥ ሸለቆ ከብት አርቢዎች ናቸው። እነርሱ ከተፈጥሮ እንጂ ከሰው ብዙ የማይጠብቁ ስለሆኑ፥ ሰማይ ሰማዩን እያዩ፥ ከየትም ከየትም ነፋስ ነፍሶ፥ ውሃ አዘሉን ደመና እንዳያመጣላቸውና እንዲዘንብላቸው እግዚአብሔርን ይለምናሉ።

የአፋርና የኢሳ ብሔረሰቦች እርስበርሳቸውና በአቅራቢያቸው ከሚገኙ ደገኞች ጋር በሳር ግጦሽ ምክንያት ዘወትር ይጣላሉ። ሰውም ሆነ እንስሳ ሆዱን ለመሙላት ሲል ማድረግ ያለበትን ሁሉ ያደርጋልና፤ በጋ ሲሆን የበረሃው ሳር ተቃጥሎ ሲያልቅ፥ ቆለኞች ወደ ደጋው ሲጠጉ፥ ክረምት ሲሆንና ቆላው ሳር ሲያበቅል፥ ደገኞችም ወደአቅራቢያቸው የስምጥ ሸለቆ ከብቶቻቸውን ሲያሰማሩ፥ ግጭት ይጀመራል። ይህ ከተፈጥሮ ሁኔታ ጋር የተያያዘ የሚመስል ግጭት ከጥንት ጀምሮ የቀጠለ ነው። አንድ መንግሥት ቢሄድ፥ ሌላም ቢከተል፥ ለስምጥ ሸለቆ ከብት አርቢዎች ያሰበላቸው ያለ አይመስልም።

አገራችንን በተደጋጋሚ ድርቅ ሲያጠቃት፥ "ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ለሕዝብ ማሰብ ያለበት መንግሥት አይደለም እንዴ!" ብለው የሚጠይቁ ባላገሮች፥ የሚያገኙት ምላሽ ሞት ብቻ ሲሆን፥ አንድ ገና ትምህርት ቤት ያልገባ የስድስት ዓመት ልጅ ነበር የሚከተለውን የበሰለ አስተያየት በኢትዮጵያ ቴሌቪዢን የሰጠ፡

አሁን ካለ አባትና እናት ብቻዬን የቀረሁኝ፥
እኔም ባለ ብዙ ዘመድ ነበርኩኝ፥
አጎቶች፥ አክስቶችና አያቶችም የነበሩኝ፤
እናትና አባቴ ከራሳቸው እየቀነሱ ሲመግቡኝ፥
እነርሱ በየቀኑ እየሞቱ፥ እኔ ብቻዬን እንድኖር አደረጉኝ።
ክረምትና በጋ ሲመሳሰል፥
ከዛሬ ነገ ይሻላል ሲባል፥
መሬት ሲታረስ፥ ተቆጥቦ የተቀመጠ እህል እንዲሆን ሰብል፥
ሲበተን፥ ሲዘራ፥ በተስፋ ወደ መሬት ሲጣል...፥
አዬ!...ጥሬ እህል ካለ ዝናብ አይበቅል..።

---

[9] ስለ እውቀትና ሥልጣኔ፥ ማንነትና ድኅነት፥ ስለ ሥይጣኔም ከሁለተኛው መጽሐፍ ይመለከቷል።

አምናና ካቻምና አንዱ ከሌላው የማይሻል፥
አየሩ ሲደርቅ፥ የጸሐይ ሙቀት ሲያቃጥል፤
ምን ይደረግ? ምን ይደረግ፥ ምድሪቷ ምግብ አልሰጥ ስትል?
ሳሩ ጎመን ነው ተብሎ እንዳይበላ፥ እርሱም ጠፍቷል፥
ሁሉ ነገር አመድማ፥ ቡናማ መስሎ ይታያል፥
ምን ይደረግ? ምን ይደረግ፥ ምድሪቷ ምግብ አልሰጥ ስትል?

ዳመናን የሚመከት ዛፍ ቅጠል ከሌለበት፥ ከደጋው የኢትዮጵያ ክፍል፥ እስከ ቆላው፥ ቁጥቋጦ እንኳን ከማያበቅል፥ በንዳድ ያለቀው ሕይወት እንዴት ይረሳል - እንዴት ይረሳል።

በአፋር ሸለቆ ውስጥ፥ ሃብት ንብረት የተባሉ ከብቶች፥
ፍየሎች በጎችና ግመሎች፥ ሰዎችም የቆላው አገር ዘመዶች፥
ሳር ቅጠል ሲፈልጉ የደከሙ መጋቢዎች፥ የት ገቡ የኛ ሰዎች?
ከአስር ከብት ጋር አንድ ሰው ተዳብሎ ሲሞት፥
ክንብል - ክንብል በያለበት፤
ነጫጩ ብቅ ብቅ ሲል፥ በዚህም በዚያም አጥንት፥
ገና የአለም መጨረሻ ሳይሆን፥ የፍጥረታት እልቂት።
እናንተ ነፍሶች፥ የሱማሌ የኢሳና የአፈር ወገኖች የሆናችሁ፥
ከምሥራቁ ተራራ እስከ ምዕራቡ ተራራ፥
በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ሞታችሁ የቀራችሁ፥
አይዟችሁ ትኖራላችሁ፤ በአይምሮአችን እየታሰባችሁ።

ያለፈው አለፈ። መጪውም ሳይዘገይ ይመጣል። ለዚህ በሰሜን አፍሪካ በተደጋጋሚ ለሚከሰት ድርቅ ማቃለያ ዘዴዎች ይበጅለት።

የወደፊቷን ኢትዮጵያችንን ለመታደግ ሁሉን ነገር በፍቅርና በአንድነት አስበን፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም[10] ተምረን፥ ስለ ዘላቂ መፍትሄም ቢታሰብበት መልካም ነው።

---

[10] ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት ፈርኦን በጥሩ ቀን እህል እያጠራቀመ ቆይቶ፥ ድርቅ ሲሆን ሕዝቦቹን ከረሃብ አዳናቸው። ዘፍ.41፡28-36

# ምዕራፍ አራት

## ምድራዊት ኢትዮጵያ ሰማያዊ

እነሆ! ከደርግ የሰባት ዓመታት የግዛት ዘመን በኋላ ከአገሬ ወጥቼ፥ ከወያኔ አስራ አንድ የግዛት ዘመን በኋላ (በድምሩ 18 ዓመታት በኋላ - በ1998 ዓ.ም. እንደ አውሮፓ አቆጣጠር)፥ ከቤተሰቤ ጋር ወደ ኢትዮጵያችን ሄድኩ፤ የሳቅና የጨዋታ፥ የሃዘንም ሆነ የደስታ፥ የተለያዩ ትዝታዎችን ከሚያስታውሰን ሥፍራ።

ከቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ መሃል ከተማ እስከንገባ ድረስ፥ ሳርና ቅጠሉ፥ አፈርና ድንጋዩ፥ ሁሉም ከፈረንጅ አገሩ ለየት ያሉ ናቸው። በደራረቁ ሳሮቹ መካከል ደረቅ አፈር፥ አልፎ አልፎም የለመለሙ ሳሮች፥ ልምላሜና ድርቀት እዛው በዛው፤ በልምላሜና በድርቀት መካከል ትላልቅና ትናንሽ ድንጋዮች፥ እንዲሁም ጠጠሮች (እንዴ!)።

ከላይ በዛፎች ላይ ተንጠልጥለው ቅጠሎቹ ምንም አይሉም፤ እንዳው መታዘብ፥ ቅሬታና ሃዘን፥ በምድራችን ላይ ስለሚታየው ከፍና ዝቅ ሁሉ (እንዴ!)።

እንዳው ሁሉም - ሳሩም ቅጠሉም፥ አፈር ድንጋዩም አብረው ሆነው፥ "ከጥንት ጀምሮ ያንተነትህ መሠረቱ እኛ ነን እኮ! ከኛ በቅለህ ሌላውን መሆን ላትችል ለምን ጥለኸን ሄድክ? ....በቃ ይቅር፤ ሁሉም ይቅር፤ ግን እናንተ ደህና ናችሁ?" እያሉ ሰውን በናፍቆት ሰቀቀን ውስጥ ይከታሉ፤ ብዙ ሺህ ዓመታት ወደ ኋላ እየጎተቱ።

እኛስ ወዳገራችን ተመልሰን የመጣነው፥ ከዘመዶቻችን ተቀላቅለን፥ ላጭር ጊዜም ቢሆን ኑሮን ከወገኖቻችን ተቃምሰን፥ ስለ አገራችንም ከፉውንም ደጉንም አይተን ለመመለስ ነበር። ገና ከአይሮፕላን ስንወርድና ያገራችንን አየር ስንተነፍስ፥ ሰው ከገዛ አገሩ ለቆ መውጣት እንደሌለበት፤ ስደት ማለት እራስን በትንሽ በትንሹ እየቆረሱ ለሌላው መስጠት እንደሆነ ነበር የተሰማን ስሜት።

መናኸሪያችን አዲስ አበባ የሁላችን መገናኚያ፥ የኋላ ዘመን መሰባሰቢያ፥ መረካከቢያም ስለሆነች፥ ይህ የዛሬው አመጣጣችን የመጨረሺያ አለመሆኑን እናውቃለን። አዲስ አበባ ስንገባ የተሰማን የደጋግ መንፈሶች ስሜት ኢትዮጵያውያን (ያሉትም፥ የሞቱትም) ከሩቅ - ከዳር አገር ተጠራርተው አብረው የሚኖሩበት ዘመን መቃረቡን ያበስራል።

አዎ! ሰዎች ጮኸውባታልና፥ ደጋግ መንፈሶችም በዝተውላታልና፥ ዛሬም ቢሆን ነገ፥ እንደ ስሟ የምትሆንልን እርሷ ናት። መጨረሻያው ሲቃረብ፥ ኑ! ግቡልኝ! የምትል፥ አስተናጋጅ - ቆንጆ ሞቃት ቤት፥ እርሷ ናት አዲስ አበባ - ከኢትዮጵያ - ከመሃል አገር - ከአፍሪካ፥ ከአለም ዙሪያም - ሰውን በሰውነቱ አክብራ የምትቀበል፥ ለሰው ልጅ በእጩነት የተቀመጠች፥ ትላንት የምናውቃት፥ ዛሬን ያየናት፥ የወደፊቷን ስንመለከታት፥ በህንጻዎቿና በመንገዶቿ ማማር ሳይሆን፥ በደጋግ ሕዝቦቿ፥ ሳይበላ የሚጠገብባት ሥፍራ የምትመስል የፍቅር ከተማ።

ከከተማዪቱ ማማር በስተጀርባ፥ የድሆች መብዛት፥ የሥራ ፈቶችም መበራከት ያሳዝናል። ሆድ ዛሬ ጦሙን ቢያድር፥ ነገም ከነገወዲያም እንዳይደጋገምበት የቀን ተቀን ኑሮአቸውን ለሟሟላት የሚሯሯጡ ብዙዎች ናቸው። እንዲሁም፥ ከጥቂት ጊዜ የወለዳቸው ቱጃሮች በስተቀር፥ ከፍና ዝቅ ያለ ኑሮን የቀመሱ፥ ቢሯሯጡም አልሆን ብሏቸው ተስፋ የቆረጡ አሉ፤ ብዙ ስለደከሙ - ከድህነት ጋር ብዙ ስለቆዩ - ምድራዊ ሕይወት ስልች...ት ብሏቸው ለተመለከታቸው በግድ ኑሩ የተባሉ ይመስላሉ።

እኛስ ቢመረን ተለይተንሽ፥ ብትናፍቂን መጣንልሽ፤
አንቺም እንደ ወትሮው ሞቃት ነው መንፈስሽ፤
ግን ምነው የከፋሽ መሰልሽ?
ምነው ኀስቆል አለ ሰውነትሽ?
ችላ ተባልሽን? ወይንስ ተጠላሽ?
    አንቺ ከፍጥረትሽ በመንፈስ የተሞላሽ ሆነሽ፥
    የገነት ውሃዎች ሲፈሱብሽ፥
    የበኩር ልጅ አብቅለሽ፥
    የዘር[11] ግንድ ከጉያሽ፥
    ልጆችሽንም በአለም ዙሪያ ዘርተሽ፥
    ሁሉም በያሉበት ሲያፈቅሩሽ፥
    ማነው የሰደበሽ? እንዳትኩራሪ በታሪክሽ፥
    የበሽታ፥ የድህነት መናኸሪያ ብሎ የጠራሽ።

[11] በዚህ መጽሐፍ እና በሚከተሉትም "ዘር" የሚለው ቃል የሚያመለክተው፥ የሰው ዘር፥ የዝንጀሮ ዘር፥ የአሳ ዘር፥ እና ሌሎችም የፍጥረታት ዝርያዎችን (የዘር መደቦችን) ነው።

ኢትዮጵያ፥ ዛሬ ምድራዊነት ቢያጣጥልሽ፥
ዕጹብ ድንቅ ነሽ ለሚያፈቅሩሽ፤
ሰማያዊነት ነውና፤ እውነተኛው መልክሽ።
ኢትዮጵያ፥ ዛሬ ምድራዊ ሃብት ባይኖርሽ፥
ሃብታም ነሽ አብሮነትን በሚሹ ልጆችሽ፥
የሕዝቦች ደግነት ነውና ሃብትሽ፥
አምልኮተ እግዚአብሔር ነውና ተስፋሽ።

ቀኑን ሙሉ በየመንገዱ የሚቀመጡ የዛፍ ጥላ እንኳን ቢያገኙ ጥሩ ነበረ። ዛፎች በየቤተቹ መካከል እና በየመንገዶቹም ዳርቻ ቢተከሉ ኖሮ፥ ቅጠሎች የጸሐይን ብርሃን ወደ ኃይል ለውጠው፥ ሕይወት አግኝተው ሲበራከቱ የከተማውን የአየር ሙቀት (ቃጠሎ) ይቀንሱት ነበር። ዛፎቹ ሰውን በጥላ ሲያቀዘቅዙት፥ የመሬቱንም አቧራ ሲይዙለትና ንጹህ አየር ሲሰጡት፥ ለአይን ውበት ከመሆናቸውም በላይ ለጤንነትም ይጠቅማሉ። ይህንን የተገነዘቡ፥ ዛፍ እየተከሉ ምድሪቱን ሲያሳምሯት - ይህንን በጎ ሥራ መንግሥት ተመልክቶ ዝም ከሚል፥ ሕዝቦች በያሉበት፥ በዛፍ መራቆት የደረቀውን መሬት በእጽዋት እንዲሸፍኑት መመሪያ ቢሰጥ ጥሩ ነበር ።

አሁንም (የ1998 እይታ) ቢሆን ከሰው የሚወጣ "ደረቅና ፈሳሽ በካይ" አፈሩንና ውሃውን እየበከለው ነው። ይህ ችግር በተለይ በአንዳንድ የሕዝብ ቁጥር በበዛበት አካባቢ (በከተማዎችና በመንደሮች) በገሃድ እየታየ ነው። የሕዝቦች ጤንነት እና የአካባቢ ጤንነት የተያያዙ መሆናቸውን ሠፊው ሕዝብ የተረዳ አይመስልም። በመንግሥት ደረጃም አስፈላጊው የአካባቢ ንጽሕና ካልተደረገ በስተቀር፥ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር የሕዝቡም ጤንነት ይባባሳል።

ከሰው የሚወጣውን "በካይ" ለአይን እንዳይታይ ብቻ በቀዳዳ ቢደብቁት፥ በመሬት ላይ ከሚፈስ ውሃ ጋር መገናኘቱ ይቀራል እንጂ፥ ከከርሰ ምድር ውሃ ጋር መነካካቱ አይቀርም። ያለው አማራጭ ከሰው የሚወጡ "በካዮችን" መቅበር ሳይሆን፥ በተወሰኑ ሥፍራዎች እያጠራቀሙ መሄጃቸውንና መድረሻቸውን መወሰን (በቁጥጥር ውስጥ ማዋል) ነው።

ለአካባቢ ጤንነት የሚወጣው ገንዘብ ለሕዝቦች ጤንነት ከሚወጣው ገንዘብ ጋር የሚደጋገፍ መሆኑ እየታሰበ፥ አስፈላጊውን መንግሥታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያበቃ ገንዘብ መመደብ ይገባል። ሰውም የራሱ ጤንነት እና የምድሪቱ ጤንነት (ንጽሕና) የተያያዙ መሆናቸውን በደንብ መማር ይኖርበታል።

በየመንገዱ ሠራተኛውና ለማኙ አብሮ ይርመሰመሳል። አንዳንድ ፖለቲከኞች ለድሃ ገንዘብ መስጠት የሰውን የፖለቲካ ንቃት ያዳክመዋል፤ ለተሻለ የመንግሥት ስርዓትም እንዳይታገል ያደርገዋል፤ አለዚያም ሥራ መሥራትን ትቶ የሰው እጅ ብቻ እየተጠባበቀ እንዲኖር ያደርገዋል (ያሰንፈዋል) ይላሉ። ግን፥ ምንም ቢባል ምንም፥ በድሆች ወገኖቻቸው ላይ መጨከን የማይቻላቸው ደጋግ ሰዎች፥ ከቤት ወደ ሥራ፥ ከሥራም ወደ ቤት ሲሄዱ፥ በየመንገዱ ተኮልኩሎ ለሚለምን ሁሉ (እጁን ቢዘረጋም ባይዘረጋም) ሳንቲሞችን ጠብ ጠብ እያደረጉ ማለፍ የተለመደ ሆኗል። ለማኞች በአንድ ቀን የሚሰበስቡት ገንዘብ ቢቆጠር አንድ የቀን ሠራተኛ ከሚያገኘው ሳይበልጥ አይቀርም የሚሉም አሉ (ሊሆን ይችላል)።

ጤነኞቹና ኑሮ የተሳካላቸውን ኢትዮጵያውያኖች በያሉበት ያገራቸውን ድሃ እንዲያስታውሱና እንዲረዱ፥ መስጠት የሚችሉ የመስጠትን ዕድል እንዲያገኙ ሲቀሰቀሱ፡-

እባካችሁ የኔ ጌቶች፥ ተወዳጆች የእግዜር ሰዎች፥
ምኞቴ ነው ፍላጎቴ፥ እንድትሆኑ ጤነኞች፤
ጸሎቴ ነው፥ ልመናዬ፥ እንድትሆኑ ደስተኞች።
እኔስ ሆኜ ቀረሁ በሽተኛ፥ የማልችለው ሠፍሮብኝ፥
መግቢያ አጣሁኝ መሸሸጊያ፥ ካቅሜ በላይ ሆነብኝ፤
ወድቄአለሁ ተመልከቱኝ፥ የእሳት አጥር ታጥሮብኝ።
አትጨክኑብኝ እያያችሁ፤
እኔምኮ ነኝ ወገናችሁ።
ቸሩ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤
ሰላም ፍቅር ያብዛላችሁ፤
በረከቱን ያድላችሁ፤
ዜማ መላእክት ያሰማችሁ፤
የምድር ሰማይ ያርግላችሁ፤
ከጭንቀት አውጡኝ እባካችሁ፤
አትለፉኝ - እርዱኝ በአምላካችሁ።

ኢትዮጵያችን ድሆች ሃብታሞችን እየለመኑ የሚኖሩባት አገር ስትመስል፥ ለማኙም፥ ሰጪውም ከሥጋዊነቱ አብልጦ ለነፍሱ እንዲያስብ አድርጎታል ያሰኛል። ጥንት ከማውቃት ኢትዮጵያ ለየት ያለ ነገር ቢኖር፥ ሰዎች ከምን ጊዜውም የበለጠ

ሃይማኖተኞች በመሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ፥ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ፥ ሲጸልዩ፥ ሰማያዊ መዝሙር ሲዘምሩ ይሰማሉ። ይህ በጣም ደስ ይላል፤ ግን በአንጻሩ በሃይማኖት ፉክቻ በጠላትነት እስከ መተያየት መድረስ፥ ብሎም መጣላት እጅጉን ያሳዝናል።

ከዛ የሃይማኖት አልባ ዘመን በኋላ፥ ሰዎች በኢትዮጵያ ምድር ልብ ገዝተው ወደ ሃይማኖት ተመለሱ። ግን በአሁኑ ጊዜ የሃይማኖቶች ግጭት በየቤተሰቡ እየገባ፥ ሰዎች በገዛ ከፉቶቻቸው ልዩነቶችን እያከረሩ የማሕበራዊ ኑሮ መናወጥን ፈጥረዋል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት እና ሌሎችም ጻድቃን የደከሙበትንና ያስፋፉትን የክርስትና ሃይማኖት ኦርቶዶክስም ፕሮቴስታንትም ይኮትኩታት (ያልማት)። እመቤታችን ቅድስት ማርያም ስለ ምድር ኃጢአት አለቀሰች እንጂ፥ ወገን አልለየችም። እመቤታችን ስሟ መጨቃጨቂያ ሲሆንባት፥ እርሷም ልጇም ደስ አይላቸውም። ሰው ሁሉ የየራሱ ሃይማኖት ለራሱ ይሁነው፤ ሁሉንም ውደዱ እንጂ፥ በመካከላችሁ አለመግባባትና ጭቅጭቅ አይፈጠር፤ የክርስቶሳዊነት አላማው በሰዎች መካከል ልዩነቶችን በፍቅር አስተሳስሮ፥ ማንም ለሌላው ራሱን ዝቅ በማድረግ፥ ለእግዚአብሔር እየሰገዱ መኖር ነውና።

የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ልክ አይደለም፤ የኛ ብቻ ነው ልክ፤ የኛን የሚያጸድቀውን ተከተሉ በማለት፥ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ድረስ እየሄዱ ወረቀት የሚበትኑ መኖራቸውን ሰምተን እጅጉን አዘን። እነኚህ ግለሰቦች ጥቂቶች ቢሆኑም፥ እንደነርሱ የሚያስቡ ሁሉ ይመከሩ።

ሰዎች እርስ በርስ ሲጣሉ የሚጎዱት የገዛ መንፈሳቸውን (እራሳቸውን) ነው። እግዚአብሔርን ተገን አድርጎ ሌላውን ማጥቃት የሰይጣን ተንኮል እንጂ፥ መንፈሳዊ ሥራ አይደለም። በኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶች ቢያብቡ እግዚአብሔር የፈቀደው ነውና፤ እንደ ጥሩ መታየት ይኖርበታል።

ተው! ተው! ተው! እምነታችሁን ለራሳችሁ አድርጉ እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ቤት ደጃፍ ደርሳችሁ በመንፈስ ላይ ሁከት አትፍጠሩ። የምትሠሩት ሥራ ሁሉ በበጎ መንፈስ ተነሳስታችሁ ቢሆንም፥ ውጤቱ መጥፎ ከሆነ እናንተን ጥፋተኛ ያደርጋችኋል። የጥሩ ሥራ ጥሩነቱ የሚረጋገጠው እንዳጀማመሩ ውጤቱም ሲያምር ነውና፤ ወረቀት ስትበትኑ የሚያስከትለውንም ውጤት እያሰባችሁ ይሁን።

እናንት የወንጌሉን ቃል ተከትላችሁ እራሳችሁን ትመራላችሁ፤ ግን ቅዱሱ መጽሐፍ፡- ወደ አሕዛብ ሂዱና አስተምሩ (ማቴ. 28፡19-20) አለ እንጂ፥ በአብ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁ አማኞች ዘንድ፥ ከሚሰግዱበትም ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ድረስ ሄዳችሁ የነርሱን ሃይማኖት አስተካክሉላቸው አላለም።

በአንድ ጻድቅ ስም ቤተ ክርስቲያን እያሡሩ ጻድቁን ለመምሰል የሚጥሩ ሕዝቦች ሃይማኖታቸው የቀና ነው እንጂ፥ የተወላገደ ሊሆን አይችልምና፤ በከንቱ አትቃወሙ።

እናንት ወንጌላውያን፥ የክርስቶስ ተከታዮች የሆናችሁ ደጋግ ሰዎች ሆይ! የደግነታችሁ መጨረሻ ከፋትን እንዳያመጣባችሁ ተጠንቀቁ። እናንት ስለምታውቁት ሁሉ የገለጸ አምላክ ለሌሎችም እንደየአቅማቸው የሚያሳውቅ (ያሳወቀ) መሆኑን አስቡ። ክርስቶስ እንዲህ አለ፤

“የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ። ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምጼንም ይሰማሉ፤ አንድም መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ።” ዮሐ. 10፡ 16

የዚህን ጥቅስ ትርጉም ሙሉ በሙሉ ሊያውቅ የሚችል ከሰው የተፈጠረ ሊኖር አይችልም፥ ከራሱ ከክርስቶስ በስተቀር። ግን ልዩነቶቻችንን ከተለያየ በረት እንደመግባት ብንቆጥረው፥ የራስ ያልሆነውን ሃይማኖት በማጥላላት፥ ራሱ ክርስቶስን መስሎ፥ “ኑ ከዚህ በረት ግቡ፥...” እያሉ ሰውን ከማስጨነቅ ይልቅ፥ ዞሮ ዞሮ ያ አንድ የሆነው እረኛ - ጌታችን ፈልጎ ያገኛቸዋል፤ ከተለያየ በረት ብንሆንም፥ በእረኛችን አንድ መንጋ ልንሆን እንችላለን ብሎ በአዎንታዊነት መመልከት ይቀላል (ይሻላል)።

ለመሆኑ ከዚህ ምድር ውጪ ሌሎች በረቶች ቢኖሩስ ማን ያውቃል? እኛ ሁላችንም በአንድ በረት ውስጥ ያለን ብንሆን እና፥ “እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ..” ሲል ከዚች ምድር ሌላ - ሌሎች የጠፈር ምድሮች ያሉበት ሥፍራ እሄዳለሁ ማለቱ ቢሆንስ? ማን ያውቃል። በማያውቁት ነገር መጣላት ይቅር፤ በክርስቶስ መንፈሳዊ አንድነትና ፍቅር ተስማምተን እንኑር።

## <u>**ቋንቋዎች እና ፊደሎች**</u>

ባላገሮች ወደ ከተማ ገብተዋል። እነርሱ የዋህነታቸውን ይዘው ሲገቡ፥ ከተሜዎች አዘኑላቸውና አስተናገዷቸው - አበሏቸው፥ አጠጧቸው። እነርሱ ግን ለከተሜዎች ምንም አላደረጉላቸውም። ግን የተፈጥሮ ቻይነታቸውንና ትእግስተኛነታቸውን አስተማሯቸው፤ ደግነታቸውንና ፍቅራቸውንም ገለጹላቸው።

ከጊዜ ብዛት ከተሜው ከባላገሩ ብዙ ነገር ተማረ። የአነጋገሩ ስልት ተለወጠ። አማርኛችን በትግርኛና በኦሮምኛ ተከልሶ፥ በሌሎች ቋንቋዎችም ተነካክቶ፥ ለሁሉም የሚጣፍጥ ቋንቋ ሆነ። ከመንፈሳዊ መዝሙርና ከዘፈንም ጋር ግንባር ፈጥሮ አማርኛ የፍቅር ቋንቋ ሆኗል፤ እንደሰው ቋንቋውም ልስልስ።

የወቅቱ የአገራችን ሕብረተሰባዊ የኢኮኖሚ እርከኖች በአማርኛ ውስጥ የሚካተቱ የአራዳ ቃላትን ፈጥሯል። ለሚጠቀሙባቸው ውስጣዊ ስሜቶቻቸውን (ሁኔታቸውን) በበለጠ የሚገልጡበት ነውና፤ ለእነርሱ ያ ጥርት ያለ ቋንቋቸው ነው።

ባጠቃላይ፥ በሰዎች ንግግር ውስጥ ትህትናን የሚገልጹ ቃላት (እንደ "እናትዬ" የመሳሰሉ) በብዛት ይሰማሉ፤ የሰዎችም የርስ በርስ ግንኙነት፥ ትእግስትና ፍቅር በግልጽ የሚታይበት ሆነ። ድሃና ሃብታም ተረዳድቶና ተቻችሎ የሚኖርበት አገር - በእውነት ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው።

ጥንት ከማውቃት ኢትዮጵያ ለየት ያለ ነገር ቢኖር፥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በላቲኑ መጻፋቸው ነው። በጥንት ዘመን የሕዝቦች መገልገያ ፊደል ኢምፔሪያሊስት ሆኖ ሌላውን ፊደል ሲወር አላየንም፤ አሁን ግን ኢትዮጵያ በፈቃዷ የራሷን ፊደል በላቲን ፊደል አስወርራለች። እኛው ራሳችን ነን ራሳችን ያስወረርነው እንጂ፥ የላቲን ፊደል ራሱ ኢምፔሪያሊስት ሆኖ ፊደላችንን (ወይንም ቋንቋችንን) ለማጥፋት አልተነሳም። ለእስዊሂሊ፥ ለሶማሊያና ለሌሎች ቋንቋዎች የኛ የግዕዝ ፊደል ከላቲን ፊደል የበለጠ የሚጠቅም ሆኖ ሳለ፥ በኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ብቻ ተወስኖ መቅረቱ በእውነት የሚያሳዝን ሆኖ ሳለ፥ በአሁኗ ኢትዮጵያችን የግዕዝ ፊደል ተጠቃሚውን ሕዝብ ወደተወሰኑ ሕብረተሰቦች - ቤተሰቦች (ጎሳዎች - ብሔረሰቦች) ማሽጋሸጉ ለወደፊት የሚያስከትለውን ክፉ ጎን ያልተገነዘብን ይመስላል።

በግዕዝ ፊደላችን ላይ ሰረዝም ሆነ ቅጥል በማድረግ፥ ፊደሉን ከማንኛውም ቋንቋ ጋር ማዋሃድ ሲቻል፥....ሕዝቦችን የሚያስተሳስሩ እውቀቶችን በማዳበር ፋንታ፥ ሕዝቦችን የሚያለያዩ የእውቀት ጨለማዎችን መፍጠር፤ ይህ እና በዚህም መንገድም ከሆነ በአገራችን ውስጥ ዘለአለማዊ ልዩነትና ብቸኝነት እንዲኖር የታሰበው፥ ይህንንስ ዝም ብሎ የሚያይ አይኖርም።

አንድ ቋንቋ በደንብ የሚታወቀው በንግግር ብቻ ሳይሆን በጽሑፍም ሲደገፍ ነው። የግዕዙን ፊደል ለአማርኛ ምንባብ የሚጠቀሙ የኦሮሚያ ሕብረተሰቦች፥ ቋንቋውን በደንብ ካላወቁት ለማንበብ ይከብዳቸዋል፤ ቋንቋውን በደንብ ሲያውቁት ማንበብና መረዳቱ ይቀላቸዋል። እንዲሁም የግዕዙን ፊደል ለኦሮሚኛ ምንባብ የሚጠቀሙ ሌሎች ሕብረተሰቦች፥ ኦሮሚኛን በደንብ ካላውቁት፥ ለማንበብ ይከብዳቸዋል፤ ቋንቋውን በደንብ ሲያውቁት፥ ማንበብና መረዳቱ ይቀላቸዋል። ግን፥ ከመሃል የላቲኑ ፊደል እንደ ጋሬጣ ተተከለና፥ የግዕዙ ፊደል የሚጫወተውን ሚና መመልከት አቃተን።

እስራኤላውያን ከተለያየ አገር ዜግነታቸውን ፈልገው (መርጠው) ወደ እስራኤል ሲገቡ፥ በመጀመሪያ ቋንቋቸውንና ፊደላቸውን ከሚያጠኑበት ኡልፓን

ከተባለ ሥፍራ ይሰነብታሉ። ከዚያም ተምረው ሲወጡ፥ በአንድ ብሔራዊ (እብራይጥ) ቋንቋ ይግባባሉ። የእብራይስጥን ቋንቋ ካለ ፊደሉ ማጥናት እንደሚከብድ፥ የኛንም (አማርኛ፥ ኦሮሚኛ፥ ትግርኛ...) ቋንቋዎች፥ ካለ ራሳችን ፊደል መማርና ማዳበር ቀላል አይሆንም።

የእንግሊዝኛ አረፍተነገሮችን በግዕዝ ፊደል ማስቀመጥ የሚቀለውን ያህል፥ የአማርኛን (ወይም የኦሮሚኛን) አረፍተነገሮች በላቲን ፊደል ማስቀመጥ ያን ያህል ቀላል አይሆንም። ይህም የሚያስየው፥ የኛን የግዕዝ ፊደል ብቃትና ችሎታ ነው (በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል)።

ሕዝቡ ለራሱ የሚቀለውን ብቻ ሳይሆን፥ የሚጠቅመውንና የሚሻለውን፥ በዘለቄታዊነት ለወደፊቱ ትውልድ የሚያዋጣውን በራሱ ያውቃል። በዚሁ በአሁኑ ሁኔታ ከቀጠለ ግን፥ በላቲኑ እና በግዕዙ ፊደል የሚጻፉትን መጻሕፍት ሁሉ እያነበቡ የሚያድጉ ልጆች፥ በኋላ በላቲን ብቻ ከሚጠቀሙት ጋር መግባባት እንዳያቅታቸው ያሰጋል። ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የሆነውን ፊደል ከአገር ለይተው ቢያወጡት፥ ሕዝቦች በአስተሳሰብ፥ በኑሮና በባሕል ይራራቃሉ። ይህ ሲሆን፥ የእድገትና የእውቀት መዛባት፥ አለመግባባትም አብሮ ያድጋል። ይህ የሚያስከትለውን መዘዝ የአሁኑ ትውልድ አስቦ ፈጣን እርምጃ ካልወሰደ በስተቀር፥ አሁንም ሆነ ወደፊት ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ተግባብተው በሰላም እንዳይኖሩ መሰናከል መሆኑን ልብ ይሏል።

ሕዝቦች በአስተሳሰብ፥ በኑሮና በባሕል ሲቀራረቡ (የሚያቀራርባቸው መንገድ ሲበዛ)፥ ከእኩልነታቸውና ነፃነታቸው ባሻገር አንድነታቸውም ይጠናከራል፤ በአንድነታቸውም አብሮ በመሥራት የጋራ ብልጽግናቸው ያብባል። አንድነትና አብሮ መሥራት ሳይኖር ብልጽግና ከየት ይመጣል? ብልጽግና ማንን ይጠቅማል (ምንስ ትርጉም ይኖረዋል) ሕዝቦች አንድነትን መሥርተው አብረው ካልኖሩ።

የላቲኑ ፊደል የመጣብን፥ ይህ (የምናስበው የሕዝቦች አንድነት) እንዳይሆን "ታስቦም/ሳይታሰብም" ሊሆን ይችላል። ግን፥ ለሕዝቦች አንድነት የሚቆረቆር ሕዝባዊ አስተዳደር ቢኖር፥ ይህንን አቢይ ጉዳይ ለዘረኞችና ለአክራሪዎች ለቆ ችላ በማለት ፋንታ፥ ለወደፊት የሚያስከትለውን ብሔራዊ ጉዳት ከወዲሁ በመመልከት፥ ፈጣን እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው።

ብዙሓኑ የኦሮሚያ ሕብረተሰብ በዘላቂነት የሚጠቅመውን በሚመርጥበት ጊዜ፥ በጥሞና (በእርጋታ) ካለ ምንም የፖለቲካ ተጽንኦ እና ካለምንም ጥላቻ (ኢትዮጵያዊነቱንም እያሰበ ) ቢሆን ጥሩ ነው።

“ለኔ የሚጠቅመኝ የትኛው ነው?” ከማለት ይልቅ “ለሁላችንም (ለኢትዮጵያ-ለኤርትራ - ለምሥራቅ አፍሪካ) የሚጠቅመው የትኛው ነው?” ብሎ ለሁላችንም ከማሰብ ጋር ሲሆን፥ ዘላቂ ጥቅም የሚኖረውን ለይቶ ማወቅ ይቻላል።

የተቀረውም የኢትዮጵያ ሕዝብ አጠቃላይ ምርጫ አካሂዶ፥ ይህን ክብነት የበዛበት፥ ሲያዩት እንደ ማሽላ ቆሎ የፈካ፥ ጥንታዊነትን የሚያስታውስ ቆንጆ ፊደል እየተወ፥ ወደ ላቲኑ መሸጋገር ይሻለኛል ካለ፤..ሁሉም በስምምነት ሲሆን መልካም ነው።[12]

## አጠቃላይ የሕብረተሰብ ችግር

አንዳንድ ሰዎች ምክር አነሳቸው፤ ኑሮና ብልሃቱ ጠፋባቸው። ሥራው በተለይ ምክር በመስጠት የሕብረተሰብን ችግር ማቃለል የሆነ የሬዲዎ ፕሮግራም ቢኖር ጥሩ ነበር። ትምህርት ቤቶች በምድር ስለመኖር ጉዳይ (ኑሮና ብልሃቱን) አያስተምሩም። እናትና አባቶችም የሚያውቁትን በግልጽ ለልጆቻቸው አይነግሩም። ኋላ ቀር (ጎጂ) ባህል ያደናቆራቸው እናትና አባት እነርሱ ያለፉበትን ነው ለልጆቻቸው የሚያስተላልፉት። ለወደፊት ተወልደው የሚያድጉ ልጆች ከመጪው ዘመን ጋር እንዴት ስምም ሆነው እንደሚኖሩ ተለይቶ አልታወቀም።

ልጃገረዶች ገና ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ (ማህጸናቸው ልጅ ለመታቀፍ ሳይደርስ) ገና በልጅነታቸው እያገቡ በእርግዝና ይታመማሉ፤ ሽንታቸውንም መቋጠር የማይችሉ ይሆኑና ይሰቃያሉ። አለማወቅን (የሚጎዱ ልማዶችና ድንቁርናዎችን)፥ በተለይ በአለም የተወገዙና ጎጂ ልማዶችን ከቤተሰብ፥ ከሕብረተሰብና ከአገር ውስጥ አለማጥፋት፥ ከኋላቀርነት ተገንጥሎ እንደማይታይ አልተገነዘብንም። የብዙሐኑ ኋላ ቀርነት ካልተወገደ በስተቀር፥ ሥልጣኔ ግንጥል ጌጥ ነው የሚሆነው።

ባጠቃላይ አገራችንን ከገጠማት ችግሮች መካከል፥ ለአያድርስ (AIDS) በሽታ የተጋለጡት እጅጉን ያሳዝናሉ። ይገርማል! ይደንቃል! ሰው ካልሞተ ብዙ ነገር ያያል። እነኛ መሄጂያ አጥተው በዚህ አስነዋሪ ተግባር ተዘፍቀው የቀሩት፥ ከሞቱት የተረፉት ሴትኛ አዳሪዎች - ከነርሱም መካከል በአያድርስ (AIDS) በሽታ የተሰቃዩ አሉ፤ በእሳት ውስጥ ሌላ እሳት እየተቃጠሉ ስለሆነ፥ ይታያሉ እንጂ ይኖራሉ አይባልም።

---

[12] በተጨማሪ “የሙሙዬና የማማዬ ምክር” የተሰኘውን ግጥም ከሁለተኛ መጽሐፍ ይመለከቷል።

ሥጋዬ አፈር መሰለ፥ በስባሽነቱን በቁሜ መሰከረ፤
ያ ሁሉ ውበት፥ ያ ሁሉ ቁንጅና ሄደ በረረ።
ሰው ሆኜ እንደ ሰው ሳልቆጠር፥
ተምሬ፥ ሥራ ይዤ እራሴን እንዳላስተዳድር፥
በሞትና ሽረት መካከል ስወጠር፥
ምነው ምናለበት ነበር፥ ለበሽታ ምግብ ሆኜ ከምቀር፥
አዬ!.. ምናለበት ነበር ጥንቱን ሰው ሆኜ ባልፈጠር።

ሰውነት ሲውረገረግ፥ በዝማሬ ስሜት ሲነቃነቅ፥
ይህ ደስ የሚያሰኝ ውስጣዊ ስሜት፥
የመኖርን ጣዕም የሚያንጸባርቅ፥
በተፈጥሮአዊ - መንፈሳዊ ክስተቶች የሚተላለፍ፥
ከዝቅተኛ ሰብአዊነት ወደ ከፍተኛ ሰብአዊነት፥
ይህ ሕይወት ትፍስሂት።
እዬ! "እንዲህና እንዲያ እኮ ነበር.." ብሎ - ሆኖ ቀረ፥
ሁሉም በአንድ አያድርስ ተሰበረ።

ግን፥ ይህ እንጂ እኮ ነው፥ ጣፋጭ ኑሮ ማለት፥
ትንሽ - ትንሽ ሰቅየት፥ አልፎ - አልፎም ማቃሰት።
ይህ እንጂ እኮ ነው፥ የመኖር ለዛ፥
ቀኑን ሲቆጥሩት እንዲበዛ።

እህህ!... እድሜ ሳይገፋ፥
በሽታ ሲገፋ፥
ኑሮ ሲከረፋ።

እንዲህ ነዋ ዕድሜ ሲያጥር፥
በልጅነት ላይ እርጅና ሲጠነክር፥
መቃብርም በጎልማሶች እንዲከበር።
መጥኔ "ብዙ - ብዙ" ለመኖር ሲሉ የሚደክሙ፥
ሞት መሆኑን ያላወቁ፥ መድኃኒቱ የህመሙ።

ሰው ሁሉ በአያድርስ ታማሚዎች ላይ ይፈርዳል። ይህ የአገር (የሕብረተሰብ)፥ የመንግሥትም ችግር ነው እንጂ፥ በግለሰቦች ላይ ብቻ የሚላከክ ኃጢአት አይደለም። የአገር አስተዳደር የሕብረተሰብን ሞራል የሚጠብቅና የሚንከባከብ መሆን አለበት። መፍረድ ቢኖርብን በሁላችንም ላይ እንፍረድ፡- ለምን ሞራላዊነታችንን በጋራ አልጠበቅንም?

ለምን ከሃይማኖታዊ ተቋሞች ራሳችንን አገለልን?

ለምን የቤተሰብ ፍቅር አጣን?

ለምን ከጨዋነት ብልግናን መረጥን?

ለምን የቀድሞውን ጥሩውን ባህላችንን ትተን መጥፎውን ወረስን?

ከመንፈሳዊነት ምድራዊነትን የማስቀደም ትርፉ፥ በመንፈስ መቁሰል ብቻ ሳይሆን በአካልም እየደቀቁ መሞት መሆኑን ተመለከትን።

ይኸው እኮ ነው ትርፉ፥

የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሲረሱ፤

መንፈሳዊነትን ሲንቁ፤

በምድራዊነት ብቻ ሲገሰግሱ፤

ምድራዊ ደስታን ብቻ ሲመርጡ፥

የሥጋን ግልጋሎት ለእርኩስነት ሲያውሉ።

የአያድርስ በሽታ ከኢትዮጵያ የሚጠፋው የዛሬ ህጻናት (የነገ ጎልማሶች) ቤተሰብና ጠቅላላ ሕብረተሰቡ በፍቅር ተሳስሮ፥ የገዛ ሕይወቱን ማክበርና መንከባከብ እንዳለበት ሲማር ነው።

በአስተዳደግ ጉድለት ምክንያት አንዳንድ ልጆች ማድረግ የሚገባቸውን ለይተው ስለማያውቁ ነው ችግር ውስጥ የሚገቡት። ያለፈውስ አለፈ፤ ህጻናት እንዲያውቁና እንዲጠነቀቁ መነገር ያለበት ገና ከፍ ሳይሉ (ገና 13 ዓመት ሳይሞላቸው) ነው። አያድርስ በብልግና የሚመጣ በሽታ መሆኑን ልጆች ገብቷቸው፥ እራሳቸውን ከዚህ በሽታ ለማራቅ፥ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መምከር ያስፈልጋል።

ከሚቀጥለው ትውልድ ቀጥሎ፥ የኢትዮጵያ ልጆች አያድርስ እንዳያገኛቸው ለማድረግ የሞራል (የግብረገብነት) እና የሃይማኖት ትምህርት በሠፊው ማስተማር ያስፈልጋል። ስለ መንፈሳዊነትና ስለ መንፈሳዊ ኑሮ ካልተሰበከ፥ አለማዊ ኑሮ ሲከብድ በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡ ግለሰቦች ለገዛ ሕይወታቸው የማይሳሱ፥ ለጤንነታቸውም የማይጠነቀቁ ይሆናሉ። ዘወትር እራሳቸውን ስለሚያሳንሱም፥ በምድር መኖርና

መሞት ካለ ምክንያት ይመስላቸዋል። በግዴለሽነት ስለሚኖሩም፥ የዘለአለም ጸጸት የሚከት ድርጊት ውስጥ ሲገቡ እንኳን አይታወቃቸውም (አይታያቸውም)።

በአያድርስ በሽታ የሚሰቃዩ ሁሉ ስለበሽታው ስለማያወሩ፥ የዝቅተኛነት መንፈስ እየተሰማቸው፥ "የሰው ልጅ ጠባዩ ይቃኛል በግድ፥ እኔስ የቀረልኝ ምድርን ትቶ መሄድ...፤" በማለት የተቀረውን እድሜአቸውን እንኳ በሚገባ ሳይጠቀሙበት ያልፋሉ። የሌሎችን ስሜት ለመጠበቅ ሲሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ያፍራሉ። እነኚህን የሚወደዱ ሴቶችና ወንዶች ወጣቶች፡- "ኑ! ከውጪ ሆናችሁ አታልቅሱ፤ ከኛ ጋር አብረን እንሁን፤.." እያለ የሚያደፋፍራቸው ጠፋ።

እራሱ የማያለቅስ፥ አይዟችሁ አታልቅሱ የሚል ጠፋ፤ ለቀስተኞችም የሚያለቅሱት ለሟች ሳይሆን በቁም ለሚሰቃዩት ሆነ። የሟች መለየት በቋሚዎቹ ላይ በአለማዊና በመንፈሳዊ መንገድ ጉዳት የሚያስከትል ሲሆን፥ በዚህች አስደንጋጭና አስፈሪ ምድር ላይ ብቻዬን ቀርቼ እንዴት ሆኜ እኖራለሁ የሚል ውስጣዊ ስሜት እየቀሰቀሳቸው ምርር ብለው ያለቅሳሉ።

አዎ! ልቅሶም ብዙ አይነት ነው። እንጀራ ከሌማቱ እንዳይጠፋ ሠርቶ የሚገባ የልጆች አባት፥ ከውጪ አያድርስን ሸምቶ ሲገባ፥ ባልና ሚስት ሲታመሙ፥ ምግብ ከቤት ሲጠፋ፥ ልጆቹም "ራበን....ራበን.." ብለው ሲያለቅሱ የሚለቀስ ልቅሶም አለ። አንዳንድ ጊዜም እንዲህ አይነቱ ልቅሶ ጅማትን ወጥሮ፥ ትኩሳትና የራስ ምታት በሽታን የሚያመጣ ይሆናል። ኑሮ ከአቅም በላይ ሲሆን፥ ሃዘን ሲበዛና ከድህነት ጋር በጤንነት መኖርም ሲያቅት፥ አይምሮ "ለኔስ የሚቀለኝ ይህ ነው" ይልና ይሳነፋል፤ የዛን ጊዜ ሰው መደበኛ ሥራውን እየረሳ፥ መቀባጠር ይጀምራል፥ እብደትም ይከተላል።

አንዳንድ እናቶች፥ አባቶች፥ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ስለ ልጆቻቸው በጠና መታመም እንጂ፥ በምን በሽታ እንደታመሙ ስለማይነገራቸው አያውቁትም፤ ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ከለቅሶ ጋር የተደባለቀ ጸሎት ከማድረግ አያቋርጡም።

የቤተ ክርስቲያን ጸሎትና ስነ ስርአት ሁሉ ሲገባደድ፥ ሰውም መስቀል ተሳልሞ ወደየቤቱ ሲሄድ፥ እናት ወደ ኋላ ጎተት ብላ ትቀራለች፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ያለበት ስዕል አጠገብ ትቆማለች። ፈራ ተባ እያለች፥ እንደምንም የተቸነከረውን የክርስቶስን እግር ነካ ታደርግና አንገቷን ትደፋለች። እንዲህም ትላለች፡

"እነሆ! ሰማይ ዙፋንህ፥ ምድርም የእግርህ መርገጫ....፤ አንተም እንደ ሰው በጠባብ ደረት ተወስነህ፥ .....አንተም እንደ ሰው በምድር ላይ መከራን የተቀበልክ አምላክ ሆነህ፥...ችግሬንና መከራዬን እያየህ፥.... እያየህ፥...ጌታዬና መድኃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ምነው ጨከንክብኝ፤ ምነው ጨከንክብኝ፤ ምነው ጨከንክብኝ........."።

አዎ! በኢትዮጵያ ጨለምለም ያለውን ሥፍራ ለተመለከተ፥ ከሰማይ ነጭ ደመና የራቀውን ያህል በረከቱም እንዲሁ ርቋል ያሰኛል። ሰውም ወደ ፈጣሪ አምላኩ ይጣራል። እርሱም "ሁል ጊዜ ይሰማል፤ ግን ብዙውን ጊዜ መልስ ሳይሰጥ ዝም ይላል..."። ሰው ለሰው ደጅ ሲጠና፥... ተለማኝ ሰው ለማኝ ሲሆን፥.... ይህን ሁሉ እያየ እግዚአብሔር ዝም ይላል?

ሕዝቦች አለቀሱ በልባቸው፤ ምነው እግዚአብሔር ጨከነ ብለው። ደጋግ ሰዎች ግን የማያቋርጥ እርዳታ ያደርጋሉ፤ እነርሱ ችግረኞችን ለመርዳት ሲሉ፥ እነርሱ ራሳቸው ለማኞች ሆነው (ልመናን ተለማምደው)። የእግዚአብሔር ደግነት ከነኚህ ደጋግ ሰዎች ያነሰ ነው ወይ እንዴ? ከሰው በላይ ሆኖ የሚያይ አምላክ የሰዎችን ደግነት እያየ የራሱን ደግነት ማሳየት አቃተው ወይ?

አልገባኝም። እግዚአብሔር ሲያስብ እሩቅ፥ ጊዜውም ረጅም...። አይ!! ..እራሴን አመመኝ፤ ዞረብኝ፤ ምነው ጥንቱን እንደወጣሁ በቀረሁና ባልተመለስኩ አሰኘኝ፤ ምላሴ ተኮላተፈ፤ ተንተባተብኩ፤ መናገርም አቃተኝ። ከምድራዊነት ራቅ ብዬ ካላሰብኩ ይህን ስሜት ልቆጣጠረው አልቻልኩም፤ አንዳንድ ጊዜ ምድራዊ ስሜታዊ አስተሳሰብ መንፈሳዊነትን ያስረሳልና።

አዎ! የእግዚአብሔር ደግነት ከሰዎች ደግነት አያንስም። ደግነቱን በአካላዊ መንገድ ብቻ ሳይሆን፥ በመንፈሳዊም መንገድም መመልከት ይገባል። ምንም እንኳን ሥጋ ሲጎዳ ሃዘን የማይቀር ቢሆንም፥ በመንፈሳዊነት ሰማያዊ ደስታ ሊሰማን ይገባል። ሰው መንፈሳዊነቱን ረስቶ ሥጋዊነቱን ብቻ በማስደሰት ከተወሰነ፥ ብዙ ችግር ሊደራረብበት ይችላል። በጨዋነት አድጎ በጨዋነቱ የዘለቀ ሰው የአያድርስ በሽታ አይነካውም። እግዚአብሔር ሰው ጨዋ ሆኖ በኑሮው ተደስቶ ይኖር ዘንድ ይፈልጋል። ጨዋነት ብቻ ነው የመጨረሻ መፍትሔ ሊሆን የሚችል።

"አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ፥ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና፥ ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ፥ ርስት ትሆኑልኛላችሁ። እናንተም የካህናት መንግሥት፥ **የተቀደሰም ሕዝብ** ትሆኑልኛላችሁ። ..።" ኦሪት ዘጸአት 19፡1 - 6

**<u>ደብረሊባኖስ</u>**

አዲስ አበባ ጥቂት ቀናት ቆየን። እኔም ባለቤቴን እንዲህ አልኳት፡- "ተወልደን ባደግንባት በዚህች በኢትዮጵያ ምድር፥ ድሮ በኃይለ ሥላሴ፥ ቀጥሎም በደርግ፥ አሁንም በኢሕአዴግ፥ ብዙ ብዙ አስጨናቂና አስደሳች ትርኢይቶችን እየተመልከተን አይምሮአችንን ሳናጨናንቅ አልቀረንም። ከመጣንበት ከመመለሳችን በፊት አገሩንና ሰውን የት ሄደን በድጋሚ እንመልከት?

ከውጪ የሚመጣ ሰውማ (በተለይ አገሩን በደንብ የማያውቅ ዳያስፖራ) የአዲስ አበባን ፎቆች፥ የከተማ ዘናጮችንም ያስተውልና፥ ወደ ትላልቅ ሬስቶራንቶችና ሆቴሎች ገብተው የሚዝናኑትን ያይና፥ የኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲሁ ያማረበት - ያለፈለት ሊመስለው ይችላል። እስቲ ጊዜአችንን ለመጠቀም ያህል፥ ከአንድ ለየት ያለ ሥፍራ ብቻ እንሂድ።”

እርሷም እንዲህ አለች፥ እንደተለመደው ረጋ ብላ፡- “ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ለመሄድ እቅድ አውጥተን የለም? ወደዛው እንሂድ እንጂ።”

ይህን ዝነኛ ገዳም ሳናይ አንመለስም ብለን ወስነን ስለነበር፥ ወደ ደብረ ሊባኖስ አመራን። ምን አይነት ሥፍራ ነው ይሄ? ከመሬት እስከ ሰማይ በቆመ የአለት ገደል የተገነባ አጥር፥ በዙሪያው ተፈጥሮአዊ የዝቅጠ አለቶች ርብርብ፥ ከበላያቸውም የእሳት ወለድ አለቶች፥ ሁሉም ተስማምተው እንደ ግርግዳ፥ በክብነቱ፥ በቁመናው እና በውበቱ ግርማ ሞገስ ያለው ሥፍራ። ዝቅ ብሎ ከረባዳው ሥፍራ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ያለበት - ከዚህም ሥፍራ የደብረሊባኖስ ገዳም።

በሃሳብ ብቻ ሳይሆን፥ ያንን በደብረ ሊባኖስ ገደል ክልል ያለ መሬት ከታች ከአዘቅቱ ሆነው ወደ ላይ ሲመለከተት፥ የገደሉ ጫፍ ሰማይን የሚነካ ይመስላል። የገደሉ ግርማ ሞገስ ሌላውን የመሬት ክልል ሂድ ወደዛ ብሎ በማባረር፥ ለራሱ በራሱ የሆነ ሌላ መሬት በመክበብ አዲስ አለም የፈጠረ ነው የሚመስለው። ምድርና ሰማይን የሚያገናኝ፥ የማይታይ ጎዳና ያለ ይመስላል። ሰላምና ተስፋ የሞላበት፥ ምድራዊነትን የሚከላከል የመንፈሳውያን ምሽግ፥ ይህ ገዳም በእውነት እጹብ ድንቅ ነው።

ከደብረ ሊባኖስ ገዳም በደረስን ጊዜ ይህ ነው የማይባል እረፍት ተሰማን። ገዳሙ የአለምን ችግሮች ሁሉ ሊጋፈጥልን የሚችል መሰለን። እውነት ነው፤ ለጊዜውም ቢሆን፥ የአለምን ችግሮች ሁሉ ተጋፍጦልናል ማለት እንችላለን፤ እዛ በቆየንበት ወቅት ሁሉ፥ ምድራዊ ችግሮቻችንን ሁሉ ረስተን በመንፈሳዊነታችን ብቻ ደስታን ሸምተናልና።

ከዚህ ገዳም ሳለን ሰውነታችንን ሁሉ አቅፎ፡- “አይዟችሁ፤ ከዚህ አለም ውጣ ውረድ እረፍት የምታገኙት በመንፈሳዊነታችሁ ስትንቀሳቀሱ ነው..፤” የሚል ስሜት ተሰማን (እንጃ፤ መሰለን፤ ብዙ ብዙ መንፈሳዊ ስሜት ታሰበን)። ደብረ ሊባኖስ ስለመጣን፥ በስባሽ በሆነ ሥጋችን የማናያቸውን ጻድቁ አባታችን ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን በመንፈስ የዳሰስናቸው መሰለን።

በደብረ ሊባኖስ በቅዱሱ አባታችን ስም የታነጸው ቤተ ክርስቲያን እጅግ የተዋበ ነው። እኛም ከገዳሙ አድረን በማግስቱ በባለቤቴ እናት (እናቴ) እየተመራን፥ በጧት ሄደን ጠበል ተጠመቅን። ካስቀደስንም በኋላ፥ መንፈሳውያን ድሆች

ወደሚገኙበት፥ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተሰሜን ካለው ሥፍራ ሄድን። ከዚህም ሥፍራ በደረስን ጊዜ እጅግ በጣም ብዙ ድሆች በእንጨትና በአሮጌ ጨርቅ በተሠሩ ትናንሽ ቤት መሳይ ዳሶች ውስጥ ትፍግፍግ ብለው ተመለከትን። አንዳንዶቹ ቁጭ ብለው፥ አንዳንዶቹም ተኝተው ይታያሉ። የታመሙትን ካልታመሙት መለየት አይቻልም። ሁሉም በሥጋ ቀሰስተኞች ስለሆኑ፥ ወደ መንደር ሄደው የሚለምኑ አይደሉም።

በመካከላቸው ያልታመሙ (ጤነኞች) ቢኖርባቸውም፥ የሚበሉት ምግብ የልባቸው ትርታ እንዳያቋርጥ የሚረዳ እንጂ፥ የእግር ጉልበት ሰጥቶ ከቦታ ቦታ የሚያላውስ፥ እየጮሁም ለመለመን የሚያበቃ የእስትንፋስ ኃይል (አቅም) የሚሰጣቸው አይደለም። ድህነታቸውን ተቀብለው፥ እራሳቸውን አሳንሰው፥ ካለ ምንም ምድራዊ ፍላጎት ይኖራሉ።

ከዚያው ሥፍራ መጥቶ የሚመጸውታቸውን የሚጠባበቁ አይደለም፤ ከሰማይ ምግብ የሚመጣላቸው ይመስላል እንጂ። በሥጋው የተጎዳ ሰው ከቀደሙ መንፈሳውያን ጋር የተያያዘ መንፈሱ ያጸናዋልና፤ ድህነትን ተቀብለው፥ በቤተ ክርስቲያን ዝማሬ ተማርከው፥ ከፈጣሪያቸው ጋር በጸሎት እየተገናኙ ይኖራሉ።

ከዚህ ሥፍራ የሚመጡና ከዚሁ የሚቀሩ ወንዶችና ሴቶች፥ የተለያየ ምድራዊ ሕይወት ያሳለፉ ናቸው። ምድራዊነት ሲገፋቸው፥ እነርሱም ከምድራዊነት ሲርቁ ሲርቁ ነው ከዚህ ከደብረ ሊባኖስ የወደቁት።

ታዲያ፥ የእያንዳንዱ ታሪክ ቢመዘገብ፥ የጠፈር አካላት ተመሳጥረው፥ ልክ ወደዚህ ቦታ እንዲመጡ ያስገደዷቸው ይመስል፥ የትም ቢሄዱ የትም፥ ወደ እግዚአብሔር ካልተጠጉ በስተቀር እንደማይሆንላቸው እርግጠኞች ሆነው ስለቆዩ ነው ከዚህ ሥፍራ ይመጡ ዘንድ ግድ የሆነባቸው። በገዳሙ አባቶች መንፈሳዊ እይታ ስለተፈቀደላቸው ነው፥ መጨረሻቸውን ከዚሁ ሥፍራ ያበጃጁት።

የደብረ ሊባኖስ መንፈሳውያን ከቤተ ክርስቲያን ተጠግተው፥
በገዳም የድሆች መንደር መሥርተው፥
በአባታችን መንፈስ ክልል ተወስነው፥
ከውጪው አለም ተገልለው፥
በመጽዋቾች እርዳታ ተንጠልጥሎ ነፍሳቸው፥
በረሃብ በሕማም ሲጣደፍ ሞታቸው፥
ሰማይ ቤት ለመሄድ፥ ዛሬና ነገን ተጠባብቀው፥
ሌት ተቀን ጸልየው፥ ሌት ተቀን ጸልየው....፤

ይህን የሚመስል ነው ምድራዊ ሕይወታቸው፤

በምድራዊ አይኖቻችን ስንመለከታቸው።

ወደ መንደር ስንሄድ፥ ብዙ ለማኞችን ተመለከትን። እነኚህ በምድራዊነታቸው ተስፋ ያልቆረጡ፤ በመንፋስዊነታቸውም ጥንካሬ ምድራዊ ጉስቁልናን መቋቋም ያልቻሉ ነው የሚመስሉት። እነኚህስ፥ በሚለምኑበት ጊዜ፡- "እንደምንም ብዬ በምድር ልኑር፥ ስለማላውቀውስ ሰማያዊ አለም ብዙ አልጨነቅም.." እያሉ የሚያስቡ ነው የሚመስሉት። ግን እነሱም በማይለምኑበት ጊዜ፥ ነፍስና ሥጋቸውን ከቤተ ክርስቲያን ጸሎት ማላቀቅ አይፈልጉም። ስለዚህ፥ ከዚያ የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ርቆ መሄድ አይሆንላቸውም።

አዬ!! ለኛስ ከባድ ነው የሚሆን፥ እንዲህ አይነት ኑሮ፥

ካለ ፍርኃት ተረጋግቶ፥

ከምድራዊ ውጣ ውረድ ተለያይቶ፥

በልዝብ ቋንቋ ተግባብቶ፥ ምስጋናን አብዝቶ፥

የተገኘውን በልቶና ጠጥቶ፥

በማወቅና አለማወቅ ትንንቅ፥ ትእግስትን አብዝቶ፥

እጅግ የከብዳል ኑሮ፥ ከዚህ ሥፍራ፥

ሰው ሥጋን ከነፍሱ ሲለይ ከሚታይበት፥

ሕዝቦች ሁሉ እንዲህ በርቀት ከደቀቁበት፥

ጨርቃም ለማኝ በሆኑበት፥

ግን ከፍታና ዝቅታ በጠፋበት።

ባለቤቴ በነኚህ ድሆች ልቧ ተነካ። ለድሆች የመደብነው ገንዘብ ወዲያውኑ አለቀ። "ከእንግዲህ ከዚህ ሥፍራ መቆየታችን ለምንድነው? በይ እንሂድ" አልኩ ኮከቤን። እርሷ ግን ልቧ ተንጠለጠለ። ኮከቤ ደግ ሴት ናትና፥ መንፈሷን ከዚህ ሥፍራ ልታላቅቀው አልቻለችም (አልፈለገችም)። በተለይ አንድ ሰው፡-

"ኑ እባካችሁ፥ ድሆችን ለመርዳት የማደርገውን ተመልከቱልኝ" እያለ ሲጋብዘን፥ ኮከቤ ሰውዬውን ተከትላ መሄድ ፈለገች። እኔን ደግሞ አንዱ ዲያቆን፡-

"እዚህ ደርሰህ አሰቦን (አባታችን ቆመው የጸለዩበትን ዋሻ) ሳታይ ትሄዳለህ?" ይለኛል። ገድላቸውን ሳነብ ያነባሁት እንባ ትዝ አለኝና፥ ተመልሶ እንደሚመጣ ሰው ሆኜ ችላ አልኩት።

"በገድላቸው የተጻፈውን ሁሉ የዘመኑ ሰው በቀላሉ አይቀበለውም...፤" በማለት ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ (1951) አስፍረውታል። እሳቸው የታሪክ ጸሐፊ ናቸውና፤ የዘመኑ ሰው ስለአባታችን የተተረከውን በቀላሉ የሚቀበለውን ብቻ መዝግበው የተቀረውን ትተውታል። ግን የአባታችን ታሪክ በደንብ ባለመታወቁ እየጸጸታቸው የሚከተለውን ጽፈዋል፡-

"የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ታላቅነትና መንፈሳዊነት ከሚያስረዱት ከብዙዎቹ ነገሮች ውስጥ አንባቢ ሊረዳላቸው የሚገባው በጳጳስነት ሲገዙ ኖረው፥ በዚያው በዘመናቸው ጳጳስ እንዲመጣ መፍቀዳቸው፥ ከመጣ በኋላም[13]፥ ለሥልጣኑ ሳይጓጉ፥ ሳይቀኑም፥ ጠብና ጦርነትም ሳያስነሱ በሰላም አስረክበው፥ እርሳቸው ወደገዳማቸው መግባታቸውን ነው።" ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 1951 (የኢትዮጵያ ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ፥ ገጽ 19)።

ኮከቤም፡- "እነኚህን ድሆች በተደራጀ መንገድ መርዳት ይቻል ይሆናልና፥ ወደዚህ ሰውዬ እንሂድ" ብላ ጨቀጨቀችኝ። እኔም፡-

"እባክሽ ጊዜም የለን፤ አውቶብሱም ያመልጠናልና እንሂድ" ብዬ አከላከልኳት፤ ቅር እያላት አውቶብሱ ውስጥ ገባን። መንገድ ስንጀምር፥ እህ! እያልን..... በሃሳብ ተዋጥን። የባለቤቴን መንፈሳዊ ቅንአት እንዳልነካም እየተጠነቀቅሁ ቀስ ብዬ ተናገርኩ፡-

"ኮከብዬ፤ እኔም እኮ ምኞቴ የሥጋ ያይደለ፥

ምነው መንፈሴ ከደሆቹ ወገኖቼ ጋር በተቀላቀለ።"

እርሷም እንዲህ አለች፡-

"እንዳየሽውና እንደተመለከትከው፥

በኢትዮጵያ በዝቷል ድሃው።

የተማረውም ያልተማረውም፥ ድህነትና ልመናን ሰልጥኖበት፥

ሆድ ሲርበው፥ እንጀራ ልመና፥ ከቤት ወደ ቤት ጉትት...ጉትትትት።

በጎስቋላ ሥጋ - በተጨማደደ ፊት፥

ውስጣዊነት ሲተካ በውጫዊነት፥....

---

[13] "... አባ ዮሐንስ ከግብጽ ከመጣ በኋላ፡- "ለኔ ለምጻተኛው ይህ ሥራ አይገባኝም፥ ይህንስ የምወደው ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቀድሞም ታዝዤ ነበር፤ በመልአኩም እጅ ክህነት የሚሰጥበትን መጽሐፍና ቅብን ሚሮኑን ልኮልኝ ነበር፤ እነሆ እኒህ ናቸው" ብሎ አሳየውና ለሱ ሰጠው።" ገድለ ተክለ ሃይማኖት (ታህሳስ 15 ቀን 1946 ዓ.ም. ገጽ 205 – 206)።

የኛስ ኑሮ ምንድን ነው ከዚያ ማዶ፤
ከአገር ከወገን ርቆ፥ ከባዕድ አገር ተሰዶ፤
ምንድነው የኛ ሩጫ፥ ለሥጋ ብቻ ተስገብግቦ፥
ዘለአለማዊነትን አርቆ፥ ጊዜያዊነት አቅርቦ።
ገንዘብ ለመሥራት ተጣድፎ፥
ፍላጎትን አብዝቶ፥
በፍቅረ ነዋይ  ተጠምዶ፥
መንፈሳዊነትን ረስቶ።

የፈረንጅ አገር ምግብ በልተን ጠገብን፤
ከሁሉም በላይ ተራብን።
እንዴት እናርካ ጥማችንን?
ምን እናድርግ በኑሮአችን፤
ተወስነን እንዳንቀር ለራሳችን።

ከእንግዲህስ አቅማችን በፈቀደ፥ እኔና አንተ እነኚህን የደብረሊባኖስ ድሆች እንርዳ። እስቲ አስብበት፤" አለችኝ በአንክሮ። እኔም "እሺ....." አልኩ ከልቤ (አብረውኝ እሺ የሚሉ ሰዎች እንዲኖሩ እየተመኘሁ)።

የገዳሙን ሥፍራ ለቀን ወደአቀበቱ ከፍ ከፍ እያልን ስንወጣ፥ ከሩቅ የሚጣራ "ነገር" ያለ መሰለ።

የጻድቁ አባታችን ልጆች የሚኖሩበት የድሆች መንደር - በደብረሊባኖስ ያለ መንፈስ እኛን ከቶ ሊለየን የፈቀደ አልመሰለኝም።

አይረሳምና ሥራቸው፥ ድሆችን የሰበሰበው መንፈሳቸው፥
እሱው ሳይሆን አይቀርም ከሩቅ የሚጣራው፥
የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደግነታቸው።
ማንም ይሁን ማን የሰው ደግነቱ፥
የሩቁን የሚስብ፥ ፍቅር ኃያል ነው ስበቱ፤
ደግ ሰው እጁን ሲዘረጋ መታየቱ፥
መንፈሳዊ አብሮነት ነው ሕይወቱ፤
ፍቅር፥ ደስታ ነው ውጤቱ።

እህህ!..ወይ የጊዜ ርዝመት፥
ቅጽበት እንደ ሺህ ዓመት።
ሰው መሆን ሲያስመርር፥
ሲያደናቅፍ ደግነት፥
አብሮ መኖር ሲያቅት፥
ስጦታን መቀበል፥
መስጠትም ሲያዳግት።
አይከለከልም ምኞቴ፥
የጻዲቁን አባት መንፈሳዊ ሕይወት መመኘቴ፥
ለኔ ብቻ አይደለም፤ ለኢትዮጵያችን ሁሉ ቢዳረስ፥
በከተማም፥ በገጠርም - ያ የደበረ ሊባኖስ ደግ መንፈስ።
በቃ! በቃ! በቃ! ምድራዊት ኢትዮጵያ፥
በእውነት አንቺ ነሽ መስተዋት - የሰማዩን መመልከቺያ።
ኪሩቤል የሰይፍ ነበልባል የያዘብሽ፤
በምድርና በገነት መካከል - አንቺ ኬላ (ድንበር) ነሽ።
ለአብርሃምና ለዘሩ፥ የዘለአለም ምሕረቱ እንዲጸናልሽ፥
የማርያም ጸሎቷ አይለይሽ።
እምዬ ማርያም፥ ቤዛይት አለም፥
እግዚእትነ ማርያም፥ የምንል ልጆችሽ፥
እኛ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የምንወድሽ፥
ተማጽነንብሻል ዛሬ፥ ስለፍቅርሽ፥
ምልጃሽን አታቋርጪ፥ እንዳንጠፋ ከሃሳብሽ።

በመሬት የመኖር ግዴታችን እነኚህን ድሆች አብረናቸው እንድንቆይ አላደረገንምና፤ ቅር ቅር እያለን ተለየናቸው። በዛች አንድ ቀን ጧት፥ የብዙ ድሆች መንፈስ ሞቅታ ከዚህ ከምናየው አካላዊ አለም የተለየ ስሜት አሳድሮብን አዲስ አበባ ገባን፤ ከዚያም ጥቂት ቀናት አድረን በግድ ወደ ፈረንጅ አገር ተመለስን።

***ያ ቀን ያልፉል***

ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ ሰማይ እንደዘረጋች፥ እግዚአብሔርም ስለ ሕዝቦቹ የዘለአለም ምሕረቱን እንደሚያስብ ማወቃችን - ይህ ነው ታላቁ ተስፋችን። ኢትዮጵያ አንድ ድሃ አገር ሆና፥ በውስጧም ያሉ ሰዎች ብዙዎቹ ተቸግረው፥ በበሽታም እየተሰቃዩ በሃዘንተኛነት የሚኖሩ ሆነው ሳለ፥ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ይታያሉ። ምንም ችግር ቢበዛባቸው፥ የፈጠራቸውን አምላካቸውን ተመስገን ብለው ሲያመሰግኑት፤ በእውነት ይህ እንዲህ ያለው ጠባይ መልከ ሰማይ እንጂ መልከ ምድር አይመስልም።

በእርግጥ እግዚአብሔር የሰው መንፈሱን እንዲሁም ሥጋውን እንዳይጎዳ ያስብለታል። ታዲያ በድህነት የኖሩ፥ ወይንም ምድራዊነት በቃን ብለው ወደ ገዳም የተጠጉ ሁሉ፥ ለተቀረ ሕይወታቸው ፍጹም መንፈሳዊ መልክ ለመስጠት ይነሳሉ፤ በእግዚአብሔር ቸርነትና ፈቃድ ለመኖር ይወስናሉ፤ እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ በእርሱ የመንፈስ ክልል ውስጥ መቆየትን መርጠው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጠጋሉ። ምድራዊ ጥቅም ባያገኙም፥ የመኖርን እድል ስለሰጣቸው ብቻ፥ ስንሞት ፈጣሪያችን ይወስደናል እያሉ በተቀረው እስትንፋሳቸው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይኖራሉ።

“እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን።” መዝ. 150፡6

በእውነት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መንፈሳዊነታችን የሚያንጸባርቀውንም ክፍል (ምድራዊት ኢትዮጵያ ሰማያዊ መሆኗን) ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይገባል። በአገራችን በየጊዜው የሚከሰተው መጥፎ ነገር ሁሉ ጣደፍ ጣደፍ እያለ ቢያስጨንቀንም፥ መጨረሻው ያማረ እንዲሆን የሚያደርገው፥ ምድራዊነታችን ብቻውን አይደለም፤ በመንፈሳዊነታችን የሚገኝ ደግነታችንም ጭምር ነው እንጂ። አገራችን ሰማያዊ ምድራዊ አይደለችም፤ ምድራዊ ሰማያዊ ናት እንጂ። ምድራዊነት ብቻ አይደለም ታሪካችን የኛ። ምድራዊት ኢትዮጵያችን ሰማያዊትም ናት - ሰማያዊም ነው ታሪካችን የኛ።

እጆች <u>ሲዘ</u>ረጉ ወደ ሰማይ፥ <u>አለ</u> ሌላ ሕይወት የማይታይ፤

ወደ ታች ያይደለ፥ ወደ ላይ፥ ወደ ላይ፥ ወደ ላይ።

በምድራዊነት ጥጋብ የለም፥

ምድራዊ ሰው በቃኝን አያውቅም፤

በመንፈሳዊነት እልጠግብ ባይነት የለም፥

መንፈሳዊ ሰው ረሃብን አያውቅም።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሊነግሥ አልመጣም፤

ኢትዮጵያም ምድራዊት ብቻ አይደለችም፤

ምድራዊነት አይጸዳም፤ አያምርም፤
ምድራዊነት ስለማይጸዳ፥ ስለማያምርም፥
ኢትዮጵያ ምድራዊነት ብቻውን አልተስማማትም፤
ያ ቀን ያልፋል፤
ኢትዮጵያችንም ወድቃ አትቀርም።

**በረከተ ጸሎት**

ቸሩ እግዚአብሔር አምላካችን፥
በመንፈስ - በሥጋ ፈጣሪያችን፤
ስንጨነቅ አንተው ነህ መጽናኛችን፤
ስንፈራም አንተው ነህ ብርታታችን፤
ስንጠቃ አንተ ነህ መከታችን፤
አለማወቅ ሲያሳውረን፥ አንተ ነህ ብርሃናችን፤
አንተው ነህ እውነት - መመሪያችን።
አቤቱ አምላካችን፥ ተስፋችን - መመኪያችን፥
ባንተ መንፈስ ክልል ምንጊዜም እንድሆን፥
ጠብቅ ልጆችህን፤ ተመልከት ፍጥረትክን።
የሰማይ መንግሥት አልታይ ቢለን፥
እምነት ከእውነት አልሰምር ቢለን፥
በአለማዊነታችንም እንቅፋት ቢበዛብን፥
ምድራዊ ችግሮች ተስፋ ቢያስቆርጡን፥
ቸሩ እግዚአብሔር አምላካችን፥
ባንተ ነው ትኩረታችን፤
ባንተ ነው ተስፋችን።
ከጨለማ/ከጉድጓድ አውጣን፥
ቀናውንም መንገድ አሳየን፤
ድርጊታችን ሁሉ ወዳንተ የሚመራ ይሁንልን።

**ኢትዮጵያ ልጆችሽ ያንቺው ናቸው**

(መዝሙር - መንፈሳዊ)

አዝማች

ኢትዮጵያ ልጆችሽ ያንቺው ናቸው፥

አይለይም ከሕዝብ ልቡናቸው - አይርቅም ከወገን መንፈሳቸው።

አንቺ ቅዱስ አገር፥ ትዝታዬ፥

ሳልምሽ አድራለሁ ባይምሮዬ - ሳልምሽ አድራለሁ ባይምሮዬ።

ምድራዊ ችግሮች -- ከሩቅ በተናቸው፥

በአካል ተለዩ -- ወጡ ካገራቸው።

ይህ ችግር ጊዜያዊ -- ከቶም ይበቃዋል፥

ሁሉም ከሄደበት -- ፈጥኖ ይመለሳል።

አዝማች

እናንት ያገር ልጆች -- ትት በያለበት፥

መልካሙን አስቡ -- አትራቁ ከእውነት፤

በብልጭልጭ ነገር -- መታለሉ ይቅር፥

ለሕዝቦች እናስብ -- ለራስ ማሰብ ሳይቀር።

አዝማች

ከወዴት ይገኛል -- ተወዳጅ ድሃ ሕዝብ፥

በጠባዩ ሃብታም -- በሌለው የሚጠግብ፥

ይህ መንፈስ ይጎልምስ -- ውብ ቆንጆ መልካችን፥

ሁላችን እናስብ -- ለውድ አገራችን።

አዝማች

ለማግኘት አንጓጓ -- ለመስጠት እንሩጥ፥

ከቶ ምንም የለም -- ከመንፈስ የሚበልጥ፤

ችግር የሚረሳው -- ደስታም የሚገኘው፥

ለሌላው በማሰብ -- በእምነት በመኖር ነው።

አዝማች

# ምዕራፍ አምስት

## ኢትዮጵያችን እና አንድነታችን

እሾከና አሜከላ በበዛበት ምድራችን የምንመላለስ እኛ፥ ስለ ኢትዮጵያችን ማሰቡን አላቋረጥንም። ለምን ነበረ በገዛ አገራችን ተደላድለን መኖር ያቃተን? ለምንስ ተሰደን፥ ከባእድ አገር ለመኖር ተገደድን።

ከሰው ለተፈጠረ የማይገባ፥ ብዙ ድርጊት የተፈጸመባት አገር ውስጥ ያደግን እኔና ወገኖቼ (ያሉትም የሄዱትም) ኢትዮጵያን (ኤርትራንም ጨምሮ) አላጠፉናትም፤ ኢትዮጵያ አሁን እንደሚያዩአት ሳይሆን፥ ከዘመን ዘመን ተሸጋግራ፥ ልዩ ሆና በክብር ተቀምጣለች ከአይምሮአችን።

አገሩን ለቆ መሰደድን ማን መረጠው?

እጣ ክፍላችን ይኸው ሆኖ ነው እንጂ የተገኘው፥

በሄድንበት ሁሉ እንግዳ ሰው፥

ክብራችን ኢትዮጵያዊነት፥

ምንጊዜም ከኛ ጋር ነው።

ያገራችንን - የመሬቱን - ያፈሩን፥ የድንጋዩን፥ የሳር የቅጠሉን፥

የጫካውን፥ የሸለቆውን፥ የሜዳውን የተራራውን፥

የእርሻውን፥ የበረሃውን፥ የዱሩን፥ የቀዬውን፥

የከተማውን፥ የመንደሩን፥ ከዳር እስከዳር ሁሉን፤

አንረሳም ለምንጊዜም፤

የተወለድንበት በሥጋም በመንፈስም፥

ትዝታዋን የአገራችንን።

በኢትዮጵያችንስ ተስፋ አንቆርጥም፥

ለውጥ ቶሎ ቢመጣ፥ ባይመጣም፥

ጊዜው ቢያጥር፥ ቢረዝምም፥

ኢትዮጵያችን ከአይምሮአችን ተረጋግታ ተቀምጣለች፤

እርሷም በፈጣሪዋ ጊዜዋን ትጠብቃለች።

እነሆ! በኢትዮጵያችን ውስጥ ከሚታየው መደናቆር አንጻር - ከየአቅጣጫው ጎላ ብሎ ከሚሰማው ከንቱ ወሬ አንጻር - የኢትዮጵያችን (የኤርትራችንም) ሂደትና መጻኢ ያሳስበናል። የብዙሓን ጩኸትና ልቅሶ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛና እየመረረ ሲመጣ፥ በሰው ሁሉ አይምሮ ሰርጾ የሚገባ ሃሳብ ከጠቅላላ የሰብአዊነት ሁኔታ ጋር ይያያዛል። ስለዚህ የተሻለ ለውጥ እስኪመጣ ድረስ የሰብአዊነት መንፈስ እርፎ አይተኛም።

በውጪ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያንም/ኤርትራውያንም ይህን ወደ ሰማይ የወጣ ጩኸትና ልቅሶ ሰምተው እጅጉን አልቅሰዋል።

አንዳንዶቻችን ዝም ብለን ቆየን፥

ጥሩ መንግሥት የመጣ፥ ግድያ፥...ከእስር ቤት መታጎርም ቀርቷል መስሎን፥

ሲያልፍ መጥፎው ቀን፥ ስንጠብቅ ጥሩውን፥

ብዙ ዘመን አለፈብን፥ ከእውነታው ርቀን፥

ለአንዲት ኢትዮጵያ መቆም አቃተን፥

በተበታተነ ሃሳብ እየተጨቃጨቅን።

ግን አሁን አልተቻልንም፥ እንባ ተናነቀን፥

የዝምታ ትኩሳት አንገላታን።

ወይ ጉድ! ስንቱን አሳየኸን? ስንቱን?

የሚያዝኑት፥ የሚያለቅሱት አስለቀሰን።

የወደፊቷ ኢትዮጵያ አሳሰበቺን።

በችኮላ ሳይሆን በቀስታ፥ ፊት ለፊት ሳይሆን በእጅ አዙር፥

ተቃዋሚ - ተቀናቃኝ ሁሉ እንዲሰወር፥

ጥንትም እንዲሁ ነበር፥

የአዲስ መንግሥት የተለመደ ፈሊጥ፥

የመቆያ ምሥጢር።

አምባገነኖች ለሚደግፏቸው ደጎች፥

ለሚቃወሟቸው ተናዳፊዎች፥

የሕዝቦች እልቂት የማይሰማቸው ጨካኞች፥

ከፋፍለው 'ሚገዙ "ልዝብ ሰይጣኖች።"

ከእንግዲህ ማነው የሚያይለት? የሕዝቡን ጉዳቱን፥
እንግሊዝ፥ ፈረንሳይ ወይንስ አሜሪካን?
እባክህ አምላካችን አታሳየን ጉዱን፤
በቃችሁ በለን፥
የሃዘን እንጉርጉሮ በሽታ ሆነብን፤
ኢትዮጵያን/ኤርትራን ጠብቃት፤
አንተው ተመልከተን - አትሰውር ፊትክን።

በሰው ልጅ መከፋት ማርያም ታለቅሳለች፤
ሃዘን አልቀረላት፥ ኢትዮጵያን እያየች።
እመቤቴ ማርያም አታቋርጪ ጸሎትሽን፥
እባክሽ ለምኚው አስራት የሰጠሽን ልጅሺን፥
ምህረቱን እንዲያወርድልን፤
ደጉን መንግሥት እንዲያመጣልን።

ይህ መጽሐፍ በተጻፈበት ወቅት በኢትዮጵያችን ውስጥ እጅጉን ዘግናኝ የሆኑ ግፎች እየተፈጸሙ ነው። ዝርዝር ጉዳዩን ከዚህ ለማስፈር ይህ መጽሐፍ አቅም የለውም፤ ሆኖም ከመመላለሺያ አለማችን፥ እስከ መኖሪያ አገራችን (ኢትዮጵያችን፥ ካናዳችን፥ አሜሪካናችን..)፥ በፖለቲካ እና በሃይማኖት አክራሪዎች እንቅስቃሴ ምክንያት የመኖር ህልውናችን ሲናጋ እያየን ዝም ብለን እንዳንቀመጥ፥ በተለይ የህብረታችን እና የአንድነታችን ጉዳይ እጅጉን ያሳስበናል።

ኢትዮጵያ ሕዝቦቿን ሁሉ የምታቅፍ መሆኗ እንዳይታወቅ፥ ሕዝቡን በሃይማኖት እና በጎሳ እየከፋፈሉ ለማጣላት፤ በፖለቲካም ሕዝቦች የሚፈልጉትን እንዳያውቁ ለማድረግ፤ የኢትዮጵያ መሪዎችም የሥልጣን ዘመን በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መከፋፈልና እርስ በርስ መጣላት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ተስተላክሎ ከተቀመጠ ቆይቷል።

ሆኖም፥ ዝርዝር ጉዳዮችን ትቶ፥ አጠቃላይ ሂደቶችን ለተመለከተ፥ የኢትዮጵያችን ነገር ማንም ሰው የተባለ ፍጥረት ሊገባው በማይችል ሁኔታዎች፥ አንዳንድ ክስተቶች ሲፈጸሙና፥ ኢትዮጵያችን በአንድ ሰማያዊ ኃይል ስትመራ ነው የተመለከትነው። እስላምም ሆነ ክርስቲያን እግዚአብሔር በእርሱ የሚያመልኩትን ይሻል። ስለዚህ፥ እግዚአብሔር ዝም ብሎ አያይምና፤ ሕዝቦች ሁሉ፥ "ልክ ናቸው ልክ አይደሉም፥" ሳይል፥ በሕብረት ሆነው በአንድ ቃል የሚለምኑትን ሰምቶ፥ እንደ የጋራ

ፍላጎቶቻቸው ይፈጽምላቸዋል (በሕዝቦች በጎ ፈቃድና ንቃተ ሕሊና እርሱ ጣልቃ አይገባምና)። እግዚአብሔር ሕዝቦች ተባብረው በአንድነት የሚጠይቁትን እርሱ ሲሰጣቸው፥ የእነርሱ ልመና አግባብ ያለው (ልክ) ከሆነ ይጠቅማቸዋል፤ ልክ ካልሆነም ለወደፊቱ በጋራ ይማሩበታል።

ከዚህ መጽሐፍ አቅም አንጻር ተነስተን፥ አንዳንድ ወሳኝና አቢይ ክስተቶችን ብቻ በመመልከት፥ ለወደፊት የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድ ሆነው አምላካቸውን እያመለኩ፥ በሰላምና በፍቅር እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን የበጎ ፈቃድና የንቃተ ሕሊና ብቃት እንመለከታለን።

***ታሪካዊ ቅድመ ሁኔታዎች***

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) በትግራይ ውስጥ ታላቅ ምሽግ በአሲምባ መሥርቶ ነበር። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ የነበሩት (ወያኔዎችም) በኋላም የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ግንባር (ኢሕአዲግ) በወቅቱ በከፍተኛ ደረጃ በጦር ተደራጅቶ ከነበረው የኤርትራ ነፃ አውጪ ጋር ግንባር ፈጥረው ነበር።

የኤርትራ ነፃ አውጪዎችም የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ብለው፥ ወያኔዎችን ተጠቀሙባቸው። ወያኔዎች ከኤርትራ ነፃ አውጪዎች ጋር ሲወዳጁ፥ የኢሕአፓን የጦር ግንባር (ኢሕአሠን) "እናንተ ኤርትራ የኢትዮጵያ ኮሎኒ (ቅኝ ግዛት) መሆኗን ክዳችኋል፤ ስለዚህ ኤርትራ ነፃ እንድትወጣ ፍላጎት የላችሁም.." በማለትና በሌሎችም በጥቃቅን ቅራኔዎች ጠመዷቸው፤ ቅራኔውም እየተባባሰ መጣ። ጥንትም እራሱን በራሱ መከፋፈል ግድ እስኪሆንበት ድረስ ከእውነት ፈቀቅ ማለትን የማያውቅበት ኢሕአፓ፥ ከወያኔዎች ጋር ተጣላ።

ኢሕአፓን ጥንትም ሁለት እውነቶች አጨቃጨቁት እንጂ፥ ውሸት ሥር ሰዶ የፖለቲካ መሳሪያ አልሆነበትም። ለታክቲክ ተብሎ እውነት ያልሆነው ሁሉ ሲነገር፥ በተለይም በፖለቲካ መመሪያ ውስጥ የሚካተት አላማ አገር የሚገነጥል ሲሆን፥ ከእንደዚህ አይነቱ የፖለቲካ ድርጅት መወዳጀት ያቃተው የኢሕአፓ የጦር ግንባር - የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ከትግራይ ለቆ መውጣት ግድ ሆነበት (ተገደደ)።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁልቁል ወደ ረመጥ የነዳ፥ ፋሺስታዊው ደርግን የጣለ ወያኔ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ውለታ መሥራቱን ታሪክ አይክደውም። ሆኖም፥ የሥልጣን ተቀናቃኝ ይሆኑብኛል በማለት ብዙ ባይፈራ እና ለተያዙት ለታሰሩት ኢሕአፓዎች ምህረት ቢያደርግ ኖሮ፥ ይህ የርህራሄ ጎኑ አንድ ሊያስወድደው የሚችል

መልካም ምግባር ይሆንለት ነበር። ገና ከጥንቱም ከኢሕአፓዎች ጋር ባይጣላ፥ እነርሱንም አቅፎ፥ አብሮ መሥራት ቢችል ኖሮ፥ ኢሕአፓዎችም (አከራሪዎቹ)፥ ለአገራቸው ሲሉ ትንሽ ለዘብ ማለትን ቢያውቁበት ኖሮ፥ ምናልባት በሁለቱ ጣምራነት የሚመሠረት መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዘላቂ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ያዘጋጀው ነበር። ይህ ሳይሆን ቀረና፥ በጊዜው የነበሩ ሌሎችም የፖለቲካ ኃይላት ሙሉ በሙሉ ከሕዝቦች ጋር ሳይሆኑ ቀሩና፥ ጥንካሬም ጎደላቸውና፥ "ሌሎችም ሁናቴዎች" በአገራችን ተፈጠሩና፥ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ባይሆንም፥ የጠላቴ (የደርግ) ጠላት ወዳጄ ሊሆን ይገባዋል በማለት አብሮ ለመሥራት የተመኙ የነቁ የፖለቲካ ድርጅቶችም አልሆነላቸውም፤ ቢሞከሩም አልተሳካላቸውም።

ከትግራይ ተባሮ ጎንደር፥ ከጎንደርም ተባሮ ሱዳን የገባው፥ በየጫካው የተጣለው፥ የኢሕአፓ ወታደር (ኢሕአሠ) ቀባሪ ያጣው፥ እንዲሁም ከመላው ኢትዮጵያ በየአገሩ የተሰደደው፥ የሞተውም፥ ያልሞተውም፥ አሁንም በመንፈሱ እውነትን እንደጨበጠ ነው ያለው። ብሩህ ተስፋ የሚታያቸው፥ ተነሱ - ተነሱ እያሉ የሚቀሰቅሱን፥ አሁንም የሚታገሉ ብዙሓን ናቸው። ወድቀን አልወደቅንም፤ ብዙ ጎበዛዝት አሉ ከጎናችን።

ለወደፊቷ ኢትዮጵያችን አንድ ነገር እናድርግ ብለው የተነሱ ብዙዎች ነበሩ። ለአንድ አገር ሲባል መስማማት ያቃታቸው ኃይላት ሁሉ፥ ተስማምቶ አብሮ መሥራት አለመቻል ዋናው ምክንያቱ፥ ከጥንትም በኃይል ሥልጣን የጨበጡት ወያኔዎች አሁንም ይህ ኃይላቸው እንዳይቀንስባቸው ሲሉ፥ በስምምነት አብሮ መሥራትን አልወደዱም። የነርሱ ፍላጎት ሕዝቦችን በወቅቱ በነበሩ ልዩነቶች (ፖለቲካ፥ ጎሳና ሃይማኖት....) እርስ በርስ እያጋጩ፥ እነርሱ በሥልጣን ለመቆየት ነበር።

ወያኔዎች በስውርና በግላጭ በኢትዮጵያችን ላይ የፈጸሙትን ሁሉ፥ ይህ መጽሐፍ በዝርዝር ለማቅረብ አይችልም።

የአገር መሪዎችን የፖለቲካ አቅጣጫ በመገምገም፥ ይህ የወያኔ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የማያዛልቅ መሆኑን የተረዱ ጥቂቶች ነበሩ። በእርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ "ሁሉም በስነ ስርአት ይፈጸምልን.." በማለት፥ ከቀን ወደቀን ሲፈጸም የተመለከተውን አድሎአዊነት ተቃወመ እንጂ፥ ከደርግ በኋላ ወያኔም ሆነ ማንም ሥልጣን ቢይዝ ግድ አልነበረውም።

እስቲ ምን ነበረ የቀድሞው (የመጀመሪያው) የወያኔ መንፈስ? በኃይለ ሥላሴ ዘመን፥ የቀዳማዊ ወያኔዎችን ጦርነት ያስታውሷል። ይህ ጦርነት ወያኔዎች በንጉሡ ላይ ያስነሱት የአመጽ ጦርነት ነበር። የአመጹም ዋናው ምክንያት ሕዝቡ ከሚችለው በላይ ቀረጥ ስለተጨመረበት ነበር።

የጥንቶቹ ወያኔዎች ከምሥራቅና ከደቡብ ትግራይ የተውጣጡ ጦረኞች ነበሩ። እነርሱ እንደዛሬዎቹ ቁልጭ ያለ የፖለቲካ መመሪያ ሳይኖራቸው፥ በንጉሡ ከተጫነባቸው የኢኮኖሚ ውጥረት ለመላቀቅ ነበር ታጥቀው የተነሱት።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር፥ የጣልያን መንግሥት በ1890 ኤርትራን፤ በ1936 ኢትዮጵያን፥ ሶማሊያንም ጨምሮ ሲቆጣጠር ነበር። በ1941 እንግሊዞች እና ኢትዮጵያኖች ጣሊያኖችን ከዛ አካባቢ አባረሯቸው። ከ1941 ጀምሮ እስከ 1952 ድረስ ኤርትራ በእንግሊዝ ጠባቂነት (protectorate) ሥር ነበረች። በዚህን ጊዜ ውስጥ (በ1943) ውስጥ ነበር የቀድሞው የወያኔ ጦርነት የተቀሰቀሰው።

የዛን ጊዜ የትግራይ ተቃዊሚ ኃይላት (ቀዳማዊ ወያኔዎች) በንጉሡ በኩል የተሰለፈውን የኢትዮጵያ ጦር ክፉኛ ስላጠቁ፥ የትግራይም መገንጠል የሚያሰጋ ስለነበረ፥ እንግሊዝም በዚህ ሳቢያ ትግራይንም ከኤርትራ ጋር በአንድነት በበላይ ጠባቂነት (protectorate) ሳቢያ አስተዳድራለሁ እንዳይል፥ ፈጣን እርምጃ መውሰድ አስፈለገ።

ስለዚህ፥ በንጉሡ ትእዛዝ፥ ቀዳማይ ወያኔዎች በአየር ኃይል ተደበደቡ። የወያኔዎች አመጽ ከሸፈ፤ በኢትዮጵያ ባንዲራ ሥር እራስን በራስ ለማስተዳደር የተነሳሱትም አልሆነላቸውም፤ ለመገንጠል የፈለጉም አልተሳካላቸውም። የወያኔዎች ትግል ተዳፍኖ ቆይቷል። በወያኔ ጦርነት ሳቢያ የትግራይ ሕዝቦች እንደ ጠላት በቦምብ መደብደባቸው እጅጉን ያሳዝናል፤ ይጸጽታልም።

ባላባቶች ከያለበት እንዳይነግሡ፥

እንዳትፈረካከስ አገራችን፥

እንዲጠናከር ማእከላዊው መንግሥታችን፥

በወያኔ አሳቦ እንግሊዝ እንዳይወስድብን ትግራይን፥

እንዳይጋራ ሥልጣን የንጉሡን፥

በቦንብ ተደበደቡ ወገኖቻችን፤

ለፍትህ፥ ለነፃነት የታገሉ ጀግኖቻችን።

በኋላ ተቀየረ እንጂ፥ የትግራይ ነፃ አውጪዎችም (የደሃራይ ወይም የዳግማዊ ወያኔዎች) መንፈስ ከጥንቱ የወያኔዎች መንፈስ ጋር የተያያዘ ነበር (ይሆን?)። ዳግማዊ ወያኔዎች በጥንቱ የወያኔ መንፈስ በመደራጀት፥ ይህን በ1943 የተፈጸመውን የሕዝቦች እልቂት ለቅስቀሳ ተጠቅመውበት ይሆናል።

ግን ከጥንትም በንጉሡ፥ በኋላም በደርጉ፥

በደል ቢደርስበት ሕዝቡ፥

እስቲ የትግራይ ገዳማት ይመስክሩ፥

ቂም በቀል ያውቃል ወይ አገሩ።

የዛሬዎቹ ወያኔዎች የትግራይን ሕዝብ አይወክሉም። የትግራይን ሕዝብ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ የሚገነጥለው ኃይል አይኖርም። ከዛሬዎቹ ወያኔዎች መካከል፥ ትግራይ ከእናት አገሯ ተገንጥላ፥ ሕዝቦቿም ለብቻቸው ነፃነታቸውን ያውጃሉ፤ አሊያም ከኤርትራ ጋር ይቀላቀሉ ብለው የሚያስቡ ይኖራሉ። ነገር ግን፥ ይህ ይሳካል ብለው ያመኑ ወያኔዎች፥ ስለራሳቸውና ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ የማያውቁ መሆናቸውን ታሪካዊ ክስተት ይመሰክርባቸዋል።

ሕዝቦችን በጎሳ[14] በመከፋፈል ላይ የተመሠረተ የአስተዳደር ፍልስፍና፥ የተለያዩ ጎሳዎችን (የሕብረተሰብ ክፍሎችን) በግድ አንድ በማድረግ ላይ ከተመሠረተ የአስተዳደር ፍልስፍና አይሻልም። በእርግጥ በእኩልነትና በዲሞክራሲያዊ ነፃነት ላይ ያልተመሠረተ አንድነት ምንም ትርጉም የለውም። መፍትሔው በቅድሚያ ዲሞክራሲያዊ ነፃነትና እኩልነት፥ ቀጥሎም አንድነት ነው።

እኩልነት ሲባል፥ በሃብት አለመበላለጥን ብቻ አይደለም የሚያመለክተው። አንዱ የሕብረተሰብ ክፍል በሌላው ላይ የበላይነት ሳያሳይ፥ በሃብት መበላለጥ ኖረም አልኖረም ሕዝቦች ሁሉ በሰብእናቸው ተከብረው፥ የሁሉም ኢትዮጵያዊነት በእኩልነት ሲታይ፥ ያ ነው እኩልነት። አንዱ የሕብረተሰብ ክፍል በሌላው ላይ የበላይነት እያሳየ፥ በአገራችን አንድነት አለ ቢባል ግን፥ ያ አንድነት የይስሙላ አንድነት ነው የሚሆነው እንጂ፥ በውስጡ ፍቅር እና ሰላምን ያካተተ ፍጹማዊ አንድነት ሊሆን አይችልም።

ዳግማዊ ወያኔዎች ደግ አሳቢዎች ቢሆኑ እንኳን፥ ነገሮችን በተገላቢጦሽ ነው የሚመለከቱት። የሚገርመው ነገር፥ ደጋግ ሃሳቦችን ከኢሕአፓ ይኮርጁና፥ በተገላቢጦሽ ያስቀምጡታል። ለምሳሌ ኢሕአፓ፥ "ሕዝቦች በቅድሚያ ለእኩልነትና ለዲሞክራሲያዊ ነፃነት መታገል አለባቸው.." ሲል የነበረው፥ በዚህ መሠረት የሚመጣ አንድነት ፍጹማዊ መሆኑን ስለሚገነዘብ ነው።

የዳግማዊ ወያኔዎች አስተዳደር ግን እኩልነትና ዲሞክራሲያዊ ነፃነትን ሊያመጣ ስለማይችል፥ እነርሱም ይህንን ስለማይፈልጉት፥ "እያንዳንዱ ጎሳ

---

[14] ሕብረተሰብ፥ ብሔረሰብ፥ ቤተሰብ ይባል እንጂ ዘር አይባልም፤ የሁላችንም ዘር የሚመነጨው ከሰው ዘር ነውና። ይህንንም የሰው ዘር መከፋፈል ካስፈለገ፥ የጥቁር ዘር፥ የነጭ ዘር፥ የቢጫ ዘር ብሎ መከፋፈል ይቀላል።

(እኩልነትና ዲሞክራሲያዊ ነፃነት ባይኖረውም) ለየግሉ ቢደራጅ፥ ጎሳዊ አንድነት ይኖረዋል..” ይላሉ። እና በዚህ ካለአግባቡ “ዘር” የሚል ስም የተሰጠው “የጎሳ ፍልስፍና” መሰረት፥ ኢትዮጵያችን ምንም ሳትጠቀም፥ የገዢዎችን ፍላጎት ማሟያ ብቻ ሆና ቀርታለች። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብዙ ቆይተው፥ በመጎዳታቸውና እየተጎዱም ነው “ዘር” የሚሉት የጎሳ ፖለቲካ የማያዋጣቸው መሆኑን - ኢትዮጵያችንን እንደሚከፋፍላት፥ ጉዳት ላይም እንደሚጥላቸው የተገነዘቡት።

ደርግ የወደቀው በዳግማዊ ወያኔዎች ትግል ብቻ እንዳልሆነ እየታወቀ፥ እንዲህ የትግራይ ዜጎች (ከጥቂት የሌሎች ብሔረሰቦች ጋር) ብቻቸውን አገሪቷን ሲገዙ ማየት ያልፈለጉ  እጅግ አዘኑ።

የኢሕአፓና የሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች፥ በወያኔዎች ሲታሰሩ፥ ሲገደሉ፥...ይህን እና የመሳሰለውን የታሪክ መጥፎ ጎን የሚመዘግብ የሕዝቦች አይምሮ አልተኛም። ስለዚህ የኢትዮጵያችን ነገር፥ ከሽማግሌዎች አይምሮ የማይጠፋ፥ ወጣቶችን የሚቆጠቁጣቸው፥ ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችንም የማይረሱት ጉዳይ ሆነ።

ተቃዋሚ (ተቀናቃኝ) የፖለቲካ ድርጅቶች፥ ከሕዝቦች ሁሉ ጋር ተባብረው፥ በዲሞክራሲ ተወያይተው፥ አገራቸውን አስቀድመው፥ በርህራሄ፦ ለሰው፥ ለእንስሳቱ፥ ለእጽዋቱ፥ ለአፈሩ፥ ለሳሩ፥ ለቅጠሉ፥ በአጠቃላይ ለሰብአዊነትና ለተፈጥሮ አስበው፥ እንዲህ በተቀደሰ መንፈሳዊ ፖለቲካዊ አመለካከታቸው ለእርቅ፥ ለሰላም፥ ለሕብረትና ለአንድነት ከተነሱ፥ እነርሱን የሚቋቋማቸው ኃይል ቢመጣ፥ “የሰማይ ኃይላት” ዝም ብለው አያዩም።

በአሁን ጊዜ በኢትዮጵያ ሥልጣን ላይ ያሉ ሁሉ ከሕዝቡ ጎን ሆነው ሕዝቡ የሚፈልገውን ባያደርጉ፥ የነርሱ ታሪክ የጥፋት መልእክተኞች ሆነው፥ በሰይጣናዊ ልባምነት፥ ለሕዝቦች እልቂት ምክንያት ከሆኑት የደርግ ባለ ሥልጣኖችና ከመሪያቸው ጎን ይደመራል።

እውነትን በማጣመም የሚገኝ ትርፍ ጊዜያዊ ነው፤ መጨረሺያው ኪሳራ ነው። ሕዝቡ በተጣመመ እውነት እየተመራ ብዙ መቆየት አይችልም። ከእንግዲህ የትግራይ ሕዝቦችን መንፈስ ከተቀሩት የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚለይ ኃይል አይኖርም። ጥንትም መንፈሳዊነት የገነነባት አገር ውስጥ ሰይጣናዊነት ሥር አይሰድም።

ክርስቲያኑ የሱዳን ሕዝብ ሳይሰልም በፊት፥ ከጥንት ኢትዮጵያ የሚለው ስም በምሥራቅ አፍሪቃ የሚኖሩትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነበር። አንድ የነበረው ታላቅ ሕዝብ  ተከፋፈለና ኢትዮጵያ ትንሽ አገር ሆነች። ምናልባት አሁንም ይህቿን ትንሽ አገር እንደገና ትንሽ ለማድረግ፥ ከተቻለም ለማጥፋት የሚፈልጉ ኃይላት ይኖሩ

ይሆናል። ግን፥ ጥሩ መንግሥት እንዳይመጣ የታገሉ የእርኩስ መንፈሶች ሴራ በዚህ አይቀጥልም።

በአራቱም ማዕዘን አለምን ዞሯታል፤
እየደጋገመ ሕዝቦችን ቀጥቅጧል፤
ኢትዮጵያን ለመምታት እቅድ ተዘርግቷል፤
የሰይጣን ክፉ አይን አክሱምን አይቷታል፤
ረዳት እንዲሆኑት ብዙ ሰው መልምሏል፤
ግን የእሳት ግርግዳ አቃጥሎ ገርፎታል።
ደጉ ብሔረሰብ አስተውሏል ገብቶታል፤
አምሃራይ ከትግራይ የማይለይ ሆኗል፤
የኦሮማይ ፍቅር ኢትዮጵያን አዳርሷል።

**<u>ኤርትራችን/ኢትዮጵያችን</u>**

ከውስብስቡ ፖለቲካ ባሻገር፥ ኤርትራውያን እና ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በአንድነት እየተሰባሰቡ ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ/ኤርትራ እየተወያዩ ናቸው። መልካሙ የነርሱ ሃሳብ መሬት ወድቆ አይቀርም፤ ይበቅላል፤ ያለመልማል፤ ፍሬም ያፈራል። የኤርትራውያንን ኢትዮጵያዊነት የሚሽር ኃይል ከቶ አይኖርም። ምድራዊ ጥላቻ በመንፈሳዊ ፍቅር ይደመሰሳል።

አንዳንድ ጥራዝ ነጠቅ ፖለቲከኞች ኤርትራዊነትን ከኢትዮጵያዊነት ለይተው የሚያዩት በጥላቻ ወይንም በውስጡ መንፈሳዊነት ከሌለበት ደረቅ ፖለቲካ በመነሳት ነው። በዚህች ለሁላችንም በምትበቃ አገር ተስማምተን እንዳንኖር የግለሰቦች የሥልጣን ጥም ነው ያጣላን፤ የአገር ፍቅር ሳይሆን።

ካለ ኢትዮጵያ ኤርትራ ብቻዋን መሆን ይከብዳታል። ኢትዮጵያም ካለ ኤርትራ ብቸኝነት ይሰማታል።

ኤርትራም እንደ ኢትዮጵያ ስልል ባለ ድምጽ ለተሻለ መንግሥት የምትጮህ አገር ሆናለች። መሰናክሎች ከታለፉ በኋላ፥ ለሁላችንም የዲሞክራሲ፥ የአንድነትና የሰላም ጊዜ በቅርብ መምጣቱ አይቀርም፤ እግዚአብሔር ለርሱ የሆኑትን ሕዝቦች በምድር ላይ በሰላም ለመኖር እንዲችሉ ያደርጋቸዋልና።

ሕዝቦች ታግለው የሚፈልጉትን ቢያገኙ የሚጠላ የለም። ግን ወንድም የገዛ ወንድሙን እንዲጠላ የሚያደርግ፥ በውሸት ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ በጣም

ያሳዝናል፤ ውሸት ከነገሠበት አለም ውስጥ መኖራችንም ያሳዝናል። ሰው ግን እውነትን በራሱ ፈልጎ በማግኘት ፋንታ፥ ሌሎች የፖለቲካ አቀንቃኞች የሚሉትን ብቻ እየሰማ በጥላቻ አለም ውስጥ ይዘፈቃል። ብዙ ሰው ከፍርኃት የተነሳ የልቡን ከመናገር ይቆጠባል።

የአንድ አገር ከሁለት ወይም ከዚያም በላይ መሰንጠቅ አይደለም የሚያስፈራው፤ በአንድ ባህልና ልምድ፥ በአንድ ሃይማኖታዊና ስነ ልቦናዊ አመለካከት ያደጉ ወንድማማቾች መካከል ገብቶ ሰውን ከሰው የሚያለያይ፥ በውሸት ላይ የተገነባ እኩይ የጥላቻ ፖለቲካ ነው እጅጉን የሚያስፈራው።

ከእርስ በርስ ግድያ በኋላ ለሁላችንም እርሱ እግዚአብሔር መልካም መንግሥት ያመጣልናል።

ኤርትራችን ከኢትዮጵያችን የማትለይ ናት። ለአንድነት በታገሉ ኤርትራውያን አርበኞች ብርታት እና በኢትዮጵያም ከፍተኛ የመዋሃድ ፍላጎት ምክንያት፥ ኤርትራ በ1962-11-14 ከኢትዮጵያ ጋር ተዋሃደች (አንድ ሆነች)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አንድነትን ያልፈለጉ ኤርትራውያን፥ ለትጥቅ ትግል እራሳቸውን አዘጋጁ። ከብዙ ዓመታት ጦርነት በኋላ፥ በ1993-05-27 ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ራሷን የቻለች አገር ሆነችና ነፃነቷን አወጀች።

ኢትዮጵያ ከደርግ አገዛዝ ስትላቀቅ፥ ኤርትራም ነፃነቷን ስታውጅ፥ በሁለቱም አገሮች ጦርነት አብቅቶ ሰላም የሰፈነ ይመስል ነበር። እየቆየ ሲሄድ፥ በተለይም ከባድማ ጦርነት በኋላ፥ የሚዋደዱ ሕዝቦችን የሚያጣሉ የአገር መሪዎች፥ እነርሱ ከአገራቸው ፍቅር ይልቅ የገዛ ሥልጣናቸውን ለማቆየት ሲታገሉ ሰላም ደፈረሰ።

ኤርትራ ነፃነቷን ስታገኝ በደስታ ብዛት ያለቀሱ እንደ ደስታቸው አልሆነላቸውም። መሪያቸው (በማወቅም ሆነ ባለማወቅ) የኤርትራን ነፃነት ለራሱ እና ለደጋፊዎቹ መደሰቺያ ያደረገው መሰለ (እርሱን የሚወዱት/የሚጠሉትም) ነበሩ/አሉ።

የሰው ልጅ የራሱን ሃሳብ ስላቀረበ መታሰርና መገደል የለበትም ነበር። የኤርትራ ሕዝብ የተጠማውን ሰብአዊ መብቱን (የተመኘውን ዲሞክራሲ) አለማግኘቱ ለብዙ ዓመታት በትግል ያሳለፈውን ጊዜ ካለ በቂ ምክንያት እንደሆነ አደረገው (አስመሰለው)።

ምናልባት (እኛ ከምናውቃቸው ኤርትራውያን ጓደኞቻችን በስተቀር) በዚህ ጉዳይ ላይ ግድ የሌላቸው ብዙዎች ይሆናሉ፤ ሆኖም አብዛኛው ኤርትራዊ ለብዙ ዓመታት ሲያልመው የነበረውን ፈጣን እድገት ሳያገኝ መቅረቱ ቅሬታ ውስጥ ሳይከተው አልቀረም።

እኛም ዲሞክራሲን አስቀድመን፥
ተከራክርን ነበር ለሙብታቸው፥
ከሁሉም ፍቅር ይበልጣል ብለን፥
ቆመን ነበር ከጎናቸው።
እነርሱም ጥልቅ ጉድጓድ ምሰው፥
የባንዲራቸውን ምሶሶ በመሃል ኢትዮጵያ ውስጥ ተክለው፥
ነፋስ የነፃነታቸውን ምልክት (ባንዲራ) ሲያውለበልበው፥
ደስ ብሎን ነበር ስለደስታቸው።

ነፃነት ሲባል ስሙ አንድ፥
ግልጋሎቱም የጋራ የመሰላቸው፥
እጅግ አዝነዋል ከልባቸው፤
"ኢትዮጵያ ስትጠላ፥
ይቆሸሻል ባንዲራው፥
የኤርትራም ነፃነት ትርጉም ያጣል" ብለው።

የታገሉት - የታሰሩት፥
ብዙሓን ታጋዮችም ለፍልፈው፥
የሞቱትም በድምጽ አልባ መንፈሶቻቸው፥
በገዛ አገራቸው ስቃይና ጭቆና በዝቶባቸው፥
እነርሱም፡-
"ከእንግዲህ በቃ!.....ይአክል! ይአክል!...." ሲሉ ሰማናቸው።

የተቻላቸው፥
የሰላምና የፍቅር መርሆ ይዘው፥
አገር ለቀው ወጡ፥
እንደገና ስደትን መርጠው፥
"ምዕብዳን ምዕብዳኑስ አውሮፓ ይሃሸይ" ብለው።

እንደወጡስ ከዛ አይቀሩም፥
ይመለሳሉ ካገራቸው፤
ለአንድነት ይቆማሉ ጎሳና ሃይማኖት ሳይለያያቸው።

ልጆቻችን ከልጆቻቸው፥
አንድላይ እንቀድሳለን፥
ይዋሃዳል እጣናችን ከእጣናቸው፥
አንድ ላይ እንሰግዳለን፥
በመስጊዳችን በመስጊዳቸው፤
ይህ ብቻ ነውና መፍትሔው፥
በሥጋውም በመንፈሱም ለሚኖር ሰው።

**እውነት ለምንጊዜም**

ሰው ለምን እውነትን ይፈራል? እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያችን እውነትን የማይፈራ ፖለቲካ አላገኘችም፤ ኤርትራችንም እውነትን የማይፈራ ፖለቲካ አላገኘችም።

ሰው ለምን እውነትን ይፈራል? ይገርማል! ፖለቲካ እውነትን መደበቂያ ሲሆን። በውስጡ ውሸትን የደበቀ ፖለቲካ አሸናፊነቱ ለጊዜው ብቻ'ኮ ነው። ከብዙ እውነቶች መካከል ትንሽ እውነት በትደበቅ፥ ያቺ ትንሽ ውሸት ብዙውን እውነት ልታደቀው ትችላለች።

ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ ወሬዎችን የሚሰሙ ሰዎች - "የትኛው ነው እውነት?" ብለው ይጠይቃሉ። ግን'ኮ! ግድየለም፤ ማንኛውም ነገር ለማንም ሰው እውነት ቢሆንለት፥ ይሁንለት። የኢትዮጵያ ሕዝብ (የአለም ሕዝብም ቢሆን) እግዚአብሔርን አምላኩ ማድረግ እስኪችል ድረስ እውነትን አያገኛትም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እውነትን እስኪያገኝ ድረስ እጅጉን ይቸገራል፤ ይሰቃያል፤ ብዙ መከራም ይደርስበታል፤ ይኸውም እውነትን በሚፈሩ ፖለቲከኞች እየተወናበደ ነው። እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያችን የመንግሥት ሥልጣን ለመጨበጥ የሚጣደፉ ሁሉ በእውነት ለራሳቸው ሥልጣንን በመፈለግ እንጂ፥ በእውነት ለእውነት በመቆም አይደለም።

የኤርትራ ፖለቲከኞች ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ስለፈለጉ ብቻ ለአፍ የሚቀፍ ውሸት ተናገሩ - እጅግ የሚቀፍ ስድብን ተሳደቡ፤ ምንም ሳይሳደቡም እውነተኛ ትግልን ታግለው ኤርትራ ነጻ መውጣቷ አይቀሬ ነበር። ግን ከእውነቶቻቸው ጋር ውሸቶችንም ስለቀላቀሉ፤ ስለተሳደቡ ባገኙት ድል እምብዛም ደስ ያላላቸው ወጣቶች ብዙዎች ሆኑ።

አሁንም አሌ የማይባል እውነት ይህ ነው፡- ኢትዮጵያውያን ሁሉም ወንድሞች ናቸው እንጂ ጠላት አይደሉም። ለዚህም ምስክሮች የምንሆን፥ ከኤርትራውያን ወንድሞቻችን ጎን በመሆን - እስከ መገንጠል መገንጠልንም ጨምሮ ለዲሞክራሲያዊ መብታቸው እውቅና የሰጠን ኢሕአፓዎች - የዘር ግንዳችን ቢመዘዝ በኢትዮጵያ የሚገኝ ብሄር ሁሉ - እኛ ነን።

አሌ የማይባለው የኢሕአፓ ውሸት እና ደካማነት ደግሞ ይህ ነው፡- የአንጃዎችን እውነት (የመኢሶኖችንም ቢሆን) ከራሱ ጋር አዋህዶና አቅፎ - ግንባር ፈጥሮ - በአንድ የተዋሃደ እውነት ለመታገል አለመቻሉ።

ስለ ዲሞክራሲ መብት የታገሉ ኢሕአፓዎች ሁሉም የፖለቲካ ብስለት ኖሯቸው፥ የታሪክ አዋቂዎች፥ ፈላስፎች፥ ተመራማሪዎች ሆነው አይደለም። ከዚህም ይምጣ ከዚያ፥ እውነትን ሲሹ አንድ እውነት የሚመስል ነገር አገኙና ነፍሳቸውን ከዚያ አሳረፉት። እውነትን የማይፈራ ሞትንም አይፈራም። ከሞት የተረፈ ሁሉ እንዲሁ ውስጣዊ እውነቱ እየቆረቆረው እንዲሁ ይለፈልፋል፤ እንዲሁም ይጽፋል።

አሁንም ቢሆን በኢትዮጵያችን ውስጥ የፖለቲካ ኃይላት ሁሉ የሚታገሉት በእውነት ለአንድ ለኢትዮጵያችን ቢሆን ኖሮ፥ የሁሉም ፖለቲካ አንድ ብቻ ይሆን ነበር። ሰው ለምን እውነትን ይፈራል? ይገርማል፤ እውነትን ከፖለቲካ የሚያስበልጡ ጥቂቶች ናቸው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ነጥቦች እንመልከት፡-

ዳግማዊ ወያኔ የደርግን መንግሥት ገርስሶ ሥልጣን ሲይዝ፥ "ይህ የወያኔ መንግሥት ለኢትዮጵያችን ይጠቅማል ወይንስ አይጠቅምም?" ብለው ከመጠየቃቸው ይልቅ፥ አስቀድመው የወያኔን መንግሥት ገና ከጥንስሱ ሲደግፉ የነበሩ የደርግን መንግሥት ክፉኛ የሚጠሉት ነበሩ። ገና ከጥንስሱ ሲኮንኑ የነበሩ ደግሞ የደርግ ደጋፊዎች የነበሩ ሲሆኑ፥ በትግራይ ሕዝቦች ላይ ያነጣጠረ የትግራይ ብሄር ጥላቻ ያደረባቸውም "እንዴት ትግሬ ይግዛኝ..." በማለት በትምክህተኝነት ስሜት ተነሳስተው እንጂ፥ በቅድሚያ ለኢትዮጵያችን እና ለሕዝቦቿ በማሰብ አልነበረም።

እንግዲህ በተጠቀሱት ምክንያቶች ብቻ መረጃዎችን ለሕዝቦች ያቀብሉ ዘንድ የተመደቡ ጋዜጠኞች - ሪፖርተሮች (ሌሎችም ፖለቲከኞች እና ወሬ አቀባባዮች) ልክ እንደየስሜቶቻቸው እውነትን ያጋንናሉ - ያጣምማሉ - ያዛባሉ - ደግሞም ይዋሻሉ (ቅልጥጥ ያለ ውሸት)፥ ሰሚውም ይወናበዳል።

አሁንም ቢሆን የወያኔ መንግሥት ለኢትዮጵያችን ያበረከታቸው አያሌ ጥሩ ጥሩ ጥሩ ነገሮች እንዳሉ እያየ የሚክዱ ብዙዎች ናቸው። አሁንም ቢሆን የወያኔ መንግሥት ለኢትዮጵያችን ያበረከታቸው አያሌ መጥፎ መጥፎ ነገሮች እንዳሉ እያዩ የሚክዱ ብዙዎች ናቸው።

አሁንም ቢሆን እውነትን እያጣመሙ የሚለፈልፉ (የሚጽፉም) ብዙዎች ናቸው። ከነኚህ መካከል ጥቂቶቹ ለፖለቲካ ፍጆታ ብለው ነው፤ ግን እነርሱ የሚመለከቱት የሚያገኙትን ጊዜያዊ የፖለቲካ ድል እንጂ ተከታዩን የኢትዮጵያችንን መጻኢ አይደለም።

መረጃዎችን ለሕዝቦች ያቀብሉ ዘንድ የተመደቡ ጋዜጠኞች - ሪፖርተሮች (ሌሎችም ፖለቲከኞች እና ወሬ አቀባባዮች) እውነትን ብቻ የሚያስተጋቡ ቢሆኑ ኖሮ፥ ሕዝቦች በእውነት ብዛት አስተሳሰባቸው በአንድ አቅጣጫ ይነጽር ነበር። የሕዝቦችን አስተሳሰብ በአንድ አቅጣጫ ሲነጽር፥ ለአንድነትና አብሮ ለመሥራት ይቀላል፤ እድገትም የሚፋጠነው የዛን ጊዜ ነው።

ጥሩ መንግሥት የሕዝቦችን ጩኸት ይሰማል፤ አብሪተኛና አምባገነን መንግሥት ግን የራሱን መመሪያ ብቻ ነው ይዞ የሚጓዝ። እውነት ከብዙሃኑ የምትደበቀው እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ብቻ ስለሆነ፥ መንግሥት ሕዝብን፥ ሕዝብም መንግሥትን የሚሰማበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም (በግድም ሆነ በውድ)።

የቀድሞዎቹ ኢሐፓዎች "ጊዜያዊ መንግሥት" እያሉ ሲጮሁ የነበረው ካለ ምክንያት አልነበረም። የ"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" አስፈላጊነት እንዳይገባቸው አይምሮአቸውን የዘጉ ፖለቲከኞች በእውነት አስፈላጊነቱ ሳይገባቸው ቀርቶ ሳይሆን፥ ሕዝቦችን የሚወክል ኃይል ባቋራጭ መጥቶ እኛ ልንጨብጠው ያቀድነውን ሥልጣን ይቀማናል ብለው ነው (ይሆናል)። ወይንም አንዳንድ ጊዜ ደረቅ እውነት የማያዋጣ ይሆንና፥ በፖለቲካ የበሰሉ ፈላስፎች፥ "ይህንን እውነት የምትለውን ከጎን አስቀምጥና፥ አሁን ለኢትዮጵያችን የሚስማማት ምንድነው በሚል ላይ ብቻ እናተኩር..." ይላሉ። ግን በቅንነትና በእውነት ደረቅ እውነት ሊለሰልስ አይችልም? ወይንስ ደረቅ እውነት ድርቅ ብሎ ቢቆይ ሕዝቡ ያንን ደረቅ እውነት መቀበል ያቅተዋል?

ሁሉንም ሕዝብ አንደ ብጤው - እንደየራሱ እውነት የሚመራ መሪ (ግለሰብ/ፓርቲ) ነው የታጣው። "እናንት ሁላችሁም እውነት ይኖራችኋል፤ ግን ባሁኑ ጊዜ ምርር ክርር ያለውን እውነት እናስቀድም..." እያለ - እያግባባ፥ የሁሉንም እውነት እያቀፈ በማዕከላዊ ኃይል የሚመራ መሪ (ግለሰብ/ፓርቲ) ነው የታጣው።

መሪ (ግለሰብ/ፓርቲ) ሲባል በተደጋጋሚ የምናየው የራሱን እውነት ከሕዝቦች እውነት የሚያስበልጠውን - ለራሱ ሥልጣን ብቻ የሚተጋውን ነው። ያማ ባይሆን ኖሮ የመሪ (ግለሰብ/ፓርቲ) እውነት እና የሕዝቦች እውነት ባንድላይ ይነጽርና ይሰምር ነበር።

ሰው ለምን እውነትን ይፈራል? በቀድሞው ኢሕአፓም ሆነ አሁን ሕዝቡን ከሚወክል (ከማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል - ወይንም ባሁኑ ጊዜ የፖለቲካ

ፓርቲዎች ሁሉ የሚሳተፉበት) የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግሥት - የሽግግር መንግሥት ያስፈልጋል ቢባል፥ ይህንን ደረቅ እውነት በሚከተሉት አቅጣጫዎች መመልከት ይቻላል፡-

1) ሠፊው ሕዝብ የሚፈልገውን ዘላቂ መንግሥት ራሱ ሊመሠርት የሚችለው ሕዝቡ በእውነተኛ ዲሞክራሲያዊ መድረክ ሲሳተፍና፥ ማንም ሰው ካለ የብሄር፥ የሃይማኖትና የፖለቲካ ልዩነት በእኩል ተሳትፎ ምርጫ ሲያካሄድ ስለሆነ፤
2) ሠፊው ሕዝብ የሚፈልገውን ዘላቂ መንግሥት ራሱ ሊመሠርት የሚችለው፥ በአንድ ፓርቲ የበላይነት ስላልሆነ፤
3) የሽግግር መንግሥት በቅድሚያ ሲቋቋም፥ ሠፊው ሕዝብ የሚፈልገውን ዘላቂ መንግሥት ራሱ ይመሠርት ዘንድ፥ ራሱን ለሥልጣን እንዲያዘጋጅ ጊዜ ሊያገኝ ስለሚችል።

ከላይ የተጠቀሱትን፥ በቲዎሪ ደረጃም ቢሆን፥ እንደ ደረቅ እውነቶች በመውሰድ፥ በሽግግር መንግሥት ልዩነቶች ባንድ ላይ ስለሚጠቃለሉ፥ ምናልባት ብዙ ውዝግብ አይኖርም፥ የሕግ የበላይነትንም ለማረጋገጥ ይቀላል ተብሎ ሊታሰብ ይችላል።

ሠፊውን ሕዝብ የማይወክል መንግሥት የሰፊውን የሕዝብ ስሜትና ፍላጎት ስለማይከተል፥ በጊዜአዊ የሽግግር መንግሥት ያሉትን ፓርቲዎች ሁሉ የሚያቅፍ፥ የሕዝቦችን ስሜት (ፍላጎት) የሚከተል (የሚሰማ)፥ ጥሩ መሪ (ግለሰብ/ፓርቲ) ቢኖር፥ የዛ የመሪ (ግለሰብ/ፓርቲ) እውነት እና የሕዝቦች እውነት ባንድነት እንዲነጽር ማድረግ ይቀላል ተብሎም ሊታሰብ ይችላል።

ለአንድ አገር ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ምርጫ ማድረግ ወሳኝ ነው። ነገር ግን ምርጫ መደረጉ ብቻ ጥሩ ውጤት ለማምጣቱ ምንም ዋስትና አይኖርም ሙሉ ዲሞክራሲ ሳይሰፍን፤ ለዚህም ይሆናል ከሁሉ በፊት የሽግግር መንግሥትን እንመሥርት የሚባለው። ሆኖም፥ ስግብግብ ፖለቲከኞች "ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት" እያሉ የሚጮሁት ለራሳቸው ሥልጣን መቆናጠጪያ ሊያደርጉትና፥ አንዴ በጊዜያዊ መንግሥት ስም ሥልጣን ከያዙ ወዲያ በዛው ሙጭጭ ብለው ለመቅረት ይሆናል (ማን ያውቃል?)።

ብዙ ደረቅ እውነቶች ይኖራሉ። በማለስለስም ሆነ የበለጠ በማድረቅ፥ በእውነት ላይ ምንም ውሸት ሳይጨምርበት ሕዝቦችን በቀናው መንገድ የሚመራ መሪ (ግለሰብ ወይንም/እና ፓርቲ) ነው የታጣው።

የአገር ተቆርቋሪዎችና ፖለቲከኞች ለፖተሊካ ሥልጣን ብቻ ሳይሆን፥ እውነቱን እውነት፥ ውሸቱንም ውሸት እያሉ ለአገር የሚጠቅመውን ብቻ ማሰብን

ቢለማመዱ፥ ጠቅላላ ሕዝቡን  በአንድ አገር (በአንድ እውነት) ውስጥ ማስተባበር ያን ያህል ከባድ አይሆንም ነበር።

የሚታሰበው ሁሉ መፍትሄ ሊሆን ይችላል - ሁሉንም እንደ ልኩ እየወሰዱ፥ አብሮ በመወያየት ወደ ፊት መራመድ ነው ያስቸገረው።

በኢትዮጵያችን ውስጥ እውነት ስትነገር ብቻ ነው ዝም ብላ የምትነገር? ሊይዟት ሊጨብጧት ሲሉ ሮጣ ታመልጣለች? አይደለም። በእውነቶች መካከል የውሸት ደንቃራ እየገባና ሰዉን ለሁለት እየከፈለው፥ ሕዝቡም በዚህ ምክንያት ቀላሉን እና አስፈላጊውን ነገር ከመተግበር ችላ ስለሚል ነው። ለምሳሌ፡ ኢትዮጵያ አገራችንን ለማሳደግ (ለማበልጸግ) በቅድሚያ ሕዝቦች በሰላም፥ በአንድነት፥ በሕብረት እና በፍቅር አብረው መሥራት ይኖርባቸዋል።  ይህንን ኃይለ ቃል የሚያፈርስ ውሸት እየተሰበከ ነው፥ ወደፊት መራመድ ያስቸገረው።

ይህቺን መንፈሳዊነት የሚያመዝንባትን አገራችንን (ኢትዮጵያን/ኤርትራን) ወደፊት እንድትራመድ ማድረግ የሚቻለው፥ በቅንነት፥ በመንፈሳዊነት፥ በእውነት ሲሆን ብቻ መሆኑን - አገራችንን ለማሳደግ የሚወሰደውም ጎዳና ሰላማዊ ሊሆን የሚችለው፥ ቅድሚያ ለሕብረትና ለአንድነት ሲሰጥ፥ ሕዝቡም የሚመራውን አካል የሚሰማ - የሚከተል ሲሆን መሆኑን ልብ ይሏል።

**<u>ለውጥና እንቅስቃሴዎች</u>**

ኢትዮጵያችን በአንድነቷ ጸንታ እንድትቆይ የሚያደርጋት መንፈሳዊ ጸጋ አላት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠብ መንጃ ይዞ ባይዋጋ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን፥ ወደ መስጊድም እየሄደ መጸለዩን ያውቅበታል።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይወዳታል። ለዚህ ነበር የወያኔ መንግሥት መምጣት ግዴታ የነበረ። ግን ሕዝቡ ሁሉ በቃችሁ (ይአከለኩም) ሲል፥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ፍላጎት ተለይቶ ለወያኔዎች የማይገባቸውን ጊዜ አይሰጥም። እስካሁን እና ከአሁን በኋላ ጊዜው ለብሔረሰቦች ሁሉ እኩል ለሚያስብ መንግሥት ተመቻችቷል።

የረከሰው የሰው ልጅ ጠባይ በገሃድ እየታየ፥ ውሸታምና ከዳተኛ በዝቶ፥ ሰው እርስ በርሱ ሲባላ፥ የማይጠግበውን የሥጋ ከርሱን ሲሞላ፥ ሞራላዊነቱን (መንፈሳዊነቱን) ረስቶ፥ እንስሳዊነቱን ሲያጎላ - ውሸታምነት፥ ራስን ወዳድነት፥ የሥልጣን ጥም፥ ክፋት፥ ውዳሴ ከንቱ፥ ስግብግብነት፥ ትምክህተኛነት፥ እብሪተኛነት፥ አከራሪነትና ጀብደኛነት..፥ ይህ ሁሉ ሕዝቦችን ለመምራት የማይሆን መጥፎ ጠባይ

ከሁሉ ቦታ እየታየ፤ የሰው ልጅ ይህን ሁሉ አስከፊ ጠባያት ተሸክሞ፥ ሠፊውን ሕዝብ በቅንነት የሚያስተዳድር መንግሥት እንዴትና ከወዴት ይገኛል?

ዘረኛነት[15] እና አክራሪነት ሳይጠፉ እንዴት ነው ተደማምጦና በጥሞና ተወያይቶ አብሮ መሥራት የሚቻል?

እንግዲህ ማስተዋያ አይምሮ ያለው ያስተውል። መጠላትን የማይወድ፥ መወደድን ይወቅበት። ከምድራዊነታችን ባሻገር በሦስተኛው መጽሐፍ ላይ እንደተመለከተው፥ የዘር መደብ የሚያመለክተው፥ የተለያዩ የፍጥረታት ዝርያዎችን ነው። ለምሳሌ፡ የሰው ዘር፥ የዝንጀሮ ዘር፥ የአሳ ዘር፥ እና ሌሎችም።

የሰውን ዘርም ከፋፍለን እንመልከተው ከተባለ፥ በእርግጥ ዋነኞቹ ክፍፍሎች (በቆዳ ቀለም፥ በተክለ ሰውነት እና በገጽታ) በሦስት ዋና ዋና የሰው አይነቶች ይከፈላል። ይኸውም ነጭ የሰው ዘር(race)፥ ጥቁር የሰው ዘር(race)፥ ቢጫ የሰው ዘር(race)። ሦስቱም የሰው ዘር ስለሆነ አንድ የሰው ዘር (human race) ይባላል።

እንግዲህ በዚህ አንጻር ሲታይ፥ ኦሮማይ ብሎ ዘር የለም፤ አምሃራይ ብሎ ዘር የለም፤ ትግራይ ብሎ ዘር የለም፤ ጉራጌ ብሎ ዘር የለም፤ አፋር ብሎ ዘር የለም፤ ወላይታ ብሎ ዘር የለም፤ ኩናማ ብሎ ዘር የለም፤ ..ወ.ዘ.ተ..። ዛሬ በኢትዮጵያችን ያለነው ሕዝቦች የምንዋደድ፥ በተለያዩ ስሞች የምንጠራ ቤተሰቦች ነን፡- የኦሮማይ ቤተሰብ፥ የትግራይ ቤተሰብ፥ የአምሃራይ ቤተሰብ፥ የጉራጌ ቤተሰብ፥ የአፋር ቤተሰብ፥ የወላይታ ቤተሰብ፥ የኩናማ ቤተሰብ..ወ.ዘ.ተ....።

በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሕዝቦች፥ በአካል (በበራሂ)፥ በቋንቋ፥ እና በባህል ይቀራረባሉ፤ እንዲሁም ግለሰቦች ከአንድ ቤተሰብ እየወጡ ወደሌላው ይገቡና በቋንቋና በባህል ልዩነቶች ሳይበገሩ፥ ከመዋደድና ከመፋቀር የተነሳ፥ ልክ እንደ አንድ ቤተሰብ ይሆናሉ። በዚህን ጊዜ ቤተሰብ የሚለውንም መለዮ ለገዛ ቤተሰባቸው ይተውና፥ ቤተሰቦችን በሚያጠቃልል በአንድ መልዮ ይጠቀማሉ (ኢትዮጵያዊነት)።

መበተንና መሰብሰብ ጠፈራዊ የተፈጥሮ ሕግ ስለሆነ፥ ለወደፊት የኢትዮጵያ ቤተሰቦች እየተቀራረቡ ይመጣሉ፥ ብሎም በአንድ ዜጋ ይጠቃለላሉ - ሁሉም ለአንድነት። ሕዝቡ ለወደፊት አንድ ቅዱስ ሕዝብ ይሆን ዘንድ በጠባዩ፥ በአመለካከቱና በእምነቱ ጠንከር - ቀና ማለትን ካወቀበት፥ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያደርገዋል።

---

15 ዘረኛነት - በሰዎች መካከል የሚኖሩ ልዩነቶችን ሁሉ በመጥፎ በማየት፥ ራስን ከፍ ሌላውን ዝቅ በማድረግ ላይ የተመሠረተ አድሎአዊ አመለካከት ነው። ብሔረሰቦችን እንደ ዘር መቁጠር ደግሞ ኢሳይንሳዊ ነው።

በኢትዮጵያችን የተጨቆነ ሕዝብ ሁሉ አሁን ነቃ ብሏል። የእግዚአብሔር እርዳታ ከሰማይ ሲወርድ እያየን፥ በምድራዊ ስግብግብነት ወደ እርስ በርስ ጦርነት የማምራት ዝንባሌ ቢያድርብን፥ የዛን ጊዜ ከምህረቱ ቁጣው ይቀድማል።

የአገር መሪዎች ለሆዳቸው ብቻ ብለው የማይኖሩ ቢሆን፥ የሕዝቡን ኑሮ በሁለት አቅጣጫ (በሥጋውና በመንፈሱ) ተመልክተው የሚፈልገውን ያደርጉለት ነበር። ግን፥ በሰው ልቦና ውስጥ የተቀመጠ ከፋት፡- ለሆዴ ብቻ ማለት፥ ከመንፈሳዊነትም መራቅ፥ በቅንነት ለጋራ ደህንነት በማሰብ እስኪለወጥ ድረስ፥ ያ የምናስበው መልካም ስርዓት በቶሎ አይምጣም።

ስለዚህ፥ የሰው ልጅ እድገት በራሱ ከሚያደርገውም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ ሰብአዊ መብቱን ሕዝቡ በራሱ እስኪያገኝ ድረስ፥ እየታገለ፥ እየተማረም ይቀጥላል።

ጫካ ገብተው የታገሉትም፥ ከቢሮአቸው ቁጭ ብለው የታገሉትም ሁሉም ሥልጣን ሲይዙ፥ ሕዝቦችን ረስተው ለሆዳቸው ብቻ በማሰባቸው፥ ተዋርደው፥ ከሰው በታች ሆነው እስከመገደል የደረሱትን አይተናል (በኢትዮጵያ በሌሎችም አገሮች)።

ሲያዩአቸው ብልጦች የሚመስሉትን የአገር መሪዎች ሁሉ የምድራዊነታቸው መንፈስ ሲያታልላቸው፥ ከስነአመክኖአዊ አስተሳሰብ ውጪ ያደርጋቸውና፥ በምድር ለመኖር እንኳን የሚያበቃ እውቀትን ይነፍጋቸዋል። እግዚአብሔር ማስተዋሉን ይስጠን።

ለኢትዮጵያችን ፊውዳሊዝም አልበጃትም፤ ሶሻያሊዝም አላዛለቃትም፤ ካፒታሊዝምን አልደረሰችበትም፤ ምድራዊ ፖለቲካ ብቻውን (ካለ መንፈሳዊነት) በቂ አልሆነላትም፤ እርሷ - ኢትዮጵያ/ኤርትራ አንዲት የእግዚአብሔር አገር ናትና።

በኢትዮጵያ/ኤርትራ የወደፊቱን (የመጪውን) መንግሥት ጥሩ የሚያደርገው፥ ለሕዝቦች የሚጠቅም መንግሥት መመሥረት የሚቻለው፥ በከፍተኛ የመንፈሳዊነት እድገት መሆኑን ልብ ይሏል። ወደድንም ጠላንም እስከአለም ፍጻሜ ድረስ የሚያደርሰን ሥጋዊነታችን ከመንፈሳዊነታችን ጋር ሆኖ ነው እንጂ ብቻውን አይደለም።

በኃይለ ሥላሴ ዘመን የሕዝቦች መንፈሳዊ ጤንነት የተጠበቀ ስለነበር፥ በመጠኑ የሚኖር ሰው ደስተኛ ነበር።

የሚያጠግብ እንጀራ ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ገዳማት በኢትዮጵያ አይበዙም ነበር። የሁለተኛው አለም ጦርነት በዘረኛነት ቢቀሰቀስ፥ ለሦስተኛው አለም ጦርነትም

ተዳፍኖ ቢቀመጥ፥ ኢትዮጵያችንን ምድራዊ ችግር (ዘረኛነትም ቢሆን) አይገድላትም።

የአለም ሕዝብ በጋራ ያድግ ዘንድ ግዴታ ስለሆነ፥ ለአንድነትና ለጋራ ብልጽግና እንቅፋት ሆነው ብዙ መቆየት የፈለጉ ከእንግዲህ አይችሉም። ሕዝቡ የሚለውን የሚያዳምጥና ሕዝቡን በእኩልነት የሚመራ የአገር መሪ ወሳኝ ነው።

በኢትዮጵያ መካከለኛ መደብ ጠፍቶ፥ የድሃና የሃብታም መደብ ብቻ ተለይቶ፥ ድሆች ሃብታሞችን እየለመኑ የሚኖሩባት አገር ሆና አትቀርም ኢትዮጵያችን።

ካሁን በፊት በኢትዮጵያችን የነበረው የመንግሥት ስርዓት ለማንም ባለ አይምሮ ጉልህ ሆኖ የሚታይ የክፋት ወጥመድ የተዘረጋበት ነበር። ይህ የክፋት ወጥመድ በክልል (ዘር የሚሉት - ብሄር - ብሄረሰብ) የተዋቀረ የፌደራሊዝም የመንግሥት አስተዳደር (ስርዓት) ነው። በዚህ የክፋት ወጥመድ ውስጥ ብዙዎችን የሚስቡ የፖለቲካ መርዛማ ምግቦች ተቀምጠዋል። እነኚህም ምግቦች- ውስጣዊ የራስ ወዳድነትን ጠባይ የሚቀሰቅሱ ናቸው። እነኚህን ምግቦች እየተመገቡ ሰዎች እርስበርስ ሲጨራረሱ መንግሥት እያየ ዝም ብሏል።

የምዕራቡን አለም በመንግሥታዊ አስተዳደር ብናደንቅም፥ በጠፈራዊ ንቃተ ሕሊናቸው ከሚደነቁት ተግዳሮቶች መካከል ጥቂቶች ይሆናሉ። ግን ለወደፊት የአለም ሕዝቦች በግድ (በችግር) ተምረው፥ ሁሉም በጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና መንፈሳውያን መሆናቸው አይቀርም።

ከእንግዲህ የወደፊቱ የኢትዮጵያ መንግሥት የሕዝቦች ሁሉ የአንድነት ምልክት ይሆናል። ሕዝቡም የራሱን ኢኮኖሚ ለማዳበር ተስማምቶ፥ ተከባብሮና ተቻችሎ፥ አብሮ ይሠራል ተግቶ። በኢትዮጵያ/ኤርትራ ብዙ ጥገና ይደረጋል፤ የተበላሸው ይስተላከላል፤ በጥላቻ የታነጸ አይምሮ በፍቅር ይታደሳል። አንዱን ከፍ አድርጎ ሌላውን ዝቅ ሳያደርግ፥ ካለ ምንም አድልኦ የሚያስተዳድር መንግሥት ይመጣል። የዛን ጊዜ ኢትዮጵያ (ኤርትራንም ጨምሮ) በቀናው ጎዳና እስከ አለም መጨረሻ ድረስ ወደ ፊት ትጓዛለች።

ይህ ወሳኝ ጊዜ መሆኑን አንባቢ ያስተውል። ከእንግዲህ መጪው ጊዜ በጣም አስፈሪና አስከፊ ቢሆንም፥ በግራና በቀኝ ከሚታየው የሰዎች እልቂት በስተጀርባ ሰብአዊነት በማያቋርጥ ጉዞ ወደፊት ይገሰግሳል፤ መጨረሻው ጥሩ መሆኑ አይቀርም። ውሸት በያለበት ሲረግፍ እውነት በምትኩ ሲያብብ እያየ የማያምን አይኖርም።

ጊዜው መንፈሳዊነትን የትግል መሳሪያ ማድረግን ይጠይቃል። ሥጋዊና መንፈሳዊ ሆኖ ለተፈጠረ ሕዝብ የሚበጀው፡- እስላም ክርስቲያን ሳይል - ሁሉንም በእኩልነት የሚመለከት - የጠቅላላ የሕዝቦችን ሁሉ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ ሕይወት የሚንከባከብ መንግሥታዊ አስተዳደር ነው።

ይህቺ አለም ውሸቶችን ታቅፋ ለዘለአለም ተደላድላ አትቀመጥም፤ በምክንያት ትናወጣለች። እግዚአብሔርም ኢትዮጵያን እያየ ዝም ብሎ አይተዋትም። ስለዚህ ስለ አገራችን ድምጻችን ከማሰማት እና ከመጸለይ አናቋርጥ። ኢትዮጵያ ከምንጊዜውም የበለጠ ወደፊት እንድትራመድ የሚያስችላትን መንፈሳዊ አንድነትን እግዚአብሔር እንዲሰጠን፥ ለአገሪቷ ልማትና የጋራ ብልጽግና፥ ለሕዝቦቿም ሰላምና ፍቅር እንዲሰጣት በሕብረትና በአንድነት ሆነን እንለምነው።

አብሮነታችን (አንድነታችን) ከሌለ፥ በምድራችን ተደላድለን መኖር ያቅተናል። የሰው ልጅ ክፉ የሚሆነውና አብሮነትን የሚጠላው፥ ምድራዊ መንፈስ አንቆ ስለሚይዘው ነው።

እኛ ሁላችንም ምድራዊያን ብቻ ብንሆን ኖሮ፥ ምንም ሳናጉረመርም፥ ጥሩና መጥፎውንም ሳንለይ፥ በምድራዊነታችን ብቻ "ተደላድለን" እንኖር ነበር። ግን በተፈጥሮአችን የጥሩነት መንፈስ ስላለብን፥ መጥፎውን አይተን በቸልተኝነት ማለፍ ስለሚያቅተን እናስባለን፤ እንዲህ እያልን፡-

አንድ ግለሰብ በራሱና ለራሱ (ለሥጋውና ለነፍሱ) የሚበጀውን ሁሉ ቢያደርግ፥ ግን ከራሱ አልፎ ከጎኑ ላለ ሰው እንግዳ ሆኖ ብቻውን ቢቀመጥ፥ ይህ ምን ትርጉም አለው? የመንፈሳዊነት ግቡ ምንድነው? ጥቅሙ ለራስ ብቻ ከሆነ፥ ለሕብረተሰብ፥ ለአገር ለወገንም ካልጠቀመ።

ግለሰብ ለራሱ የሚያደርጋቸው ሁሉ አብረውት ይሞታሉ፤ ለሌላው የሚያደርጋቸው ግን ዘለአለማውያን ናቸው።

እያንዳንዱ ሰው ከግላዊነቱ እየወጣ፥ ችግሩን፥ ደስታና ሃዘኑን ሕብረተሰብአዊ ቢያደርገው ለሁላችንም የጋራ መፍትሔ ለማግኘት ይረዳል። የሰዎች ስሜት መንፈሳዊ ሲሆን፥ በጋርዮሽም ሲተሳሰር ደስታም ሆነ ሃዘን የጋራ ይሆናል። ሃዘኑም ቢሆን ተስፋና ደስታ አዘል ይሆናል እንጂ፥ ፍጹማዊ ሃዘን አይሆንም።

በማንኛውም ጊዜ (ለክፉም ሆነ ለደግ)፥ ሰዎች እርስ በርስ ሃሳብ ለሃሳብ ሲለዋወጡ፥ ትንሽ - ትንሽ አንዱ ሌላውን ይመስላል። በዚህን ጊዜ ክፉቶችና ደግነቶች ሁሉ ካንዱ ወደ ሌላው ይዛመተና ሁለት አቢይት ማዕበሎች ይፈጠራሉ። የክፋት ማዕበሎች ሲደማመሩ ሰው እርስ በርሱ ይጨራረሳል። የደግነትም ማዕበሎች

ሲደማመሩ ማሕበራዊ ግንባታ ይሆናል፤ ሁለቱ ተቃራኒ ማዕበሎች ሲደነቃቀፉ ደግሞ ምንም ሳይሠራ እድሜ መፍጀት ብቻ ይሆናል።

ለጊዜው ነው እንጂ ሥጋ አይጠቅምም፤ ምድራዊ ኑሮ ሲያስመርር ብንመለከት እንጂ፥ መንፈሳዊ ኑሮ ጾጸት ሲሆን አላየንም። ከምድራዊነታችን ባሻገር ሰማያዊ እና ዘለአለማዊ አለም ውስጥ የሚከተን፥ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የመጣ፥ በኋላም ወደ እርሱው የሚመለሰው ጥሩው ሕያው መንፈሳችን ነው። አገራችን (ያቺ) ለረጅም ዓመታት በአለም ታውቃና ተከብራ የቆየችው በሰላም ወዳድ ሕዝቦቿ ፍቅር እና አንድነት ነው።

የጥንት ኢትዮጵያውያኖችን/ኤርትራውያኖችን ሕብረተሰብአዊ አንድነት በሚመለከት፥ የውጪ ጸሐፊዎች እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፡-

"…Men are united by infinity of ties which would count for nothing in Europe. They live together in a reciprocal dependence and solidarity which they value highly and consider a matter of pride, and which influences all they do…" Davidson Basil, 2005 (Page 115)

ወደ አማርኛ ሲተረጎም፡- "ሰዎችን እርስበርስ አገናኝቶ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ተቆጥሮ አያልቅም፤ በአውሮፓ እንዲህ ያለ ነገር የለም። ሕይወታቸው እርስበርስ በመረዳዳትና በመደጋገፍ የተጠናከረ ስለሆነ፥ የሚያደርጉት ሁሉ አንድነታቸውን የሚያጸና ነው። እነርሱም ይህን አብሮ መኖር እንደ ታላቅ ጸጋ ስለሚቆጥሩት ይኮሩበታል፤ የሚያደርጉት ሁሉ ከዚሁ የአብሮነት ጠባይ ጋር የተያያዘ ነውና።"

እንዲህም ሲነገርላት የቆየች አገራችን በድህነትና በረሃብተኛነት ብትታወቅም፥ ያ ሰማያዊ ጠባይ ከሕዝቡ ዘንድ አልጠፋም (ድሃና ረሃብተኛ ሁሉ እንዳይሞት፥ ተረዳድቶ የሚኖር አንድ ቅዱስ ሕዝብ)።

አዎን! ከኢትዮጵያችን ላይ ምድራዊነት ቀስ በቀስ እየተገፈፈ፥ በሰማያዊነቷ ብቅ ብላ ደምቃ የምትታያቸው ብዙዎች ናቸው። ስለሆነም፥ "ለአገራችን ምን እናድርግላት? ምን እናቆይላት? ምንስ እንሥራላት?" እያሉ የሚያስቡላትና የሚጨነቁላት ብዙዎች ናቸው። ሁላችንም በአዎንታዊነት ተባብረን ውዲቷን አገራችንን በማስቀደም በአንድነት ከተነሳን፥ ይህች በመንፈሳዊ ጎኗ ቆንጆ የሆነች አገር በሥጋዊ ጎኗም አምራና ደምቃ የምትታይበት ወቅት መምጣቱ አይቀርም።

እንደ ኢትዮጵያ ክርስቲያንና እስላም አብሮ በሚኖርበት አህጉራት ሁሉ አክራሪዎች የሚፈጥሩትን ሽብር ለማባባስ የሚታገሉ ሰዎች ሁሉ፥ ኢትዮጵያን የሚጠብቁ መላእክት እያዩ ዝም እንደማይሉ ይገንዘቡ።

የሰው ልጅ በታጋሽነቱ አክራሪዎችን (በሃይማኖትም፥ በፖለቲካም) በጉያው ታቅፎ እየተጎዳ ብዙ ቆይቷል። ከበደል ጋር እየኖሩ፥ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ሳይታወኩ መቀጠል የማይቻልበት ደረጃ ላይ እንደሚደረስ ሁሉ፥ በተፈጥሮው የአጥፊነት ዝንባሌ ያለው ሰው አስቀድሞ ይጠፋ ዘንድ ግድ ይላል።

ብሔረሰቦች ሁሉ ተጠራርተው፥
እናቶች፥ አባቶች፥ ከነልጆቻቸው፥
ቄሶችም፥ ሼኮችም አጀብ አጀብ አድርገው፥
ሁሉም ከንፈሮቻቸውን ከፍተው፥
ጥርሶቻቸውን ገልጠው፥
አብሮ በመሆን ብቻ ተደስተው፥
ሰው ምን ይለኛል በማይባልበት አዳራሽ ተሰባስበው፥
በዘፈን፥ በእልልታ፥ በእስክስታና በሽጎዬ፥
ወደላይ - ወደላይ ጮቤ ረግጠው፤......
አቤት ማማራቸው፥ እንዲህ ሲጎላ ጥሩነታቸው።
ግሩም ነው፥ ድንቅ ነው፥
የሰው ማንነቱ - ሁለንተናው፥
አዎንታዊነቱ ውስጣዊነቱን ሲገልጠው፤
በግላጭ ሲታይ ቁንጅናው፥
በመንፈሳዊ ኃይል ውዝዋዜው፤
ተዋዶ ለሚኖር ሰው፥ ለደስታም ወሰን የለው።

እንዲህ የልዩነትን - የአለመደሰትን ጉም የሚያባርር፥
አሉታዊነትን በፍጹም አዎንታዊነት የሚቀይር፥
ሃብት፥ እድሜ፥ ጾታ፥ ጎሳና ሃይማኖትን የማይለይ ፍቅር፤
ይህ እንጂ እኮ ነው፥ በበጎ ፈቃድ የሚመጣ መከባበር፥
የእኩልነት፥ የነፃነት፥ የሕብረት እና የአንድነት ምሥጢር።

እንዲህ እንዳሁኑ አይደለችም ኢትዮጵያችን፥
እርሷን እስክናገኛት - ያምሮታችን፥
አያቋርጥም "ሥራችን"፥ እንደየችሎታችን።

እግዚአብሔር ይሰማል - ፈጣሪያችን፥
ሕዝቦቹንም ይጠብቃል - አምላካችን፥
የአለማችን (ያገራችን) አየሩን፥ አፈሩን ድንጋዩን፥
ሁሉንም እንዲባርክልን፥
እንለምነው - አያቋርጥ ጸሎታችን፥
እግዚኦ ማለታችን፥ እግዚኦ ማለታችን።

ሥርቶ አደር የሆነ ሁሉ በሕይወቱ ውጣ ውረድ ምን አይነት መንግሥት እንደሚመራው ያውቃል (ይገነዘባል)። ስለዚህ፥ አገራችን ወደ እርስበርስ ጦርነት ስትገባ ዝም ብሎ መመልከት አልተቻለም። ገበሬዎች፥ አርብቶ አደሮች፥ ነጋዴዎች፥ አስተማሪዎች፥..ወ.ዘ.ተ. መጥፎ መንግሥት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሕይወታቸውን አውኮት ስለነበረ፥ ወደውም ሆነ ሳይወዱ ፖለቲከኞች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ይህም ማለት እንዳው በደፈናው ስለ መንግሥት ለውጥ ያወራሉ (ይወያያሉ) ማለት ነው እንጂ፥ እንደ ታላላቅ የፖለቲካ ሳይንቲስቶች በጥቃቅን ትንታኔዎች ውስጥ ይገባሉ ማለት አይደለም። ስለሆነም፥ ዘርፈ ብዙ የሆኑ የፖለቲካ ችግሮቻችን ለመፍታት የግድ መሠረታዊ የመንግሥት አስተዳደር ለውጥ እንደሚያስፈልግ ብዙዎች በአጽናኦት ይጠባበቁ ነበር። ያ ቀን የደረሰ ይመስላል። ካለ ምንም የደም መፋሰስ በውስጣዊና በውጫዊ ግፊት ብቻ የመጣ ለውጥ ሥር ነቀል ለውጥ ሲሆን - መሠረታዊ ለውጥን ሲያመጣ ደስ ይላል።

ለውጥ በአብዮት (ሪቮሉሺን) ወይንም በጥቃቅን የጥገና ለውጥ (በሪፎርም) ይመጣል። አብዮት ተካሂዶም መሠረታዊ ለውጥ ላይመጣ ይችላል፤ አብዮት የማያስገኘውን መሠረታዊ ለውጥ በሪፎርም ማግኘት ይቻላል። ስለዚህ፥ በአገራችን የተጀመረው ሪፎርም (ጥቃቅን ለውጥ) መሠረታዊ ለውጥን ያስገኝልናል እያለ በደስታ የሰከረ ሕዝብ “ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ..” እንዳሆነበት ይሰጋል።

አያሌ ደስ ደስ የሚሉ ጥቃቅን ለውጦች ይታያሉ፤ ነገር ግን፥ በብሄር - ብሄረሰብ (በክልል) የተዋቀረ ፌደራሊዝም እና በውስጡ የተጠነሰሰ የክፉት ወጥመዶችን ሁሉ በጣጥሶ፥ በሕዝቦች መካከል ፍቅር፥ ሕብረት እና አንድነትን ለመመሥረት እርምጃዎች ለጊዜው በጉልህ አይታዩም (ተደብቀው ይሆናል)።

ያ “መሠረታዊ ለውጥ - ካለ አብዮት መቼ ይሆን የሚመጣልን?” እያሉ ሕዝቦች ሲጠይቁ፥ በየጊዜው የሚያንጸባርቁት ውስጣዊ ስሜት፥ የቀድሞውን የወያኔ መንግሥት ምን ያህል ይጠሉት እንደነበረ ያሳያል። ለምሳሌ፡- የድጋፍ መግለጪያ

ወይንም የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎችን ሲያደርጉ በአረንጓዴ፥ ቢጫና ቀይ ባንዲራችን ላይ ምንም ሌላ ተጨማሪ ምልክት የሌለውን ባንዲራችንን ይዘው ነው።

ለውጡ ሥር ነቀል ለውጥ ካልሆነ - መሠረታዊ ለውጥን ካላመጣ፥ የሕዝቡ ምናባዊ ደስታ ወደ ገያዳዊ ቅሬታ ይለወጣል። "ሚዳቋ እዚያ ቅዝምዝም እዚያ.." እንደሚሉት አይነት ይሆናል። ሕዝቡ ዘረኛነትን የሚያጠፋ፥ ወደ አንድነትና ሕብረት የሚመራው መሠረታዊ ለውጥን ይሻል።

ሕዝቡ ምንጊዜም መሠረታዊ ለውጥን በታላቅ ተስፋ እንዲጠባበቅ የሚያደርገውን ስነ አይምሮአዊ ብርታቱ እንዳይዳከም፥ አዎንታዊ ምኞቱም እንዳይጨል ማበረታታት ያስፈልጋል።

ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር አብሮ የሚጓዝ መንግሥት ሲመጣ፥ ያ መንግሥት ጥሩ ይሆናል፤ ምክንያቱም፥ በምድራችን ፍጹምና ጥሩ ሕዝብ ስለማይኖር ያ ሕዝብ ፍጹምና ጥሩ እስኪሆን ድረስ መጠበቅ ያስፈልጋል እንጂ፥ "እኔ ጥሩ መንግሥት ስለሆንኩ እኔን ብቻ ስማኝ..." የሚል መንግሥት አምባገነን (ዲክታቶር) ነው ሊሆን የሚችል። ይህንን በምሳሌ እንመልከት፡-

እስራኤል ንጉሥ እንዲነግሥላቸው ሳሙኤልን በጠየቁት ጊዜ፥ ያ የሕዝቡ ጥያቄ ወቅታዊና ትክክል እንዳልነበረ እግዚአብሔር ያውቃል፤ ነገር ግን የሕዝቡን ቃል እንዲሰማና የፈለጉትን እንዲፈጽምላቸው የሚከተለውን ለሳሙኤል ነገረው፡-

"እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው፥ "በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን ናቁ እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ።" ፩ኛ ሳሙ. 8፥7

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቃሉን የሚሰማለት መንግሥት እስካሁን አላገኘም፤ አሁንስ መሠረታዊ ለውጥን ከመንግሥት እንደማያገኝ ተረድቶታል፤ ግን በምን አይነት መንገድ እንደሚያገኝ ግራ ገብቶታል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የመብዛታቸውን ያህል በያለበት ወሬ በዛና ኢትዮጵያዊ የሆነ ለሕዝቦች ሁሉ የሚጠቅም ርዕዮት ጠፋ። ያቺ ትንሽ የተስፋ ዝናብን ያቀፈች ዳመና በየት በኩል ነፍሳ መቼ እንደምትዘንብ ማን ያውቃል?

ሕዝቡ እግዚአብሔርን ሲሰማ፥ መንግሥትም ሕዝቡን ሲሰማ፥ የዛን ጊዜ ሁሉ ነገር ደህና ይሆናል።

አንድ ፖለቲከኛ ማንነቱን እየደበቀ ጥሩ ሰው የመምሰል ችሎታ ስላለው፥ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ ሕዝቦችን በጠቅላላ ካለ ጎሳ (ብሔረሰብ) ልዩነትና ካለ አድልኦ፥ በቅንነት የሚያገለግል፥ በእውነት የሕዝቦችን ጥቅም ከግል ጥቅሙ አስበልጦ

የሚያይ መሆን አለመሆኑን ከፖለቲካው አቋሙ ብቻ (ወይንም ከንግግሩ ብቻ) ማወቅ አይቻልም።

ስለዚህ፥ ለወደፊቱ፥ የአገራችን (ኢትዮጵያ/ኤርትራ) ዜጎች ለአገር መሪነት እጩ ሆነው ከሚቀረቡት የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው መካከል ለመምረጥ ወደ ምርጫ ሥፍራ ከማምራታችው በፊት፥ የእጩዎቹን መንፈሳዊነት በማገናዘብ፥ አንዳንድ ቁልፍ ጥያቄዎችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ የተሻለ ውጤት ሳያመጣ አይቀርም። ለምሳሌ፡-

1. ይህ ለእጩነት የቀረበ ግለሰብ (ፓርቲ/ድርጅት) በእውነት አንዱን ብሔረሰብ ከሌላው አስበልጦ የማያይ ነው ወይ?
2. ለግል ሳይሆን ለጋራ ሰላም፥ ፍቅር እና ብልጽግና ያስባል ወይ?
3. ይህ ግለሰብ (ፓርቲ/ድርጅት) በጠባዩ የውሸታምነት፥ የጠበኛነትና የአክራሪነት (ወ.ዘ.ተ...) ዝንባሌ ይታይበታል ወይ?
4. ከዚህ የተረፈው መለኪያ የፖለቲካ (የውስጥና የውጪ)፥ ሶሻል እና የኢኮኖሚ አጀንዳ ነው።

በአገራችን (በኢትዮጵያም በኤርትራም) ብዙ ቅን አሳቢ ፖለቲከኞች (ስለ ሕዝባዊ አስተዳደር የተማሩ) አሉን። በጥሞና የሚያዳምጣቸውና የሚከተላቸው ያስፈልጋል። ለወደፊት አዲስ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሲቋቋም፥ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች መሪዎቻቸውን እየተከተሉ አገሪቷን ለማሻሻላል የሚያበቃውን ተሳትፎአቸውን ይቀጥላሉ። ይህም የተቆራረጠ ነፃነት ይገጣጠምና "ዘረኛነት" ይጠፋና፥ እኩልነት ይሰፍንና፥ ኢትዮጵያዊነት ይገነና ብሔራዊ አንድነት ይጠናከራል (ይህ ነው ከነፃነትና ከእኩልነት ቀጥሎ የሚመጣ ፍጹማዊ አንድነት ማለት)።

ከብት አርቢዎች፥ "ዝናብ ከወዴት በኩል ዘነበ? ወዴትስ ብንሄድ ይሻላል?" እያሉ መረጃዎችን እንደሚለዋወጡ ሁሉ፥ ለወደፊት ፖለቲካ ለተራው ሰው እርስ በርስ መወያያ (የቀን ተቀን ኑሮውን ለማሟላት ዘዴ መቀየሺያ፥ የዛሬውና የወደፊቱን ትውልድ በስነ ስርዓት ስለሚያስተዳድር ስርዓት ማመቻቺያ) ይሆናል እንጂ፥ መጨቃጨቂያና ጸብ መፍጠሪያ፥ መሰዳደቢያና ማጋደያ አይሆንም።

በእርግጥ መንግሥታት በራሳቸው ጥሩ እንዲሆኑ ሕዝቦች በቂ ጊዜ መስጠት ይገባቸዋል። ግን በታሪክ እንደታየው ሁሉ፥ መንግሥታት በሥልጣን ላይ ብዙ ሲቆዩ ልክ ሰውነት ውስጥ ብዙ እንደተንሰራፋ ፓራሳይት ነው የሚሆኑት። ስለዚህ፥ መንግሥታት በሥልጣን ላይ ብዙ ሲቆዩ፥ "በሕዝቡ ላይ ፓራሳይት ሆንኩ ወይ?" ብለው እራሳቸውን ቢጠይቁ፥ ከዚያም አልፈው፥ የሕዝቡን የልብ ትርታ እያዳመጡ፥

በሥልጣን እስከ ቆዩበት ድረስ የተቻላቸውን ቢያደርጉ፥ በበጎ ሥራቸው ታሪካዊ ሥፍራ ይኖራቸዋል።

አግባብ የሌለው ጩኸት የሚያሰሙ ሰዎች፥ አግባብ ያለው ጩኸት የሚያሰሙትን ይሸፍናሉ። በዚህን ጊዜ ብልጥ መንግሥት፥ ጥሩም ሆነ መጥፎ፥ የመቆያ ጊዜው ይራዘምለታል።

አግባብ የሌለው ጩኸት የሚያሰሙ ሰዎች፥ አላማ በሌለው ፖለቲካ እየተመሩ ፖለቲካን የሕዝቦች ተስፋ ማስቀረጪያ፥ መጨቃጨቂያና መሰዳደቢያ ብቻ በማድረግ፥ ለተንኮለኛ መንግሥት ጊዜ ማራዘሚያነት ያደርጉታል። ለዚህም ነው፥ ብሔረሰቦችን ሁሉ በእኩልነት የማያዩ፥ ምድራዊ መንፈስ አንቆ የሚይዛቸው ዲክቴተሮች እና ግብረአበሮቻቸው ከሚገባው በላይ በሥልጣን ላይ የሚቆዩት።

ሌሎች ምድራዊ መንፈስ አንቆ የሚይዛቸው ፖለቲከኞችም ሥልጣን ሲይዙ ሕዝቡን ይረሱታል። ታዲያ መቼ ነው እኛ ከራሳችን ሰማያዊ - መንፈሳዊ ጠባዮቻችን የምንማር?

ጠቅላላ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ካለ አድልኦ አስተዳድራለሁ ብሎ የሚነሳ የፖለቲካ ድርጅት (ፓርቲ) በዲሞክራሲ የሚያምን ቢሆን፥  የራሱ በሥልጣን ላይ መቆየት አያሳስበውም፤ ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ለመስማማት ይጥራል እንጂ።

ጥሩ መንግሥት (እንዲሁም ጥሩ ሕዝብ) ለገዛ አገሩ ጠላት ሊሆን አይችልም። ስለዚህ፥ ለወደፊት መልካም መንግሥት ሲመሠረት፥ እርስ በርስ መደነቃቀፍ እንዳይመጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። አለበለዚያ፥ ያው የተለመደው ጠላትነት ይፈጠራል። ከውጪ ከሚመጣ የጠላት ጥቃት የሚብሰውም ይኸኛው ነው።

የሕዝቦች መንፈስ አይተኛም። በአጠቃላይ ሲታይ፥ ማንኛውም  በምድር ላይ የሚሠራ ሥራ ሁሉ፥ እስከሞት የሚያደርስ፥ ጦርነት..ወ.ዘ.ተ.. ቢሆንም፥ ሰብአዊነትን እስከ ተወሰነው ደረጃ ድረስ ለማድረስ ስለሆነ፥ ወደ መጨረሻያው ገደማ (የአለም መጨረሻያ መሆኑ ሲረጋገጥ)፥ ይህ ምድራዊ ሥራ ሁሉ ወደ ልዩ ፍጹማዊ አለም የሚከት መሆኑ ይረጋገጣል።

እስከዛው ድረስ ግን፥ “እኛ ወደ ፍጹማዊ አለም በሚያስኬደው ጎዳና ስንጓዝ ሰብአዊነትን የት አደረስነው?” በማለት እራሳችንን መጠየቅ ተገቢ ነው። በጊዜ ውስጥ ውሸት ሥፍራውን ለእውነት እየለቀቀ ሲሄድ፥ ውሸት በያለበት ሲረግፍ፥ እውነት በምትኩ ሲያብብ፥ “...እኔን የአገሬ ሕዝብ እንዴት ያየኛል?” የማይል የአገር መሪ

“አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል” እንደሚባለው፥ ጥሩው እያለለት መጥፎውን እየሠራ ጥላቻን ያተርፋል።

በኢትዮጵያችን ውስጥ ከአለማዊ ድርጊቶች ይልቅ መንፈሳዊ ድርጊቶች ስለሚያመዝኑ፥ በመንግሥታዊ አስተዳደር በኩል የተጨቆኑ ሕዝቦች ለፈጣሪ አቤቱታ ያቀርባሉ፤ ምላሹም በየጊዜው ይከሰታል። ይህንን የማያይ የአገር መሪ፥ መንፈሳዊ አይኑ የታወረ፥ በምድራዊነቱ ብቻ የሚንቀሳቀስ፥ ለራሱም የሚበጀውን የማያውቅ ሞኝ ነው።

በየወቅቱ የሚከሰተውን በመንፈስ አርቅቆ በመመልከት፥ የእግዚአብሔር ሥራ ይገለጣል። የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ “ማየት የሚችል” ይማራል፤ የተማረውም ያስተምራል። የእግዚአብሔርን ሥራ “ማየት የማይችል” ደግሞ አይማርም፤ ስለይማርም ያልተማረውን ያደናቁራል።

እንደ እግዚአብሔር ታጋሽ የለም፤ እንደ እግዚአብሔር ቁጣም የሚጎዳ የለም። የሕዝቦች ምሬት ሰማይ ወጥቷል፤ እግዚአብሔርም ሰምቷል። ምድራዊና መንፈሳዊ ሂደቶች የራሳቸው ምክንያቶች ቢኖራቸውም፥ እኛ በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ የወደፊቱን የማናውቅ በመሆናችን፥ በውዴታ እና በግዴታ የምንንቀሳቀስ ፍጡሮች ሆን እንጂ፥ “ሁሉም” አለ (ይታያል) ካጠገባችን። እስቲ እዩት፡-

ለትግልም መድረኩን ሳያገኝ የቆየው፥

በድምጽ አልባ ጩኸት የጮኸው፥

አይናከስ ነብሩ፥ አይባላ አንበሳው፥

እንዳው ጩኸት በዝቶ እንጂ እኮ ነው፤

“ማነው ልክ? ማነው ሃሰተኛ?” ሳይባል የተበየነው፤

ያም ሆነ ይህ፥ ለሁሉም ቀን አለው፤

ቅንነት የጎደላቸው፥ ለጊዜው ቢደላቸው፥

ይሄዳሉ፥ ሁሉን ጥለው።

ሕዝቦችም የሚገባቸውን መንግሥት ያገኛሉ። ግን “እንዲህ አይነት ጨካኝ መንግሥት ለምን ወደኔ መጣ?” ብሎ እራስን መጠየቅም ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ከራሱ ታሪክ እየተማረ ስህተቶቹን ላለመደጋገም ሲጥር ብቻ ነው መሻሻል የሚመጣው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ተቀናቃኝ (ተቃዋሚ) ኃይላት አንዱ የሌላውን ጉድለት (ድክመት) በማስተጋባት (እርስ በርስ በመነቃቀፍ) እስከዛሬ

ያጠፉት ጊዜ አዎንታዊ ገጽታ ይኖረዋል እንላለን (አሉታዊነትን መደጋገም እንዳይሆንብን)።

ይኸውም፡- እስካሁን በሰላማዊ መንገድ የተደረገው መነቃቀፍ እርስ በርስ እንዲተዋወቁ ስላደረጋቸው፥ ለወደፊት እርስ በርስ ከመጠፋፋት ያድናቸዋል። ከእንግዲህ ተቃዋሚ (ተቀናቃኝ) ኃይላት ሁሉ፥ በእውነት ለኢትዮጵያችን የሚያስቡ ከሆነ፥ በሰላምና በፍቅር በጋራ መሥራት የሚችሉበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም።

ከእግዚአብሔር ቸርነት ጋር፥ ሁላችንም መጪውን የመቀየስ ችሎታ አለን። ይቅር ብንባባል ነው የሚሻለው። መጥፎውን ሁሉ በአዎንታዊነት ወደ ጥሩ ለመለወጥ የሚታገሉ ወድቀው አይወድቁም።

አካባቢውን በአሉታዊነት የሚያጨልም፥ እርሱ በውስጡ ብርሃን የሌለው ነው። የሰው ልጅ ከጠባብ ምድራዊ - ሥጋዊ ርዕዮት እየተላቀቀ፥ ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና ይኖረው ዘንድ ግዴታ እየሆነ ነው የመጣው።

ከምድራዊነት ባሻገር ያቺን ቆንጆ፥
እዩአት እንጂ ኢትዮጵያን፥
ተመልከቱት እንጂ ፍቅሯን - ደግነቷን፥
በጉያዋ ታቅፋ በመንፈስ የሚዋደዱ ልጆቿን።
ለእርቅ የሚያስብ ሲጠፋ አስተዋይ፥
መጥፎ ቀን በዛብን፥ ጥሩውን ቀን ሳናይ።
ከምድር የሚበቅለው የሚሆን በረከት፥
ሲኖሩባትም ደስ የሚላት መሬት፥
ሕዝቦች ሲስማሙ ነው፤ ሲቀድም አንድነት።
ዝናቡም ይዘንባል፥ የተዘራውም ይበቅላል፤
የበቀለውም ይመረታል፥ ምርቱም ይዳረሳል፤
ብሩም ይከመራል፥ የተከመረውም ይከፋፈላል፤
ጥሩውን (እግዚአብሔርን) የሚያስብ፥ ያጣውን ያገኛል።
መጥፎውን የሚያስብ፥ ያገኘውን ያጣል።
ሲረዱት የማያውቅ፥ ነዝናዛ፥ ነትራካ፥
ቢበላም አይጠግብ፥ ቢጠጣም አይረካ።
ወገኖች ነጽሩ አሾልካችሁ፥

አሉታዊነትን ትታችሁ፤
ያ.....ውና፥ ከዚያ ማዶ፤ ያ ቆንጆ አገር - አገራችሁ፤
መደሰቿያ፥ መቦረቂያ ሥፍራችሁ፤
ስትኖሩበት ሞቅ ይላል ቤታችሁ፤
በስደትም የሄዳችሁ፥
ስትመጡ ተመልሳችሁ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያችን እጅጉን አድጋለች - በጥሩውም በመጥፎውም። ዝርዝር ጉዳዩን ለመግለጽ ይህ መጽሐፍ ብቃት የለውም። ከዚህም ከዚያም የሚሰነዘሩ ፖለቲካዊ ትችቶች አይነታቸው ብዙ ስለሆነ ሁሉንም ማየት ከባድ ነው። ለወደፊት ታሪክ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ ጥቂት ሁናቴዎችን (ትችቶችን) እንጠቅሳለን የደረስንበት (2011 ዓ.ም.) ለማንጸባረቅ ያህል ብቻ።

ከአጠቃላይ ትችቶች የምንገነዘበው ባሁኑ ወቅት ያለው መንግሥት ባለ ሁለት ገጽታ ይመስላል። እኛ ከዚህና ከዚያ መሪ (ግለሰብ/ፓርቲ) ምን አለን? ከኢሐፓዎችስ ምን አግኝተናል? ከ ሀ እና ከ ለ? ከደብተራውስ? እንዲሁም፥ ሰው የሆነውን ሁሉ ታዝቧል ይህ መጽሐፍ። ከእውቀቶች ሁሉ ባሻገር፥ እኛ ሁላችንም አንድ ነገር ብቻ እናውቃለን። ይኸውም፡- ባሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን የሚመራት መንግሥት እጅግ መጥፎ ቢሆን እንኳን፥ ቸሩ እግዚአብሔር ያንኑ መንግሥት ጥሩ ሊያደርገው ይችላል።

ባጠቃላይ ሲታይ፥ የደረስንበት ጊዜ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም፤ ብዙ ደስ ደስ የሚሉ እርምጃዎች ተከናውነዋል። እነርሱን ከጎን እንተዋቸውና፤ ከሰብአዊ ስሜት አንጻር ብቻ በመነሳት፥ የሕዝቦችን ጩኸት እንጥቀስ።

በእርግጥ እውቀቶች በብዙ አቅጣቻ ያደጉበት ወቅት ነው በኢትዮጵያ። ግን የኢትዮጵያችንን መፃኢ እድል የሚወስነው የእውቀት ብዛት ወይንም የአዋቂዎች ብዛት ሳይሆን ትንሽ እውነት ነው።

“ለምን ይህ ሆነ? ለምን ይህ ተፈጠረ? እንዴት ይህንን ማሻሻል አልተቻለም? ለምን የሕዝቦች ፍላጎትና ጩኸት ከመሪያቸው አመራር ጋር አልሰመረም? በኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ የበላይነት ጠፍቶ፥ በያለበት እጅግ ዘግናኝ የሆኑ ወንጀሎች ሲፈጸሙ እንዴት አገሪቷን ሰላም የሚያሳጡ ኃይሎችን መቆጣጠር አቃተ?

“የፖለቲካውን ምህዳር ለማስፋት - ዲሞክራሲን ለማለማመድ....” በሚል ፈሊጥ አገራችንን በአላስፈላጊ ጥላቻ ወደ ግድያ - ወደ እርስ በርስ እልቂት፥ ወደ መከፋፈልና ወደ ውድቀት የሚመሯትን ኃይላት በቁጥጥር ውስጥ ማዋል ሲቻል

ተውናቸው። እነርሱም ኃይላቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጠናከሩ ብዙ መጥፎ መጥፎ ሥራዎችን ፈጸሙ።

በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ መንጫጫት እጅግ በዛ በኢትዮጵያችን፤ የሰዉ ሃሳብ ለሁለት ተከፈለ። ሕዝቡ ብዙ ለማድረግ ሲችል፥ ከሁለት በተከፈለው አስተሳሰቡ ምክንያት፥ ያለው ምርጫ ወሬ ብቻ ሆነ።

መንግሥት በአጥፊዎቹ ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ እንዳይወስድ የጊዜው ሁኔታ ባይፈቅድለትም፥ "ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም"ና፥ የኢሰብአዊ ድርጊቶች ጠንሳሽ ማን እንደሆነ ሕዝቡ እንዲያውቀው ቢደረግ እንኳን፥ ለውጥ ፈላጊው ሕዝብ፡

1ኛ) ለወደፊት ከሚመጣበት አደጋ ራሱን ለመከላከል ይረዳዋል።

2ኛ) በለውጡና በመሪዎቹ ላይ ምንም ጥርጣሬ ሳያሳድር በአዎንታዊነት እና በተስፋ ወደፊት ይጓዛል።

በምድር ቆይታችን ብዙ ቦታ አድርሶናል (በምናብ - በሃሳብ - በተግባር) - ማወቅ የሚገባንን እና የማይገባንን እንኳን በደንብ ሳንለይ፥ ልናውቅ የምንችለውንም፥ ልናውቅ የማንችለውንም - ይህንንም ያንንም እየነካካን፥ በብዙ የእውቀት ዘርፎች ለመራቀቅ በቃን።

ከልጅነት እስከ እውቀት ኑሮአችን ሁሉ - ከምድሪቱ ጋር ስምም ሆኖ ለመኖር ያደረግነው ጥረት - አንዱ የእውቀት ዘርፍ - በምድራዊ እውቀት (ሳይንስ ጠቀስ እውቀት) አራቀቀን። ደግሞም፥ ያንን የማይቀረው ሞትን እጅግ ስለምንፈራው፥ ከምድር ተለይተን የምንሄድበትንም ሥፍራ ለማወቅ ያደረግነው ጥረት - ሌላው የእውቀት ዘርፍ በ"ሰማያዊ እውቀት"(ሃይማኖት ጠቀስ እውቀት) አራቀቀን።

እውቀት - ከማወቅ እስከ አለማወቅ፥

በሳይንስ ወይንም በሃይማኖት መራቀቅ፥

ሁሉም የነፍስ ጥያቄ መሆኑን አውቀናል፤

አንድም እንሞታለን - አንድም እንኖራለን፥

አይኖች ብዙ አይተው ፈዘዙ፥

ጆሮችም ብዙ ሰምተው ደነዘዙ፥

ልብ እና አንጎል ለየብቻ ዋሉ፥

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያ ተከፋፈሉ፤

አብራኮቻችን እየቆሰሉ ተለያዩ፥

ማንነታቸውን ተነጥቀው ስለቆዩ።
ጥሩ ስም - ጥሩ አስቦ፥ ጥሩ ተናግሮ፥ ጥሩ ለሚሠራ ብቻ ‘ማይደል?
ሰውን እንደ አሮጌ እቃ ከቤት አስወጥቶ መጣል፥
ለዚህ ግፍ የማን አይምሮ ችሎ ይቀመጣል?
ጥሩ በሚባል መንግሥት - ይህ እንዴት ይሆናል?
ችግርን ሲስቸግሩት፥ ሌላ ችግር ይወልዳል፤
    የሕዝቦችን ጥያቄዎች ሁሉ መመለስ ባይቻል፥
    ለምን በሕዝቦች ላይ ችግር ይጨመራል?
    በጎን ወይንስ ከላይ - ቀጭን ትእዛዝ በኩል።
    መቼም ሰው ከኖረበት ሲፈናቀል፥
    ያልተፈናቀልው አይቶ ዝም አይል፥
    ለተሰነዘረ ጥቃት ምላሹ ቢውል ቢያድር፥
    ግፍ ፈጻሚው ከመጠየቅ  አይቀር።
ችግሮች እያየናቸው  እየቀረቡን ሲመጡ፥
ብዙ እውነቶች ለየብቻ እየተቀመጡ፥
ለኢትዮጵያችንስ እኔ ብቻ እበቃለሁ እያሉ፥
ግለኛ አስተሳሰብን ሰበኩ - ሕብራዊነትን እያጣጣሉ።
እኛም - እየኖርን ሞተናል - እየሞትንም ኖረናል፥
አንድ ቀን - ያችን ቀን ስንጠባበቅ - በተስፋ ብቻ ጠግበናል።
    ካለ አንድነት - ካለ ሕብረት - ማን ሠርቶ በለጸገ?
    ወይንስ ማን በልጽጎ ሕብረትን አገኘ፥
    ቃላትም ማባበያ - መለማመጫ፥
    እንጀራ አስኪሆን ድረስ ጉርሻ፥
    ብልጽግና - ሳይራመዱ ሩጫ፥
    ዝምታን ያለማክበር ፍዳ፥
    እስከ ጦርነት ድረስ - ሰው ሁሉ ሲጎዳ፥
ግን ለምን ሰው ማወቅን ተሳነው?
ዑራኤል ለዕዝራ ያስተማረው፥

"ከምድራዊነታችን ባሻገር" ያለው፥

ዲሞክራሲ ለምድራዊነት፥

ዲሞክራሲ ለመንፈሳዊነት፥

ዲሞክራሲ ለምድራዊ - ሰማያዊ ኑሮ - ለነጻነት።

በምድር ላይ ካለ ብዙ ችግሮች ብዙ ጊዜ ለመቆየት፥ ለሕብረተሰባዊ አንድነት ቅድሚያ መስጠት፥ ሰው የሆነውን ሁሉ በሰውነቱ ማወቅና ማክበር ግዴታ ይሆናል። ማንም ኢትዮጵያዊ ለራሱ ብቻ ሳይሆን፥ ለመላው ኢትዮጵያ የሚያስብ መሆኑ በተግባር ሲታይ  ነው እምነት የሚጣልበትና ሕዝቦችን መምራት የሚችል። ሕዝቦች መሪያቸውን ካልሰሙና ካልተከተሉ በስተቀር አገር ወደፊት ልትራመድ አትችልም።

በአሁኑ ጊዜ ያ የርኩስ መንፈስ ተምሳሌት የሆነ የኖሌ ሃውልት አሁንም በአርሲ ተገትሮ ይሳደባል። አክራሪ ዘረኞች የሆኑ ፖለቲከኞች (ምሁራንም ጭምር) በተደበቀው መጥፎነታቸው ለየመጡበት ብሄሮቻቸው (አማራ፥ ኦሮሞ፥ ጉራጌ፥ ትግራይ፥...) እያደሉ፥ መርዛቸውን ይረጫሉ። በየጊዜው የሚደፋውም የዘረኝነት መርዝ ንጹሁን - ጤነኛውን - ደጉንና ድሃውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እየመረዘ፥ ሁሉን ብሄረሰብ ከግሩ በታች ቀጥቅጦ እየገዛ መኖርን የሚመኘውን ዘረኛ እስከመከተልና እርስ በርስ እስከመገዳደል ተደርሷል።

በቃ! እውነትን መጠቀም ለሚያውቅበት ብዙ እውቀት አያስፈልግም፥ ከብዙ እውቀት ትንሽ እውነት ይበቃል። ታሪኮች - መረጃዎች- ሃቆች - እውነቶች - ባጠቃላይ እውቀቶች ሁሉም ተደማምረው ኢትዮጵያችንን ከፍ ካላደረጓት፥ ማወቅ ምን ይሠራል? ድንቁርና ይሻላል።  በቃ! ዘረኝነትን የሚያቀነቅን አዋቂ ምንም አይረባትም ለአገራችን።

አንድን ብሄር ለይቶ መሳደብ ምን ይጠቅማታል ለኢትዮጵያችን? አንዱ ጎሳ (ብሄር) ሌላውን ሲሳደብ በእሳቱ ላይ ቤንዚን የሚያርከፈክፉ እኩይ ፖለቲከኞችም እርስ በርስ መሰዳደቡ እንዲቀጥል ሲያደፋፍሩ፥ "ኸረ የኢትዮጵያችን ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ ወዴት ነው የምናመራው?" ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

የጋርዮሽን ዘመን አልፈን፥ ባሪያ፥ ጨዋ፥ ከሚባልበት የባርያ ስርአት ተሻጋግረን፥ የፊውዳልን ዘመን ረግጠን፥ በሶሺያሊስት አገዛዝ ታሽተን፥ አሁን ያለንበት ዘመን ማንነታችንን ያጣንበት ዘመን ቢመስልም፥ የእኛን ማንነት የሚወስን፥ ያሳለፍነው እና ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ተጨምሮበት፥ በሕዝቦች አጠቃላይ ንቃተ ሕሊና እና በርዕዮታችን የሚወሰነው የወደፊቱ እድል ፈንታችንም ነውና፤ ውስጣዊ ማንነታችንን እንመርምር።

ከመጥፎነታችን ባሻገር፥ ጥሩነታችንንም በራሳችን ማግኘት እንችላለን። ጥሩነታችን ኢትዮጵያዊነታችን፥ አንድነታችን፥ ሕብረታችን ነው።

ደጋግ ሕዝቦች ባሉበት የከፋት መርዞችን እየነሰነሱ ያለፉት ያገር መሪ የተባሉ ሁሉ፥ እነርሱ ባልጠበቁት መስመር፥ አንድነታችን እንዲጠናከር ምክንያት ሆነውልናል። ዛሬ ውስጣዊ ማንነታችን ብቅ ብሏል፤ የሼኩና የቄሱ አክራሪ አለመሆን፥ የሕዝቡም ሰላማዊነትና መንፈሳዊነት፥ ባልታሰበ የፍቅር ሰንሰለት አስተሳስሮናል። ፈረንጆች (blessing in disguise) እንደሚሉት አይነት፥ ክፋቶች ደግነትን ባይወልዱም፥ በኢትዮጵያችን የክፋቶች እድገት ልክ አባ ጨጓሬ ወደ ቢራቢሮ እንደሚለወጥ ሆኖልናልና፤ ይህንን የተሰፋ ጭላንጭል በመጠቀም በአዎንታዊነት ወደፊት እንግፋ።

**ተፈጸመ**

በእውነት ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ፍጹምና ኃያል፥
ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ነው።

አስጀምሮ ላስጨረሰን ለፈጣሪ አምካችን ታላቅ ምስጋና ይድረሰው።
አሜን።

የሚከተለውንም “ከምድራዊነታችን ባሻገር” ሁለተኛውን የግጥም መጽሐፍ በቀጣይ እንዲያነቡ ተጋብዘዋል።

**በረከተ ጸሎት**

እኛ በሰማይ የሚኖሩትን ሁሉ ከኛ ጋር በመንፈስ እንደሚኖሩ አድርገን ነው የምንቆጥረው። ባጠገባችን ያለውን ሰው ጸልይልን እንደምንል ሁሉ፥ ሰማያውያንንም ጨምረን - ማርያምን፥ መላእክትን እና ጻድቃንን ሁሉ እባካችሁ ጸልዩልን ብለን እንለምናቸዋለን። ይህም በምድር እየኖሩ ሰማያዊ ኑሮን መለማመድ ነው። ከያቅጣጫው ለኢትዮጵያችን ጸሎት ይብዛላት፤ ቸሩ ፈጣሪያችን ከክፉ ነገር ሁሉ እንዲሠውራት።

**ጸሎት**

አቤቱ እግዚአብሔር አምላካችን ፈጣሪያችን ሆይ!

እኛ ሰዎች አብረን ስንኖር በፖለቲካ፥ በሃይማኖት እየተለያየን እርስ በርሳችን ከመጣላት የሚያድነንን፥ ሰላማችንን እና አንድነታችንን የምናገኝበትን መንገድ አንተ ታሳውቀን፥ አንተም ትመራን ዘንድ እንለምንሃለን።

አቤቱ እግዚአብሔር አምላካችን ፈጣሪያችን ሆይ! ቅዱስ መንፈስህን ከአለም ሕዝቦች አታርቅ። ሕዝቦች ሁሉ ለፍቅር፥ ለሰላምና ለአንድነት የሚቻኮሉ፥ በጽድቅ ጎዳና በአንተ ፈቃድ የሚመላለሱ እንዲሆኑ፥ በጎውንም መንገድ እንዲሹ አንተ እርዳቸው።

አቤቱ እግዚአብሔር አምላካችን ፈጣሪያችን ሆይ! ያንተ የሆኑ ሕዝቦች ሁሉ በያሉበት የእውነት ሰዎች ለመሆን በሚያደርጉት ጥረት ቅዱስ መንፈስህ እንዳይለያቸው እንለምንሃለን።

አቤቱ እግዚአብሔር አምላካችን ፈጣሪያችን ሆይ! ኢትዮጵያን አገራችንን ባርክልን፤ መልካሙንም መንግሥታዊ አስተዳደር አንተ አምጣላት።

አቤቱ እግዚአብሔር አምላካችን ፈጣሪያችን ሆይ! ኢትዮጵያን አገራችንን ጠብቅልን፤ ለሕዝቦቿም ሰላም፥ ፍቅር እና አንድነት ስጥልን። አሜን።

# ዋቢ መጻሕፍት

(ለአራቱም መጻሕፍት)


Abdullah Yusuf Ali (Translation by), 2002: **The Qur'an**, Published by Asir Media.

Bartusiac Marcia (edited and with Introduction), 2006: **Archives of the Universe**, Vintage Books, A Division of Random House, INC. New York.

Bhaktivedanta Swami Prabhupada A.C (His Devine Grace), 1972, 1983: **Bhagavad Gita As it is,** The Bhaktivedanta Book Trust

Charles Darwin, 1958: **The Origin of Species**, Signet Classics.

Close Frank, 2009: **Anti Matter,** Oxford University Press.

Coogan Michael D., 2003: **World Religions,** Duncan Baird Publications, London.

Davidson Basil, 2005: **Africa in History**; Touchstone, Rockfeller Center, New York, N.Y.

Drage Hale Rosemary, 2004: **Understanding Christianity**, Duncan Baird Publishers, London.

Ehrlich Carl S., 2003: **Understanding Judaism**, Duncan Baird Publishers, London.

Elain Murray Stone, 2004: **A Saint and His Lion, the Story of Tekla of Ethiopia,** Paulist Press.

Hammond, 2002: **Concise Atlas of World History**, 6th Edition, Map Makers for the 21st Century; HarperCollins Publishers.

Hausman Gerald, 1997: **The Kebra Nagast**: St. Martin's Press, New York

Hawking W. Stephen And Leonard Mlodinow 2010: **The Grand Design**; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 1988: **A Brief History of Time**, From The Big Bang to Black Holes; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 2005: **The Theory of Everything**, Fate of The Universe; Phonix Books.

Houston Drusilla Dunjee, 2007: **Wonderful Ethiopians of The Ancient Empire**; Nuvision Publications, LLC, Sioux Falls, SD, USA.

Jackson G. John, 1939 And 1985: **Ethiopia and the Origin of Civilization**; Nuvision Black Classic Press, Baltimore, MD. USA.

John Brockman (Editor), 2010: **This Will Change Everything**, Ideas That Will Shape The Future; Harper Collins Publishers, New York, NY. 10022.

Laszio Ervin, 2006: **Science and The Enchantment of The Cosmos**; The Rise Of The Integral Vision Of Reality, Inner Traditions, Rochester Vermont.

Leslau Wolf, 1976: **Concise Amharic Dictionary**, Amharic - English, English - Amharic, Otto Harrassowitz – Wiesbaden, Commercial Printing Press, Adds Ababa, Ethiopia

Mary And John Gribbin, 2003: **From Atoms to Infinity**; Icon Books.

Muhaiyaddeen Bawa M.R., 1987, revised 2004: **Islam and World Peace, Explanations of a SUFI,** The fellowship Press, Philadelphia, PA.

Oldstone Moore Jennifer, 2003: **Understanding Confusianism**, Duncan Baird Publishers, London.

Rana Fazal & Ross Hugh 2004: **Origin of Life**; Navpress, Colorado Springs, CO80920.

Ross Hugh 2010: **Beyond the Cosmos**, **What Recent Discoveries in Astrophysics Reveal About the Glory and Love of God,** 2010:Signalman Publishing, Orlando, Florida.

Southwood, Richard 2002: **The Story of Life**, Oxford University Press.

Steinberg Milton, 1975: **Basic Judaism**, Harcourt Brace Jovanovich, Publishers. San Diego, New York, London.

Vorilhon Claude, 1983፡ **Le Livre Qui Dit La Verite**

Wallis Budge (1932): **The Kebra Negast,** Oxford University Press, London, Humphrey Milford.

ልዑለ ቃል አካሉ (መምህር)፥ 1994፤ ***ሥርአተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፥*** አትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ ዩ ኤስ ኤ፥ አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ (አዘጋጅ)፥ 1978፤ **ገድለ አቡነ አረጋዊ፥** ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ (አዘጋጅ)፥ 1992፤ **መልክአ ሚካኤል በአማርኛ፥** ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ (አዘጋጅ)፥ 1964፤ **መዝሙረ ዳዊት ወጸሎታት ዘነቢያት ወመዐልየ ዘሰለሞን**፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1951)፤ **የኢትዮጵያ ታሪክ** 2ኛ መጽሐፍ።

ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት (አሳታሚ)፥ 1990፤ **ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው**፥ ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አቡነ ሽኑዳ 3ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ (ውርስ ትርጉም በዲያቆን ታደሰ ወንድም አገኘሁ)፥ 1993፤ **የንስሐ ሕይወት፥** ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

አባ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ፥ 2009፤ **በአዲስ መሠረት ላይ የነበረው ጥረት፥** Washington D.C. 20018 USA.

አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ **የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፥ 1998፤ **ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት፥** ኅትመተ ብራና ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አንዱ ዓለም አባተ (የአጸደ ልጅ)፥ 2010፤ **ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ፥** እና ሌሎች ግለ-ወነች።

ብሩህ ዓለምነህ፥ 2010፤ **የኢትዮጵያ ፍልስፍና የዘርርዓ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ (ከነሐተታቸው)**

ኢንተርናሺናል መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፥ 2001፤ **መጽሐፍ ቅዱስ**፥ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፥ International Bible Society.

ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ 1991፤ **ትምህርተ መለኮት**፥ ሁለተኛ እትም፥ ንግድ ማተሚያ ቤት ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

ዓባይነህ ካሴ፥ 1992፤ **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**፥ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አንደኛ መጽሐፍ፥ አሳታሚ ማሕበረ ቅዱሳን፥ አዲስ አበባ።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1992፤ **አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት**፥ ሁለተኛ እትም።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1995፤ **ሚሊንየም እንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት**፥ Revised Edition.

እሸቱ ታደሠ ወንድም አገኘሁ (ዲያቆን) እና ደጀኔ ሽፈራው በላቸው (ዲያቆን)፥ 1991፤ **ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ**፥ ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

ወሰኔ ይፍሩ፤ አዘጋጅ፤ 1990፤ **ሄኖክ**፤ በየዓመቱ የሚታተም የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት፥ 1101 S.W. Washington St. Suite 129 Portland, OR 97205

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (አሳታሚ)፥ 1980፤ **መጽሐፍ ቅዱስ**፥ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፥ መጀመሪያ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፥ United Bible Societies Africa Regional Centre, Nirobi, Kenya.

የጥንት ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1983፤ **ተአምረ ማርያም**፥ አንደኛ መጽሐፍ፥ አዘጋጅና አከፋፋይ ተሰፋ ገብረ ሥላሰሴ፥ አዲስ አበባ።

የጥንት ሊቃውንት እንደጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1946፤ **ገድለ ተክለ ሃይማኖት**፥ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ዲበኩሉ ዘውዴ፥ 1986፤ **ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና**፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ጥዑመ ልሳን ካሳ (ሊቀ ካህናት - ርዕሰ ደብር)፥ 1981፤ **ያሬድና ዜማው**፥ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።